መንፈሳዊ ቃላትና ጥቅማቸው

ክፍል አንድ
(1 - 100)

የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ
ቅዱስነታቸው አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ እንደጻፉት

አያሌው ዘኢየሱስ እንደተረጎመው

መስከረም ፪ ሺህ ፩ ዓ.ም.
አዲስ አበባ

ምስጋና

- የትርጉሙን ረቂቅ ውድ ጊዜያቸውን መሥዋዕት በማድረግ አንብበው ገንቢ አስተያየታቸውን ለሰጡኝ ለቀሲስ ጌታቸው ደጀኔ፣ ለዲያቆን ሲራክ ዘኢየሱስና ለዮሴፍ አረጋ፤
- አተረጉማቸው ዘንድ የእንግሊዘኛ መጻሕፍቱን ለሰጡኝ ለጌዴዎን ጸንጠሌዎንና ለማኅሌት ሰሎሞን፤
- መጻሕፍቱ ተተርጉመው እንዲወጡ በተለያየ መንገድ ለረዱኝ እኅቶቼ ለዕሌኒ ዘኢየሱስ፣ ለዕሌኒ በርሔና ለሌሎችም ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ በሙሉ መንፈሳዊ ምስጋናዬን በእግዚአብሔር ስም አቀርብላቸዋለሁ።

የመጻሕፍቱ የእንግሊዘኛ ርዕስ፡- "Words of Spiritual Benefit."

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን
ደንብና ሥርዓት ጠብቆ የተዘጋጀ መጽሐፍ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

አድራሻ፡- ደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን
ወይም
በስልክ ቁጥሮች 0911 15 75 96፤0911 61 59 15
አዲስ አበባ

መግቢያ
ክፍል 1 (ከ1 - 50)

እነዚህ ቃላት ረዣዥም ጽሑፎችን ለማንበብ ጊዜ ለሌላቸው ሰዎች አመቺ በሆነ መንገድ የተዘጋጁ ስለሆኑ አጫጭር ግን ብዙ ናቸው። (ከ1 እስከ 200)

እያንዳንዱ ቃል ልዩ መንፈሳዊ ትርጉም ስለሚሰጣችሁ በተናጠል ራሱን ችሎ እንዲነበብ ሆኖ ተዘጋጅቷል።

ይህን ጽሑፍ በእጆቻችሁ የምናስገባው በእውቀታችሁ ላይ ለመጨመር ሳይሆን በሕይወታችሁ ላይ ለመጨመር ነው።

የእነዚህ ቃላት የመጀመሪያ ክፍል ይህ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ማተሚያ ቤት ለኅትመት ገብቷል።

በቅርቡ ከተጨማሪ ቃላት ጋር እስክምንገናኝ ድረስ . . .

ሺኖዳ ሣልሳዊ
ሐምሌ 10 ቀን 1989 (ኢ.አ.አ.)

መግቢያ
ክፍል 2 (ከ51 - 100)

ከዚህኛው መጽሐፍ ርዕስ በታች እንደተመለከተው በሁለቱ ክፍል መጻሕፍት ውስጥ 100 መንፈሳዊ ጥቅም የሚሰጡ ቃላቶችን እነሆ አቅርበንላችኋል። ይሁን እንጂ በመካከላችን ያለው ውይይት እየተራዘመ የሄደ ይመስላል።

ከእነዚህ መጻሕፍት በተጨማሪ ተከታትሎ የሚቀርብና ልዩ አቀራረብ ያለው ሦስተኛ ክፍል መጽሐፍ አለ።

የሚታተመውም ከቀደሙት ርዕሶች ጋር ተመሳሳይ በሆነውና «መንፈሳዊ ቃላትና ጥቅማቸው - ክፍል ሦስት» በሚለው ርዕስ ነው።

እነዚህ መጻሕፍት የሚታተሙበት ዋና ዓላማ ሁላችንም አንድ ልብ ይኖረን ዘንድ ነው። ይህ ልባችንም የክርስቶስ ልብ ነው። 1ኛ ቆሮ 2:16።

ሺኖዳ ሣልሳዊ

በስመ አብ፣ወወልድ፣ወመንፈስ ቅዱስ፣አሐዱ አምላክ፤አሜን።

ከተርጓሚው

ውድ አንባብያን ወገኖቼ በሙሉ! ከዚህ መጽሐፍ ቀደም ሲል ከብፁዕ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ መንፈሳዊ መጻሕፍት መካከል «የተራራው ስብከት»፣ «የዲያብሎስ ውጊያዎች»፣ «የነፍስ አርነት»፣ «የተሰፋ ሕይወት»፣ «መንፈሳዊው ሰው»፣ «መንፈሳዊ ውጊያዎች»፣ «መንፈሳዊው መንገድ»፣ «የባሕታውያን አባቶች ሕይወትና የመዝሙራት ተመስጦ»፣ «መንፈሳዊ ጾም» እና «እግዚአብሔርና ሰው» የተባሉትን አሥር መንፈሳዊ መጻሕፍት እግዚአብሔር ፈቅዶልኝ በተከታታይ ተርጉሜ ማቅረቤ በእናንተ ዘንድ ይታወቃል። ከዚህ በተጨማሪ ከቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ መንፈሳዊ መጻሕፍት መካከል አንዱን «ሀብታምና ድሀ» በሚል ርዕስ ተርጉሜ ማውጣቴ አይዘነጋም።

አሁንም ቸር፣ መሐሪ፣ ይቅር ባይና ርኅሩኅ የሆነው ልዑል እግዚአብሔር ዕድሜና ጤና፣ ብርታትና እውቀት ሆኖኝ ይህን **"Words of Spiritual Benefit."** የተባለውን ባለ አራት ክፍል ተከታታይ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ መንፈሳዊ መጽሐፍ ቃል በቃል «መንፈሳዊ ቃላትና ጥቅማቸው» ብዬ በመተርጎም እንዳቀርብ የማያልቅ ቸርነቱን ስላበዛልኝ ክብርና ምስጋና ለእርሱ ይድረሰው!

«መንፈሳዊ ቃላትና ጥቅማቸው» ብዬ የተረጎምሁት ይህ መጽሐፍ ባለ አራት ክፍል ተከታታይ መንፈሳዊ መጽሐፍ በእንግሊዘኛ የታተመው፡- ክፍል 1 (ከ1-50)፤ ክፍል 2 (51-100)፤ ክፍል 3 (101-150) እና ክፍል 4 (ከ151-200) ተብሎ ነው። ከተለያየ አቅጣጫ ስመለከተው ግን እነዚህን አራት ተከታታይ መጻሕፍት አራት ጊዜ ከማሳተም ይልቅ ሁለት ጊዜ ማሳተሙ ለሁላችንም የበለጠ ጥቅም ይኖረዋል ብዬ ስላሳሰብሁና ስለመከርሁበት ሁለቱን ክፍል ማለትም ክፍል 1 (ከ1-50) እና ክፍል 2 (51-100) አንድ መጽሐፍ፤ሌሎቹን ሁለት ክፍሎች ማለትም ክፍል 3 (ከ101-150) እና ክፍል 4 (151-200) አንድ መጽሐፍ አድርጌ አሳትሜዋለሁ። በዚህ መሠረት ይህ በእጃችሁ ላይ ያለው መጽሐፍ ክፍል 1 (ከ1-50 እና ክፍል 2 ከ51-100) መጻሕፍትን አጠቃሎ የያዘ ባለ ሁለት ክፍል አንድ መጽሐፍ ስለሆነ «መንፈሳዊ ቃላትና ጥቅማቸው» - ክፍል 1 (1-100) ብዬ ሰይሜዋለሁ።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከቁጥር 1-100 ድረስ ያሉት ቃላት በተለያዩ መንፈሳዊ ርዕስ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ ማብራሪያዎች የሚሰጡ ናቸው። እያንዳንዱ ርዕስ ጉዳይ ራሱን ችሎ የተብራራው አጭርና ግልጽ በሆነ ቋንቋ ስለሆነ አንባቢው መጽሐፉን በማንኛውም ጊዜ ከፊት ወይም ከመካከል ወይም ከመጨረሻ ተነሥቶ በቀላሉ ማንበብ ይችላል። አንባቢው አንዱን ርዕስ ጉዳይ በጥሞና አንብቦ ሲጨርስ ካነበበው አንድ ርዕስ ጉዳይ ላይ በልቡ የሚቆይ አንድ መንፈሳዊ ጥቅም ወይም ፍሬ ነገር ያገኛል። ከዚህ በተጨማሪ ስለ አንድ መንፈሳዊ ርዕስ ጉዳይ ማወቅ ለሚፈልግ ወይም በዚህ ርዕስ ጉዳይ ላይ መንፈሳዊ ጽሑፍ ለሚያዘጋጅ ሰው እነዚህ ዝርዝር ቃላት መነሻ ሆነው ሊያገለግሉት ይችላሉ። ከእነዚህ ዐበይት ምክንያቶች የተነሳ ይህ መጽሐፍ እስከ ዛሬ ድረስ ከተረጎምኋቸው የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ መንፈሳዊ መጻሕፍት መካከል በአቀራረቡ ለየት ያለ መጽሐፍ ነው።

በአጠቃላይ ሁለት መቶውም ቃላት ታላቅ መንፈሳዊ ጥቅም የሚሰጡ ቃላት ናቸው። ስለሆነም ከእነዚህ ቃላት መንፈሳዊ ጥቅም ለማግኘት የሚፈልጉ ሁሉ ይህን የመጀመሪያውን ባለ አንድ መቶ ቃላት መጽሐፍ እንዲያነቡ እመክራለሁ። ቀሪውና ሁለተኛው ባለ አንድ መቶ ቃላት መጽሐፍ (ከ101-200) እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በቅርቡ በእጃችሁ ይገባል። እነዚህን ቃላት አንብበን ለመናገር ብቻ ሳይሆን አንብበን በሕይወታችን ለመግለጽ እንድንችል እግዚአብሔር ብርታቱን፣ ጽናቱንና ቆይታውን ያድለን፤አሜን።

እያሌው ዘኢየሱስ

ተ.ቁ.	ማውጫ	ገጽ

(1) እርምጃ 7
(2) ከሰዎች ጋር ስለ መግባባት 7
(3) በጥቂቱ መታመን 9
(4) ደስታ . . . አሁንም ደስታ 10
(5) የምክንያቶች ችግር 11
(6) ጾምና መንፈሳዊነቱ 12
(7) ስንፍና እንክርዳድ 13
(8) ችግሮችን የማቃለያ መንገዶች 14
(9) በጭንቀት ጊዜ የሚያጽናኑ ቃላት 15
(10) በሥራ ያልተገለጠ አሳብና ተግባራዊ ሕይወት 17
(11) የሰው ቁጣ 18
(12) መንቻካነት 19
(13) መስቀሉ በሕይወታችን ውስጥ - «ሀ» 20
(14) ቅንነት 21
(15) በጎ ቃላት 22
(16) ጉጉት 23
(17) አነጋገርህ ይገልጥሃል 24
(18) ተግባራዊው ሰው 25
(19) መማር 26
(20) እውነተኛ ደስታና የተሳሳተ ደስታ 27
(21) ለዝምታ የሚደረጉ ጥቂት ልምምዶች 29
(22) የእምነት ደረጃዎች. 29
(23) ጸሎት 30
(24) በእውነትና በሐሰት መካከል ያሉ «ኃጢአት ሠርቼያለሁ» የሚሉ ቃላት. 31
(25) የአዲስ ዓመት ጸሎት 33
(26) ንስሓና ጸጸት 34
(27) የሰብእና ጥንካሬ 35
(28) ክርስትና. . የጥንካሬ ሃይማኖት 36
(29) የክርስቲያን ጠባይ 37
(30) አቤቱ ጌታ ሆይ፤ስብሰባዎችንን አስታውስ፤ቀድሳቸውም. 38
(31) መንፈሳዊ ጾም 39
(32) በነነዌ ጾም ወቅት የሚደረጉ ልምምዶች 40
(33) የእውቀት ችግሮች 41
(34) የጋብቻ ትርጉም ምንድር ነው? 42
(35) ፍርሃት. 43
(36) መስቀሉ በሕይወታችን ውስጥ - «ለ» 44
(37) የምትናገረው መቼ ነው? 46
(38) የልብ ሰላም. 46
(39) መስቀልህን ተሸከም፤የምትሰቀል እንጂ የምትሰቅል አትሁን! . . 47
(40) በበዓለ አምሳ ወቅት የሚኖር መንፈሳዊነትህ 48
(41) የቅንዓት ትርጉም ምንድር ነው? 49
(42) ጠብ. 50
(43) መንፈሳዊው መንገድ. 52
(44) ብልሀቱ ወይም ዘዴው. 53
(45) ልጆቹን በማክበር ውስጥ ያለ የእግዚአብሔር ትሕትና. 54
(46) ጥበብ 55
(47) ዘለዓለማዊነትህ 56
(48) ሦስቱ የቅድስና ሥራዎች 57
(49) ልባም ፍቅርና ሰነፍ ፍቅር 58
(50) ምቹ ጊዜ 59

ተ.ቍ.	ማውጫ	ገጽ

(51) በምድረ በዳውና በፀጥታው ውስጥ 60
(52) አግባብነት የሌለው ጥላቻ 61
(53) መለያየት 62
(54) መጠቀም የሚፈልግ ሰው 63
(55) ጥብቅ ሥራ 64
(56) እኔ ብቻ 65
(57) ሕልም 66
(58) የራስ አሳቦች 67
(59) ፀጥታ 68
(60) መልካሙ መንገድ 69
(61) መሠረታዊው የቅድስና ሥራ 70
(62) የፍቅር ትርፍ 71
(63) መስቀል 72
(64) እምነት 73
(65) ጸሎት 74
(66) የመሥዋዕትነት ሕይወት 75
(67) ለቅድስና ሙሉ መሆን 76
(68) የቅዱሳን በዓላት 77
(69) ከእግዚአብሔር ጋር መሥራት 78
(70) መንገዳችሁን መርምሩ 79
(71) ከስሕተቶች መጠቀም 80
(72) ዕድገት 82
(73) የዘገየ አሳብ 83
(74) በዓመቱ መጨረሻ 84
(75) በጥቂቱ የታመነ 85
(76) ሙሉው እውነት 86
(77) ንስሓ ስለ መግባት 87
(78) የጥምቀት በዓል ተመስጦ 88
(79) ዓመፅ ወይስ ጥብቅነት 89
(80) ሁለቱ ደረጃዎች 90
(81) ጥቂትና ብዙ 91
(82) ጥቅም 92
(83) ሥርዓቶች 93
(84) ፈተናዎች 94
(85) ሁሉም ነገር ለመንፈሳዊነታችሁ ይሁን 95
(86) ንስሓና ፍጹምነቱ 96
(87) ለእኛ የሆነ የእግዚአብሔር ፍቅር «ሀ» 97
(88) ለእኛ የሆነ የእግዚአብሔር ፍቅር «ለ» 98
(89) የፍቅር መሥዋዕት 99
(90) የእግዚአብሔር መፍትሔዎች 100
(91) እግዚአብሔር አለ 102
(92) ሌላው እይታ 103
(93) ቅንነት 104
(94) የቤተ ክርስቲያን ሰላም 105
(95) ሌሎች እንዲሰናከሉ ምክንያት መሆን 106
(96) የመከራ ክብር 107
(97) ዕርገት 108
(98) የሐዋርያት ጾም 109
(99) የሚጠቅም ቃል 110
(100) ራስን መውደድ 112

(1)
አርምሞ

አርምሞ (ዝምታ) መንፈሳዊ ሰው ካሉት ድንቅ ችሎታዎች መካከል አንዱ ነው። ይህ ደግሞ የልብ፣ የነርቭ፣ የአሳብ፣ የስሜት፣ የጠባይና የሰውነት አርምሞን ያጠቃልላል። የዝምተኛ ሰው ልብ ምንም ዓይነት ምክንያት ቢገጥመውም ፈጽሞ አይታወክም። ችግሮቹ ምንም ዓይነት ነገር ቢያደርሱበትም ዝምታውን አያጣውም። ነቢዩ ዳዊት ይህን አስመልክቶ ሲናገር፦ «ሠራዊትም ቢሰፍርብኝ ልቤ አይፈራም፤ሰልፍም ቢነሣብኝ በዚህ እተማመናለሁ።» (መዝ 26:3) ብሏል። እንዲህ ዓይነቱ አርምሞ ከእምነት የሚመነጭ አርምሞ ነው።

አንድ ሰው ውስጣዊ ሰላሙን ሲያጣ በዐይኖቹ ፊት የሚመለከታቸው ነገሮች ሁሉ የታወኩ ይሆኑበታል፤ቀላሉም ነገር ውስብስብ ይሆንበታል። ይህ ውስብስብነት የሚመጣው ግን ከውጭ ሳይሆን ከውስጥ ነው። ልብ ከተረጋጋ ነርቮቹም ይረጋጋሉ። በዚህ ዓይነት መንገድ የሰው ቁጣ ገንፍሎ አይወጣም፤ ይልቁንም ችግሩን በፀጥታ ውስጥ ሆኖ ያቃልለዋል።

የሰው አዕምሮ አንድ ችግርን ማቃለል ከተሳነው ነርቮቻችን ለማገዝ በመካከል ጣልቃ ይገባሉ። የተነሣሱት ነርቮች የመፍትሔ እጦትን ሲያሳውቁ ይችላሉ፤ነርቮቹ ይበልጥ እየታወኩ በመጡ ቁጥር ደግሞ ይበልጥ ይነሣሳሉ።

የተረጋጋ ልብ እና ነርቭ ያለው ሰው የአሳብና የድርጊት ዝምታን ገንዘቡ ማድረግ ይችላል። አሳቦቹ ምንም ዓይነት ሁከት የሌለባቸውና የተመጣጠኑ ይሆናሉ። ስለሆነም ድርጊቱን የሚፈጽመው ከቁጣ ወይም ከጭንቀት በራቀ መንገድ በአርምሞና በትክክለኛነት ነው።

ሰው ውስጣዊውን ሰላም እንዲያገኝ የሚረዳው ውጫዊው ሰላም ነው። ይህም በውስጡ ምንም ዓይነት የሚያውክ ሁኔታ የሌለበት ሰላማዊ አካባቢን ይፈጥራል። ምክንያቱ ይህ በመሆኑም መነኮሳት ከሁከት፣ ከሰዎች ጫጫታ ወይም ከሚያውክ ወሬና ግጭት ርቀው በምድረ በዳ ውስጥ በሰላም ይኖራሉ። እነርሱ እንደዚህ ያለውን አርምሞ ተላምደውታል።

የመለየትና የብቸኝነት ሕይወት በአጠቃላይ አርምሞን ያመጣል። የዚህ ምክንያቱም ስሜቶቻችን ሁሉ ስለሚረጋጉ ነው። ቅዱሳን አባቶቻችን ስሜቶች የአሳቦች መንገድ ናቸው ይላሉ። የምታዩት፣ የምትሰሙትና የምትዳስሱት ነገር ሁሉ አሳብ ይሰጣችኋል። ስሜቶቻችሁ ወሬ ከመሰብሰብ ተለይተው በእረፍት ላይ ከሆኑ አሳቦችን ከማሰብ እፎይ ትላላችሁ።

ፀጥ ያለ ቦታ የስሜትን መረጋጋት ያግዛል፤ይህ ደግሞ ወደ አሳቦች፣ ወደ ልብና ወደ ነርቭ መረጋጋት ያመራል። ብዙ ሰዎች ጫጫታ ካለበት ስፍራ ርቀው የሚሄዱት የአዕምሮ ሰላምን ለመፈለግ ነው።

ባላቸው ብርታት ሁሉ አርምሞን ለማግኘት በፍቅር የሚፈልጉት ሰዎች እንዳሉ ሁሉ ያለ ሁከትና ያለ ጫጫታ መኖር የማይችሉ ሰዎችም አሉ። አርምሞ ለእነርሱ አሰልቺ ነገር ነው።

(2)
ከሰዎች ጋር ስለ መግባባት

የሰዎችን ልብ በማሸነፍ ከእነርሱ ጋር ለመግባባት የሚያስችሉ ብዛት ያላቸው መንገዶች አሉ። ይህን ማድረግ ከቻልህ በፍቅር ወደ መንፈሳዊነት ልትመራቸው

ትችላለህ:: መጽሐፍ ቅዱስ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፦ «ነፍሶችንም የሚሰበስብ እርሱ ጠቢብ ነው::» ምሳ 11:30::

ሀ/ በአንተ ሕይወት ውስጥ ሰዎች የሚናፍቁት ተስማሚ ነገር ይኖራል::

ለ/ ለሰዎች የሆነውን ነገር የማትሻ ከሆንህ ይወዱሃል:: እነርሱ ሊያገኙ የሚሞክሩትን ወይም በእነርሱ ዘንድ ያለውን ለመውሰድ የምትፈልግ መሆንህን በመግለጥ ጠላቶችህ እንደ ሆኑ ሆነው እንዲሰማቸው አታድርጋቸው::

ሐ/ የሌላውን ሰው ድካም በመቻል በትዕግሥትህ፣ በይቅርታህና በግልጽ ልብህ አሸንፈው:: እንዲህ ዓይነቱ ሰው ለብቻው ሲሆን የሠራው ሥራ በእርግጥ ይጸጸተዋል::

መ/ ሌሎች ሰዎችን በማወደስ አድናቆትህን እንዲገነዘቡ አድርጋቸው:: መልካም ሥራዎቻቸውን እንዳወቅህላቸውና እንዳደነቅህላቸው እንዲያውቁም አድርጋቸው::

ሠ/ ሌሎች ሰዎችን አክብር፤ለእያንዳንዱ ሰው ትሕትና አሳይ:: ይህን የምታደርገው ለታላላቆች ወይም እንድታከብራቸው ለተገደድህባቸው ሰዎች ብቻ ሳይሆን በዕድሜ ታናናሾችህ በደረጃም ከአንተ ዝቅ ለሚሉትም ጭምር መሆን አለበት::

ረ/ ሰዎችን ለመገንባት እንጂ ለማፍረስ አትሥራ::

ሰ/ ሰዎችን በተደጋጋሚ አትገሥጻቸው፤ይህን ማድረግ ካለብህም ማንንም ለመጉዳት ወይም ላለማመን ስትል አታድርገው:: በእነርሱ ላይ ሂስ እንድትሰጥና ለመጉዳት ወይም ላለማመን ስትል አታድርገው:: በእነርሱ ላይ ሂስ እንድትሰጥና ለእነርሱ ጠላት ሆነህ እንድትቆም የሚያደርግህን ቃል ወይም ድርጊት ለይተህ አታገኝ::

ሸ/ ለሌሎች ሰዎች ምክንያት በመፈለግ ስለ እነርሱ ያለ ምንም ግብዝነት በትክክለኛው መንገድ ለመሟገት የምትችለውን ሁሉ አድርግ::

ቀ/ ምንጊዜም ቢሆን ለመስጠትና መሥዋዕት ለመሆን ዝግጁ ሁን:: ለአንድ ሰው ምንም ልታደርግለት ባትችልም እንኳ መልካም ቃል፣ ፈገግታና እውነተኛ ሰላምታ አቅርብለት:: ለሁሉም ሰው ልታደርግ የሚገቡህን ነገሮች ያለ ምንም ውድቀት ፈጽም::

በ/ ሰዎችን ሁሉ በትሕትና፣ በተረጋጋ ሁኔታና በየውሃት (በየዋህነት) ውስጥ ሆነህ ተመልከት:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በገላትያ መልእክቱ ውስጥ እንደተናገረው የውሃት ከመንፈስ ፍሬዎች መካከል አንዱ ነው፦ «የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት ነው::» ገላ 5:22::

ተ/ ሰዎችን መረዳት ብቻ ሳይሆን እነርሱም አንተን በፀጥታና በመልካም መንፈስ እንዲረዱህ አድርጋቸው:: ይህን በማድረግህም ከእነርሱ ጋር በጋራ መረዳዳት፣ በፍቅርና በሰላም መኖር ትችላለህ::

ቸ/ በሰዎች ደስታና ኀዘን ላይ ተካፋይ ሁን፦ «ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ፤ከሚያለቅሱም ጋር አልቅሱ::» ሮሜ 12:15:: የሰዎችን ልብ ለማጽናናት ዕድሉን አትጣው::

(3)
በጥቂቱ መታመን

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ «በጥቂቱ ታምነሃል፤በብዙ እሾምሃለሁ፤. . .» ማቴ 25:21::

ይህም ማለት በምድራዊ ነገሮች ላይ ታማኝ ሆነህ ስትገኝ በሰማያዊ ነገሮች ላይ እሾምሃለሁ ማለት ነው:: በዚህኛው ዓለም ውስጥ ታማኝ ሆነህ ከቆየህ በዘላለማዊነት ውስጥ እሾምሃለሁ ማለትም ነው::

ይህ መመሪያ በብዙ መስኮች ላይ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል. . .

+ ዘመዶችህን በመውደድ ላይ ታማኝ ሆነህ ከተገኘህ እግዚአብሔር ጠላቶችህንም በመውደድ ላይ ይሾምሃል:: ጠላትህን የምትወድበትን ጸጋ ያድልሃል ማለት ነው::

+ በትርፍ ጊዜዎችህ እግዚአብሔርን የምታገለግል ከሆንህ በሕይወትህ ጊዜ ሙሉ በእርሱ ላይ ትኩረት የምታደርግበትን ፍቅር ያድልሃል::

+ የፈቃድ ኃጢአቶችን ከአንተ በማስወገድ ላይ ታማኝ ሆነህ ከተገኘህ እግዚአብሔር ያለ ፈቃድ ከሚመጡ ኃጢአቶች ነጻ ያወጣሃል::

+ ንቁ ኅሊናህን ከክፉ አሳቦች የምትጠብቅ ከሆንህ እግዚአብሔር ንቁ ያልሆነው ኅሊናህን ንጽሕና ያድልሃል፤ከዚህ በተጨማሪ የሕልሞችህን ንጽሕናም ያድልሃል::

+ ልጅ እያለህ ታማኝ ከሆንህ እግዚአብሔር ውጊያዎች በሚበዙበት በወጣትነት ዘመንህ ውስጥም ታማኝነትን ያድልሃል::

+ ሌሎች ሰዎች ላይ በቃላት ብቻ የማትፈርድባቸው ሆነህ ለመገኘት ታማኝ ከሆንህ ይበልጥ አስቸጋሪ በሆነው በአሳብ እንዳትፈርድባቸው ያስችልሃል::

+ ልክ እንደዚሁ ራስህን ከውጪያዊ ንዴት በመጠበቅ ላይ ታማኝ ሆነህ ከተገኘህ እግዚአብሔር ከውስጣዊ ቁጣ፣ ንዴትና ቅናት ነጻ ያወጣሃል::

+ በተለመዱ መንፈሳዊነቶች (በመንፈስ ፍሬዎች) ላይ ታማኝ ሆነህ ከተገኘህ እግዚአብሔር የመንፈስ ስጦታዎችን ያድልሃል፤ በመጀመሪያው ላይ ታማኝ ሆነህ ካልተገኘህ ሁለተኛውን ፈጽሞ ልታገኘው አትችልምና::

እግዚአብሔር በመጀመሪያ የሚፈትሽህ በጥቂት ነገር ነው:: በዚህች በጥቂቷ ነገር ላይ ታማኝ መሆንህን ካረጋገጥህ እርሱ በሚበልጠው ነገር ላይ ይሾምሃል:: ውድቀትህንና አለመታመንህን በጥቂቷ ነገር ላይ ከገለጽህ ግን እግዚአብሔር በሚበልጠው ነገር ላይ አይሾምህም:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላልና፦ «ከእግረኞች ጋር በሮጥህ ጊዜ እነርሱ ቢያደክሙህ ከፈረሶች ጋር መታገል እንዴት ትችላለህ?» ኤር 12:5::

ብዙ ሰዎች ዝቅተኛውን ኃላፊነት መወጣት ሳይችሉ ከፍተኛውን ኃላፊነት ለመቀበል ማሰባቸው እጅግ አስደናቂ ነገር ነው:: እነዚህ ሰዎች በተሰጣቸው ጸጋ ሳይጠቀሙ ተጨማሪ ጸጋ እንዲሰጣቸው የሚጠይቁ ናቸው:: ይህን ሲያደርጉም «በጥቂቱ ታምነሃል፤በብዙ እሾምሃለሁ፤...» የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል በመዘንጋት ነው:: ይህ ቃል ለእነርሱ እንደ ሁኔታው የሚወሰንበት ነው የሚሆነው::

(4)
ደስታ . . . አሁንም ደስታ

ለብልሽት፣ ለዓለማዊ ጉዳዮችና ለፈንጠዝያ የሚያበቃ ዋጋቢስ ደስታ አለ::
ንጉሥ ሰሎሞን ከፀሐይ በታች በደከመው ድካም ውስጥ ያገኘው ከንቱ ደስታ (መክ 1:3) እና ከነነዌ ሰዎች ድኅነት ይልቅ ለነቢዩ ዮናስ የበቀለችለት ተክል የሰጠችው ጊዜያዊ ደስታ ለዚህ ምሳሌ ይሆነናል:: «ከወዳጆቼ ጋር ደስ እንዲለኝ አንድ ጠቦት ስንኳ አልሰጠኸኝም፤. . .» (ሉቃ 15:29) በማለት ለአባቱ ወቀሳ ያቀረበው የጠፋው ልጅ ታላቅ ወንድም የሻተው ደስታ ከእነዚህ ደስታዎች ጋር ተመሳሳይ ነው::

ሐዋርያት ርኩሳን መናፍስትን ባስወጡ ጊዜ ከተሰማቸው ደስታ ጋር የሚመሳሰልና በተሰጧቸው ስጦታዎች የተሳሳተ ደስታ የሚደሰቱ አንዳንድ ሰዎች አሉ:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን አስመልክቶ ለሐዋርያቱ የተናገራቸው እንዲህ በማለት ነበር:- «ነገር ግን መናፍስት ስለ ተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ፤ስማችሁ ግን በመንግሥተ ሰማያት ስለ ተጻፈ ደስ ይበላችሁ::» ሉቃ 10:20::

ከሁሉም የሚከፋው ደስታ ግን የሌሎች ሰዎችን መከራ በመመልከት የሚመጣው ደስታ ነው:: በሌሎች ሰዎች ጥፋት የሚደሰቱ ሰዎች አሉ:: ሐዋርያው ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል:- «ፍቅር . . . ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤. . .» 1ኛ ቆሮ 13:6:: ጠቢቡ ሰሎሞንም እንዲህ በማለት ተናግሯል:- «ጠላትህ ቢወድቅ ደስ አይበልህ፤በመሰናከሉም ልብህ ሐሴት አታድርግ፤. . .» ምሳ 24:17:: እንዲህ ያለው ክፉ ደስታ ፈንጠዝያ ተብሎ ይጠራል::

የተቀደሰው ደስታ ግን ከመንፈስ ፍሬዎች መካከል አንዱ ነው:: ገላ 5:23::

ሐዋርያት ጌታን ባዩ ጊዜ ደስ ብሏቸዋል:: ሰብአ ሰገልም ኮከቡን ሲመለከቱ ተደስተዋል:: ጻድቃንም የተቀደሰ ሥራቸውን የድካም ውጤት ሲመለከቱ ይደሰታሉ፤ «በልቅሶ የሚዘሩ በደስታ ያጭዳሉ::» (መዝ 125:6) ተብሎ ተጽፎአልና::

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ድኅነታችን ደስታና ስለ እረኞቹ ደስታ ገልጾልናል:: መልአኩ ለእረኞቹ የምሥራቹን ያበሠራቸው እንዲህ በማለት ነበር:- «. . . ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና፤. . . ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና. . .» ሉቃ 2:10እና11፡ መዝሙረኛው ዳዊት ስለ ድኅነት ደስታ ሲዘምር «የማዳንህን ደስታ ስጠኝ. . .» (መዝ 50:12) ብሏል:: የጠፋው ልጅ አባትም «. . . ይህ ወንድምህ ሞቶ ነበረ ሕያው ስለሆነ ጠፍቶም ነበር ስለ ተገኘ ደስ እንዲለን ፍስሐም እንድናደርግ ይገባናል. . .» ሉቃ 15:32::

ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ ሰው ምክንያት በሰማይና በምድር ታላቅ ደስታ ይሆናል:: መልካሙ እረኛ የባዘነው (የጠፋው) በጉን ሲያገኘው «. . . ደስ ብሎት በጫንቃው ይሸከመዋል. . .» ሉቃ 15:15:: ከዚህ በተጨማሪ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሏል:- «. . . ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል::» ሉቃ 15:7:: ሳንቲሟ የጠፋባት መበለት ባገኘችው ጊዜ እጅግ ደስ ስለሚላት ጎረቤቶቿ ከእርሷ ጋር ደስ እንዲላቸው ጠርታቻዋለች::

እኛም በማንኛውም የጸጋ መገኛ ደስ እንሰኛለን . . .

ነቢዩ ዳዊት እንዲህ ብሏል:- «ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ::» (መዝ 121:1)፤«የወንዝ ፈሳሾች የእግዚአብሔርን ከተማ ደስ ያሰኛሉ፤. . .» መዝ 45:4::

ጻድቅ ሰው ፈተና እና ተግሣጽ ሲደርስበትም ደስ ይለዋል:: ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል:- «ወንድሞቼ ሆይ፤የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት::» ያዕ 1:2እና3:: ስለሆነም ሁላችንንም ፈተና እና መከራ ሲገጥመን ደስ ሊለን ይገባናል::

ከሁሉ የሚበልጠው ታላቁ ደስታ «. . . ወደ ጌታህ ደስታ ግባ!...» (ማቴ 25:21) የሚለው የመንግሥተ ሰማያት ደስታ ነው:: ይህ ደስታ በእግዚአብሔር የምንደሰትበትና የእርሱን ወዳጅነት የምናገኝበት እውነተኛ ደስታ ነው:: እስካሁን ድረስ ወደ መንግሥቱ ስላልገባን እርሱን በተስፋ እንጠብቃለን:: ሐዋርያውም «በተስፋ ደስ ይበላችሁ፤» (ሮሜ 12:12) ብሎናል::

(5)
የምክንያቶች ችግር

ብዙ ሰዎች ኃጢአቶቻቸውን ለመሸፈን ሲሉ ምክንያት ይደረድራሉ:: ይህን የሚያደርጉትም በሰዎች እንዳይወቀሱ ወይም ውድቀታቸውን በመልካም ሥራዎች ለማመካኘት ሲሹ ነው::

እንደዚህ ያለው የማመካኘት ስህተት ከአዳምና ከሔዋን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ጥንታዊ ስህተት ነው:: ሔዋን እባብ የሚነግራትን ማዳመጥ ባይገባትም ያመካኘችው በእርሱ ነው:: ስለሆነም የሰጠችው ምክንያት ተቀባይነት አላገኘም::

ልክ እንደዚሁ አዳምም ሔዋን የሰጠችውን ፍሬ አልቀበልም ማለት እየቻለ ተቀብሎ ከበላ በኋላ በእርስዋ ላይ አመካኝቷል::

ወደ ሲዖል የሚወስደው መንገድ በምክንያቶች የተሞላ ነው የሚለው አባባል ምንኛ እውነት ነው! መክሊቱን መሬት ቆፍሮ የቀበረው ባሪያ እንኳ ከመጥፎ ድርጊቱ የሚከፋ ምክንያት ለጌታው አቅርቧል:: እርሱ ጌታውን ካልዘራበት የሚያጭድ ካልበተነበትም የሚሰበስብ ጨካኝ ሰው እንደ ሆነ አድርጎ ነበር የተናገረው!

ብዙ ሰዎች ለመዝናናትና ጉብኝት ለመሄድ የሚበቃ ሰፊ ጊዜ እየመደቡ ለጸሎት የሚሆን ጊዜ የለንም ብለው ምክንያት ያቀርባሉ:: እነዚህ ሰዎች ለመጸለይ ፍላጎት የሌላቸው ሰዎች ናቸው::

ለእግዚአብሔር አሥራት የማያወጡ ብዙ ሰዎች ምክንያት አድርገው የሚያቀርቡት በቂ ገንዘብ የለንም የሚል ነው:: ያላትን ሁለት ሳንቲም በመስጠት አሥራት ያወጣችው መበለት ግን ምክንያት ስለ መስጠት አላሰበችም:: በሰራፕታ ትኖር የነበረችው መበለትም ከዚህችኛዋ መበለት ጋር ተመሳሳይ ድርጊት ነው የፈጸመችው:: እርሷ በረሀቡ ዘመን እጅግ የሚያስፈልጋትን ዱቄትና ዘይት ነው ለነቢዩ ኤልያስ ያቀረበችው::

ብላቴናው ዳዊት ከጎልያድ ጋር ላለመዋጋት ብዛት ያላቸው ምክንያቶችን ማቅረብ ይችል ነበር! እርሱ ወታደር ስላልነበር በፈቃደኝነት ለመዋጋት ይወጣል ብሎ የጠበቀው አንድም ሰው አልነበረም:: ጎልያድ ግዙፍና ብርቱ ሰው ስለ ነበር እንኳንስ ብላቴናው ዳዊት ትላልቆቹም ሰዎች ይፈሩት ነበር:: ይሁን እንጂ የዳዊት እሳታዊ ቅንዓት ምክንያቶች ያቀርብ ዘንድ አልፈቀደለትም::

ከኢየሱስ ክርስቶስ በስተ ቀኝ የተሰቀለው ወንበዴ እምነትን ላለመቀበል ብዙ ምክንያቶችን ማቅረብ ቢችልም እንኳ ይህን ፈጽሞ አላደረገውም:: ሲሰቅሉት ራሱን ለማዳን ያቃተው የሚመስለውን ጌታ እየተመለከተ እንዴት በእርሱ ሊያምን ይችላል!

በእርሱ ላይ የሚያፌዙትና የሚዘብቱበት ሰዎች ቃላት በጆሮዎቹ ውስጥ ቢያስተጋቡበትም እንኳ ላለማመን ምክንያቶች እንዲሆኑት አድርጎ ሊወስዳቸው አልፈቀደም።

ዳንኤል በአናብስቱ ጉድጓድ ውስጥ ሊጣል ባለ ጊዜ ፍርሃት ምክንያት ሆኖ በማቅረብ ሠለስቱ ሊያስቀረው አልቻለም። ልክ እንደዚሁ ፍርሃት ምክንያት ሆኖ በማቅረብ ሠለስቱ ደቂቅን በእቶን እሳት ውስጥ ከመጣል አላስቀራቸውም።

እግዚአብሔር አምላክ ልጁን መሥዋዕት አድርጎ ያቀርብ ዘንድ አብርሃምን በጠየቀው ጊዜ በእርጅናው ወራት ያገኘው አንድ ልጁን ፍቅር ምክንያት አድርጎ ሊያቀርብ አልወደደም፤ ልጁን ከረዥም ዓመታት በኋላ በተገባለት ቃል ኪዳን መሠረት ያገኘው ቢሆንም እንኳ!

ሽባ የነበረው ሰው ወዳጆች እንፈልግ ቢሉ ብዙ ምክንያቶችን ማቅረብ ይችሉ ነበር። ይሁን እንጂ በፊታቸው የነበሩት እንቅፋቶች ምክንያት ሆነው አላቆሟቸውም። እነርሱ የቤቱን ጣራ በማንሳት ሽባውን በቃሬዛው ላይ እንደ ተጋደመ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት አውርደው አስቀምጠውታል።

መከራዎችን የሚያሸንፍ ሰው መከራዎቹን ምክንያት አድርጎ አያቀርብም፤የውስጡን እውነተኛነት ያረጋግጥባቸዋል እንጂ።

ፈቃዱ ደካማ የሆነው ወይም የደከመ ውሳኔ ያለው ሰው ግን «. . . አንበሳ በመንገድ አለ፤አንበሳ በጎዳና አለ ይላል።» (ምሳ 26:13) ተብሎ የተጻፈውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ያስታውሰናል።

(6)
ጾምና መንፈሳዊነቱ

ጾም የሥጋ ሥራ አይደለም . . . ለተወሰኑ ሰዓታት ከምግብ መከልከልና የሥጋ ተዋጽዖ ያለባቸውን ምግቦች አለመመገብ ማለት ብቻም አይደለም። በጾም ውስጥ መንፈሳዊ ጉዳይ አለ . . .

የመጀመሪያው መንፈሳዊ ጉዳይ ፈቃድን መቆጣጠር ነው።

በተቆጣጠርነው ከዚሁ ተመሳሳይ ፈቃድ የምንመገበውን ምግብ እንቆጣጠራለን። ከዚህ በተጨማሪ አንድ ሰው ተገቢ ባልሆነ አገላለጽ ለሌላ ሰው ትእዛዝ መስጠት የለበትም፤አሳቡንና ስሜቶቹንም መቆጣጠር አለበት። ማር ይስሐቅ የተባለው መጽሐፍ እንዲህ ይላል:- «አንደበትን ከመከልከል ምላስን መከልከል ይሻላል፤ልብን መከልከል ግን ሁለቱንም ከመከልከል ይሻላል።»

በመንፈሳዊ ጾም ውስጥ ሁለተኛው ጉዳይ ንስሐ መግባት ነው።

በነነዌ ጾም ውስጥ ሰዎቹ ከምግብ ብቻ እንዳልተከለከሉ እንመለከታለን። እነዚህ ሰዎች ከክፉ ሥራቸውና በእጃቸው ካለው ግፍ ነው ሙሉ ለሙሉ የተመለሱት። ከዚህ በኋላ ስለ እነርሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲህ ተብሎ ተጻፈ:- «እግዚአብሔርም ከክፉ መንገዳቸው እንደ ተመለሱ ሥራቸውን አየ፤እግዚአብሔርም ያደርግባቸው ዘንድ በተናገረው ክፉ ነገር ተጸጸቶ አላደረገውም።» ዮና 3:8-10። በዚህ ቃል መሠረት እግዚአብሔር ከጾም ይልቅ ንስሓን ይቀበላል ማለት ነው።

ስለሆነም ጾም በእግዚአብሔር ፊት በትሕትና እና በጸጸት መደረግ አለበት፤ልክ የነነዌ ሰዎች እንዳደረጉት። እነርሱ ከትሕትና እና ከጸጸት በተጨማሪ

ማቅ ለብሰው በአመድ ላይ ተቀምጠዋል። ይህ በኢዩኤል ጾም ውስጥም ተገልጧል:- «. . . ጾምን ቀድሱ፤ ጉባኤውንም አውጁ፤. . . ሙሽራው ከእልፍኙ ሙሽራይቱም ከጫጉላዋ ይውጡ። የእግዚአብሔርም አገልጋዮች ካህናት ከወለሉና ከመሠዊያው መካከል እያለቀሱ:- አቤቱ ለሕዝቡ ራራ፤ . . .» ኢዩ 2:15-17።

በጾም ውስጥ መንፈስን የመመገብ አዎንታዊ ጎን ስላለ ጾም ማለት ሥጋን ከመብል ማራቆት ማለት አይደለም።

በመሆኑም ጾም ከጸሎት ጋር የተያያዘ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታዋቂ የሆኑት አጽዋማት ማለትም የነህምያ፣ የዕዝራ፣ የዳንኤልና የነነዌ ሰዎች ጾም ከቤተ ክርስቲያን ጸሎት ጋር የተያያዙ ናቸው። ይህ «ጾምን ቀድሱ፤ጉባኤውንም አውጁ . . .» በሚለው ቃል ውስጥ ግልጽ ነው።

ይህ ደግሞ መንፈስን ከፍ-ከፍ ለማድረግና ሥጋን ለማጎሳቆል መንፈሳዊውን ዕድል ይሰጣል።

ሥጋን ማጎሳቆል ምክንያት ነው፤ዋናው ዓላማ ግን መንፈስን በጸሎት፣ በተመስጦ፣ በንባብ፣ በሁሉም የጸጋ ስጦታዎች ከፍ ማድረግ ነው፤ይህ ደግሞ ከሥጋዊ እንቅፋቶች በራቀ ሁኔታ መከወን አለበት።

እዚህ ላይ እግዚአብሔር መንፈሳዊ ያልሆኑ አጽዋማትን አለመቀበሉን ማስታወስ ያስፈልገናል። ከእነዚህም መካከል የግብዞች ጾም (ማቴ 6:2)፣ የፈሪሳዊው ጾም (ሉቃ 18:11) እና ነቢዩ ኢሳይያስ የገለጸው የተሳሳተ የጾም መንገድ (ኢሳ 58:3-7) ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

(7)
ስንዴና እንክርዳድ

የእናንተ ተግባር እንክርዳዱን መንቀል አይደለም፤እንደ ስንዴው ማደግ እንጂ። የስንዴው አጫጅ ሲመጣ የስንዴያችሁን ጎተራ ሞልቶ ስለሚያገኘው የእርሱ ጎተራ እስኪሞላ ድረስ ሠላሳ፣ ስድሳና መቶ ፍሬ ይሰበስባል።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሌሎች ሰዎችን ስሕተት በመቃወም ጊዜውን አላባከነም።

እርሱ በዚህ ምድር ሳለ የሥጋዌ ዘመኑን ከሰዎች ስሕተትና ጥፋት እንዲሁም ከኅብረተሰቡና ከቤተ ክርስቲያን ጋር በመታገል አላሳለፈውም። የእርሱ ትኩረት የአዳዲስ መመሪያዎችን መሠረት መጣል፣ መገንባት፣ ሰዎች በእነዚህ መመሪያዎች እንዲያምኑና በሁሉም ሥፍራዎች እንዲያስፋፉ ማድረግ ነበር።

እንክርዳዱን በመሰብሰብ ላይ ማተኮር ኃይል ማባከን ነው።

ዲያብሎስ ባላችሁ ጊዜ ሁሉ በተለያዩ ችግሮች ባተሌ ሊያደርጋችሁና ማብቂያ የሌላቸው ስሕተቶችን ሊያቀርብላችሁ ዝግጁ ነው። የእርሱ ዋና ዓላማ እነዚህን ስሕተቶች በመዋጋት ራሳችሁንና የእግዚአብሔርን መንግሥት ከመገንባት እንድትርቁ ማድረግ ነው።

እንክርዳዱን በመንቀል ውስጥ ውስጣዊ ሰላማችሁንና ከሰዎች ጋር ያላችሁን ሰላም ልታጡት ትችላላችሁ፤በትግል ውስጥ መኖርን ጀምራችኋልና።

ስለሆነም አርምሞአችሁን፣ የመንፈስ እርጋታችሁንና ትሕትናችሁን ጨምራችሁ ታጡታላችሁ። እነዚህ ችግሮች ማብቂያ የሌለውን በሁከት የተሞላ ሁኔታና በማያቋርጥ ቍጣ እንድትከበቡ በሚያደርጓችሁ ልዩነቶች ውስጥ እንድትቆዩ ያነሳሷችኋል።

ጨዋነታችሁንና ዝምታችሁን እንዳጣችሁት እንዲሁ ፈገግታችሁንም ታጡታላችሁ። ሰዎች ሁልጊዜ በእናንተ ላይ የሚመለከቱት ፈገግታ የሌለበት ጭጋጋማ ገጽታን ነው። ንዴትና ኀዘን ስለሚቆጣጠሯችሁም ለእግዚአብሔር ስትሉ የደረሰባችሁ ንዴትና ኀዘን አድርጋችሁ ትቀበሉታላችሁ።

ይህ ደግሞ ወደ ልብ ጭካኔ ይመራችኋል . . .

ሁልጊዜ የተሳሳቱት ላይ ትፈርዱባቸዋላችሁ፤በስሕተቶቸው ላይ ታምጻላችሁ፤ ይህን በማድረጋችሁም በእነርሱ ዘንድ ያለውን እንክርዳድ እንደ መንቀል አድርጋችሁ ትወስዱታላችሁ። ሁልጊዜ ሰዎች ላይ ትጮሃላችሁ፣ ሰዎችን ትገሥጻላችሁ፣ ትቆጣላችሁ፣ በማንኛውም ነገርም ትበሳጫላችሁ።

በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ ለሰዎች ያላችሁን ፍቅርና ጨዋነታችሁን ታጡታላችሁ። በመሆኑም በሌሎች ሰዎች ዘንድ ያለውን እንክርዳድ ስትሰበስቡ በእናንተ ውስጥ ያለውን ስንዴ ትነቅሉታላችሁ። ከዚህ በኋላ ሰዎች በሁሉም ነገር ውስጥ የሚመለከቷችሁ እንክርዳድ አድርገው ነው።

በተመሳሳይ ጊዜ ስንዴያቸውን ጠብቀው እንክርዳዶቹን መንቀል የሚችሉት በጣም ጥቂቶች ናቸው። በመሆኑም እንክርዳዱን እንነቅላለን ሲሉ ስንዴውን እንዳይነቅሉ እግዚአብሔር ልጆቹን ይከለክላቸዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ «ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉ አትመልሱ. . .» (ሮሜ 12:16) ብሎ በመናገሩ መልካም ብሏል።

እንክርዳዶቹን ለመንቀል ወይም ለመሰብሰብ ተመራጩ መንገድ እነርሱን በመልካም ሥራ ማሸነፍ ነው። አንድ ጠቢብ ሰው «ጨለማውን ከማውገዝ ሻማ አብራ» በማለት ተናግሯል።

(8)
ችግሮችን የማቃለያ መንገዶች

ማንኛውንም ሰው ችግሮች ይገጥሙታል፤ጠቃሚው ነገር ግን ከችግሮች ጋር ተጋፍጦ መፍትሔ ላይ መድረስ ነው።

አንዳንድ ሰዎች የገጠማቸውን ችግር በኃይልና በድርድር ለማቃለል ይሞክራሉ ወይም ምድራዊ ኃይል ወይም የድርጊትና የቃላት ኃይልን ይጠቀማሉ።

አንድ ሰው ችግር የፈጠረው ሰው ላይ በቁጣ ቃል ሲናገርና ኃይል ሲጠቀም ይችል ይሆናል። ከእነዚህ ሰዎች ጋር ግጭት የመፍጠሩ ውጤት ግን የእነርሱን ወዳጅነትና ፍቅር ማጣት ይሆናል።

ሌላ አንድ ሰው ደግሞ ሥልጣኑን በመጠቀም፣ ትእዛዝ በማስተላለፍና ማገጃ በመጣል ለተከሰተው ችግር መፍትሔ ይሰጣል። ይህ በአባትና በልጅ፣ በባልና በሚስት እንዲሁም በአለቃና በበታች ሠራተኞቹ መካከል ሊከሰት ይችላል። አንዳችም የሚያስወጣው ነገር ስለሌለ ሥልጣንን መጠቀም ለእርሱ ቀላል ነገር ነው። ይሁን እንጂ ሥልጣን በራሱ ብዛት ያላቸው ተመሳሳይ ጠቦችን በውስጡ ያቀፈ ሊሆን

ይችላል። ይህ ደግሞ በሥልጣን ላይ ዓመፅ ወደ ማስነሣት ይመራል። ችግሩ ገና ከጅምሩ መፍትሔ ካገኘ ግን በልብ፣ በስሜቶችና በግንኙነቶች ውስጥ ሊቀር ይችላል።

አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ከችግር መሸሽን እንደ መፍትሔ አድርገው ስለሚቆጥሩ ከችግር ይሸሻሉ።

እነዚህ ሰዎች ችግርን ሊያስተላልፉት ወይም ሊርቁት ወይም ሊያመልጡት ይሞክራሉ። ችግሩ ከጥቂት ቆይታ በኋላ ተመልሶ ሊከሰት ስለሚችል፣ ስለሚያውካቸውና ስላላቃለሉት መፍትሔ ሊሆን አይችልም።

አንዳንድ ሰዎች ደግሞ በመርሳት የአንድን ችግር መፍትሔ ለማግኘት ይሞክራሉ።

አንድ ሰው ምንም ዓይነት ችግር እንደሌለ አድርጎ ራሱን ሊያሳምን ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ ሰው የሌላውን ሰው ዓይኖች በመጨፈንና ችግሩን እንዳይመለከተው በማድረግ እንዳይጨናነቅ ለማድረግ የሚሞክር ይመስላል። ይህ ሰው ስለ ችግሩ አይናገር፣ አያስበው፣ አያጥናው እንጂ ባለበት ስፍራ እንዳለ ይቆያል።

በተገቢው መንገድ፣ ፀጥ ባለ አሳብና በጥበብ ከተመለከቱት ግን ለእያንዳንዱ ችግር ብዙ መፍትሔዎች አሉ። ንጉሥ ሰሎሞን ችግሮች ሲያጋጥሙትና ሲጋፈጡት መፍትሔ የሚሰጣቸው በዚህ ዓይነት አካሄድ ነው።

ቅዱሳን አባቶቻችን እንደሚያደርጉት አንድን ችግር በእግዚአብሔር ፊት በማስቀመጥ፣ በመጸለይና በመጾም መፍትሔ ማግኘት ይቻላል።

አንዳንዶቹ ችግሮች አስቸኳይ ፈጣን ውሳኔ ሲፈልጉ ሌሎቹ ደግሞ መፍትሔ የሚያገኙት በትዕግሥትና በጽናት ነው።

ሌላ ችግር በመፍጠር ለችግር መፍትሔ ለማግኘት መሞከር ተገቢ አይደለም።

ልክ እንደዚሁ የተሳሳተ ነገር በመፈጸም ወይም መንፈሳዊ ያልሆነ ዘዴ በመከተል ለችግር መፍትሔ ማምጣት አይቻልም። ይህን የሚያደርጉ ሰዎች ለችግሮቻቸው መፍትሔ ለመስጠት ሲፈልጉ ይዋሻሉ ወይም ያፌዛሉ ወይም ዙሪያ ጥምጥም ምክንያት ያቀርባሉ ወይም ሰዎችን የሚያታልሉ ዓለማዊ ዘዴዎችንና ማታለያዎችን ይደረድራሉ።

(9)
በጭንቀት ጊዜ የሚያጽናኑ ቃላት

ነቢዩ ዳዊት ለእግዚአብሔር እንዲህ ብሎት ነበር:- «ለባሪያህ ተስፋ ያስደረግኸውን ቃልህን አስብ። ቃልህ ሕያው አድርጎኛልና፤ይህች በመከራዬ ደስ አሰኘችኝ።» 118:49እና50።

እናንተም እንዲሁ በጭንቀትና በመከራ ጊዜ የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት (ጥቅሶች) ካስታወሳችሁ ትጽናናላችሁ፡-

+ «. . . እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።» ማቴ 28:20።

+ «በአንቺ ላይ የተሠራ መሣሪያ ሁሉ አይከናወንም. . .» ኢሳ 53:17።

+ «. . . እኔ ነኝ አትፍሩ አላቸው።» ዮሐ 6:20።

+ «እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል፤እናንተም ዝም ትላላችሁ።» ዘጸ 14:14።

+ «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን፤ሰዎች በእኛ ላይ በተነሡ ጊዜ፤ቍጣቸው በላያችን በነደደ ጊዜ፤በዚያን ጊዜ ሕያዋን ሳለን በዋጡን ነበር፤. . . ለጥርሳቸው ንክሻ ያላደረገን እግዚአብሔር ይባረክ። ነፍሳችን እንደ ወፍ ከአዳኞች ወጥመድ አመለጠች፤ወጥመድ ተሰበረ እኛም አመለጥን። ረድኤታችን ሰማይንና ምድርን በሠራ በእግዚአብሔር ነው።» መዝ 123:2፤3፤6-8።

+ «ጻድቃን እጃቸውን ወደ ክፋት እንዳይዘረጉ፤የኃጥአን በትር በጻድቃን ዕጣ ላይ አይኖርም።» መዝ 124:3።

+ «እነሆም እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፤በምትሄድባትም መንገድ ሁሉ እጠብቅሃለሁ፤ ወደዚህችም ምድር እመልስሃለሁ፤የነገርሁህን ሁሉ እስካደርግልህ ድረስ አልተውህምና።» ዘፍ 28:15።

+ «ከአንተ ጋር ይዋጋሉ፤ነገር ግን አድንህ ዘንድ እኔ ከአንተ ጋር ነኝና ድል አይነሡህም፤ይላል እግዚአብሔር።» ኤር 1:19።

+ «. . . እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፤ማንም ክፉ ሊያደርግብህ የሚነሣብህ የለምና አትፍራ፤. . .» ሐዋ 18:9እና10።

+ «በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ነገር ግን አይዞአችሁ፤እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ።» ዮሐ 16:33።

+ «ከትንሽነቴ ጀምሮ ብዙ ጊዜ ተሰለፉብኝ፤ነገር ግን አላሸነፉኝም። ኃጢአተኞች በጀርባዬ ላይ መቱኝ፤ኃጢአታቸውንም አስረዘሟት። እግዚአብሔር ጻድቅ ነው፤የኃጢአተኞችን አንገታቸውን ቆረጠ።» መዝ 128:2-4።

+ «ገፋኸኝ፤ለመውደቅም ተንገደገድሁ፤እግዚአብሔር ግን አገዘኝ።» መዝ 117:13።

+ «በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ፤አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤. . .» መዝ 22:4።

+ «በአጠገብህ ሺህ በቀኝህም አሥር ሺህ ይወድቃሉ፤ወደ አንተ ግን አይቀርብም። በዐይኖችህ ብቻ ትመለከታለህ፤ የኃጥአንንም ብድራት ታያለህ።» መዝ 90:7እና8።

+ «እግዚአብሔር ከክፉ ሁሉ ይጠብቅሃል፤ነፍስህንም ይጠብቃታል። ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም እግዚአብሔር መውጣትህንና መግባትህን ይጠብቃል።» መዝ 120:7እና8።

+ «እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው፤የሚያስፈራኝ ማን ነው? እግዚአብሔር የሕይወቴ መታመኛዋ ነው፤የሚያስደነግጠኝ ማን ነው?. . . ሠራዊትም ቢሰፍርብኝ ልቤ አይፈራም፤ሰልፍም ቢነሣብኝ በዚህ እተማመናለሁ።» መዝ 26:1እና3።

+ «ኃያል ሆይ፤በቍንጅናህና በውበትህ ሰይፍህን በወገብህ ታጠቅ።» መዝ 44:3።

+ «. . . የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።» ማቴ 16:18።

(10)
በሥራ ያልተገለጠ አሳብና ተግባራዊ ሕይወት

በሥራ ያልተገለጠ አሳብ በልምድ ያልተደገፈ ወይም በትክክል እውነተኛ ጥናት ያልተካሄደበት አሳብ ብቻ ነው። እንዲህ ዓይነቱ አሳብ በመንገዱ ላይ ምንም ዓይነት እንቅፋት ሳይገጥመው ነገሮች ሁሉ በሚገባ እንደሚከናወኑ የሚያስበው አሳብ ነው። ይህን አሳብ የሚያስበው ሰው በአእምሮው ውስጥ የሚከተላቸው መመሪያዎች አሉት።

ይህ ደግሞ በሁለት ሀገሮች መካከል በባሕር ላይ ያለው ርቀት በእርግጠኝነት ብዙ ማይሎች እንደሚሆን አድርጎ የሚናገረውን ሰው ይመስላል። መርከቡ በተወሰነ ፍጥነት ቢቀዝፍ በዚህ ቀንና በዚህ ሰዓት ይደርሳል ይላል . . . መርከቡ ገሀድ በሆነው ሐቅ መጓዙን ሲቀጥል በማዕበል ወይም በነፋስ ሲመታ መጓዙን ሲቀጥል አይችልም ወይም በትግል ሲንቀሳቀስ ይሞክራል ወይም አቅጣጫውን ይቀይራል። ከዚህ የተነሣ ይህ መርከብ ከብዙ ቀናት በኋላ ይደርሳል ወይም ከነጭራሹ አይደርስም።

ገሀዱ ሐቅ በእንቅፋቶችና በመሰናክሎች የታጠረ ስለሆነ ማንም ሊያውቀው አይችልም። ይህን ሊያውቅ የሚችለው በተግባራዊው ሕይወት ውስጥ ልምድ ያለውና የሕይወትን መስፈሪያ እስከ ደቂቃ ድረስ ወርዶ በዝርዝር የሚናገረው ሰው ነው።

በሥራ ያልተገለጠውን አሳብ የሚያስበው ሰው ግን ጠረጴዛው አጠገብ ተቀምጦ የሚጽፈው አሳቡን ነው፤አሳቡን ብቻ! ከዚህ በኋላም ለምን በሥራ ላይ ሊውል እንዳልቻለ በማሰብ ግራ ይጋባል። ሂስ ሊሰጥና ሊወቅስም ይነሣል! ከወቀሳው አልፎ በመሄድም እስከ ክስ ሊደርስ ይችላል። ሌላው እንኳ ቢቀር ሌሎች ሰዎችን ስለ ቸልተኝነት ወይም ስለ ግድ የለሽነት ወይም ስለ እውቀት ጉድለት ይከሳል!!

በሥራ ባልተገለጡ በእነዚህ ክሶች ምክንያት ሊመጡ ስለሚችሉት እንቅፋቶች ግን የሚገነዘበው ነገር አይኖረውም። «ከሰነፍ ለሚብሰው አሳቢ ወዮታ አለበት!» የሚለው አባባል ከዚህ ጋር ይሄዳል።

ይህ ሰው የጉዳዩን ሁኔታ፣ ተግባራዊ መፍትሔዎችንና እንቅፋቶችን መገንዘብ ቢችል ኖሮ ብዛት ያላቸው አሳቦቹን ማገጣጠም ወይም ማገናኘት በቻለ ነበር።

አንድ እንቅፋት በጥበብ የታቀዱ እቅዶችን ሊለውጥ ይችላል።

እውነትን መጋፈጥ የሚችልና የሕይወት ተሞክሮ ያለው ተግባራዊ ሰው ነገሮችን በሚገባ ስለሚረዳ እንደ እርሱ እቅድና ግጥምጥም ሊቀጥል አይፈልግም።

እርሱ ስለሚራመድበት ምድር ያውቃል . . . አንዳንድ እቅዶችን ያስባል . . . ይህንንም ግንዛቤው ውስጥ ያስገባል . . . የሚገጥመው ውድቀት ሁሉ በልምዱና በእውቀቱ ላይ የሚደመር ይሆናል። ይህ ደግሞ የወደፊት እሳቤውን ይበልጥ ተግራባዊ ያደርግለታል።

በሥራ ያልተደገፈ ወይም በቃል ብቻ የሚገለጥ አሳብ የሚያስብ ሰው ብዛት ያላቸው ትእዛዛትንና ውሳኔዎችን በማስተላለፍ ተሐድሶ እንደሚያመጣ አድርጎ

ያስባል። ተግባራዊ አሳብ የሚያስበው ግን የእነዚህ ውሳኔዎች ውጤታማነት እስከ ምን ድረስ እንደ ሆነ ይጠይቃል።

እርሱ አንድ ውሳኔ ሲወስን የእድገት መስመሩን ለመመልከት ይችል ዘንድ ተግባራዊነቱን ይከታተላል። እድገቱ እየተንቀሳቀሰ ነው ወይስ ቆሟል? ከቆመ ለምን? ለዚህ መፍትሔው ምንድር ነው? ሌላ ማሻሻያ አስፈልጎታል? ይላል።

ወንድሜ ሆይ፤አሳብህ በሥራ ያልተደገፈልህ ሰው አትሁን፤ሌሎችን ለመውቀስ ችኩል አትሁን፤ይልቁንም ሐቅ የሆኑትን ነገሮች አጥና ተግባራዊም ሁን።

(11)
የሰው ቁጣ

አንዳንድ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ሲባል የሚመጣ ንዴት ይኖራል። ይሁን እንጂ በንዴቱ ውስጥ ግልፍተኛነትና አልበርድ ባይነት አይኖርም፤ይህ ንዴት መንፈሳዊ ቅንዓት ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ስለ ሰው ቍጣ እንዲህ በማለት ተናግሯል፦ «. . . የሰው ቍጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሠራምና።» ያዕ 1፡20።

ቅዱሳን አባቶቻችን ቍጣን በማውገዝ የተናገሯቸው ብዙ ብሒሎች አሉ።

ማር ኦውጎሪስ እንዲህ ብሏል፦ «የተቆጣ ሰው ጸሎት የረከሰና ተቀባይነት ያጣ ዕጣን ነው፤የተቆጣ ሰው መሥዋዕት ተቀባይነት የለውም። ቍጣ የዕብደት ድርጊት ነው . . . ሰዎችን እንደ አውሬዎች ያደርጋቸዋል . . . የተቆጣ ሰው ዐይኖች በደም የተሞሉ ክፉዎች ናቸው፤ የጨዋ ሰው ፊት ግን ብሩኅ ሲሆኑ ዐይኖቹም በክብር ይመለከታሉ።»

አባ አጋቶንም እንዲህ ይል ነበር፦ «የተቆጣ ሰው ሙት ቢያስነሣ እንኳ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም፤ ሰዎችም እርሱን አይቀርቡትም።»

አንድ ትልቅ ሰው ደግሞ ይህን ብሏል፦ «ወንድሙ ሲጨቃጨቀው ልቡ የማያዝንበት ሰው እንደ መላእክት ነው። ሲጨቃጨቀው መልሶ የማይጨቃጨቀው ከሆነ ድርጊቱ ስለሚጸጽተው ፈጥኖ ይታረቀዋል፤ሙግት የሚፈጥሩ ሰዎች ጠባይ ይህ ነውና። ከዚህ በተቃራኒው ወንድሞቹን የሚያውክና በእነርሱ የሚናደድ ሰው በልቡ ውስጥ ጥላቻ ይሰፍራል። እንዲህ ዓይነቱ ሰው የዲያብሎስ ተከታይና ለእግዚአብሔር ያልታዘዘ ነው። ስለሆነም ይህ ሰው የወንድሞቹን ኃጢአት ይቅር እስካላለ ድረስ እግዚአብሔርም የእርሱን ኃጢአቶች ይቅር አይልለትም።

ሶሪያዊው ቅዱስ ኤፍሬም ደግሞ እንዲህ በማለት ተናግሯል፦ «ቍጡ ሰው ራሱን ይገድላል። ለወቀሳ እንግዳና ሰውነቱ በየጊዜው የሚጠወልግበት በሽተኛ ይሆንበታል። መንፈሱ በኀዘን ስለሚዋጥ በሰው ሁሉ ዘንድ የተጠላ ይሆናል።»

ይኸው ቅዱስ ኤፍሬም ሶሪያዊ «ቅናትን በልቡ ውስጥ የሚሸሽግ ሰው በጭኑ ላይ እባብ የሚያስቀምጥ ሰውን ይመስላል። ጭስ ንቦችን እንደሚያባርር ሁሉ ጥላቻም እውቀትን ከልብ ውስጥ ያባርራል።» ብሏል።

አባ ኢሳይያስ «ቍጣ አንተ የምትፈልገውን ያለ ምንም ትሕትና በኃይል እንድታገኘው ይመኛል።» በማለት ተናግሯል።

ቅዱስ አውግስጢንም ስለ ቍጣ የሚከተለውን ተናግሯል፦ «ቍጣ ምንድር ነው? ቍጣ ለበቀላ የሚሆን ፍላጎት ነው. . . እኛ እንደምንፈጽመው ጥቃት እግዚአብሔር በእኛ ላይ በቁጭት የተሞላ የብቀላ እርምጃ ሊወስድብን ባይፈልግም እኛ ለራሳችን ብቀላ በመጠየቅ በየዕለቱ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት እንሠራለን?!

የኒሲስ ጳጳስ የነበረው ቅዱስ ጎርጎርዮስ «ቍጣ ጥቁሩን ምሬት በመላ ሰውነት ላይ ያሰራጫል።» በማለት ተናግሯል።

የእሲውቱ ቅዱስ ዮሐንስ ደግሞ እንዲህ ብሏል፦ «የቍጣ መሣሪያ የሚጎዳው የሚጠቀምበትን ሰው ነው . . . በልብ ውስጥ ያለ ቍጣ በግንድ ውስጥ እንዳለ ምስጥ ነው።»

ቁጣን በማስመልከት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተዛማጅ ጥቅሶችን ብንፈልግ የሚከተሉትን እናገኛለን፦ «በነፍስህ ለቍጣ ችኩል አትሁን፤ቍጣ በሰነፍ ብብት ያርፋልና።» መክ 7፡9።

እንዲህም ይላል፦ «ከቍጡ ሰው ጋር ባልንጀራ አትሁን፤ከወፈፍተኛም ጋር አትሂድ፤መንገዱን እንዳትማር፤ለነፍስህም ወጥመድ እንዳታገኝህ።» ምሳ 22፡24።

(12)
መንቻካነት

ትሑት ሰው አመለካከቱን ሲያቆምና የተሳሳተ መሆኑን በጸጋ በመቀበል ይህን ስሕተቱን ሲያርም ይችላል።

የዋህ ሰው ደግሞ ከሁሉም ሰው ጋር ስለሚግባባ ብዙ አይከራከርም ወይም አይመናቸክም።

እርሱ የሌላውን ሰው አሳብ የሚመለከተው በአክብሮትና በማዕርግ እንጂ እንደሚያዳላ ሰው ወይም እንደ ጠላት አይደለም። በሰውየው አመለካከት ውስጥ ያለውን በጎ ነገር ይፈልጋል፤ ትክክል ሆኖ ካገኘውም ይቀበለዋል።

አንዳንድ ሰዎችን ስታነጋግራቸው አዕምሮአቸው ማንኛውንም ነገር ለመረዳት ሙሉ ለሙሉ እንደ ተቆለፈ አድርገው ሊያሳስቧችሁ ይሞክራችኋል። ለእነዚህ ሰዎች ከራሳቸው አመለካከት በስተቀር ሌላ ምንም ነገር በእነርሱ ዘንድ ተቀባይነት የለውም። በመንቻካነታቸውም ማንኛውንም ጉዳይ ያለ ምንም ውይይት ተቀባይነት ያሳጡታል።

አንድ ሰው የእርሱን አመለካከት የሚቃወሙ ብዛት ያላቸው ተቃውሞዎች ቢኖሩ፣ ደረጃቸው ምንም ከፍ ያለ ቢሆንና ንግግራቸው የተፈለገውን ያህል አሳማኝ ቢሆንበትም ባይሆንበትም በመንቻካነቱ ሊቀጥል ይችላል።

ይህ እልህ ከተዳፈነ ኩራት የመጣ ሊሆን ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ ሰው አመለካከቱን ተሸናፊ ላለማድረግ ራሱን ከፍ ማድረግና ኩራት አንቀው ይይዙታል።

አንድ ሰው በአንድ ሰው መንቻካነት ላይ ለረዥም ጊዜ ሊቆይ ይችላል።

አንድ ሰው በመመናቸክ ቆይታ ውስጥ የሚመጡ መጥፎ ውጤቶችን፣ ውጤቶቹ በሰውየው የተሳሳተ አመለካከት ላይ ተጣብቀው መቆየታቸውንና የሰውየውን መንቻካነት ቢመለከትም ግድ ላይሰጠው ይችላል።

መናፍቃን ሁሉንም አብያተ ክርስቲያናትም ሆነ ምኩራብ ስለማይሰሙና ቤተ ክርስቲያንን በግድሴሽነት ስለሚከፋፍሉ ችኮ ለሆኑ ሰዎች ምሳሌዎች ይሆኑናል።

ችኮ ሰው ሰዎችንም ሆነ ራሱን ያጣል። ከዚህ በተጨማሪ እምነቱን አልፎ ተርፎም ዘላለማዊነቱን ያጣል።

በተመሳሳይ ጊዜ የልብ ንጽሕናውንም ያጣል . . . ከዚህ የተነሣም ትሕትና፣ ፍቅር፣ መረዳትና ጨዋነት በእርሱ ዘንድ አይኖሩም።

በመንቻካነትና ትክክል በሆነው በጥብቅነት መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። እኛ መንቻካ የምንለው ነገር በተሳሳተ ነገር ላይ የሙጢኝ ማለትን ነው።

መንቻካ የሆኑ ሰዎች መንቻካነታቸውን የሰብእናቸው ጥንካሬ አድርገው ከመቁጠራቸው በተጨማሪ በተቃውሟቸው ውስጥ ራሳቸውን ጀግኖች አድርገው መመልከታቸው አስደናቂ ነገር ነው።

አንዳንድ ሰዎች ደካማ በሆነ ሰብእናቸው እነዚህን ሰዎች ሊያደንቋቸው ይችላሉ። ታዲያ እነዚህ ሰዎች በእነዚህ ሰዎች ሲታጀቡ መንቻካነታቸው ይበልጥ እያደገ ይሄዳል። በቁጥር የበዙ አጋሮች እንዳሏቸው አድርገውም ይቆጥራሉ። ይህንንም፣ ለአመለካከታቸውና ለአስተሳሰባቸው ትክክል መሆን በቂ ማስረጃ አድርገው ያቀርቡታል።

መጽሐፍ ቅዱስ ችኩነትን ከልብ ደንዳናነት ጋር ያገናኘዋል . . .

በጥፋቶቻቸው ላይ የሚመናቸኩ ችኮ ኃጢአተኞች ልባቸው ደንዳና ስለሆነ የጸጋ ሥራ አያለሰልሰውም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል፦ «ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ፤. . .» ዕብ 3:7።

(13)
መስቀሉ በሕይወታችን ውስጥ - «ሀ»

የመስቀል በዓልን በምናከብርበት ጊዜ የሚከተሉትን ነጥቦች እናስባለን፦

+ ከመስቀሉ ጋር ያደረግነው የመጀመሪያ ግንኙነት ፄተገለጠው በጥምቀቱ ውስጥ ነው፤ይህም ኃጢአት ባሪያዎቹ እንዳያደርገን አሮጌው የእኛ አዳም በተሰቀለ ጊዜ ነው።

+ ቤተ ክርስቲያን በሰማዕታት ዘመንና ከዚያ በኋላ በተከተሉት የሥቃይ ዘመናት ውስጥ መስቀሉን ተሸክማለች።

+ የመስቀሉ ውበት የተገለጠው ቤተ ክርስቲያን በደስታና በትዕግሥት ወይም ያለ ምንም ማማረርና ማጉረምረም መስቀሉን በመሸከሟ ነው።

መስቀሉን ቤተ ክርስቲያን የምትፈልገውና የምትቀርበው ሆኖ ስለ ተሰጠ ተናፋቂ ሆኗል።

ክርስቲያኖች ሞትን የተቀበሉበት መንገድ አሕዛብን አስደንቋቸዋል። መስቀሉ ክርስቲያኖች ዓለምን ከነ ድሎቱና ፈንጠዝያው የሚክዱበትና በዘላለም ሕይወት ውስጥ የሚገኝ የእምነት ደስታ ነፀብራቅ ነው።

እስር ቤቶች ሞትን በደስታ ለመቀበል የተዘጋጁ ክርስቲያኖች መዝሙራትና ጸሎቶች የሚያስተጋቡባቸው ቤተ መቅደሶች ሆነው ተቀይረዋል።

+ መስቀሉን የምንሸከምበት ሦስተኛው ምክንያት ጠባቡ ደጅ ነው።

አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ሲል ራሱን ያስገድዳል። ራሱን ከዓለምና በውስጧ ካለው ምኞት ይለያል። ስለ እግዚአብሔር ብሎም ሁሉንም ነገር ይክዳል። የሚክደውም በጾም፣ በመታመን ፣ ራስን በመግዛትና የሌሎችን ጥቃት በመቻል ነው።

+ የድካም መስቀል በዚህኛው ምክንያት ውስጥ ሊካተት ይችላል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «. . . ነገር ግን እያንዳንዱ እንደ ራሱ ድካም መጠን የራሱን ደመወዝ ይቀበላል።» (1ኛ ቆሮ 3:8) ብሎ የተናገረውን ቃል በማሰብ ሰው እግዚአብሔርን በማገልገል ውስጥ ሥጋና ምኞቱን ይሰቅላል።

ክርስትና ከመስቀሉ ጋር አይነጣጠልም።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ . . .» (ዮሐ 16:33) እና «. . . ስለ ስሜ በሰዎች ዘንድ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ . . .» (ማቴ 10:22) የሚሉትን ቃላት በግልጽ አስቀምጦልናል።

+ እኛ በመስቀሉ ሐሴት እናደርጋለን፤በደስታ እንቀበለዋለን፤ ኃይላችን መሆኑንም እንገነዘባለን። ቅዱስ ጳውሎስ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፦ «የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፤ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና።» 1ኛ ቆሮ 1:18።

(14)
ቅንነት

ምናልባት ከአንዳንድ ሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት በቅንነት ላይ የተመሠረተ ነው ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። ለመሆኑ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ተመሳሳይ ቅንነት አለው?

ለእግዚአብሔር የምንገባቸው ቃል ኪዳኖች ቅን ናቸው? ስለ መንፈሳዊ ሕይወታችን የምንወስናቸው የግል ውሳኔዎቻችን ጥብቅነት አላቸው? ወይስ ለማንኛውም ነገር ግድ እንደሌለንና ተግባራዊ እርምጃ መውሰድ እንደማንችል ለሰዎች ቃል ኪዳን ከገባን በኋላ የገባነውን ቃል ኪዳን እናፈርሳለን?

ለእግዚአብሔር የምንገባቸው ስእለቶች ጥብቅና ቅን ናቸው? ወይስ በሕይወታችን ውስጥ በጣም ወሳኝ በሆኑ ወቅቶች ከእግዚአብሔር ጋር ጠቃሚ ቃል ኪዳኖች ከገባን በኋላ እነዚህ ወሳኝና ከባድ ወቅቶች ሲያልፉ እነዚህ ቃል ኪዳኖቻችንን ልንሰርዛቸው ወይም ልንቀይራቸው እንሞክራለን?

ከእግዚአብሔር ጋር የተቀደሰ ሕይወት ለመምራት በሙሉ ልባችን ወስነን ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል ስንዘጋጅ ይህ ውሳኔያችንን እንጠብቃለን ወይስ የልባችንን ውጥኖችና የንስሓ ሕይወታችንን ፈጽመን እንዘነጋቸዋለን?

አጥብቀን ልንከተለው የሚገባን ቁርጥ ያለ መስመር አለን ወይስ ልክ ነፋስ አንድ ላባን በፈለገው አቅጣጫ ወዲያና ወዲህ እንደሚያነፍሰው ነን?

በመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ ከትክክለኛው መንገድ ሳይወጣ፣ ጸጋ ለሚገኝበት ዘዴ ቸልተኝነት ሳያሳይና ያለ ምንም ስንፍና ያገለግል ዘንድ በተወሰኑ መመሪያዎች የተገደበ ቅንነት ሊኖር ይችላልን?

ንስሐ በመግባታቸው ላይ ጥብቅ የሆኑ እንደ ሙሴ ጸሊም፣ እንደ አውግስጢንና እንደ ግብጻዊቷ ማርያም ያሉ ሰዎች ቅዱሳን ንስሐ ገብተዋል:: እነርሱ ዳግም ተመልሰው ይኖሩበት ዘንድ ወደ ቀደመ የሕይወት ዘይቤያቸው ፈጽሞ አልተመለሱም::

ከእግዚአብሔር ጋር ጓደኝነትና ወዳጅነት የመሠረቱ ሰዎች ከእርሱ ጋር ያላቸውን ወዳጅነት አይክዱም:: እነርሱ ጥብቅ በሆነ አካሄድ ለእርሱ የሚታመኑ፣ ለእርሱ መንፈሳቸው የተነሣሣና ለእርሱ ፍቅር ተግባራዊ ምላሽ የሚሰጡ ይሆናሉ::

በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ውስጥ ጥብቅ የሆኑ ሰዎች በፈተና ወይም በመከራ አይናወጡም:: እነርሱ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደሶች መሆናቸውንና የእርሱ መንፈስ በውስጣቸው እንደሚያድር አይዘነጉም:: እነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆኑና የእርሱን ምሳሌና አርአያ መጠበቅ እንዳለባቸውም አይረሱም::

በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ውስጥ ቅን የሆኑ ሰዎች ቅንነታቸውን በአነጋገራቸው፣ በአገልግሎት ውስጥ ባለ ጠባያቸው፣ በአምልኮታቸው፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር ባላቸው ግንኙነትና ልባቸውን በሚዋጋው በአሳብና በስሜት ውጊያ ውስጥ ጥብቅ የሆነ እርምጃ በመውሰድ ይገልጣሉ::

እነዚህ ሰዎች መመሪያዎች አሏቸው፤ለእነዚህ መመሪያዎቻቸውም የሚታዘዙ ናቸው::

ቅንነት የእግዚአብሔር ልጆች መለኪያ ስለሆነ ሁላችንም በቅንነት እንኑር:: ቅንነት የጽናት መኖር ማስረጃ ነው::

(15)
በጎ ቃላት

+ በጎነት ከመንፈስ ፍሬዎች መካከል አንዱ ስለሆነ መንፈሳዊው ሰው በጎ ቃላትን እንጂ መጥፎ ቃላትን አይጠቀምም:: አንተ በቃላትህ በጎነትና በስምምነትህ ነው የምትታወቀው?

+ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሣምራዊቷ ሴት ጋር እንዴት እንደተነጋገረ አስተውል:: ሴቲቱ ኃጢአቷ ከባድ ቢሆንም ክርስቶስ እንዲህ ነበር ያላት:- « . . . ባል የለኝም በማለትሽ መልካም ተናገርሽ፤አምስት ባሎች ነበሩሽና፤አሁን ከአንቺ ጋር ያለው ባልሽ አይደለም፤በዚህስ እውነት ተናገርሽ::» ዮሐ 4:17እና18:: ከአንቺ ጋር ያለው ባልሽ አይደለም፤በዚህስ እውነት ተናገርሽ::» ዮሐ 4:17እና18::

«ባሎች» የሚለው ቃል በጣም በጎ ቃል ነው:: ሰዎቹ ባሎቿ ባይሆኑም ጌታ ስለ እነርሱ መጥፎ ቃላት አልተናገራትም:: ክርስቶስ «አሁን ከአንቺ ጋር ያለው ሰው የአንቺ አይደለም» ብሎ የተናገረው ቃል እጅግ በጣም በጎ አገላለጽ ነው፤በዚህ አገላለጹ ውስጥ ሴቲቱን ሊጎዱ የሚችሉ ቃላት አልተናገረም::

+ ሰዎችን ከመጉዳት ይልቅ ልታሸንፏቸው ሞክሩ::

+ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ አቴና (አቴንስ) ሲገባ ከተማዋ በጣዖታት ተሞልታ ስላገኛት ተበሳጭቶ ነበር:: ይህ ቢሆንም ግን ሰዎቹን «የአቴና ሰዎች ሆይ፤ . እንግዲህ ይህን ሳታውቁ የምታመልኩትን እኔ እነግራችኋለሁ::» (ሐዋ 17:23) ነበር በትሕትና ያናገራቸው::

+ እግዚአብሔር አምላክ ስለ ኢዮብ ሲናገር በበጎ ቃላት አወድሶታል:: እርሱ ለሰይጣን እንዲህ ነበር ያለው:- « . . . ባሪያዬ ኢዮብን ተመለከትኸውን? በምድር ላይ እንደ እርሱ ፍጹምና ቅን፤እግዚአብሔርንም የሚፈራ ከክፋትም የራቀ ሰው የለም . . .» ኢዮ 1:8:: እንደ እግዚአብሔር ማንም ፍጹም ሰው ባይኖርም እርሱ ለኢዮብ ይህን ማዕረግ ሰጥቶታል::

+ ሕዝቦቿ ቀኝና ግራቸውን ለይተው ለማያውቁትና በኃጢአተኞች አሕዛብ ለተሞላችውን ለነነዌ ከተማ እግዚአብሔር የተናገረው ቃል ምንኛ በጎና ቅን ነበር:: እርሱ እንዲህ ነበር ያለው:- « . . . ለታላቂቱ ከተማ ለነነዌ አላዝንምን?» ዮና 4:11:: በእርግጥ ነነዌ ታላቅ ነበረች ወይስ የእግዚአብሔር በጎነት ነው ታላቅ ያደረጋት?

+ እግዚአብሔር ለሰዎች ያወጣው ስም ለበጎነቱ ሌላው ምሳሌያችን ነው:: እርሱ ስምዖንን - ጴጥሮስ ትርጉሙም ዓለት፤ አብራምን - አብርሃም ትርጉሙም የብዙኀን አባት ብሎ ጠርቷቸዋል:: እርሱ ለሰዎች ያወጣቸው ስሞች ውዳሴ ያዘሉ ናቸው::

በበጎ ቃላቶቻቸው ከሚታወቁት ቅዱሳን ሰዎች መካከል ዐይነ ሥውሩ ዲዲሞስ አንዱ ነው:: ይህ ሰው በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ውስጥ የሥነ መለኮት ትምህርት ኃላፊ ነበር::

የዚህ ሰው ዓላማ ሰዎችን በመርታት ላይ ያነጣጠረ አልነበረም፤ በማሳመን ላይ እንጂ:: አንድም ጊዜ ሰዎችን ለማጥፋት አልሞ አያውቅም ነበር::

+ እግዚአብሔር አምላክ መጥፎ ቃላት የሚጠቀሙትን ያወገዘው እንዲህ በማለት ነው:- « . . . ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፤ ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሃነም እሳት ፍርድ ይገባዋል::» ማቴ 5:22::

እግዚአብሔር በጎና ሰውን ሁሉ የሚወድ አምላክ ስለሆነ መጥፎ ቃላትን አይቀበልም:: የእርሱ አንደበት ጣፋጭ ስለሆነ ከንፈሮቹ ማር ነው የሚያንጠባጥቡት::

(16)
ጉጉት

ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ነው:: እግዚአብሔር የማይወሰን አምላክ ነው:: ሰው ግን ውሱን ነው:: ይሁን እንጂ ሰው ውሱን ቢሆንም በልቡ ጥልቀት ውስጥ የማይወሰን መሆንን ይናፍቃል:: ከዚህ ጋር በሚመሳሰል ምክንያት አለመሞትንና ዘላለማዊነትን ይናፍቃል ወይም ይመኛል:: ይህ ደግሞ ተጨማሪ አድርጎ የሚገልጽልን ሰው ፍጽምናን መናፈቁን ነው:: ሰዎች በውስጣቸው የመጓጓት ስሜት የሚፈጠርባቸው ከዚህ የተነሣ ነው::

ሰነፍ ሰው ያለው በእግዚአብሔር ምሳሌ አይደለም፤በእግዚአብሔር አምሳያ ያለው ሰው ግን እንደ ቅዱስ ጳውሎስ « . . . በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴም ወዳለው እየተዘረጋሁ. . .» (ፊልጵ 3:13) በማለት ይናገራል::

ይህ ሰው መንፈሳዊ ፍጽምናን የሚፈልግበት መንፈሳዊ ጉጉት ነው:: እንደ እርሱ ፍጹም አሳባዊነት ማንኛውም ዓይነት ደረጃ ላይ ቢደርስ የደረሰበትን በመርሳት ለሚበልጠው ነገር ወደፊት ይዘረጋል::

የቅዱሳን ሰዎች ትሕትና እና በትግል ውስጥ ያለ ድካም የሚመነጨው ከዚህ የተነሣ ነው::

መንፈሳዊው እድገት የሚገኘውም ከዚህ ነው።

እንዲህ ዓይነቱ ጉጉት ተቀባይነት አለው። እንደ ቅድስና ሥራ ስለሚፈለግም ማንም አይቃወመውም።

ይሁን እንጂ ለቁሳዊ ነገሮች የሚውል መጥፎ ጉጉት አለ።

ለምሳሌ፦ ሰነፉ ባለጸጋ እንዲህ በማለት ተናግሮ ነበር፦ «. . . ጎተራዬን አፍርሼ ሌላ የሚበልጥ እሠራለሁ፤ . . . ነፍሴንም፦ አንቺ ነፍሴ፤ ለብዙ ዘመን የሚቀር ብዙ በረከት አለሽ፤. . .» ሉቃ 12:18።

በቁሳዊ ጉጉት ውስጥ ያሉ ስሕተቶች ምንድር ናቸው?

/ሀ/ የመጀመሪያው ስሕተት ልብ ስሜቷንና ጊዜዋንና ሌሎች መንፈሳዊ ፍላጎቷን ከሚቆጣጠሩት ከቁሳዊ ነገሮች ጋር መጣበቋ ነው።

/ለ/ ሁለተኛው ስሕተት ሰው ለሌሎች ሰዎች የሚኖረውን ፍቅር የሚያሳጣው ፉክክር ውስጥ መግባቱ፣ በሌሎች ድካም ላይ የራሱን ክብር ለመገንባት ያስችለው ዘንድ መፈተኑና ከእነዚህ ሰዎች ጋር መጋጨቱና እነርሱን ማጥፋቱ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሰው የእርሱ ጉጉት ወይም ምኞት የመጀመሪያው ወይም ግንባር ቀደሙ እንዲሆን ስለሚፈልግ ተቃዋሚዎቹን በሙሉ ለማስወገድ ይሞክራል።

/ሐ/ ሦስተኛው ስህሕት ጉጉት ወደ ስስት ወይም በጭራሽ ወደማይረካ ምኞት መቀየሩ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሰው የተፈለገውን ያህል ቢያገኝ ወይም ቢኖረው አይረካም።

/መ/ አራተኛው ስሕተት ምክንያቶቹ የሰውየው ጉጉት ላይ የሚደርሱት በተሳሳተ ወይም መንፈሳዊ ባልሆነ መንገድ መሆኑ ነው። በዚህም አንድ ሰው ግቡን ለመምታት ሲል አንዳንድ አሳቦቹንና መንፈሳዊነቱን ይሰርዛል።

/ሠ/ ጉጉት ለሥልጣን ሊሆን ስለሚችል ሰውየውን አምባገነን አድርገው ይቀይሩታል። ይህ ሰው ተጽዕኖ ያሳድርበት ዘንድ በመንገዱ ላይ የሚቆም ሰው ካለ ያጠፋዋል።

/ረ/ ሰው በእነዚህ የተለያዩ ጉጉቶቹ ውስጥ ዘላለማዊነቱን ይረሳል፤አቅጣጫው ሙሉ ለሙሉ የሚያመለክተውም ዓለማዊውን አቅጣጫ ነው።

(17)
አነጋገርህ ይገልጥሃል

አነጋገርህ ሰብእናህን ያሳያል ወይም ይገልጣል። በውስጥህ ያለውን ገልጦ ያወጣል። ይህ በመሆኑም እንዲህ ተብሎ ተጸፈ፦ «. . . ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህና፤ከቃልህም የተነሣ ትኮነናለህ።» ማቴ 12:37።

ንግግር በቀላሉ የሚታይ ነገር አይደለም። በፈረድኸው ፍርድ ይፈረድብሃል፤«ደንቆሮ» በሚለው ስድብህም የገሃነም እሳት ይጠብቅሃል። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተናገረው አንዳንዱ ንግግር ሰውን ያረክሰዋል። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም አንደበትን «እሳት» በማለት ገልጦታል።

የአንደበት ስሕተቶች ብዙ ናቸው። ቅዱሳን ዝምታን እንዲመርጡ አድርጓቸዋል።

ስም ማጥፋት፣ ውሸት፣ መሳለቅ፣ ንቀት፣ ከባድና ቊጣ ቃላት፣ የጉራና የትዕቢት ንግግር፣ ማጋነን፣ የግብዝነትና የማጭበርበር ቃላት፣ የሐሰት ምስክርነትና የክህደት ቃላት፣ የጭቅጭቅና የንትርክ ቃላት . . . ወዘተ ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ናቸው።

ሰውየው ራሱን የሚጎዱ ስሕተቶችና ለሌሎች ሰዎች የማሰናከያ ድንጋይ የሆኑ ስሕተቶች አሉ።

ለምሳሌ፦ በሰዎች ጆሮዎች ውስጥ የሚንቆረቆሩ የአንድ ሰው ንግግሮች የእነዚህን ሰዎች ንጹህ ልብና አሳብ ያረክሳል ወይም እምነታቸውንና ትክክል የሆነውን እውቀታቸውን ያበላሻል። ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለ ግንኙነታቸውንም ያጠፋል በመካከላቸውም ግጭት ይፈጥራል። ከዚህ በተጨማሪ ስለ ጓደኞቻቸው ያላቸውን አመለካከት እንዲቀይሩም ያደርጋቸዋል።

የንግግር ጥፋቶች ብዙ ናቸው።

በአነጋገራችን ዝግ ካልን የምናስብበትን ጊዜ ለማግኘት ዕድሉን እንደምናገኝ መጽሐፍ ቅዱስ መክሮናል። ቅዱስ ያዕቆብ እንዲህ ነው ያለን፦ «. . . ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ፤ ለመናገርም የዘገየ፤ለቊጣም የዘገየ ይሁን፤. . .» ያዕ 1:19።

በአነጋገሩ የሚፈጥን ወይም የሚቸኩል ሰው ለስሕተት የተጋለጠ ነው። ይህን በማድረጉ ሊጸጸት ቢችልም ስሕተቱ አንድ ጊዜ በእርሱ ላይ ከተቆጠረበት በኋላ ስለሚሆን ሊመልሰው አይችልም።

ይህ ይሁን እንጂ ጠቃሚ ንግግርም አለ። ከቅዱሳን አባቶቻችን ጠቃሚ መንፈሳዊ ቃል ለመጠየቅ ከምድር ጫፍ የሚመጡ መንፈስ የወለዳቸው ሰዎች አሉ።

ሰዎች ለሌሎች ሰዎች ያስተላልፏቸው ዘንድ እግዚአብሔር በአንደበታቸው የሚያኖራቸው የመንፈስ ቃላትና የጸጋ ቃላት አሉ። «በእናንተ የሚናገር የአባታችሁ መንፈስ ነው እንጂ የምትናገሩ እናንተ አይደላችሁምና።» ማቴ 10:20። በዚህ ቃል መሠረት እግዚአብሔር በቅዱሳን ሰዎች ላይ እያደረ ይናገራል ማለት ነው።

ቀና ከሆኑት ቃላት መካከል፦ የበረከት ቃል፣ የማጽናኛ ቃል፣ የማበረታቻ ቃል፣ የመፍትሔ ቃል፣ የመመሪያ ቃል፣ የማስተማሪያ ቃልና በፍቅር ከተነገረ ደግሞ የተግሣጽ ቃል ይገኙበታል።

ከእግዚአብሔር የሆነ ቃል እንዲሁ ባዶውን አይመለስም። ብርቱ፣ ሕያውና ውጤታማ ነው። ልብን ጠልቆ ይገባል፤ፍሬ ያፈራል፤ነፍሳትን ይሰውጣል።

ስለዚህ መናገር መልካም ሲሆን ብቻ ተናገር፤እንዴትና መቼ መናገር እንዳለብህም እወቅ።

(18)
ተግባራዊው ሰው

ከእውነት በራቀ እምነት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች ልብ በወለደው የፈጠራ ዓለም ውስጥ የሚንሳፈፉ፣ በአየር ላይ ቤተ መንግሥት የሚገነቡና በቁም ቅዠት ውስጥ የሚኖሩ ናቸው። እነዚህ ሰዎች ተግባራዊ ሰዎች ስላልሆኑ አንዱንም ነገር እንኳ አይጨብጡትም።

ከእነዚህ በተቃራኒ በነባራዊውና በእውነተኛው ዓለም ውስጥ ሐቅ የሆነውን ነገር ተመርኩዘው የሚኖሩ ተግባራዊ ሰዎች አሉ::

ልብ በወለደው አሳባዊ ጥበቃ ውስጥ የሚኖር ሰው ተግባራዊ አይደለም::

ልክ እንደዚሁ አሁን ላለው ጊዜ ሳይሠራ ስላለፈው ጊዜ ቁጭ ብሎ የሚያለቅስ ሰው ተግባራዊ ሰው አይደለም፤ልቅሶ አንዳችም የሚጠቅመው ነገር የለምና::

ችግር ሲገጥመው ለችግሩ መፍትሔ ሳያስብ እንዲሁ የሚፍረከረክ ሰው የተግባር ሰው አይደለም፤መፍረክረክ ከምንም ሊያድነው አይችልምና::

ስለሚመጣው ውጤት ሳያሰላስል ተግባራዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚደራደር ወይም የአእምሮአቸውን ስፋትና የአስተሳሰባቸውን መንገድ ከግምት የማያስገቡ ሰዎች ተግባራዊ ሰዎች አይደሉም::

ውዳሴ በሚያቀርቡለት ሰዎች የሚታመን ሰው፤የሳቁለትን ሁሉ ጓደኞቹ የሚያደርግ ሰውና እርሱ ያመነበትን ነገር ሁሉ እውነት ነው ብሎ የሚቀበል ሰው ተግባራዊ ሰው አይደለም::

እርሱ እንጂ ስለሆነ ብቻ እንደሚያሸንፍና ይህንኑ ማሸነፉን ሰዎች እንዲቀበሉት የሚያስብ ሰው የድርጊት ወይም የተግባር ሰው አይደለም::

ተግባራዊ የሆነው ሰው ግን ምንም ነገር ሳይዘነጋ በዙሪያው ካሉት ነገሮች፣ ከእንቅፋቶቹና ከችግሮቹ ጋር በእውነት ውስጥ የሚኖር ሰው ነው::

ተግባራዊው ሰው ከሰዎች ጋር የሚስማማው ባሉበት ሁኔታ እንጂ መኖር ባለባቸው ሁኔታ አይደለም:: እርሱ ከሚስማማቸው ሰዎች ልብ ወለድ አሳባዊነትን አይጠብቅም:: ይልቁንም እንደ ማንኛውም ሰው ደካሞች መሆናቸውንና ሰዎች በመሆናቸው ስሕተት እንደማያጣቸው ይገነዘባል::

ተግባራዊው ሰው ችግሮቹን የሚያቃልለው በልቅሶና በሰቀቃ፤ በመነጫነጭና በማማረር አይደለም፡ እርሱ ችግሮቹን የሚጋፈጠው በተቀናጀ አሳብ፣ ጥበብና ተግባራዊ መፍትሔ ነው:: እግዚአብሔር ሥራውን እንዲባርክለትና ስኬታማነትን ያድለው ዘንድ ወደ እርሱ ይጸልያል::

ተግባራዊው ሰው በቃል ብቻ አይኖርም:: እርሱ ካለፈው ሕይወቱ በመማር ለአሁኑና ለሚመጣው ጊዜ ባለው ኃይል ሁሉ ይሠራል እንጂ ቀሪውን የሕይወቱን ጊዜ ባለፈ ነገር ላይ አያሳልፈውም::

(19)
መማር

መማር በሰው ሕይወት ውስጥ ይጀመር እንጂ ፈጽሞ ማብቂያ የለውም . . .

እንዲህ ያለው መማር አንድ ሰው ከደረሰበት የሕይወት ደረጃ ተሞክሮ አንጻር የተለያዩ ቅርጾች ሊኖሩት ይችላሉ::

የልጅነት ጊዜ በሁሉም ነገር የማመን ትምህርትን የሚወክል ዘመን ነው::

እንዲህ ያለው የመማር ዘመን ትምህርትን ይሻል፤እውቀትን ይፈልጋል ይጠይቃልም፤ማንኛውንም ነገር ያለ ምንም ክርክር ይቀበላል፤ የሌሎች ሰዎችን አርአያነት በመከተል ብዙ ነገሮችን ይቀስማል::

በአንደኛ ደረጃ ወይም በዝግጅት ጊዜ ሌላ ዓይነት መማር ይጀመራል፤ይህም መረዳትና መያዝ ነው:: በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚሰጠው ውይይትና ክርክርን መሠረት በማድረግና ጉዳዩን መርምረው ካወቁት በኋላ መረጃውን በማከማቸት የሚያዝ ይሆናል::

በከፍተኛ የትምህርት ተቋም ውስጥ በሚኖረው ቆይታ ውስጥ ሌላ ዓይነት መማር ይቀሰማል:: ይህም እስከተወሰነ መጠን ድረስ ራስን ችሎ መረጃዎችን መመርመርንና ማዘጋጀትን የሚያካትት ይሆናል::

ከከፍተኛ የትምህርት ተቋም ዓመታት በኋላ ሌላ ዓይነት ትምህርት ይጀመራል:: በዚህ ጊዜ ሰው ወደ ተግባራዊ ሕይወት ይገባል::

ይህ ክፍለ ጊዜ የተደነገጉ መርሐ ግብሮች ወይም ለፈተና የተወሰኑ ቀናት የሉትም:: አንድ ሰው የሚፈተነው በማንኛውም ጊዜ፣ በማንኛውም ነገርና ያለ ምንም የቀደመ ዝግጅት ነው::

እናንተም ራሳችሁን ማዘጋጀት ያለባችሁ እንዲህ ላለው ፈተና ነው::

ከሌሎች ሰዎች ልምድ ልትማሩ ትችላላችሁ:: ከዚህ በተጨማሪ ከታላላቆች፣ ከአስተማሪዎችና ከነፍስ አባቶች ልትማሩ ትችላላችሁ:: ከመጻሕፍትም መማር ትችላላችሁ::

ሰው በጥበብና በጥንቃቄ እንዲሁም መረጃን በመመርመርና በማጣራት ከእውቀት ምንጮች ሁሉ ሊጠጣ ያስፈልገዋል::

ሕይወትን ልታውቅ፤እንዴት ተግባራዊ መሆን እንዳለብህ፤ ከሰዎችና ከበላዮችህ ጋር እንዴት መስማማት እንደሚገባህና እንዴት ከእነርሱ ጋር መነጋገር እንዳለብህ ማወቅ አለብህ::

አንድ ሰው መቼ መናገር እንዳለበትና እንደሌለበት፤መቼ ጥብቅ መሆን እንዳለበትና እንደሌለበት፤መቼ ጥንቁቅ፣ መቼ መቅጣትና መቼ ይቅር ማለት እንደሚገባው ጠንቅቆ ማወቅ አለበት::

መማርን የሚወድ ሰው ከማንኛውም ነገር ይማራል::

እንዲህ ዓይነቱ ሰው ቅልጥፍናን ከጉንዳን፤እምነትን ደግሞ ከማይዘሩት፣ ከማያጭዱት፣ በጎተራ ከማይከቱትና የሰማዩ አባታቸው ከሚመግባቸው ከሰማይ ወፎች ይማራል::

በሕይወቱ ሙሉ የሚማር ሰው ብፁዕ ነው::

እንዲህ ዓይነቱ ሰው ሌሎች ከሚያስተምሩት የበለጠ ይማራል:: ከእያንዳንዱና ከማንኛውም ነገር እውቀትን የሚቀበል ሰው ትሕትናን ገንዘብ ማድረግ ይችላል::

(20)
እውነተኛ ደስታና የተሳሳተ ደስታ

እውነተኛው ደስታ በልብ ውስጥ ያለ ደስታ ከመሆኑም በላይ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- «የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም . . . ነው::» ገላ 5:22::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ተናገረው ደስታ የሚገኘው በጌታ ነው፡፡

ይህ ይሁን እንጂ ብዛት ያላቸው የተሳሳቱ ደስታዎች አሉ፡፡

የዮናስ ደስታ ለጭንቅላቱ ጥላ ከሰጠችው ቅጠል የመጣ ሲሆን የሰሎሞን ደስታ የተገኘው ደግሞ ከፀሐይ በታች ከለፋው ልፋቱ ነው፡፡ በመጨረሻ ግን ይህ ሁሉ ከንቱና ነፋስን እንደ መጨበጥ ሆኖበታል፡፡ ስለሆነም «. . . የሰነፎች ልብ ግን በደስታ ቤት ነው፡፡» (መክ 7:4) አለ፡፡

የተሳሳተ ደስታ ሌላ ምሳሌ የተገለጠው ታላቅየው ልጅ ለአባቱ «. . . ለእኔም ከወዳጆቼ ጋር ደስ እንዲለኝ አንድ ጥቦት እንኳ አልሰጠኸኝም፤. . .» (ሉቃ 15:29) ብሎ በተናገረ ጊዜ ነው፡፡

ከኃጢአት የተቆጠረ ሌላ የተሳሳተ ደስታ አለ፡፡

ጠቢቡ ሰሎሞን «ጠላትህ ቢወድቅ ደስ አይበልህ፤. . .» (ምሳ 24:17) በማለት ተናግሯል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ደስታ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- «ፍቅር. . . ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤. . .» 1ኛ ቆሮ 13:6፡፡

ሐዋርያት ርኩሳን መናፍስት ስለተገዙላቸው በጣም ደስ ብሏቸው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመጡ እርሱ እንዲህ በማለት ገሥጸአቸዋል፡- «ነገር ግን መናፍስት ስለ ተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ፤ስማችሁ ግን በሰማያት ስለ ተጻፈ ደስ ይበላችሁ፡፡» ሉቃ 10:20፡፡

እውነተኛው ደስታ የሚገኘው በጌታ ነው. . .

መንፈሳዊው ሕይወት ከሁሉም የጸጋ መንገዶቹ ጋር የሚገኘው በዚህ ደስታ ነው

መዝሙረኛው ዳዊት ስለ ደስታ የሚከተሉትን የመዝሙር ስንኞች ደርድሯል፡- «ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ፡፡» (መዝ 121:1)፤«. . . ብዙ ምርኮ እንዳገኘ በቃልህ ደስ አለኝ፡፡» (መዝ 118:162)፤ «ነፍሴ በቅቤና በስብ እንደሚጠግቡ ትጠግባለች፤ ከንፈሮቼም ስምህን በደስታ ያመሰግናሉ፡፡» መዝ 62:5፡፡ በዚህ መሠረት ዳዊት ደስታውን የሚመለከተው ወደ እግዚአብሔር በሚያቀርበው ነገር ውስጥ ነው፡፡

ንስሓ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስታርቅ ስለሆነ ሰው በንስሓም ደስ ይለዋል፡፡

ሰማያትም የዚህ ደስታ ተካፋዮች ናቸው፡- «. . . እንዲሁ ንስሓ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሓ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል፡፡» ሉቃ 15:7፡፡

ተስፋም ሌላው የደስታ ምንጭ ነው፡- «በተስፋ ደስ ይበላችሁ . . . » ሮሜ 12:12፡፡

ሌላው ቢቀር ፈተናዎች የሚያምኑ ሰዎችን ያስደስቷቸዋል፡- «ወንድሞቼ ሆይ፤የእምነታችሁ መፈተን ደስታን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ ልዩ ልዩ መከራ ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቊጠሩት፡፡» ያዕ 1:2-3፡፡

ታላቁ ደስታ ከእግዚአብሔር ጋር በመንግሥቱ ውስጥ መገናኘት ነው፡፡ ጌታ የታመነውን ሰው ወደፊት እንዲህ ይለዋል፡- «ወደ ጌታህ ደስታ ግባ. . .» ማቴ 25:22፡፡

(21)
ለዝምታ የሚደረጉ ጥቂት ልምምዶች

በእኛ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ሰው ሙሉ ለሙሉ ዝም ይል ዘንድ አይችልም፡፡ ይሁን እንጂ የሚከተሉትን በሥራ ላይ በማዋል የዝምታ ልምምዶችን ማድረግ ይችላል፡-

1/ አጥር ምጥን ያሉ መልሶችን መስጠት፤

አንድ ቃል ወይም ዓረፍተ ነገር በቂ መልስ ሲሆን ከቻለ ወደ ተራዘመ ዝርዝርና ወደ ሰፋ መግለጫ መግባት አያስፈልግህም፡፡ አንድ ዓረፍተ ነገር በቂ ነው፡፡

2/ ስለ ማንኛውም ጉዳይ መናገርን ማቆም፤

የአንተ ጉዳዮች ያልሆኑ ሊኖሩ ስለሚችሉ ስለ እነርሱ አትናገር፤ በተለይም ከሌሎች ሰዎች ምሥጢራት ጋር የሚዛመድ ከሆነ፡፡ የአንተን ሙያ ስለማይመለከቱ ጉዳዮችም አትናገር፡፡ እነዚህም ከአንተ እውቀት የሚልቁ ሳይንሳዊ ወይም ኪነ ጥበባዊ ወይም ፖለቲካዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡

3/ ከአንደበት ስሕተቶች መራቅ፤

እነዚህም፡- እርግማን፣ ማንኳሰስ፣ ከንቱ ንግግር፣ ልፍለፋ፣ ውጤት የሌለው ክርክር፣ የቁጣ ቃላት፣ ንቀት . . . ወዘተ ናቸው፡፡

4/ በጣም አስፈላጊ ለሆነ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ንግግር አለመጀመር፤

አንድ ሰው ካነጋገራችሁ አጠር ያለ መልስ ስጡት፤ማንም ካላናገራችሁ የእናንተ መናገር አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ እስኪደርስ ድረስ ዝም ብላችሁ ቆዩ፡፡ ይህን የምታደርጉ ካልሆናችሁ አንድ ስሕተት ላይ ልትወድቁ ትችላላችሁ፡፡

(22)
የእምነት ደረጃዎች

በእምነት የደከመ ሰው እንዳለ ሁሉ እምነት የጎደለውም ሰው አለ፡፡ ሮሜ 14:1፡፡

ሌላው ሰው ደግሞ በእምነቱ ውስጥ የጎደለው ነገር እንዲሞላለት የሚፈልግ ሲሆን ሦስተኛው ሰው ደግሞ በኤማሁስ መንገድ ላይ ሲጓዙ እንደነበሩት ሁለት ደቀ መዛሙርት ልቡ ከማመን የዘገየ ሰው ነው፡፡ 1ኛ ተሰ 3:12፤ሉቃ 24:25፡፡

ከዚህ በተቃራኒ የእምነት ደረጃዎች አሉ . . .

- የመጀመሪያው፡- የእምነት ሰው፤
- ሁለተኛው፡- በትዕቢት ያልተነፋ ሰው (1 ጢሞ 3:6)፤
- ሦስተኛው፡- እምነቱ እጅግ የሚያድግ ሰው (2ኛ ጢሞ 2:13) ወይም በእምነት የተትረፈረፈ ሰው (2ኛ ቆሮ 8:7)፤
- አራተኛው፡- ሳይናወጥ በሃይማኖት የጸና ሰው (ቆላ 1:23)፤
- አምስተኛው፡- በእምነት የጸና ሰው (1ኛ ጴጥ 5:9)፤

- ስድስተኛው፡- በእምነት ባለ ጠጋ የሆነ ሰው (ያዕ 2፡5)፤
- ሰባተኛውና ከላይ ከተዘረዘሩት የሚልቀው ደግሞ እምነት የሞላበት ሰው ነው። ሐዋ 6፡5።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እንዲህ በማለት ተናግሯል፡-«እምነትሽ ታላቅ ነው፤. . .» ማቴ 15፡28።

«ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል፤» (ማር 16፡17) የሚል ቃል ስለ ተጻፈ ብርቱ እምነት አለ። ተራራን የሚያፈልስም እምነት አለ። 1ኛ ቆሮ 13፡3። ሁሉንም ነገር የሚቻል የሚያደርግም እምነትም አለ፡- «. . . ለሚያምን ሁሉ ይቻላል።» ማር 9፡23።

ከዚህ ሁሉ በፊት ግን አንተ በእምነት ውስጥ ያለህ ሥፍራ የቱ ጋ ነው? አንተ እውነተኛ አማኝ ነህ? አንተ «በፍቅር የሚሠራ እምነት . . .» (ገላ 5፡6) አለህ? በእምነት ታድጋለህ? እምነትህ ብርቱና ጠንካራ ነው? ወይስ እምነትህ እንዳይጠፋ ጸሎት ያስፈልግሃል? ሉቃ 22፡32።

ወንድሞቼ ሆይ «በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ፤ ራሳችሁን ፈትኑ፤. . .» (2ኛ ቆሮ 13፡5) ተብሎ የተጻፈው ለእኛ ነው።

ያለ ምንም ጥርጥር እምነት የሚለው ቃል ጥልቅ ትርጉም አለው።

(23)
ጸሎት

ጸሎት የሚጸለየው የእግዚአብሔርን ልብ ለመክፈት ነው። በዚህ መሠረት በእምነት ውስጥ ያለው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር በግልጽና በፍቅር ይነጋገራል። ጸሎት ማለት ሰውን በእግዚአብሔር ፊት ማቅረብ ማለት ነው።

ጸሎት ማለት ሰውና እግዚአብሔርን የሚያገናኝ ገመድ ማለት ነው። ስለሆነም ጸሎት እንዲሁ የሚደረግ ንግግር ሳይሆን ከልብና ከልብ ጋር የሚደረግ ግኑኙነት እንጂ።

ጸሎት ማለት በእግዚአብሔር ፊት የመቆም ስሜትን ማሳደር ማለት ነው። ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የሚደረግ ተካፋይነትና ከእግዚአብሔር ጋር የሚሆን ኅብረት ነው።

ጸሎት የመላእክት ምግብ ሲሆን ለመንፈሳውያን ሰዎችም እግዚአብሔርን የሚቀምሱበትና የሚያጣጥሙበት ሕይወት ነው። መዝሙረኛው ዳዊት ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- «እግዚአብሔር ቸር እንደ ሆነ ቅመሱ እዩም፤» መዝ 33፡8።

ጸሎት ለእግዚአብሔር የሚደረግ ጥማትን ያረካል፡- «ዋላ ወደ ውኃ ምንጭ እንደሚናፍቅ፤አቤቱ እንዲሁ ነፍሴ ወደ አንተ ትናፍቃለች።» መዝ 41፡1። «ነፍሴ በቅቤና በስብ እንደሚጠግቡ ትጠግባለች፤» መዝ 63፡5።

ጸሎት ራስን ለእግዚአብሔር ለማስሸነፍ የሚደረግ ሕይወት ስለሆነ «ፈቃድህ ትሁን» እንላለን።

መንፈሳዊ ቃላትና ጥቅማቸው

ጸሎት የእኛን የብርታት ጉድለትና የእውቀታችንን ማነስ የምንቀበልበት መንገድ ነው። ስለሆነም ጥበቃችንን ወደምናገኝበትና ወደሚበልጠው ይኸውም ወደ እግዚአብሔር ኃይል እንጠጋጋለን።

ጸሎት ከእግዚአብሔር መነጠላችንን ያጠፋልናል።

ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግ ግንኙነት ነው። በዚህ ግንኙነት ውስጥ እኛ ራሳችንን ወደ እርሱ ከፍ እናደርጋለን ወይም እርሱ ወደ እኛ ይመጣል።

በዚህ ጸሎት ውስጥ ሰው ፊቱን ወደ ሰማያትና ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ይመልሳል።

ጸሎት ግዴታ ወይም ትእዛዝ አይደለም። ትእዛዝ ወይም ሃይማኖት ወይም ታማኝነትም አይደለም. . . ፍላጎትና ናፍቆት እንጂ። ይህን ካልሆነ ለመታዘዝ ስንል ያለ ፈቃዳችን የምንከውነው ልምምድ ሆኖ ነው የሚቀረው።

ጸሎት ጥያቄ ብቻም አይደለም። አንድ ሰው ስለ ምንም ነገር ሳይጠይቅ መጸለይ ይችላል፤በእግዚአብሔር ውበትና ሕይወት የመስጠት እውቀት ላይ በተመስጦ መቆየት ይችላልና። ስለሆነም የማክበርና የማመስገን ጸሎቶች ጥያቄ አቅራቢ ከሆኑ ጸሎቶች እጅግ የላቁ ናቸው።

ከእግዚአብሔር በተጨማሪ ከእርሱ አጠገብ የሚቀመጥ ነገር የምንፈልግ ከሆንን እንደምናስበው በጸሎት አንደሰትም።

ጸሎት ማለት ለዓለም ሙሉ ለሙሉ መሞት፣ ምድራዊ ደስታን ፍጹም መርሳትና በሰው አሳብ ውስጥ እግዚአብሔርን ብቻ ማስቀረት ማለት ነው።

ጸሎት ማለት ሰማይና ምድርን የሚያገናኝ መሰላል ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ ጸሎት ምንም ዓይነት ዓለም ወደሌለበት ወደ ሰማያዊው ቦታ የሚያሸጋግረን ድልድይ ነው።

ጸሎት የገነት ቁልፍ ነው . . .

ጸሎት በቃላት የሚገለጹ ስሜቶች ድብልቅ ነው።

ጸሎት ያለ ቃላትና ያለ ንግግር ሊከናወን ይችላል . . . የልብ ምት ጸሎት ነው . . . የዐይን ዕንባ ጸሎት ነው . . . ከእግዚአብሔር ጋር መሆንም ጸሎት ነው..

በእነዚህ ሁሉ የጸሎት ትርጉሞች ውስጥ እናንተ በእርግጥ ትጸልያላችሁ?

(24)
በእውነትና በሐሰት መካከል ያሉ «ኃጢአት ሠርቼያለሁ» የሚሉ ቃላት

አብዛኛውን ጊዜ «ኃጢአት ሠርቼያለሁ» የሚሉት ቃላት ከእውነተኛና ከተጸጸት ልብ የሚወጡ ናቸው። ይህ የሚሆነውም ንስሓን ለመቀበልና የእግዚአብሔርን ይቅርታ ለማግኘት ነው።

+ ለምሳሌ፡- የጠፋው ልጅ ለአባቱ እንዲህ ነበር ያለው፡- «አባቴ ሆይ፤ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፤ወደፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም. . .» ሉቃ 15፡21። ይህ ልጅ የአባቱን ይቅርታ ስላገኘ የሰባው ፍሪዳ ታርዶለታል።

+ ሌላው ምሳሌያችን ዳዊት ነው፡- «አንተን ብቻ በደልሁ፤ በፊትህም ክፋትን አደረግሁ፤. . .» መዝ 50:4። በቀን ውስጥ በሚደርሱት በሰባቱም ጸሎቶች ውስጥ ይህንን ቃል እንደግመዋለን።

«ኃጢአት ሠርቼያለሁ» የሚሉትን ቃላት ንስሓን በማስከተል የምንናገራቸው ካልሆነ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አይኖራቸውም። ይህም ማለት «ኃጢአት ሠርቼያለሁ» የሚሉት ቃላት ብቻቸውን ዋጋ የማይኖራቸው ጊዜ ይኖራል ማለት ነው።

+ ፈርዖን እነዚህን ቃላት ከአንድ ጊዜ በላይ ተናግሯቸዋል። እርሱ እነዚህን ቃላት ይናገራቸው የነበረው እግዚአብሔር መቅሠፍቱን እንዲያርቅለት ሲሆን የሚናገራቸውም በፍርሃት ውስጥ ሆኖ ነበር። መቅሠፍቱ ከተመለሰለት በኋላ ግን ልቡ እን ቀድሞው ተመልሶ ይደነድን ነበር።

እግዚአብሔር ፈርዖንን በበረዶ መቅሠፍት በመታው ጊዜ ሙሴና አሮንን ወደ እርሱ ልኮ ካስጠራቸው በኋላ እንዲህ ነበር ያላቸው፡- «. . . በዚህ ጊዜ በደልሁ፤እግዚአብሔር ጻድቅ ነው፤እኔና ሕዝቤም ኃጢአተኞች ነን። የአምላክ ነጎድጓድ በረዶውም በዝቷል፤ወደ እግዚአብሔር ጸልዩ፤ እለቅቃችሁማለሁ፤ከዚያም በኋላ በዚህ አትቀመጡም።» ዘጸ 9:27። በረዶው ከቆመ በኋላ ግን ፈርዖን ልቡን መልሶ አደንድኗል።

የአንበጣ መቅሠፍት በመታው ጊዜም ሙሴና አሮንን አስጠርቶ፡- «. . . አምላካችሁን እግዚአብሔርን እናንተንም በደልሁ፤አሁን እንግዲህ በዚህ ጊዜ ብቻ ኃጢአቴን ይቅር በሉኝ፤ይህን ሞት ብቻ ከእኔ ያነሣልኝ ዘንድ አምላካችሁን እግዚአብሔርን ለምኑ አላቸው።» ዘጸ 10:16-17።

ብዙ ሰዎች እንደ ፈርዖን «ኃጢአት ሠርቼያለሁ» ቢሉም እንደ እርሱ ወደ ቀደመ ክፋታቸው ተመልሰዋል።

+ ጥፋቱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰለት በለዓም ለእግዚአብሔር መልአክ «በድያለሁ. . .» (ዘኁ 22:34) ብሎ ከተናገረ በኋላ ወደ ቀደመ ጥፋቱ ተመልሶ በድሏል።

+ ንጉሥ ሳዖልም ለነቢዩ ሳሙኤል «. . . በድያለሁ።» (1ኛ ሳሙ 15:24-30) ብሎታል። እርሱ ይህን ቃል ሁለት ጊዜ የደገመው ለንስሓ አልነበረም፤ነቢዩ በሕዝቡ ፊት እንዲያሞግሰው ስለ ወደደ እንጂ። እግዚአብሔር ስላልተቀበለው ግን ሳዖል ጠፍቷል።

+ የጌራ ልጅ ሳሚ እንደ ንጉሥ ዳዊት «. . . ባሪያህ በደለኛ እንደ ሆንሁ አውቄያለሁና . . .» (2ኛ ሳሙ 19:20) በማለት ተናግሮ ነበር። እርሱ እንዲህ ብሎ የተናገረው ስለ ፈራ ወይም ሊሸነግል ስለ ወደደ ነው። ያም ሆነ ይህ ሳሚ ተቀባይነት ስላላገኘ ጠፍቷል።

+ ሌላ ምን የሚባል ነገር አለ? ከሀዲው ይሁዳም «በድያለሁ» ብሏል።

እርሱ ብዙ ከዘገየ በኋላ ተስፋ በቆረጠ መንፈስ ለካህናት አለቆችና ለሽማግሌዎች እንዲህ ብሏቸው ነበር፡- «. . . ንጹሕ ደም አሳልፌ በመስጠቴ በድያለሁ. . .» ማቴ 27:4። ከዚህ በኋላ ከእነርሱ ተለይቶ በመሄድ ራሱን ሰቅሏል። ይሁዳም «በድያለሁ» ካለ በኋላ ጠፍቷል ማለት ነው።

(25)
የአዲስ ዓመት ጸሎት

አቤቱ ጌታ ሆይ፤ዓመቱን የተባረከ አድርገው፤

አንተን ደስ የሚያሰኝ ንጹሕ ዓመት ይሁን።

መንፈስህ የሚገለጥበት ዘመን ይሁን፤ከእኛም ጋር ይሥራ።

እጆቻችንን ያዝና አሳቦቻችንን ከዓመቱ መጀመሪያ እስከ ማብቂያው ድረስ አንተ ምራቸው።

አንተን ደስ ያሰኝህ ዘንድ ይህ ዓመት የአንተ ይሁን።

ይህ ዓመት አዲስ ዓመት ስለሆነ በኃጢአታችንና በበደላችን አናርክሰው።

እግዚአብሔር ሆይ በዚህ ዓመት ልንሠራው ባቀድነው በማንኛውም ሥራ ውስጥ አንተ ከእኛ ጋር ሁን።

እኛ ዝም እንላለን አንተ ሁሉንም ነገር ታደርጋለህ።

ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ «ሁሉ በእርሱ ሆነ፤ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም።» (ዮሐ 1:3) ብሎ እንደ ተናገረ እኛ በአንተ ደስ ይለናል።

አቤቱ ጌታ ሆይ፤ይህ ዓመት መልካም ይሁን፤

በእያንዳንዳችን ላይ ፈገግታን ግለጥ የሁላችንንም ልብ አስደስት።

በችግራችን ውስጥ ጸጋህ ይገለጥ፤የተፈተኑትንም አንተ እርዳቸው።

የአሳብ ሰላምንና ፀጥታን አድለን።

ለተቸገሩት ስጣቸው፤የታመሙትን ፈውሳቸው፤ያዘኑትንም አጽናናቸው።

ጌታችን ሆይ፤ለራሳችን ብቻ አንጠይቅህም፤

የአንተ ስለሆኑ ስለ ሁሉም እንጠይቅሃለን፤

የፈጠርሃቸው በአንተ ደስ እንዲሰኙ ነው፤ይህ ከሆነ በአንተ ደስ እንዲሰኙ አድርጋቸው።

ቃልህ ለሁሉም ልብ ይደርስ ዘንድ ስለ ተልዕኮህና ስለ ቤተ ክርስቲያናችን እንጠይቅሃለን።

ስለ ሀገራችን እንጠይቅሃለን፤መንግሥትህ በሁሉም ሥፍራ እንድትመጣም ስለ ዓለም ሰላም እንጠይቅሃለን።

ዓመቱ ፍሬያማና በመልካም ነገሮች የተሞላ ይሁን።

እያንዳንዱ ቀንና ሰዓት የራሱ የሆነ ሥራ አለው፤

አንተ የሚባክን ጊዜ ይኖር ዘንድ አትፍቀድ።

ሕይወታችንን በእንቅስቃሴ፣ በሥራና በምርት የተሞላ አድርግ፤ ለምርታማና ለተቀደሰ ልፋታችን በረከትህን አድለን።

በተግባሮቻችን ውስጥ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ኅብረት ከእኛ ጋር ይሁን።

አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ፤እስከዚህ ሰዓት ድረስ ጠብቀህ ስላቆየህንና ይህን ዓመት ስላደልኸን እናመሰግንሃለን፤ እንባርክህማለን።

(26)
ንስሓና ጸጸት

በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ምሥጢረ ንስሓ ያለው በምሥጢረ ጸጸት ውስጥ ነው። ጸጸት የሌለበት ንስሓ ከቶውኑ ንስሓ ሊሆን አይችልምና።

ጸጸት ስለ በደላችሁት በደል ከልብ የሚወጣ ጽኑ እምነት ነው።

ጸጸት በራስ ላይ መፍረድና ራስን ጥፋተኛ ማድረግ ነው።

ስለሆነም ንስሓ የራስህ የሆነ የቅጣት ፈቃድ ነው።

በዚህ መሠረት ንስሓ ማለት «ኃጢአት ሠርቼያለሁ» ማለት ወይም ኃጢአቶችህን መጥራት ብቻ አይደለም። እውነተኛ ንስሓ የሚጀምረው ከልብ ነው። ሰው የራሱን ክፉ ሥራዎች ይጥላል ዐመሉንም ይጠላል ማለት ነው።

ራሱን ጥፋተኛ የሚያደርግ ሰው በራሱ ላይ ከእግዚአብሔር ወይም ከሰዎች የሚመጣበትን ቅጣት ይቀበላል። ይህን የሚያደርገውም ቅጣቱ የሚገባው መሆኑን በማመን ነው።

ለቅጣት ማጉረምረም የሚያረጋግጠው ጸጸት አለመኖሩን ነው።

ጸጸት በኃጢአት ምክንያት ለሚከተሉ ውጤቶች የምትችለውን ያህል መፍትሔ ለመስጠት መሞከርንና በሌሎች ሰዎች ላይ ለሚደርሰው ኢ-ፍትሐዊነት ካሣ መክፈልን ያጠቃልላል።

ስለሆነም ዘኬዎስ በጌታ ፊት በጸጸት ቆሞ ለእርሱ እንዲህ ነበር ያለው፡- «. . . ማንንም በሐሰት ከስሼ እንደ ሆንሁ አራት እጥፍ እመልሳለሁ. . .» ሉቃ 19:8። እናንተም ብትሆኑ እንዲሁ መልሱ። መመለስ የሌለበት ጸጸት በቂ ጸጸት አይደለም።

ጸጸት ትሑት ልብ ይፈልጋል። በትዕቢቱና በኩራቱ የሚጸና ሰው ሊጸጸት አይችልም፤ኩራቱ ከመጸጸት ይገድበዋልና።

ካህኑ ንስሓ የገባው ሰው መጸጸቱን ሲመለከት «እግዚአብሔር ይፍታህ» ይለዋል። ሳልተጸጸተው ሰው «እግዚአብሔር ይፍታህ» አይባልም።

አንድ ሰው «እግዚአብሔር ይፍታህ» የሚለውን ቃል ሲሰማ ቃሉ የተነገረው ንስሓ ለገባው ሰው ኃጢአት መሆኑን ይረዳል።

ንስሓ የሚገባው ሰው ኃጢአት ለመሥራቱ ፍጹም እርግጠኛ ከሆነና ኅሊናው ክፉኛ የሚወቅሰው ከሆነ ጠባዩን በመለወጥ ንስሓ ይገባል። ከዚህ በተቃራኒ ሰራሱ ምክንያት የሚሰጠው ሰው ግን ኃጢአት መሥራቱን ይቀጥላል። ይህን ለማድረጉ ተጨማሪ ምክንያቱ የኃጢአቶቹ ክብደት ስለማይሰማውና እነዚህ ኃጢአቶቹ ውስጡን ስለማያውኩት ነው።

አንድ ሰው የተሳሳተ መሆኑን ሳያምን እንዴት ሊጸጸት ይችላል?! የመጀመሪያው ደረጃ ሰው ኃጢአት መሥራቱን ማመኑ ነው።

ስለሆነም ንስሓ ሁለተኛው ደረጃ ነው እንጂ የመጀመሪያው ነጥብ አይደለም። በእውነተኛ ጸጸትና ማመን በሌለበት ጸጸት መካከል ታላቅ ልዩነት አለ።

(27)
የሰብእና ጥንካሬ

የሰብእና ጥንካሬ ውጫያዊ ገጽታ አይደለም። የሚመነጨው ከሰውየው ጥልቀት፣ ከልቡ፣ ከአሳቡና ከፈቃዱ ነውና።

አንድ ሰው፡- የእውቀት ጥንካሬ፣ የመረዳትና የማወቅ ጥንካሬ፣ ነገሮችን የማጠቃለል ጥንካሬ፣ እውቀት የሚሰጡ ነገሮችን ማግኘትና መሰብሰብ እንዲሁም መረጃን ማሰባሰብና ማደራጀት የሚችል የማስታወስ ችሎታዎች ካሉት ጠንካራ ወይም ብርቱ ሰው ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

ብልኅ ሰው ጠንካራ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም።

እርሱ እውቀት ካላቸውና ብዙ ካነበቡ ሰዎች ይልቅ ጠንካራ ነው። እርሱ እነዚህ ሁለቱን ጨምሮ ገንዘቦቹ ካደረገ ደግሞ የሰብእናው ጥንካሬ ይጨምራል።

የፈቃድና የውሳኔ ጥንካሬዎች የጠንካራ ሰብእና ምንጮች ናቸው።

ራሱን ማሸነፍ የሚችል ሰው ከተማን ድል ከሚነሣ ሰው ይበልጣል የተባለው ለዚህ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ጠንካራ ፈቃድ የሌለው ብልኅ ሰው በሕይወቱ የሚወድቅ ሰው ነው፤ምክንያቱም ያውቃል ማድረግ ግን አይችልም።

የደካማ ሰብእና ምክንያቶች ከሆኑት መካከል፡- ማመንታት፣ ጥርጥር፣ ራስን የመግዛት ጉድለት፣ የፈቃድ ድካምና ውሳኔ የመስጠት አቅም ማጣት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

አንድ ሰው የሚከተለው ጾምና መንፈሳዊ ልምምዶች የሰውየውን ፈቃድና ሰብእና ያጠናክራሉ።

መንፈሳዊ ሰው በውስጡ ባለው አሸናፊነት ምክንያት ጠንካራ ነው። እርሱ ኃጢአትን፣ ዲያብሎስን፣ ሥጋን፣ ቁሳዊነትንና ዓለምን ድል ስለነሣ ጠንካራ ነው። መንፈሳዊ ውጊያዎች ውስጥ ደፍሮ ስለ ገባ የዲያብሎስ ነበልባል የሆኑ መሣሪያዎች ሊያሸንፉት አልቻሉም።

ሌላው የሰብእና ጥንካሬ ምንጮች ጥበብና ጥንቃቄ ናቸው።

ስለሆነም በጥበባቸው የሚታወቁ ሰዎች ሌሎችን ለመምራት ይመረጣሉ፤እነርሱ ሌሎች ሰዎችን ወደ እነርሱ የመሳብ ብቃቱ አላቸውና።

ድፍረት ሌላው የጠንካራ ሰብእና መመዘኛ ነው።

ስለሆነም ሰብእናው ብርቱ ነው ተብሎ የሚታወቅ ሰው ቆራጥና ደፋር ነው። ተቃዋሚ ኃይሎች ቢገዳደሩትም አይፈራም አይጨነቅምም። እርሱ አመለካከቱን የመግለጽ ችሎታ አለው። ከዚህ በተጨማሪ እምነቱን ይገልጻል ለእምነቱም ይቆማል።

በድፍረትና በችኩልነት መካከል ከፍተኛ ልዮነት አለ፤ችኩልነት ጥበብ የጎደለው ነውና።

ስለሆነም ሰብእና ጠንካራ ነው ተብሎ የሚታወቀው እርስ በእርሳቸው ለሚደጋገፉ የጠንካራ ሰብእና አቋሞች ብዛት ያላቸው ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት ሲችሉ ነው።

ይህን የምንለው በእውነተኛ ጥንካሬ እና በሥልጣን፣ በምድራዊ ኃይል፣ በዓመፅ፣ በትዕቢትና ሌሎችን በማጥቃት ላይ በተመሠረተው የተሳሳተ ጥንካሬ መካከል ያለውን ልዩነት ለማሳየት ነው።

(28)
ክርስትና. . .የጥንካሬ ሃይማኖት

ክርስትና የሚጠራቸው ቸርነትና ትሕትና ምንም ይሁን ምን የደካማ ሃይማኖት ምልክቶች አይደሉም፤የጠንካራ ሃይማኖት ምልክቶች እንጂ። መጽሐፍ ቅዱስ በእምነት ሙሉ የሆኑትን ሰዎች የሚገልጣቸው የተሳሉ የኃያላን ፍላጻች በማለት ነው። መዝ 119:4። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሲናገርም፡- «ይህች እንደ ማለዳ ብርሃን የምትጎበኝ፣ እንደ ጨረቃ የተዋበች እንደ ፀሐይም የጠራች፣ዓላማ ይዞ እንደ ተሰለፈ ሠራዊት የምታስፈራ ማናት?» (መኃ 6:10) ብሏል።

መንፈስ ቅዱስ ለሚያምን ሰው የሚሰጠው ኃይል እንዲህ ዓይነቱን ኃይል ነው።

ስለሆነም እግዚአብሔር ለሐዋርያቱ እንዲህ ብሏቸዋል፡- «. . . ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌምም፣ በይሁዳም ሁሉ፣በሰማርያም፣ እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ. . .» ሐዋ 1:8።

ከዚህ በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት ተናግሯል፡- «ሐዋርያትም የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በታላቅ ኃይል ይመሰክሩ ነበር፤በሁሉም ላይ ታላቅ ጸጋ ነበረባቸው።» ሐዋ 4:33። ይህም የሆነው በወንጌል «. . . የእግዚአብሔር መንግሥት በኃይል ስትመጣ እስኪያዩ ድረስ ሞትን የማይቀምሱ አሉ. . .» (ማር 9:1) የሚለው ቃል ለዚህ የተነገረ እስኪመስል ድረስ ነው።

በክርስትና እምነት ውስጥ የኃይል ቁንጮ የተገለጠው በሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ቃል ውሽጥ ነው፡- «ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።» ፊል 4:13።

ከዚህ በተጨማሪ ይህ ሐዋርያ በአገልግሎት ውስጥ ስላለ ኃይል እንዲህ በማለት ተናግሯል፡- «ለዚህም ነገር ደግሞ በእኔ በኃይል እንደሚሠራ እንደ አሠራሩ እየተጋደልሁ እደክማለሁ።» ቆላ 1:29። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሎታል፡- «. . . እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፤ ማንም ክፉ ሊያደርግብህ የሚነሣብህ የለምና አትፍራ፤. . .» ሐዋ 18:9እና10።

ይህ በርኩሳን መናፍስት ላይ ከሥልጣን ጋር የሚሆን ኃይል ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያቱን ሲልካቸው ይህን ኃይልና ሥልጣን ሰጥቶአቸው ነው፡- «አሥራ ሁለቱንም ሐዋርያት ወደ እርሱ ጠርቶ በአጋንንት ሁሉ ላይ ደዌንም ይፈውሱ ዘንድ ኃይልና ሥልጣን ሰጣቸው፤. . .» ሉቃ 9:1። እርሱ በጠላት ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ስለ ሰጠን በጸሎታችን ውስጥ እናመሰግነዋለን፡- «እነሆ እባቡና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፤ የሚጎዳችሁም ምንም የለም።» ሉቃ 10:19።

ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር መልክ ስላላቸው ብርቱዎች ናቸው፤ እርሱ ኃያል አምላክ ነውና።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዋህና ትሑት ቢሆንም ኃያል አምላክ ነው። ስለ እርሱ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፡- «ኃያል ሆይ፤ በቍንጅናህና በውበትህ ሰይፍህን በወገብህ ታጠቅ።» መዝ 44:4። ከዚህ በተጨማሪ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ «. . . ከእርሱ ኃይል እንደ ወጣ በራሱ አውቆ . . .» (ማር 5:30) የሚል ቃል ስለ ተጻፈ ኃያል አምላክ ነው።

ስለ እርሱ «እግዚአብሔር ኃይልን ለበሰ፤ታጠቀም፤. . .» (መዝ 92:1)፤ «በክንዱ ኃይል አድርጓል. . .» (ሉቃ 1:51) ተብሎ የተጻፈ ቃልም አለ። እርሱ ኃይሉን በምልክቶችና ድንቅ በሆኑ ነገሮች ውስጥ ገልጦአል። እንዲሁ የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች የሚል ቃል አለ። መዝ 117:15።

በክርስትና እምነት ውስጥ ኃይል መንፈሳዊ ይዘት አለው . . . ይህ ኃይል ኃጢአትን፣ ዓለምንና ርኩሳን መናፍስትን ድል የሚነሣ ኃይል ነው። ይህ ኃይል የትዕግሥት፣ የሥራ፣ ሰብእናን የሚያገለግልና ሌሎችን ለመምራት የሚውል ኃይል ከመሆኑም በላይ እምነትን ለማስጠበቅ የሚውል ኃይል ነው።

ይህ ኃይል ከስሕተት፣ ከዓመፃ፣ ከማጥቃትና ሌሎችን ለማሸነፍ ከሚውል ኃይል የራቀ ነው።

(29)
የክርስቲያን ጠባይ

ከእግዚአብሔር ጋር የሚሆን ሕይወት እንዲሁ እምነት ወይም ፍቅር ወይም መንፈስ ብቻ እንደ ሆነ አድርገው የሚገምቱ አንዳንድ ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች ከእነዚህ ውጪ ለቅድስና ወይም ለጠባይ ብዙ ግድ የላቸውም።

መጽሐፍ ቅዱስ ግን ስለ ክርስቲያን ጠባይ የሚለው ነገር አለው፤ በተለይም ኵነኔን አስመልክቶ። እንዲህ ነው የሚለው፡- «እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኵነኔ የለባቸውም። በኢየሱስ ክርስቶስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛል።» ሮሜ 8:1። በዚህ መሠረት አፀድን ሰው ከኵነኔ የሚጠብቀው በመንፈስ የሆነ ጠባዩ ነው።

መንፈሳዊው ጠባይ እግዚአብሔርን አጥብቀን ለመያዛችን ማስረጃ ነው። ሐዋርያው ይህን አስመልክቶ ከእኛ የሚጠብቀው ደረጃ በጣም ከፍ ያለ ነው፡- «. . . በእርሱ እኖራለሁ የሚል እርሱ እንደ ተመላለሰ ራሱ ደግሞ ሊመላለስ ይገባዋል።» 1ኛ ዮሐ 2:6።

በዚህ መሠረት እኛም የኢየሱስ ክርስቶስን ጠባይ ምሳሌ አድርገን በመከተል እንደ መንፈስ ፈቃድ እንመላለስ ዘንድ ይጠበቅብናል።

የክርስቲያን ጠባይ አስፈላጊነት «ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ።» (ማቴ 7:16) በሚለው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ተገልጦአል።

ይህ ጠባይ ሁለት ጎኖች አሉት፤አዎንታዊና አሉታዊ። እያንዳንዳቸው የራሳቸው የሆነ አደጋ አላቸው። ስለሆነም ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ እንዲህ ብሏል፡- «. . . ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን፤ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል።» 1ኛ ዮሐ 1:7።

ስለ አሉታዊው ጎን ደግሞ ይኸው ሐዋርያ እንዲህ ብሎ ተናግሯል:- «ከእርሱ ጋር ኅብረት አለን ብንል በጨለማም ብንመላለስ እንዋሻለን፤ እውነትንም አናደርግም፤. . .» 1ኛ ዮሐ 1:6::

ስለዚህ የክርስትና ጠባያችን ከእግዚአብሔር ጋር ላለን ኅብረት ማስረጃ ነው:: በቤተ ክርስቲያን ኅብረት ውስጥ ለመሆናችንም ማስረጃ ነው::

በዚህ መሠረት ቤተ ክርስቲያን እንደሚገባው የማይመላለሰውን ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ነገራት ከመካከል ታወጣዋለች:- «ክፉውን ከመካከላችሁ አውጡት::» 1ኛ ቆሮ 5:13::

ይኸው ሐዋርያ እንዲህም ብሏል:- «ወንድሞች ሆይ፤ከእኛ እንደ ተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን::» 2ኛ ተሰ 3:6::

ጠባይ ምንም ጥቅም እንደሌለው ተደርጎ ከተቆጠረና የሚያስፈልገው እምነት ብቻ ነው ከተባለ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ጠባይን ለምን ከፍተኛ ደስታው አድርጎ ቆጠረው? እርሱ በመልእክቱ እንዲህ ነው ያለው:- «ልጆቼ በእውነት እንዲሄዱ ከመስማት ይልቅ የሚበልጥ ደስታ የለኝም::» 3 ዮሐ ቍ. 4::

እኛ አማኞች ነን:: አማኞች እንደ መሆናችንም እንደሚገባን መመላለስ አለብን:- «እንግዲህ በጌታ እስር የሆንሁ እኔ በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችኋለሁ::» ኤፌ 4:1:: ፍሬ እንድናፈራም ተነግሮናል:- «. . . እንግዲህ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል፤ ወደ እሳትም ይጣላል::» ማቴ 3:10::

(30)
አቤቱ ጌታ ሆይ፤ስብሰባዎችንን አስታውስ፤ቀድሳቸውም

ስብሰባዎቻችን የሚደረጉት እኛ ስንገናኝ ሳይሆን እኛ ከእግዚአብሔር ጋር ስንገናኝ ነው ወይም እንደ እውነተኛ ቃል ኪዳኑ እኛ በምንሰበሰብበት ቦታ ላይ እርሱ በመካከላችን ሲገኝ ነው:- «ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና::» ማቴ 18:20::

እግዚአብሔር አምላክ ከአዳምና* ከሔዋን ጋር በገነት ተሰብስቦ ነበር፤ይህች ደግሞ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ነበረች:: ኖኅና ቤተሰቦቹ በመርከቢቱ ውስጥ ተሰብስበው ሳሉ እግዚአብሔር በመካከላቸው ተገኝቶ ነበር:: እግዚአብሔር በእቶን እሳት ውስጥ ተጥለው በነበሩት በሦስቱ ደቂቅ መካከል ተገኝቶ ነበር:: እግዚአብሔር በኮሬብ ተራራ ላይ ከሙሴ ጋር ተገኝቶ ነበር:: ይህ ስብሰባ የተባረከ ስብሰባ ስለ ነበር ሙሴ ብርሃን ወደ ሆነው እግዚአብሔር ሲጠጋ መልኩ አብርቶ ነበር::

በአዲስ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር በተገኘው ቦታ ላይ ሁሉ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ይሰበሰብ ነበር:- በተራራ ላይ፣ ሽባውን ሰው በፈወሰበት ቤት ውስጥ፣ አምስቱን ዳቦና ሁለቱን ዓሣ በባረከበት በምድረ በዳ፣ በእርሻ ማሳ ውስጥ፣ ከሣምራዊቷ ሴት ጋር ለየት ያለ ስብሰባ ባደረገበት በያዕቆብ ጉድጓድ አጠገብ እንዲሁም በማርታና በማርያም ቤት ውስጥ ተሰብስቧል::

ይህን አስመልክቶ በራእይ መጽሐፍ ውስጥ በጣም ድንቅ የሆኑ ሥዕላት እንመለከታለን:- «. . . በመቅረዞቹም መካከል የሰው ልጅ የሚመስለውን አየሁ. . .» ራእ 1:13:: ይኼኛው ሥዕል እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያኑ፣ በሕዝቡና በቀኝ እጁ መካከል ካሉት ከቤተ ክርስቲያን አለቆች ጋር መሆኑን ያሳየናል:: ከዚህ አስቀድሞ ግን

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተሰብስቦ ነበር:- «. . . ደግሞ አርባ ቀን እየታያቸው ስለ እግዚአብሔርም መንግሥት ነገር እየነገራቸው፤በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ ሕያው ሆኖ ለእነርሱ ራሱን አሳያቸው::» ሐዋ 1:3:: ይህን በመሰለው ስብሰባ ላይ ይገኙ ዘንድ በመግደላዊት ማርያምና በሁለተኛዋ ማርያም በኩል ጋብዟቸዋል:- «. . . ሄዳችሁ ወደ ገሊላ እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ተናገሩ፤ በዚያም ያዩኛል አላቸው::» ማቴ 28:10::

እርሱን ማየት በራሱ አንድ ዓላማ ነው::

እርሱ ከዚህ አስቀድሞ እንዲህ ብሏቸው ነበር:- «. . . ነገር ግን እንደ ገና አያችኋለሁ ልባችሁም ደስ ይለዋል፤ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም::» ዮሐ 16:22::

በቤቱ ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር እንሰበሰባለን:: መዝሙረኛው ዳዊት እንደ ተናገረም ወደ ቤቱ በመሄዳችን ደስ ይለናል:-«ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ::» መዝ 121:1::

እግዚአብሔር በቤት ውስጥ ከሰዎች ጋር ይሰበሰብ ነበር::

የመጀመሪያ ከሆኑት ቤቶች መካከል ቤተ ክርስቲያን የሆነው የቅዱስ ማርቆስ ቤት ነው:- «ባስተዋለም ጊዜ እጅግ ሰዎች ተከማችተው ይጸልዩበት ወደ ነበረው ማርቆስ ወደ ተባለው ወደ ዮሐንስ እናት ወደ ማርያም ቤት መጣ::» ሐዋ 12:12:: መንፈስ ቅዱስ ተሰብስበው በተቀመጡበት ቤት ውስጥ ሲወርድ የተመለከተው ቅዱስ ማርቆስ የመሰብሰብን ጥቅም ስላወቀ ለእኛም እንድንሰበሰብ አስተምሮናል::

(31)
መንፈሳዊ ጾም

ሁዳዴ ጾም (ዐቢይ ጾም) መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአርባ ቀንና ሌሊት የጾመው ጾም ስለሆነ በዓመት ውስጥ ካሉት አጽዋማት መካከል ጥንታዊውና በጣም የተቀደሰው ጾም ነው:: በዚህ ጾም ውስጥ ሰሙነ ሕማማትን እንጨምራለን፤ይህ ደግሞ ለዓመት የሚበቃ ሀብታችን ነው::

ይህን ጾም እንደ መንፈሳዊ ክፍለ ጊዜ አድርገን ለመውሰድ መለማመዳችን ጠቃሚ ነው:: ስለሆነም በዚህ ክፍለ ጊዜ ውስጥ በጾሙ መንፈሳዊነት ላይ በተመስጦ እንቆያለን፤በተመስጦ ለመቆየትም ራሳችንን እናለማምዳለን::

ጾም ማለት ከምግብ መከልከል ማለት ብቻ አይደለም፤መንፈስ ከፍ እንዲል ሥጋን የመቆጣጠሪያ መንገድ ጭምር እንጂ::

በጾም ወቅት ሥጋችሁን ሙሉ ለሙሉ ትቆጣጠሩታላችሁ? በመንፈሳዊነት እንድታድጉ የሚረዱአችሁን አሉታዊ ድርጊቶችን ለመፈጸም ፍላጎቱ አላችሁ?

ሥጋችሁን ከምግብ ስትከለክሉት ለመንፈሳችሁ ምግቧን ትሰጧታላችሁ?

ይህ ሊሆን ስለሚገባውም ጾም ምንጊዜም ቢሆን ከጸሎት፣ ከተመስጦና ከሌሎች መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች ማለትም ከንባብ፣ ከመዝሙራት፣ ከመንፈሳዊ ስብሰባዎች፣ ከመንፈሳዊ ልምምዶችና በራስ ላይ ከመፍረድ ጋር የተገናኘ ነው::

ጾም በጸሎት እንደሚታጀብ በንስሓም ይታጀባል:: በጾም ውስጥ ባላት ራስን የማዋረድ መንገድ ሁሉ የተጠቀመችው ነነዌ ለዚህ ምሳሌ ትሆነናለች:: ከዚህ

በተጨማሪ በነቢዩ ኢዮኤል የተገለጸው ጾም አለ:: ኢዮ 2:12-17:: እግዚአብሔር ምሕረትን ከሚያዋርዱበት ጾም ይልቅ ኃጢአትን በሚያቆሙበት ጾም ይደሰታል:: ስለ ነነዌ ጾም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈውን እናንባለን:- «እግዚአብሔርም ከክፉ መንገዳቸው እንደ ተመለሱ ሥራቸውን አየ፤እግዚአብሔርም ያደርግባቸው ዘንድ በተናገረው ክፉ ነገር ተጸጸቶ አላደረገውም::» ዮና 3:10::

ከዚህ ሌላ ጾም በምሕረት ሥራ ይታጀባል:: እግዚአብሔር ምሕረቱን ለእኛ እንዳደረገልን እኛም ለሰዎች ምሕረት ልናደርግ ይገባናል:: እኛን የረሀብ ስሜት ሲሰማን የሰዎች ሕመም ይሰማናል:: በዚህ ጊዜ ለተራቡት ስለምናዝን እንመግባቸዋለን::

አባቶች ስለ ጾም ከተናገሯቸው ምርጥ ብሒሎቻቸው መካከል «. . . ለእነዚህ ቅዱሳን ሰዎች የምትሰጣቸው ነገር ባይኖርህም ጾምና ምግብህን ስጣቸው::» የሚለው ብሒል አንዱ ነው:: ይህ ደግሞ በነቢዩ ኢሳይያስ ተገልጦአል:: ኢሳ 58::

ጾም ቁሳዊ ነገሮችንና ከእነርሱ ጋር የሚዛመዱ ማናቸውንም ነገሮች መርሳት ማለት ነው::

መርሳት ማለት ደግሞ ስለ ምግብ፣ ስለ ዓይነቶቹ፣ ስለ አበሳሰሉና ስለ አቀራረቡ ምንም ዓይነት ጉዳይ አለመስጠት ማለት ነው:: እነዚህ ጉዳዮች ጾም መንፈሳዊነቱን እንዲያጣና ልማድ እንዲሆን ያደርጉታል:: ነቢዩ ዳንኤል ስለ ጾመው ጾም ሲናገር ግን «. . . ማለፊያ እንጀራም አልበላሁም::» (ዳን 10:3) ብሏል::

በአጠቃላይ ከምግብ በመከልከል ምግብንና ጉጉቱን መርሳት ምናኔን አመላካች ፍንጭ ነው:: ይህ የሚሆነው ልብ መንፈሳዊ በሆኑና ለዘላለም ሕይወት በሚጠቅሙ ጉዳዮች አስቀድሞ ስለምትያዝ ነው::

(32)
በነነዌ ጾም ወቅት የሚደረጉ ልምምዶች

በነነዌ ጾም ወቅት በመንፈሳዊ ሕይወትህ ላይ ብርቱ ውጤት ለማምጣት ከፈለግህ አንዳንድ ልምምዶችን ልትከተል ያስፈልግሃል:: እነዚህን ልምምዶች ከሕይወትህ ጋር ማገናኘት ስትችል ከጾምህ ተጠቃሚ ትሆናለህ::

1/ በተደጋጋሚ ንስሐ የገባህበትና በአንተ ላይ የሚያንገዋብብ አንድ የተወሰነ ኃጢአትን ለማቆም ልምምድ ማድረግ::

2/ በጸሎትህ ውስጥ የሚካተቱ መዝሙራትን ለመማር ልምምድ ማድረግ:: በቀን ውስጥ ሰባት ጊዜ ከሚጸለዩት ጸሎቶች መካከል ከእያንዳንዱ አንዱን ወይም ሁለቱን መርጠህ መያዝ፤ በተለይም በአንተ ላይ ውጤት ትተው ሊያልፉ የሚችሉ መዝሙራትን::

3/ በተለያዩ ሰዓታት ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚነበቡ ንባባትን ለመማር ልምምድ ማድረግ:: እነዚህን ንባባት በክፍል ወይም በአንቀጽ መከፋፈልና ለእያንዳንዱ ንባብ ሦስት ወይም ስድስት ክፍል እንዳለው መገንዘብ::

4/ በተማርከው የኅሊና ጸሎት ላይ ልምምድ ማድረግ:: በዚህ ላይ ልምምድ ካደረግህ በሥራ ላይ ሳለህ፣ በመንገድ ላይ ስትሄድ፣ ከሰዎች ጋር ስትሆንና በሌላ በማንኛውም ጊዜ መጸለይ ትችላለህ::

5/ እነዚህን ጸሎቶች፣ መዝሙራትና የመጽሐፍ ቅዱስ ንባባት የተመሰጦህ አድማስ አድርገህ ተጠቀምባቸው:: ይህን የምታደርግ ከሆንህ ጸሎቶችህን በጥልቀትና በመረዳት ትጸልያቸው ዘንድ ያስችልሃል::

6/ መንፈሳዊ ንባባትን ለማንበብ ልምምድ ማድረግ:: ይህንንም ብዛት ያላቸው ንባባትን በመረዳትና በተመስጦ ከመጽሐፍ ቅዱስ በየዕለቱ በማንበብ ወይም የቅዱሳን ሰዎችን የሕይወት ታሪክ በማንበብ ወይም መንፈሳዊ መጻሕፍትን በማንበብ ማዳበር ትችላለህ:: ይህን ማድረግ ስትችል ከጥልቅ ንባባት አትራፊ ምርት መሰብሰብ ትችላለህ::

7/ በሁዳዴ ጾም ወቅት የጾሙንና የሰሙነ ሕማማት ዜማዎችን ለመማር ልምምድ ማድረግ:: ከዚህ በኋላ እነዚህን ዜማዎች በመንፈስ እስከምትሞላ ድረስ መደጋገም::

8/ በንስሐ አባትህ የበላይ ተቆጣጣሪነት የተወሰነ የጾም ደረጃ ላይ ለመድረስ ልምምድ ማድረግ ትችላለህ::

9/ ከሰዎች ጋር ለመስማማት የሚያደርሱ ብዛት ያላቸው መንፈሳዊ ልምምዶች አሉ:: እነዚህም:- ጨዋነት፣ ትዕግሥት፣ የሌሎችን ድካም መሸከም፣ ቍጣን መቆጣጠር፣ የምስጋና እና የማበረታቻ ቃላትን መጠቀም፣ ሌሎችን ማገልገልና መርዳት እንዲሁም ቸርነትና የዋህነትን መግለጥ ናቸው::

10/ በልብ ንጽሕና ውስጥ የምናገኛቸው ሌሎች ልምምዶች አሉ:: እነርሱም:- ትሕትና፣ ውስጣዊ ሰላም፣ የእግዚአብሔር ፍቅር፣ ያለ ማጉረምረም ያለኝ ይበቃኛል ማለት፣ ያለ ሁከት በፀጥታ ውስጥ መቆየት፣ በመንፈስ ቅዱስ የሚሆን ደስታ፣ እምነት፣ ተስፋ. . . ወዘተ ናቸው::

(33)
የእውቀት ችግሮች

እውቀት በአንድ ወይም በሌሎች ሰዎች ሕይወት ውስጥ ብዛት ያላቸው ጥቅሞች ቢኖሩትም አንዳንድ የሚያስከትላቸው ችግሮችም አሉት:: ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?

አዋቂ ወይም በጣም አዋቂ የሆነ አንድ ሰው ሰዎች በሌላቸው የእውቀት ደረጃ በእርሱ የእውቀት ደረጃ ብቻ ከእርሱ ጋር ይስማሙ ዘንድ ይጠብቃል:: ይህ ሳይሆንለት ሲቀር ከእነርሱ ጋር ይጋጫል:: በዚህ ጊዜ እርሱ እነርሱን፤እነርሱም እርሱን ያውኩታል::

እርሱ ከእነርሱ የሚጠብቀው እነርሱ ሊያደርጉ ከሚችሉት በላይ ነው:: ይህን ሊያደርጉ አለመቻላቸውን ሲመለከትም ልቡ በኀዘን ይዋጣል::

የመጀመሪያ ስሕተቱ ይህ ነው:- በሰዎች ጠባይ መበሳጨት::

በመሆኑም:- እንዴት ሊረዱኝ አልቻሉም?! ለምን እንደዚህ ያደርጋሉ? እንዲህ ያለውን ጉዳት ለምን ያመጡብኛል? አይረዱኝም እንዴ? ይላል::

ቀጠል አድርጎም:- ጉዳዩ እኮ ግልጽ ነው ይላል:: ይሁን እንጂ የጉዳዩ ቅለት ለእርሱ እንጂ ለእነርሱ አይደለም::

በዚህ ጊዜ ሁኔታው ከኀዘንና ከብስጭት ወደ ንዴትና ቁጣ ሊለወጥ ይችላል:: ተግሣጹና ዘለፋው እየጨመረ ሲመጣ ሁኔታውን ለማስታመም መሞከር የከፋ ያደርገዋል::

አዋቂ በሆነ ሰው የበላይ አስተዳዳሪነት የሚሠሩ ሰዎች ብዛት ያላቸው ችግሮች ሊገጥሟቸው ይችላል:: እነዚህ ሰዎች የሰውየውን መረዳትና ብዛት ያላቸው ሥራዎቹን ቢያደንቁለትም አንዳንድ ጊዜ ፈጥኖ መቆጣቱ፣ ትእዛዝ ማብዛቱና እነርሱ ሊያከናውኑ ከሚችሉት በላይ መጠበቁ አይመቻቸውም:: ያለ ምንም ምክንያት ደርሶ ይቆጣል፤እነርሱ ምክንያቶቹ ቢሆኑም እንኳ::

አዋቂ ሰው ከማንኛውም ሰው በበለጠ በሌሎች ሰዎች ላይ ይፈርዳል::

ምናልባት አእምሮው በፍጥነት ስለሚሠራ ምንም ሳያስብ ስለሚናገር ሊሆን ይችላል:: ድንገተኛ ሊሆን ስለሚችልም ስሕተቶች ላይ ፈጥኖ ይደርሳል::

አዋቂ ሰው ብቸኝነት ሊሰማው ይችላል ወይም ብቸኛ መሆንን ይፈልጋል::

እንዲህ ዓይነቱ ሰው እንዲህ ያለው ስሜት የሚሰማው ከሰዎች ብዙም የሚጠቀመው ነገር ስለሌለው ወይም ሥራቸውን ስለማይወደው ወይም ከእርሱ ጋር የሚጣጣም ጓደኝነት ከእነርሱ ማግኘት ስለማይችል ነው::

ፈላስፋው ዲዮጋን ለዚህ መልካም ምሳሌ ሊሆነን ይችላል:: እርሱ በእኩለ ቀን ፋኖስ አብርቶ ሲዘዋወር የተመለከቱ ሰዎች ለምን እንደዚህ እንደሚያደርግ ሲጠይቁት «ሰው እየፈለግሁ ነው!» በማለት መልሶላቸዋል::

በተከታታይ ስኬታማ ስለሚሆን ወይም ስለ ድንቅ ሥራው ከሰዎች ስለሚቀርብለት ወሬ ወይም ከሌሎች ሰዎች ጋር ሲነጻጸር የበላይነት ስሜት ስለሚሰማው፤ብቻ በአጠቃላይ አዋቂ ሰሆኑ ሰዎች የትሕትናን የጽድቅ ሥራ ገንዘብ እንዲያደርጉ መሞከር ከፍተኛ ጥረት ይጠይቃል::

እዚህ ላይ አንድ ብልኅ ሰው:- አዋቂው ሰው እነዚህ ስሕተቶቹን በአዋቂነቱ ፈልጎ ማግኘትና ማስወገድ ለምን ያቅተዋል? ብሎ ሊጠይቅ ይችላል::

ለዚህ መልሱ:- ስሕተቶቹን ሊያገኛቸው ይችል ይሆናል፤ስሕተቶቹም ማስወገድ ግን ሌላ ነጥብ ነው፤በአዋቂው ሰውና በመንፈሳዊው ሰው፤ በአሳብና በነፍስ መካከል ልዩነት አለና-የሚል ነው::

(34)
የጋብቻ ትርጉም ምንድር ነው?

እንደ ክርስቲያን አመለካከት ጋብቻ ማለት አንድ መንፈሳዊ ሰው ወይም የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆነ ሰው ከሌላ መንፈሳዊት ሴት ወይም የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ከሆነች ሴት ጋር የሚያደርገው ጥምረት ነው:: ጋብቻ እነዚህ ሁለት ሰዎች በምሥጢረ ተክሊል አማካይነት አንድ ለመሆን የሚፈጽሙት ኅብረት ነው::

መንፈስ ቅዱስ ተቃራኒ እምነት ያላቸውን ሰዎች ስለማያጣምር ሁለቱም ተመሳሳይ እምነት ሊኖራቸው ይገባቸዋል::

ጋብቻ የሚሰምረው እንዲህ ባለው መንገድ ነው፤መንፈስ ቅዱስ በሁለቱም ስጥ በስምምነትና በመንፈሳዊነት ይሠራልና::

ንስሐ ያልገቡ ሁለት ተቃራኒ ጾታ ያላቸውና ከመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች የራቁ ሰዎችን ማጣመር መንፈሳዊ ተግባር አይደለም::

ይህ በመሆኑም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የተጫጩ ጥንዶችን ንስሐ ትቀበላለች፤እኳርሱም ቅዱስ ቁርባን ይቀበላሉ:: ከዚህ በኋላ ሁለቱም ፍጹም የሆነ መንፈሳዊ ሕይወትን በኅብረትና በመተባበር መምራት ይጀምራሉ::

እንዲህ ያለው ጋብቻ የተጋቡት ጥንዶች መንፈሳዊ ሕይወት በአብዛኛው ፍጹምነት ሲጎድለው እንደሚገጥመው ለልዩነት የተጋለጠ አይሆንም::

ለግለሰባዊ ደንብ መመሪያዎች ለማውጣት እንሞክራለን:: ለተጋቡት ጥንዶች ሕይወት የማይቻል ሲሆን አንዳንዶች የፍቺ ምክንያቶችን ለማራዘም ያስባሉ:: ሕይወት የማይቻል የሚሆነው ለምንድር ነው? የማይቻለው ጥንዶቹ እንደ መንፈስ ፈቃድ ስለማይኖሩና የክርስቲያንን የጋብቻ ትርጉም ሳይረዱት ስለሚጋቡ ነው::

እነዚህ ሰዎች በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር መፋታትን በማይፈቅደው በኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዝ ስለማይመሩ የሚፈልጉት ኢ-ክርስቲያናዊ ወይም ኢ-መንፈሳዊ የሆነውን ጋብቻ ነው::

የተጋቡ ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ የሚኖሩ ከሆኑ የፍቺ ምክንያት ከግለሰባዊ ደንብ ሙሉ ለሙሉ የተሰየ ይሆናል:: የተጋቡን ጥንዶች ያጣመረው ታላቅ ፍቅር ፍቺን ፈጽሞ ስለማይፈቅድ ግለሰባዊ ደንብ ተፈላጊነት አይኖረውም:: ከዚህ በተቃራኒ እነዚህ ሰዎች ከመለያየት ይልቅ የፍቅራቸው ጥልቀት ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ ይሄዳል::

የክርስቲያን ጋብቻና በተጋቡት ጥንዶች መካከል ያለው ኅብረት ክርስቶስ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ካለው ኅብረት ጋር የሚመሳሰል መሆኑ በጣም ድንቅ ነው:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን አስመልክቶ ሲናገር:- «ይህ ታላቅ ምሥጢር ነው፤. . .» (ኤፌ 5:32) ብሏል::

ከዚህ የሚጠልቅ ምን ተመሳሳይነት አለ? ከዚህ የሚበልጥስ ምን ታላቅ ፍቅር አለ? «. . . እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንዲህ እንደ ራሱ አድርጎ ይውደዳት፤ . . .» ኤፌ 5:33::

የክርስቲያን ጋብቻ ውሎ አድሮ የሚያልፍና የሚያበቃ ግንኙነት አይደለም! በሕይወት ዘመን ሙሉ የሚሆን ጥምረት እንጂ:: ወንዱ ስለ ሴቲቱ የተናገረው እንዲህ ብሎ ነው:- «ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፤ሥጋም ከሥጋዬ ናት፤. . .» ዘፍ 2:23:: እርሷ የእርሱ ሰውነት ስትሆን እርሱ ደግሞ ራሷ ነው:: ሁለቱም አንድ ሥጋ ናቸው:: እርሱ ስለ እርሷ ሲል እናቱና አባቱን ይተዋል:: ይህ እንደ ምን ያለ ድንቅ ጥምረት ነው!

(35)
ፍርሃት

የልጅ ፍርሃት የሚሉት ፍርሃት አለ:: እንዲህ ዓይነቱ ፍርሃት ጨለማን ወይም ብቸኝነትን የሚያስፈራ ፍርሃት ነው:: እንዲህ ያለው ፍርሃት ሰውየው እስከሚያረጅ ድረስ አብሮት ሊቆይ ይችላል:: ይህ የአንድ ሰው ድካም ነው::

ሌላው ፍርሃት ደግሞ ከኃጢአት የሚመጣ ነው. . .

አዳም መፍራት የጀመረው ኃጢአት ከፈጸመ በኋላ ነው:: ስለሆነም «. . . ፈራሁ፤ተሸሸግሁም::» (ዘፍ 3:10) ብሏል:: ኃጢአትን የሚሠራ ሰው ሁሉ ኃጢአቱ

ይታወቅብኛል ብሎ ይፈራል። ስለሆነም ከኃጢአቱ መጥፎ ዝና ወይም መጥፎ ቅጣት ወይም መጥፎ ውጤት ይመጣብኛል ብሎ ይፈራል።

ከዚህ ሌላ በራስ ከመተማመን እጦት የሚመጣ ሌላ ፍርሃት አለ . . .

ይህ ፍርሃት፡- የውድቀት ፍርሃት ወይም ወደፊት የሚመጣ ያልታወቀ ነገር ፍርሃት ወይም በአለቃ ፊት የመቅረብ ፍርሃት ወይም አንድ ሁኔታን የመጋፈጥ ፍርሃት ሊሆን ይችላል።

ይህ ፍርሃት ከእምነት ጉድለትም ሊመጣ ይችላል። ይህ የእምነት ጉድለት በእግዚአብሔር ጥበቃና እንክብካቤ ላይ የሚያተኩር ነው። ቅዱሳን ግን በጭራሽ ፈርተው አያውቁም፤ የእግዚአብሔር ጥበቃ ከእነርሱ ጋር እንዳለና እንደሚጠብቃቸው ያውቃሉና። «በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም።» መዝ 22:4። «እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው፤የሚያስፈራኝ ማነው?» መዝ 26:1።

ከልጅነት ጊዜ አንስቶ በሚከሰት ውስብስብ የሥነ ልቦና ችግር ምክንያት ፍርሃት ሊመጣ ይችላል።

ለምሳሌ፡- አባቱ የሚጨክንበት ልጅ በቅጣት ወይም በተግሣጽ ወይም በስድብ ወይም የሠራው ሥራ ትክክል አለመሆኑ እንዲሰማው በማድረግ ፍርሃት በውስጡ ሥር ሰድዶ እንዲያድግ ምክንያት ይሆንበታል። ስለሆነም በሚሠራው ሥራ ላይ ሁሉ የማይተማመን ይሆናል፤ይፈራልም።

ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ ፈሪሃ እግዚአብሔርም አለ፡- «የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፤. . .» መዝ 110:10። ይሁን እንጂ ሰው ወደ እግዚአብሔር ፍቅር እስኪደርስ ድረስ በዚህ ውስጥ ያድጋል፡- «ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም፤. . .» 1ኛ ዮሐ 4:18። ፈሪሃ እግዚአብሔር ማለት ግን መደንገጥ ማለት አይደለም፤ አክብሮትና ቅዱስ ፍርሃት ማለት እንጂ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሎናል፡- «ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፤ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ።» ማቴ 10:28።

እግዚአብሔርን መፍራት ትእዛዛቱን ወደ መጠበቅ ይመራናል።

ቅዱስ አውግስጢን «በዚህ ዓለም የተራራ ጫፍ ላይ የተቀመጥሁ ሲመስለኝ በጥልቀት ባለው እኔነቴ ውስጥ ምንም አልሻም ምንምም አልፈራም።» ብሏል።

(36)
መስቀሉ በሕይወታችን ውስጥ - «ለ»

ክርስትና ያለ መስቀል ክርስትና ሊሆን አይችልም።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሎናል፡- «. . . እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ፤መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ።» ማቴ 16:24።

ጌታ ከዚህም የሚበልጥ ቃል ተናግሯል፡- «. . . መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም። ነፍሱን የሚያገኝ ያጠፋታል፤ ነፍሱንም ስለ እኔ የሚያጠፋ ያገኛታል።» ማቴ 10:38እና39።

መስቀሉ ከውስጥም ሆነ ከውጪ ሊሆን ይችላል. . .

ከውስጥ ስለሚሆነው መስቀል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ተናግሯል፡- «ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም፤ ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤. . .» ገላ 2:20።

ስለሆነም ራስን መካድ መስቀል ነው። ይኼኛውን መስቀል በመሸከም ስኬታማ የሚሆኑት ሰዎች ጥቂት ናቸው።

በውጪ የሚሆነው መስቀል አማኙ ሰው ስለ እግዚአብሔር ሲል በጽናት የሚሸከመው ማንኛውም መከራ ነው። ይህም በገዛ ፈቃዱ ወይም በሌሎች አስገዳጅነት ሊሆን ይችላል።

አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- «በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤. . .» ዮሐ 16:33። እንዲህም ተብሎ ተጽፎአል፡- «የጻድቃን መከራቸው ብዙ ነው . . .» መዝ 33:19። ከዚህ በተጨማሪም «. . . ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል . . .» ሐዋ 14:22።

ይሁን እንጂ መስቀሉ ከዚህ ሁሉ ሕማሙና መከራው ጋር ለእኛ የሚሆን የክብርና የደስታ ምንጭ ነው። ሐዋርያው እንዲህ ብሏል፡- «ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ።» ገላ 14።

ይኸው ሐዋርያ እንዲህም ብሏል፡- «ስለዚህ ስለ ክርስቶስ በድካም፣ በመንገላታትም፣ በችግርም፣ በስደትም፣ በጭንቀትም ደስ ይለኛል፤ስደክም ያን ጊዜ ኃይለኛ ነኝና።» 2ኛ ቆሮ 12:10።

መምህራችን ቅዱስ ያዕቆብም እንዲህ በማለት መክሮናል፡- «ወንድሞቼ ሆይ፤የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት።» ያዕ 1:2እና3።

ቤተ ክርስቲያን መስቀልን ስለምትወድ መለያዋ አድርጋዋለች።

ቤተ ክርስቲያን ልጆቿ ስለ እግዚአብሔር ሲሉ መከራ መቀበል እንዳለባቸው ታስተምራቸዋለች፤በኅሊናቸው ውስጥ ያኖሩትም ዘንድ «. . . ስለ ጽድቅ እንኳ መከራን ብትቀበሉ ብፁዓን ናችሁ።» (1ኛ ጴጥ 3:14) የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ትነግራቸዋለች።

ክርስትና መከራን ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ አድርጎ ይቆጥራል።

መጽሐፍ ቅዱስ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ይላል፡- «. . . ይህ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቶአችኋልና፤ስለ እርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ ነው እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም፤ . . .» ፊል 1:29።

በመከራና መስቀሉን በመሸከም ጊዜ እግዚአብሔር ልጆቹን አይተዋቸውም።

በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ «የጻድቃን መከራቸው ብዙ ነው፤» ከሚለው ቃል ቀጥሎ የተጻፈው «እግዚአብሔርም ከሁሉ ያድናቸዋል።» (መዝ 33:19) የሚለው ነው። ከዚህ በተጨማሪ እንዲህ የሚል ቃል አለ፡- «የኃጥአን በትር በጻድቃን ዕጣ ላይ አይኖርም።.» መዝ 124:3።

(37)
የምትናገረው መቼ ነው?

ለመናገር ስትል ብለህ የምትናገር ከሆነ ይህ አንድ ነገር ነው። ከንግግርህ አንድ ነገር ለማግኘት ብለህ የምትናገር ከሆነ ደግሞ ይህ ሌላ ነገር ነው። ይኼኛው ንግግርህ ዓላማና ውጤት ያለው ንግግር እንድትናገር ያደርግሃል።

ለዚህ ለሁለተኛው ንግግርህ ጠቃሚ ምክር ያስፈልግሃል፡-

+ ሊሰማህ የሚችል ጆሮ ሲኖር ብቻ ተናገር። የምታወራው ሰው የማያዳምጥህ ከሆነ ንግግርህን አቁም። ከተሰላቸና ከደከመ ሰው ጋር አትነጋገር፤እርሱ አካሉ ወይም ሥነ ልቦናው ወይም ያለበት ሁኔታ በድካም ውስጥ ሊሆን ይችላልና።

በሥራ በተጠመደና አንተን ለማድመጥ ከማይችል ወይም አንተን ለመረዳትና ባነሣኸው ነጥብ ላይ ከአንተ ጋር ለመወያየት ጊዜ ከማይኖረው ሰው ጋር አትነጋገር።

አንድ በጥበብ የተነገረ ቃል አለ፡- «የወርቅ እንኮይ በብር ፃሕል ላይ፤የጊዜው ቃል እንዲሁ ነው።» ምሳ 25:11።

ከሰው ጋር ከመነጋገርህ በፊት ትክክለኛውን ሰዓት ምረጥ። የምታናግረው ሰው አንተን ለማዳመጥ፣ ለመረዳትና ንግግርህን ለመቀበል በልቡም ሆነ በአሳቡ በመልካም ሁኔታ ውስጥ መሆኑንና መዘጋጀቱን ስትመለከት ተናገር።

ንግግርህ ውጤታማ እንዲሆን ከፈለግህ አድማጮችህን አሸንፍ፤ ከዚህ በኋላ ንግግርህንና ውጤቱን ታሸንፋለህ።

ብዙ ሰዎች የሚያናግሩትን ሰው ቢሆንም እንኳ በማንኛውም መንገድ ሊያሸንፉት ነው የሚያነጣጥሩት። ይህ ደግሞ ሁሉንም ጉዳይ ባለማግኘት ይጠቃለላል። ያለ ሥነ ልቦናዊ ጎን ሥነ አመክንዮ (ሎጂክ) ብቻውን በቂ አይደለም።

1/ የሚወያየውን ሰው የሚያሸንፍና እንደ ተሳሳተ በሰዎች ፊት የሚያረጋግጥለት ሰው ከዚህ ሰው ምንም ዓይነት መልካም ነገር ሊጠቀም አይችልም።

2/ ለሚያናግረው ሰው እንዲናገር ምንም ዕድል ሳይሰጥ ንግግሩን የሚያቋርጥ፣ ንግግሩ ከማብቃቱ በፊት መልስ የሚሰጥና እንደ ተቃዋሚ የሚቆም ሰው መልስ ለመስጠት ወይም ለማሳመን ያለውን ችሎታ ያውቅ ዘንድ የሚወያየውን ሰው ልብ ሊያገኝ አይችልም፤የሰውየው አመለካከት አሳማኝ ቢሆንም እንኳ።

3/ ደካማ፣ ዋጋቢስ፣ ተግባራዊና የማያሳምኑ እንደ ሆኑ አድርጎ በሌሎች ሰዎች አሳብ ላይ የሚያፌዝ ሰው ምንም ዓይነት ውጤት ሊያገኝ አይችልም።

ስለሆነም የተናጋሪውን ሰው አመለካከት አክብር፤የተፈለገውን ያህል የምትቃወመው ብትሆንም እንኳ። በትሕትና ውስጥ ሆነህም መልስ ስጠው።

የምታናግረው ሰው አእምሮ ላይ ከመድረስህ በፊት ወደ ልቡ ለመድረስ ሞክር። በዚህ ጊዜ ልቡንም ሆነ አእምሮውን በእርግጠኝነት ማሸነፍ ትችላለህ።

(38)
የልብ ሰላም

የልብ ሰላም ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች መካከል አንዱ ነው።

መንፈስ ቅዱስ በአንድ ሰው ውስጥ ሲያድር የልብ ሰላምን ያጎናጽፋል። ሐዋርያው ስለዚህ ሰላም ሲጽፍ እንዲህ ብሏል፡- «አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል።» ፊል 4:7።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሕዝቡ «ሰላምን እተውላችኋለሁ፤ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ . . .» (ዮሐ 14:27) ብሎ ስለ ተናገረ ሰላምን የሚሰጠው እርሱ ነው።

ከውጪ ምንም ዓይነት ተጽእኖ ቢገጥመውም ሙሉ ሰላም ያለው ሰው አይታወክም፣ አይጨነቅም ወይም አይረበሽም።

የእርሱ ሰላም የሚመሠረተው ከውጪ ባሉ ሁኔታዎች ላይ አይደለም፤በእግዚአብሔር ጥበቃና እንክብካቤ ላይ ባለው መተማመንና በእርሱ ቃል ኪዳኖች ላይ ባለው እምነት ጭምር እንጂ።

እግዚአብሔር እስከ አለ፣ እስከ ሠራና እስከ ጠበቀን ድረስ ምንም መፍራት አያስፈልግም። ይህ በመሆኑም ነቢዩ ዳዊት እንዲህ በማለት ተናግሯል፡- «በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ፤አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል።» መዝ 22:4።

የዳዊት ሰላም ምንጭ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የመሆኑ ስሜት ነው።

ሐዋርያት በታንኳ ሲጓዙ ጌታ ያንቀላፋ ስለ መሰላቸው ሞገዱ ሲያናውጣቸው በጣም ተጨንቀው ነበር። በዚህ ጊዜ ሰላማቸውን አጥተው ነበር። በእነርሱ ላይ የበረታው ውጪያዊው ሁኔታና የጌታ ሥራ ከእነርሱ ጋር ያለ መስሎ ስላልታያቸው ነው። ስለሆነም ጌታ ተነሥቶ ነፋሱን በመገሠጽ ሰላማቸውን መልሶላቸዋል።

ውስጣችሁ ጥብቅ ከሆነና በእምነታችሁ የጸናችሁ ከሆናችሁ ከውጪ ያለ ምንም ዓይነት ነገር አያናውጣችሁም። ነፋስና ጎርፍ እንዳልጣለውና በዓለት ላይ እንደተገነባው ቤት ሁኑ። ይህ ቤት ውስጡ ጥብቅ ነበረ።

ጠንካራ መርከብ በሚመታው ብርቱ ማዕበል ጉዳት ሊደርስበት አይችልም። ለመሆኑ መርከብ የሚጎዳው መቼ ነው? ወደ ውስጡ ውኃ የሚያስገባ ቀዳዳ ሲኖር ነው። በአንተ ዘንድ ውኃ የሚያስገባና የሚያሰጥም ቀዳዳ ይኖር ይሆን?

ቅዱስ እንጦንስ ለልብ ሰላም ምሳሌ የሚሆን ሰው ነው። ሐዋርያው ቅዱስ አትናቴዎስ ስለ እርሱ ሲናገር፡- «መሪር ነፍስና የታወከ አሳብ ያላቸው ሰዎች ሁሉ የቅዱስ እንጦንስን መልክ ሲመለከቱ ልባቸው በሰላም ይሞላል።» ብሏል።

ሰላሙ የበዛለት ሰው ይህን ሰላሙን ለሌሎች ያንቀረቅራል፤ በዚህም ለሌሎች መደላደልን ያድላል።

ስለዚህ በሰላም ውስጥ ኑሩ። ይህን ካደረጋችሁ ትደላደላላችሁ፣ በመተማመንና በመረጋጋት ይሆንላችኋል፣ በሥጋዊውም ሆነ በመንፈሳዊው መንገድ ውስጥ በመልካም ጤንነት ትኖራላችሁ።

(39)
መስቀልህን ተሸከም፤የምትሰቀል እንጂ የምትሰቅል አትሁን!

አንተ የምትሰቀል ከሆንህ እግዚአብሔር በዚህኛው ዓለም ሳይሆን በወዲያኛው ዓለም ከአንተ ጋር በመሆን ሙሉ መብትህን እንደሚመልስልህ እርግጠኛ ሁን።

ይሁን እንጂ አንተ ሌሎች ሰዎችን የምትሰቅል ከሆንህ እግዚአብሔር አንተ ከሌሎች የወሰድኸውን መብት ለእነርሱ እስከሚመልስና እስኪቀጣህ ድረስ አንተን እንደሚቃወምህ እርግጠኛ ሁን።

ሌሎችን ሰቀልህ ማለት አንድ የሚያጠቃና የሚያስቆጣ ሁኔታ በአንተ ውስጥ አለ ማለት ነው። እነዚህ ሁሉ የተለያዩ የግፍ ሥራ አመለካከቶች ከአንተ ከሚጠበቁት የጽድቅ ሥራዎች ጋር አይስማሙም ወይም ማንኛውም ተራ ሰው ከሚሻው ከሰው አሳባዊነት ጋር አይጣጣሙም።

ስለ እውነት ወይም ስለ እምነት ብለህ ብትሰቀል ግን የምትቀበለው ማንኛ ውም ዓይነት መከራ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ እንደሚታሰብ ተማመን። ይህ ጉዳይ በመንግሥተ ሰማያት አክሊል ሲያቀዳጅ በምድር ደግሞ በረከትን ያስጣል።

እግዚአብሔር፣ ቅዱሳንና ሰማያት ሁሉ በአንተ ጎን እንደሚቆሙ እርግጠኛ ሁን።

ትክክል የሆነውን ነገር የሚከተሉ ሰዎች ሁሉ ስለ ትክክለኛው ነገር ሲሉ መከራ ይቀበላሉ።

በእምነታቸው ጥብቅ ሆነው የቆዩ ሰዎች ለእምነታቸው ዋጋ የከፈሉ ናቸው።

የሰማዕታት ታሪክ ስለ እምነታቸው ሲሉ ደማቸውን ስላፈሰሱ ሰማዕታት የሚነግረን ብዙ አለው። የእኛ ታሪክ በተለይ እነዚህን በመሰሉ ታሪኮች የተሞላ ነው።

አንድ ሰው ቁጡ ቢሆንም ይህ ሁኔታ አሳባዊነቱን አያረጋግጥም። ኢ-ፍትሐዊነት ቀላልና በማንኛውም ሰው ሊደረስበት በሚቻል ርቀት ውስጥ ያለ ጉዳይ ቢሆንም ከማንኛውም ሃይማኖት ጋር አይጣጣምም።

ስለሆነም አሳባዊነትህንና ቁጣህን በመያዝ መስቀሉን ተሸከም። አንተን የሚያስፈራህ የተሳሳተ ነገር እስከ መጨረሻው ድረስ አይቆይም።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መራር ሕማምን ቀምሷል መስቀሉንም ታግሦ ተሸክሟል። ስለሆነም በማንኛውም ቦታና ጊዜ መከራ የሚቀበሉትንና የሚሰቀሉትን ሰዎች ሊያግዛቸው ይችላል።

እስቲ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥነ ስቅለት የሚያሳየውን ሥዕል ተመልከቱት፤ ትጽናናላችሁ።

ከስቅለት በኋላ የትንሣኤ ክብር እንደሚኖር ተማመኑ።

እግዚአብሔር አምላክ የኢይዝራኤላዊው የናቡቴ ደም ሲፈስ ተመልክቶ ዝም አላለም። የወሰደው እርምጃ ከባድ ነበር። 1ኛ ነገ 20:19።

ስለሆነም «እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ፤በርታ ልብህም ይጽና፤ እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ።» መዝ 26:14።

ከተሰቀልህ ክርስቶስ ከአጠገብህ ይኖራል፤ምስሉንም በአንተ ውስጥ ይመለከታል። ስለሆነም የክርስቶስ ምስል ትሆናለህ።

(40)
በበዓለ አምሳ ወቅት የሚኖር መንፈሳዊነትህ

ረቡዕና ዓርብን ጨምሮ በበዓለ አምሳ ወቅት ጾምና ስግደት የለም። በመሆኑም ቀናቱ ስለ እውነት የደስታ ቀናት ናቸው።

ይሁን እንጂ በደስታ ጊዜም መንፈሳዊ መሆን እንችላለን።

አሸክሲዚያ ዘላለማዊ ደስታ ባለበት በመንግሥተ ሰማያት ውስጥ እንዴት መንፈሳውያን ልትሆኑ ትችላላችሁ?

በዚህ ወቅት ጾምና ጸሎትን ብታጧቸውም ብዛት ባላቸው ጸሎቶች፣ መንፈሳዊ ንባባት፣ ተመስጦዎች፣ ዜማዎችና መዝሙራት ልታካክሷቸው ትችላላችሁ። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ደስታና መዝሙርን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- «. . . ደስ የሚለውም ማንም ቢኖር እርሱ ይዘምር።» ያዕ 5:13።

ድኅነትን በሚያመጣው በእግዚአብሔር ፍቅር ላይ በተመሰጠ በመቆየትም ነፍስህን በዚህ ጊዜ ልትመግባት ትችላለህ። ከትንሣኤ በኋላ የእግዚአብሔር ፍቅር ከሐዋርያቱ ጋር ለአርባ ቀናት ቆይቶአል። «አርባ ቀን እየታያቸው ስለ እግዚአብሔርም መንግሥት እየነገራቸው፤. . .» ሐዋ 1:3።

በዚህ ጊዜ ውስጥ መዝሙረ ዳዊትን በማንበብ፣ የግል ጸሎት በማድረስና እግዚአብሔርን ስለ ድንቅ ሥራው በማመስገን ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገርንና ከእርሱ ጋር መሆንን ትለማመዳላችሁ። ከእግዚአብሔር ጋር አብራችሁ መሆናችሁን ሊያስናክል ከሚችል ከማንኛውም ነገር ራቁ።

የደስታ ሕይወትን በእግዚአብሔር ኑሩት እንጂ ከመጠን በላይ በመብላትና በመጠጣት በሚሆን በሥጋዊ ደስታ ውስጥ አትኑሩት።

ጾምን ማቋረጥ ማለት ግን በምግብ ፍላጎት ውስጥ መቆየት ማለት አይደለም።

ጾም በሌለበት ጊዜም ራስን መግዛትም አስፈላጊ ነው።

(41)
የቅንዓት ትርጉም ምንድር ነው?

ቅንዓት ልብንና ፈቃድን እንደ እሳት በማቀጣጠል አንድ ሰው መልካም ነው ብሎ ያመነበትን ነገር እንዲፈጽም የሚያደርግ ነው። አንድ ሰው ጉጉ ሲሆን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «. . . ስለ ቅንዓት ብትጠይቁ ቤተ ክርስቲያንን አሳዳጅ ነበርሁ።» (ፊል 3:6) በማለት እንደ ተናገረ ለተሳሳተ ነገር እንኳ በቅንዓት የተጠመደ ይሆናል።

መዝሙረኛው ዳዊት «የቤትህ ቅንዓት በልታኛለችና፤. . .» (መዝ 68:9) ብሎ እንደተናገረው ያለ ቅዱስ ቅንዓትም አለ። በገላ 5:20 ላይ የተጠቀሰ የኃጢአት ቅንዓትም አለ። ከዚህ በተጨማሪ «ቅንዓትም እንደ ሲኦል የጨከነች ናትና።» (መኃ 8:6) ተብሎ የተጻፈላት ቅንዓትም አለች። ይህ በመሆኑም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ተናግሯል፡- «. . . ሁልጊዜ በመልካም ነገር ተፈላጊ ብትሆኑ መልካም ነው።» ገላ 4:18።

ሐዋርያው ለሮሜ ሰዎች እንደ ነገራቸው መልካም ያልሆነ ቅንዓትም አለ፡- «በእውቀት አይደለም እንጂ ለእግዚአብሔር እንዲቀኑ እመሰክርላቸዋለሁ።» ሮሜ 10:2።

+ አንድ ሰው ምንም ሳይገባው፤ያለ ምንም እውቀትና ምርመራ፤ያለ አንዳች ትክክለኛ ነገር፤እንዲያው በሰማው ነገር ብቻ ቀናተኛ ይሆናል። ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- «. . . የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን

እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል።» ዮሐ 16:2። እንደዚህ ዓይነቱ ቅንዓት ከእውቀት ጋር የተቀናጀ አይደለም። ይህ ደግሞ እንደ ጠርሴሱ ሳውል ያለ ቅንዓት ነው። እርሱ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- «. . . ነገር ግን ሳላውቅ ባለማመን ስላደረግሁት ምሕረትን አገኘሁ! . . .» 1ኛ ጢሞ 1:13።

ስለሆነም ፈጥነህ ቀናተኛ አትሁን፤ቅናትህን ከእውቀት ጋር አቀናጅ እንጂ።

ስለ ሌሎች ሰዎች የተነገሩህን ስሕተቶች ወይም የለውጥ ብቃቶች በሙሉ አምነህ አትቀበላቸው።

ሁሉንም ነገር አሰላስል፣ አጥና፣ መርምር። ከዚህ በኋላ መልካም ከሆኑት ጠባያት ጋር ተጣበቅ።

+ ቅንዓት በምክንያቱና በአገላለጽ መንገዱ የተሳሳተ ሊሆን ይችላል።

ለምሳሌ፡- ጴጥሮስ ለጌታ ካለው ቅንዓት የተነሣ ሰይፉን መዝዞ የሊቀ ካህናቱን ባሪያ ጆሮ ቆርጦ ጥሏል። የሣምራውያን ከተሞች ከሆኑት በአንዲቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች ጌታን አንቀበልህም ባሉት ጊዜ ዮሐንስና ያዕቆብ ለእርሱ ካላቸው ቅንዓት የተነሣ ተገቢ ያልሆነ ጥያቄ አቅርበውለት ነበር፡- «ጌታ ሆይ! ኤልያስ እንዳደረገ እሳት ከሰማይ ወርዶ ያጥፋቸው እንል ዘንድ ትወዳለህን?» ሉቃ 9:54።

አንድ ሰው በመስድብና በማቃለል፤በማዋረድና በማንኳሰስ፤በማሳፈርና በማጥፋት ቅንዓት የተሞላ ሊሆን ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ ሰው በመንገዱ ላይ የሚቆሙትን ሁሉ መንፈሳዊ ባልሆነ ጠባይ የሚያጠፋ የጥፋት መሣሪያ ሆኖ ሊቀየር ይችላል።

እንዲህ ዓይነቱም ቅንዓት በእውቀት የማይገለጥ ቅንዓት ነው። ምክንያቱም እንዲህ ያለው ሰው ቅንዓቱን የሚገልጥበትን ትክክለኛ መንፈሳዊ መንገድ ስለማያውቅ ነው።

በአንድ ወቅት ከአርባ የሚበዙ አይሁድ ጳውሎስን እስኪገድሉ ድረስ ላለመብላትና ላለመጠጣት ተማምለው እንደ ነበር ይታወቃል። ሐዋ 23:12-13።

+ ከራስ ወዳድነትና ከአድሎ ጋር የተቀየጠ ቅንዓትም አለ።

ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ሁለት ሰዎች ትንቢት ሲናገሩ በተመለከተ ጊዜ ስለ ነቢዩ ሙሴ የቀናው የነዌ ልጅ ኢያሱ ነው። በዚህ ጊዜ ሙሴ እርሱን እንዲህ በማለት ተናግሮት ነበር፡- «የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ነቢያት ቢሆኑ እግዚአብሔርም በእነርሱ ላይ መንፈሱን ቢያወርድ አንተ ስለ እኔ ትቀናለህን?» ዘኁ 11:29።

(42)
ጠብ

ጠብን ማንም አይወድም።

ሰዎች ጠብን ስለሚጠሉ ከጠብና ከጠበኛ ሰዎች ይሸሻሉ።

ከዚህ በተመሳሳይ ጊዜ ጨዋነትን፣ ቸርነትንና ርኅሩኅነትን ይወዳሉ።

በጠብ አማካይነት የፈለጉት ግብ ላይ ቢደረስም እንኳ ውጤቱ ጊዜያዊ ነው። ጠቡ አንድ ጊዜ ሲርቅ እንዲህ ዓይነቱ ውጤት ይጠፋል።

ስለሆነም ብዙ ጠበኛ ሰዎች በሕይወታቸው ሙሉ እንዲህ ባለው ጠባያቸው ይቀጥላሉ። ጠባቸውን ካቆሙ መውደቅን ይፈራሉ። በተመሳሳይ ጊዜም የሌሎች ሰዎችን ብቀላና ቁጣ ይፈራሉ።

በሰው ልጆች ዘመናት ሁሉ ጠብ የአምባገነን ሰዎች መሣሪያ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የሽብርተኞች፣ የዓመጸኞችና የጨካኞች መሣሪያ ነው።

እነዚህ ሰዎች የሚስማሙት ከሰዎች ፈቃድ ጋር እንጂ ከልባቸው ጋር አይደለም።

ልባቸው ደስተኛ ባይሆንና አእምሮአቸው ባያምንም የሰዎችን ፈቃድ በመቆጣጠር ነገሮችን ያከናውኑ ዘንድ በኃይል ያስገድዷቸዋል። ስለሆነም በእነዚህ ሰዎች ዘንድ ለውጥ ቢኖርም ውጪያዊ ነው። ለውጥ የሚመጣው ከልብ ውስጥ ነው።

ይህ በሞራል ላይም ተግባራዊ ይሆናል።

ጠብ የሐሰት ገጽታ ነው እንጂ ሥርዓትን አይገነባም።

ጠብ ለመንግሥት ከመገዛትና ሕግን ከማክበር ሊመጣ ይችላል እንጂ መልካምነትን የሚወድ ንጹሕ ልብን ሊገነባ አይችልም።

ለጠብ እጅ ከመስጠት የተነሣ አንድ የሆነው ሰው ሁለት ሆኖ ይቀየራል፡- ውጪያዊው ሰው የቅድስና ገጽታ ያለው ሆኖ ሲቀየር ውስጣዊው ሰው ደግሞ ኃጢአትን የሚወድ ሆኖ ይቀየራል። ይህ ሰው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «. . . በውጭ አምረው የሚታዩ በውስጥ ግን የሙታን አጥንት ርኵሰትም ሁሉ የተሞሉ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮችን ስለምትመስሉ ወዮላችሁ።» (ማቴ 24:27) ብሎ በመናገር የገለጸውን ገጽታ የሚሥል ሆኖ ይቀየራል።

እግዚአብሔር ራሱ «ልጄ ሆይ፤ልብህን ስጠኝ፤. . .» (ምሳ 23:26) በማለት ተናግሯል።

እግዚአብሔር የሚፈልገው ውስጣዊውን ልብ እንጂ ውጪያዊውን ገጽታ ወይም መልክ አይደለም።

ስለሆነም የአንድ ሰው መልካምነት የሚለካው በፍቅሩ መጠንና መልካም ለሆነው ነገር ባለው እምነት ነው።

ሰው መልካም የሆነውን ነገር ከወደደ ያለ ምንም ውጪያዊ የጠብ ግፊት፣ ያለ ምንም ፍርሃት፣ ምንም ዓይነት ዋጋ ወይም ውዳሴ ወይም ማንኛውም ዓይነት ክፍያ ሳይቀበል ያከናውነዋል።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው መልካም የሆነውን ያለ ምንም ጠብ በመጥራት ነው። እርሱ ሰዎች መልካም የሆነውን እንዲሠሩ በጭራሽ አላስገደዳቸውም፤መልካም መሥራትን እንዲወዱ እንጂ። ከዚህ በኋላ መልካም መሥራት በልባቸውና በስሜታቸው ውስጥ የሚኖር ፍላጎት ይሆናል፤ የሚሠሩትንም ሥራ ያለ ምንም ግዴታ ያከናውኑታል። እግዚአብሔር በፍርሃት የሚከተሉት ባሪያዎችን አይፈልግም።

በጠብ አማካይነት የሚመጣ መልካም ነገር የሚበጅ አይደለም።

(43)
መንፈሳዊው መንገድ

የንስሐ ሕይወት የመንፈሳውዊ መንገድ መጀመሪያ ነው። በዚህ የሽግግር ጊዜ ውስጥ ሰው በእግዚአብሔር ላይ በጠላትነት ከመነሣትና እርሱን ከመቃወም ይልቅ የእርሱን መንገድ መከተል ይጀምራል።

የአንድ ሰው ግብ የቅድስና ሕይወትን ለማግኘት ከሆነ መንገዱ ረዥም ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ቅድስናን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- «. . . ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ፤ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና።» ዕብ 12:14። እግዚአብሔርም «. . .ቅዱስ ነኝና እናንተ ቅዱሳን ሁኑ።» (ዘሌ 19:2) ብሎናል።

አንድ ሰው ሲያድግ፣ እግዚአብሔርን ምሳሌ አድርጎ ሲወስድና ወደ እርሱ መልክና ምሳሌ ሲጠጋ የሚለዋወጡ የቅድስና ደረጃዎች አሉ።

በእምነት ውስጥ ያለ ሰው እግዚአብሔር ከእርሱ እንደሚጠብቀው ከቅድስና ሕይወት ደረጃ ወደ ፍጹምነት ደረጃ የሚያነጣጥረው እንዲህ ነው።

እግዚአብሔር ይህ ፍጹምነት እንዲኖረን ያዘዘን እንዲህ በማለት ነው፡- «እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ።»

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ከተነጠቀ በኋላ ሰው ሊናገር የማይገባውን የማይነገረውን ቃል ሰምቶአል። እግዚአብሔር የበዙ ስጦታዎችንና እውቀትን ስላደለው ስሙን በአሕዛብ መካከል እንዲሸከም አድርጎታል፤ ከሌሎቹ ሐዋርያት ሁሉ የበለጠ መከራ እንዲቀበልም ሆኗል።

ይህ ቅዱስ ጳውሎስ እርሱ ስለ ደረሰበት መንፈሳዊ ከፍታ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- «አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን እንደ ተፈጸምሁ አይደለም፤ነገር ግን ስለዚያ በክርስቶስ ኢየሱስ ደግሞ የተያዝሁ ያን ደግሞ እይዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ። . . . ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ወዳለውም እየተዘረጋሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ።» ጳውሎስ ይህ ምክሩን ያጠቃለለው፡- «እንግዲህ ፍጹማን የሆንን እኛ ሁላችን ይህን እናስብ፤. . .» (ፊልጵ 3:12-15) በማለት ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ ሊይዘው ወይም ሊያገኘው የሚሞክረውና «በፊቴም ወዳለው . . .» ብሎ የገለጸው ነገር ምንድር ነው?

ይህን አስመልክቶ ለኤፌሶን ሰዎች ሲጽፍ እንዲህ ብሏል፡- «. . . ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቀቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል፤ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ።» ኤፌ 3:18እና19።

«. . . እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ።» የሚለው ቃል ምንኛ ድንቅ ነው!

ፍጹምነት በመንፈሳዊው መንገድ ውስጥ ማብቂያ የለውም።

አንዱን ደረጃ ስታልፍ ዕድገት ያመጣህ መስሎ አይሰማህም፤ስለሆነም በጸጸት ሌላ ደረጃ ትጨምራለህ።

አድማሱን የምታሳድድ ሰው ነው የምትመስለው፤ምድርና ሰማይ የሚገናኙ-በት ነው ብለህ የምታስብበት ቦታ ላይ ስትደርስ ከፊትህ ማብቂያ በሌለው ሁኔታ ተዘርግቶ ይጠብቅሃልና።

ጉዳዩ እንዲህ የሚቀጥል ከሆነ ወደ ፊት እንቀጥል።

እስከ አሁን ንስሓ ላይ ካልደረስን የመንገዱ መጀመሪያ እርሱ ነው . . . ከእግዚአብሔር መንገድ ወጥተናል ብለን መናገር እንችላለን ማለት ነው?!

(44)
ብልሀቱ ወይም ዘዴው

ብዙ ጊዜ የሰዎች ችግር የሚሆነው ዓላማው ሳይሆን ብልሀቱ ወይም ዘዴው ነው።

እያንዳንዱ ሰው ለደስታው ማለሙ እርግጥ ነው!ከነዚህ መካከል ብዙዎቹም ለሌሎች ደስታ ያልማሉ። ይሁን እንጂ የሰዉ ሁሉ የመጀመሪያ ችግር ዓላማዎቹን ለማሳካት የተጠቀመበት ዘዴ ነው።

አንዳንድ ሰዎች ፊታቸውን መንፈሳዊ ወዳልሆነው ዘዴ ሲመልሱ ሌሎች ደግሞ በሰው ክንድ ለመታመን ፊታቸውን ይመልሳሉ።

ሌሎች ደግሞ ይበልጥ ምቹና ቀላል ወደ ሆነው ዘዴ ያተኩራሉ። ይበልጥ ምቹውና ቀላሉ ዘዴ ይሁን እንጂ ስኬታማው፣ አስተማማኙና ንጹሑ ዘዴ አይደለም።

ሌላው ሰው ደግሞ ምክሩን ሳይመረምርና ሳይወያይበት ከሚቀርቡት ሰዎች ምክር ይቀበላል። ወይም ምንም ሳያረጋግጥ የሌሎችን ደረጃዎች ይከተላል።

በጣም ብዙ ጊዜ ታዲያ እነዚህ ዘዴዎች የሚመሩት ከታሰበው ዓላማ በተቃራኒ ነው።

ከዚህም የተነሣ አንድ ሰው ባለ መማር በዚሁ ሊቀጥል ይችላል።

ሰው በዚሁ ሊቀጥል የሚችለው በችኮነት ወይም ረዳት በማጣት ወይም በሌሎች በመተማመን ወይም በጊዜ ላይ ጥገኛ በመሆን ወይም አንድ ነገር ለማግኘት ሲል ነው።

ምክንያት ያለውና ብልኅ የሆነው ሰው ግን መንገዱንና ዘዴውን ይመርጣል።

እርሱ የሚመርጠው ዓላማው ላይ ሊያደርሰው የሚችለውን ትክክለኛ መንገድ ነው።

እርሱ የሚመርጠው ምንም ዓይነት ስሕተት የሌለበትን ዘዴ ነው።

እርሱ በአንድ ሰው አመለካከት ላይ ጥገኛ ሳይሆን በጥበብ የሆነውን ምክር ይመርጣል።

እግዚአብሔር ለሰው ሁለት ጆሮዎች የሰጠው የመጀመሪያውን አመለካከት በአንዱ ጆሮው ሊያዳምጥበትና የዚህ ተቃራኒ የሆነውን አመለካከት በሁለተኛው ጆሮው እንዲያዳምጥበት ነው። አእምሮ እያንዳንዱን አመለካከት ለመመዘንና የሚበልጠውን ለመምረጥ በመካከል ይኖራል።

ብልህ ሰው ዘዴዎቹ የተሳሳቱ ወይም መልካም ወደ ሆነው ነገር የማይመሩ ከሆኑ ይቀይራቸዋል።

ብዛት ያላቸው ጉድጓዶች፣ ቀዳዳዎች፣ ሕጸጾችና አደጋዎች ባሉበት መንገድ ላይ የሚቀጥል ሰው በልቡ ወይም በአስተሳሰቡ አካሄድ ውስጥ ስህተት ለመኖሩ ምንም ጥርጥር የለውም።

ብዙ ጊዜ አንድ ሰው ከትዕቢቱ የተነሣ የሌላውን ሰው ስሕተት ለማስተካከል አይፈቅድም። እርሱ የሚጨነቀው ለክብሩ ወይም ለዝናው ወይም ከተለወጠ ሰዎች ምን ሊሉት እንደሚችሉ ማሰቡ ላይ ነው። ይህ ማለት ደግሞ መንገዱ የተሳሳተ ነው እንደ ማለት ነው! ይሁን እንጂ ኩራት በሕይወታቸው መንገድ ላይ መሰናክል ሳይሆን ሕይወታቸውን የለወጡ ቅዱሳን ብዙ ናቸው።

ብዙዎች ደግሞ ሊለወጡ ስላልቻሉ እግዚአብሔር በመካከል ጣልቃ በመግባት መንገዳቸውን ለውጦላቸዋል።

ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን፦ ሎጥ፣ የጠርሴሱ ሳውል፣ ነቢዩ ዮናስ፣ ሙሴና ሌሎችም ቅዱሳን ሰዎች ናቸው።

(45)
ልጆቹን በማክበር ውስጥ ያለ የእግዚአብሔር ትሕትና

እግዚአብሔር ብቻውን ይሆን ዘንድ ስላልወደደ ሕዋውን በገዛ ፈቃዱ እስከ አሁን ድረስ እንዲኖር በማድረግ ለሌሎች ፍጥረታት ስጦታ አድርጎ ፈጥሮአል። ሰውንም በክብር የፈጠረው በትሕትናው ነው፦ «እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤. . .» ዘፍ 1:27።

የእግዚአብሔር መልክ ለሰው ልጆች የመጀመሪያ ክብራቸው ነው።

የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ደግሞ ሌላው ከእግዚአብሔር ለሰው ልጆች የተሰጠ ክብር ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ «. . . አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኗልና! አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው፤የጠራቸውን እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው! ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው።» ሮሜ 8:29እና30። «. . . ተስፋውም ፍጥረት ራሱ ደግሞ ከጥፋት ባርነት ነፃነት ወጥቶ ለእግዚአበብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር ነፃነት እንዲደርስ ነው።» ሮሜ 8:21።

ከዚህ በተጨማሪ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ክብር አክሊል፤ ሊመጣና በእኛ ውስጥ ሊገለጥ ስላለው ክብር የተገለጸውን እናነባለን፦ «. . . አብረንም እንድንከበር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን።» ሮሜ 8:17።

እግዚአብሔር ለሰው ልጅ በዚህ ምድር ከሚሰጠው የተለያየ ክብር በተጨማሪ በዘላለማዊነት ውስጥ የሚጠብቀው ክብር ብዙ ነው፦ «በእኔ ተማምኖአልና አስጥለዋለሁ፤ ስሜንም አውቋልና እጋርደዋለሁ! ይጠራኛል እመልስለትማለሁ! በመከራውም ጊዜ ከእርሱ ጋር እሆናለሁ፤ አድነዋለሁ አከብረውማለሁ።» መዝ 90:14-15።

እግዚአብሔር ለልጆቹ ክብር በመስጠት ይደሰታል።

ይሁን እንጂ ሰዎች የሚሰጡት ክብርና እግዚአብሔር የሚሰጠው ክብር ለየቅል ናቸው!የእርሱ መለኮታዊ ክብሩ ነውና።

ይህ መለኮታዊ ክብሩ ለሌሎች አይሰጥም፤በከፍታው ያለ የእርሱ ክብር ነውና። ይህ ክብር የማይወሰንና ሊናገሩት የማይቻል ክብር ስለሆነ «ክብር፣ ውዳሴና አምልኮ ለአንተ ይሁን» እንላለን።

ሰው የሚቀበለው ክብር ምንም ይሁን ምን የእግዚአብሔርን ክብር ፈጽሞ ሊቀንስ አይችልም። ከአንድ የሚነድ እሳት ላይ ምንም ሳታጎድሉ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሻማዎችን ልትለኩሱ ትችላላችሁ።

ልጆቹን በተለያዩ መንገዶች የሚያከብረው እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን። ከእነዚህ መንገዶቹም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች፣ ተአምራት መፈጸም፣ በዲያብሎስና በጠላት ላይ ኃይል ማግኘትና የመሳሰሉት ናቸው። እግዚአብሔር ልጆቹን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያዎች አድርጓቸዋል። «. . . ልጅነትና ክብር ኪዳንም የሕግም መሰጠት የመቅደስም ሥርዓት የተስፋውም ቃላት ለእነርሱ ናቸውና፤ . . .» ሮሜ 9:4።

(46)
ጥበብ

ጥበብ የሌለበት ማንኛውም የቅድስና ሥራ - የቅድስና ሥራ አይደለም።

ለምሳሌ፦ ፍቅር ከጥበብ ጋር መሆን አለበት። አለበለዚያ ወደ መንቀባረርና ጥልቅ ወደ ሆነ ጎጂ ፍቅር ሊለወጥ ይችላል።

ከዚህ በተጨማሪ ምን፣ መቼና እንዴት መናገር እንደሚገባ ለማወቅ ጥበብ ከእነዚህ ነገሮች ጋር መቀናጀት አለባት።

ጥበብ የተሟላ መሆን ያለባት በበላይ አለቆችና በጳጳሳት ብቻ ሳይሆን በሁሉም አገልጋዮች ዘንድ ነው፤በዲያቆኑም ጭምር። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ተናግሯል፦ «. . . በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ፤ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን፤. . .» ሐዋ 6:3።

ጥበብ ለተጠቃሚዎቿ ጥልቅ መንፈሳዊ አስተሳሰብን፣ ግልጽ የሆነ መረዳትን ታድላለች። ይህ ደግሞ ለመምረጥና ልዩነት ለማውጣት ይረዳል።

ቅዱስ እንጦንስን «የተመረጠው የቅድስና ሥራ የትኛው ነው?» ብለው ሲጠይቁት «መለየት ነው. . .» በማለት መልሷል። መለየት የሌለበት የቅድስና ሥራ ባለቤቶቹን ሊያጠፋቸው ይችላል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «ላይኛይቱ ጥበብ. . .» (ያዕ 3:17) እና «መንፈሳዊ ስጦታዎች . . .» (1ኛ ቆሮ 12) ተብለው የተጠቀሱ ቃላት አሉ። ከዚህ በተጨማሪ ጥበብ የሚጎድላቸው ሰዎች ሁሉ የብርሃን አባት ከሆነው ከእግዚአብሔር፣ ጥበብና መረዳት ከታደሉት ከታላላቅ አባቶችና ከመንፈሳውያን መምህራን ዘንድ ሊጠይቁ ይገባቸዋል።

አንድ ሰው ጥበብን ገንዘቡ ሊያደርጋት የሚችለው በልምድና ከራሱና ከሌሎች ስሕተት በመማር ነው። እርሱ ጥበብን ሊያገኛት የሚችለው ጠቃሚ ንባባትን በየዕለቱ ከማንበብ፣ ከጥበበኞች ጋር ከመተባበርና የአነጋገር ስልቶቻቸውንና ድርጊቶቻቸውን ከመማር ነው።

ንጉሥ ሰሎሞን እግዚአብሔርን የጠየቀው ሀብትና ሥልጣን አልነበረም፣ ሕዝቡን የሚያስተዳድርበትን ጥበብ እንጂ:: በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ከባረከው በኋላ ጥበቡን አድሎታል:: እርሱ ከተናገራቸው ቃላት መካከል «የጠቢብ ዐይኖች በራሱ ላይ ናቸው፣ሰነፍ ግን በጨለማ ይሄዳል፣. . .» (መክ 2:14) የሚሉት ይገኛሉ::

ጥበብ፡- ተመስጦና አስተሳሰብ ያስፈልጓታል:: እነዚህም ጉዳዩን ከሁሉም አቅጣጫ ለመመልከትና በሥራ ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ ሊያስከትላቸው የሚችሉትን ውጤቶች ለማጤን ይረዳሉ:: መደናገጥ ወይም ቁጣ ውስጥ ሆናችሁ ምንም ዓይነት እርምጃ አትውሰዱ::

ለጥበብ እውቀትና ሰፊ አዕምሮ ያስፈልጓታል::

ጥበብ ከመንቻካነት፣ ከትዕቢትና በአመለካከት ላይ ግትር ከመሆን ጋር አትስማማም::

(47)
ዘለዓለማዊነትህ

ብዙ ሰዎች የሚያስቡት በዚህ ምድር ስላለው ሕይወታቸው ብቻ ነው:: ምኞቶቻቸው ሁሉ በምድራዊው ሕይወት ላይ የተጠመዱ ናቸው:: ጥረታቸውና ድካማቸው ሁሉ ለዚህኛው ሕይወት ብቻ ነው:: ስለ ዘለዓለማዊነታቸው ግን እስከነ ጭራሹ እንኳ ላያስቡት ይችላሉ::

በምድር ላይ የምታሳልፈው ሙሉ የሕይወት ዘመንህ መጨረሻ ከሌለው ዘለዓለማዊነትህ ጋር ስታነጻጽረው የዓይን ጥቅሻ ያህል ነው::

በምድር ላይ ያለ ሕይወትህ እንዲህ ላለው ዘላለማዊነት ይኸውም ሕያው ለሆነ ሕይወት የሚደረግ ዝግጅት ነው::

ከዓለማዊው ክብር ጋር መጣበቅህ ቅዱሳን ማብቂያ በሌለው ክብር ውስጥ የሚቀበሉትን ክብር ሁሉ እንድታጣ ያደርግሃል::

ያም ሆነ ይህ ግን አንተ ምንም ጉዳይ እንደማይሰጠው ሰው ገና ራስህን ከዓለማዊው ክብር አልነጠልህም!!

ራስህን ጊዜያዊ ወይም ኃላፊ በሆኑ ዓለማዊ ደስታዎች መጥመድህ ዘለዓለማዊ ደስታህን ሊያሳጣህ ይችላል::

ስለሆነም በዘለዓለማዊት ጥቅም ላይ ማመን አለብህ:: ዘላለማዊነትን ዘወትር በዐይኖችህ ፊት ልታስቀምጥ ይገባሃል:: ማንኛውም ነገር ከዘለዓለማዊነት ጋር ሲነጻጸር ዋጋው በጣም ኢምንት ነው::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን አስመልክቶ ለቆሮንቶስ ሰዎች የላከው መልእክት ምንኛ ድንቅ ነው:- «የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና፣ የሚታየው የጊዜው ነውና የማይታየው ግን የዘላለም ነውና::» 2ኛ ቆሮ 4:18::

በዚህ እይታ ውስጥ ጠቢብ በሆነውና በጭፍኑ ሰው መካከል ያለው ልዩነት ግልጽ መሆኑ እውነት ነው::

ጭፍን የሆነው ሰው እይታ ቅርብ ነው፣እይታው ከሚታዩት ነገሮች አልፎ አይሄድም:: ጠቢቡ ሰው ግን አርቆ ይመለከታል፣ ከሞት በኋላ ያለውን

ስለሚመለከትም እንዲህ እያለ ያሰላስላል:- ከዚህ ሥጋዬ ስላቀቅ ምን ይገጥመኛል? ወዴት እሄዳለሁ? ምንስ እሆናለሁ?

አንተስ ወንድሜ? ምን በማድረግ ነው ባተሌ የሆንከው?

ልብህን ያኖርሃትስ በየት ነው? በወዲህ ወይስ በወዲያ? ሀብትህ ባለበት ልብህ በዚያ ይኖራልና::

ጠቢብ ሰዎች በዚህ ምድር ላይ እንግዶች መሆናቸው ስለሚታወቃቸው ተስፋቸውን በዚህ ምድር ላይ አያደርጉም:: እነርሱ የሚጠብቁት «እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ. . .» (ዕብ 11:10) ነው:: ለዘለዓለማዊነቱ ዋጋ የሚሰጥ ሰው ከምድርና ከምድራዊ ነገሮች በላይ ከፍ ከፍ ይላል:: በዚህ ዓለም ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ዓይነት ነገር አይማርከውም::

ለዚህ ሰው መላው ዓለም ከእርሱ በስተጀርባ ነው እንጂ ከእርሱ ፊት ለፊት አይደለም::

(48)
ሦስቱ የቅድስና ሥራዎች

ሦስቱ የቅድስና ወይም የጽድቅ ሥራዎች ባላቸው የሞራል መልካምነት እውነተኛ የጽድቅ ሥራዎች ናቸው:: እነርሱም:- ፍቅር፣ ትሕትና እና ጥበብ ናቸው::

ከፍቅር የተራቆተ ማንኛውም ዋጋ ያለው ነገር ሁሉ የቅድስና ሥራ ተብሎ ሊጠራ አይችልም:: ለትሕትና እና ለጥበብም ይኸው ሊባል ይችላል::

ከፍቅር የራቀ ማንኛውም ድርጊት ከእግዚአብሔር የራቀ ነው::

እግዚአብሔር አምላክ ከእያንዳንዱ የቅድስና ሥራ የሚወስደው በውስጡ ያለውን የፍቅር መጠን ነው:: በውስጡ ምንም ፍቅር ካላገኘ ግን ሙሉ ለሙሉ ይጥለዋል::

ትሕትና የሌለበት የቅድስና ሥራም በእግዚአብሔር ዘንድ የተጣለ ስለሚሆን ለፋስ ጽድቅና ለከንቱ ውዳሴ ቀለብ ሆኖ ይቀራል:: ትዕቢት በእግዚአብሔር ዘንድ እጅግ የተጠላ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል:- «እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና፣ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል::» 1ኛ ጴጥ 5:5::

ስለሆነም እያንዳንዱ የቅድስና ሥራ በጥበብ፣ በመረዳትና በመለየት ሊተገበር ይገባዋል:: ያለ ጥበብና ያለ መረዳት የቅድስና ሥራ ከጽድቅ ሥራ አይቆጠርም::

በዚህ ምክንያት ቅዱሳን የቅድስና ሥራዎቻቸውን የሚያከናውኑት ጠቢብና አዋቂ ከሆኑት አባቶች ቁጥጥር በታች በመሆን ነው:: ይህን የሚያደርጉትም እንዴት ጥንቁቅ መሆን እንዳለባቸው እንዲያስተምሯቸውና የጽድቅ ሥራዎች እንዴት መከወን እንደሚገባቸው እንዲገልጹላቸው ነው::

እውቀት አልባ የቅድስና ሥራ የፈጸሙ ሰዎች እንዴት እንደ ወደቁና እንደ ጠፉ ታሪክ ይነግረናል::

ብዙዎች ያለ ጥበብ ስለሚጾሙ በሰውነታቸውም ሆነ በመንፈሳዊነታቸው ታክተዋል:: ብዙዎች ዝምታን ያለ ጥበብ ሊተገብሩ ስለ ሞከሩ በብዙ ችግሮችና

ስሕተቶች ውስጥ ወድቀዋል። ዝምታ ለእነርሱ የቅድስና ወይም የጽድቅ ሥራ አይደለም።

ሌሎች ደግሞ ያለ እውቀት መባ ያቀርባሉ። እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ገንዘብ ለተቸገሩት ከመስጠት ይልቅ ለአታላዮች የሚሰጡ ናቸው።

ስለሆነም መለየት ሁሉንም የጽድቅ ሥራዎች ስለሚቆጣጠርና ስለሚገነዘብ ቅዱስ እንጦንስ ታላቁ የጽድቅ ሥራ ነው ብሎታል።

የክህነት ጥበቃና አገልግሎት ያለ መለየት ከሆነ ጉዳዮችን ከማስከን ይልቅ ውስብስብ ያደርጋቸዋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሐዋርያት አባቶቻችን ዲያቆናት «. . .መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸው. . .» (ሐዋ 6:3) እንዲሆኑ ወስነዋል።

ጥበብ ለጽድቅ ሥራ ጥልቀትንና እውነተኛነትን ያድላል።

ፍቅር ደግሞ ለቅድስና ሥራ ስሜትና መልካም መንፈስን ያድላል።

ትሕትና ደግሞ የጽድቅ ሥራን ከዲያብሎስ ቅናት ይሸሽጋል። በዚህም ባለቤቱን በሰዎች ልብ ውስጥ ጥልቅ ፍቅርና ትሕትና እንዲኖረው ያድለዋል።

በውስጣችን በጥልቀት ያሉት የቅድስና ሥራዎች ናቸው? ራሳችንን እንመርምር።

(49)
ልባም ፍቅርና ሰነፍ ፍቅር

ጥቂት ሕመም ቢያስከትልም ባለቤቱ የሚጠቀምበት ልባም ፍቅር አለ፤ ይህ ቢሆንም ለነፍሱና ለዘለዓለማዊነቱ ጠቃሚ ነው።

ቸርነትና ትሕትና ሊያሳይ ቢችልም ባለቤቱን የሚያጠፋ ሰነፍ ፍቅርም አለ።

አንድን ሰው ልትወደው ትችላለህ። ከዚህ በኋላ ትክክል በሆነ ወይም በተሳሳተ በማንኛውም መንገድ ላይ ትረዳዋለህ። ምናልባትም የተሳሳቱ ሥራዎቹን በማበረታታት የእርሱንም የአንተንም ታጠፋለህ። ፍቅርህ የተሳሳተ ፍቅር ይሆናል ማለት ነው።

ወይም ደግሞ አንድን ሰው ልትወደው ትችላለህ። ከዚህ በኋላ ስለ ሰውነቱ ድካም፣ ስለ ትግሉና ስለ ምናኔው ስትል ታዝንለታለህ። ይህን በማድረግህም እርሱን በመጉዳት ነፍሱን፣ አእምሮውንና መጻኢ ጊዜውን የምታጠፋ ትሆናለህ። ይህ ሰነፍ ፍቅር ነው።

ልጇን የምታፈቅር እናት ታሞላቅቀዋለች፤ታበላሸውማለች . . . ወይም ደግሞ ካደገ በኋላም ስለምታፈቅረው ከአጠገቧ እንዳይርቅ ትመኛለች። ከዚህ በተጨማሪ ለበጎ አድራጎት፣ ለምንኩስና ወይም ለቅስና ራሱን አሳልፎ እንዳይሰጥ ትገድበዋለች። ፍቅሯ በስስት የተሞላና ጎጂ ፍቅር ነው።

አንድ የታመመ ዘመዱን የሚያፈቅር ሰው የሕመሙን ክብደት ከእርሱ በመደበቅ ለዘላለም ሕይወት እንዳይዘጋጅ ዕድሉን ፈጽሞ አይሰጠውም። እንዲህ ያለው ፍቅር መንፈሳዊ ያልሆነና ጥበብ የጎደለው ፍቅር ነው።

እውነተኛ ፍቅር ልባምና መንፈሳዊ ሲሆን ዓላማውም ለነፍሳት ድኅነት ነው። ይህ ፍቅር ትሑት ስለ መሆን ሲል ብቻ እውነትን አሳልፎ አይሰጥም። የሌሎች ሰዎች ጥፋት ተባባሪም አይሆንም። እንደ እግዚአብሔር ፍቅር ንጹሕና እውነተኛ ነው።

(50)
ምቹ ጊዜ

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ «. . .ከሰማይ በታችም ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው።» መክ 3:1። መንፈሳዊው ሥራ በትክክለኛው ጊዜ መከናወን አለበት።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋን ሲለብስ «የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ . . .» (ገላ 4:4) ተብሏል። ይህ ጊዜ ትንቢት የተፈጸመበት፣ ዓለም ቃለ ክርስቶስን ለመቀበል የተዘጋጀችበትና የድኅነት ሥራ የታወቀበት እጅግ ምቹ ጊዜ ነበር።

ይህ ደግሞ በሥራ ላይ ስንሆን፣ ስንነጋገር፣ ዝም ስንል፣ ስናገለግልና ማንኛውንም ነገር ስናከናውን ምቹውን ጊዜ ከግምት ማስገባት እንዳለብን ትምህርት ሰጥቶናል። ይህ ደግሞ ተክሎች በተወሰነ ወቅት፣ በአመቺ የአየር ንብረት፣ በትክክለኛ ሙቀትና አየር ካልሆነ እንደማይበቅሉት ያለ ነገር ነው።

መነጋገርን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ «. . . ዝም ለማለት ጊዜ አለው፤ለመናገርም ጊዜ አለው. . .» መክ 3:7። እንዲህም ተብሎ ተጽፎአል፦ «የወርቅ እንኮይ በብር ፃሕል ላይ፤ የጊዜው ቃል እንዲሁ ነው።» ምሳ 25:11። ጠቢብ ሰው ዝም ማለት በሚገባው ጊዜ አይናገርም፤መናገርም በሚገባው ጊዜም ዝም አይልም።

አንድን ሰው ስትገሥጽ ምቹውን ጊዜ መምረጥ አለብህ። ይህ ካልሆነ ውጤቱ አንተ የጠበቅኸው ተቃራኒ ነው የሚሆነው። ሌሎች ሰዎች አንተ ስትናገር ለማድመጥና ለመቀበል ዝግጁ የሚሆኑበትን ምቹ ጊዜ ጠብቅ።

ማንኛውም ሰው በሥራ ሲጠመድ፣ ሲደክም ወይም ሲበሳጭ ጥያቄ አትጠይቀው፤ይህ ምቹ ጊዜ አይደለምና።

ለሁሉም ነገር ጊዜ ካለው ማንኛውም ጊዜ ምቹ ነው፤በተለይ ደግሞ ለንስሓ።

የንስሓ ጊዜ ሲደርስ ንስሓ እገባለሁ አትበል! ምቹውን ዕድል ሳገኝ ንስሓ እገባለሁ በል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል፦ «. . . እነሆ የተወደደው ሰዓት አሁን ነው፤እነሆ የመዳን ቀን አሁን ነው።» 2ኛ ቆሮ 6:2።

ያም ሆነ ይህ ይበልጥ አመቺና ይበልጥ ውጤታማ ብለን የምንይዛቸው ጊዜያት አሉ። «ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ. . .» ዕብ 4:7።

ጥቂት ሰዎች አጋጣሚውን ይጠቀማሉ። ጸጋ እግዚአብሔር በውስጣቸው የሚሠራበት ጊዜ ከእጃቸው እንዳያመልጥ አይፈቅዱም።

በሰሙት አንድ ቃል ከተነኩ ያ ጊዜ ለእነርሱ ምቹው ጊዜ ነው። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን በአንድ ቃል ወይም በአንድ የተለየ አጋጣሚ ይኸውም በአባቱ ሞት ምክንያት ሕይወቱ የተለወጠው ቅዱስ እንጦንስ ነው። እርሱ ይህን ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ ነው የተጠቀመበት። ይህ ደግሞ ዓለማዊ ደስታን እንዲረሳ አድርጎታል።

(51)
በምድረ በዳውና በፀጥታው ውስጥ

አንድ ሰው በብዙ ጭንቀትና ግርግር ከተሞላው ሕይወት ገለል ብሎ በተመስጦ፣ በጸሎትና ልቡን ለእግዚአብሔር በመክፈት ከእርሱ ጋር ለጥቂት ጊዜያት መቀመጥ መቻሉ ምንኛ ድንቅ ነገር ነው!

እንዲህ ባለው ሁኔታ ውስጥ ሰው የሚመርጠው እርጋታና ጸጥታን ነው።

ከእግዚአብሔር ጋር ስንነጋገር እኛና እርሱ ብቻ መሆናችን ተገቢ ጉዳይ ነው።

ይህ በመሆኑም እግዚአብሔር አብርሃምን ከሀገሩና ከወገኖቹ ለይቶ የወሰደው ከእርሱ ጋር ብቻ ወደሚሆንበት ወደ አንድ ተራራ ነበር።

በዚያ ተራራ ላይ አብርሃም ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠርቷል . . .

ሙሴ በተቀደሰው ተራራ ላይ በገለልተኝነት ለአርባ ቀናትና ለአርባ ሌሊት ከእግዚአብሔር ጋር ከቆየ በኋላ ነው ሕጉን፣ ትእዛዛቱንና ታቦቱን የሚያዘጋጅበትን መመሪያ ከእርሱ የተቀበለው።

ከዚህ በተጨማሪ ኢየሱስ ክርስቶስ አንዳንድ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ገለል ወዳለ ተራራ ብቻቸውን ይወስዳቸው ነበር።

ነቢዩ ኤልሳዕ የቀርሜሎስን ተራራ ፀጥታ ተለማምዶት ነበር።

መጥምቁ ዮሐንስ ለሠላሳ ዓመታት የኖረው ወይም ያደገው በምድረ በዳ ውስጥ ነበር።

ነቢያትም እርጋታና ፀጥታን ተለማምደውት ነበር።

ሙሴ ነቢይ ከመሆኑና ለአመራር በእግዚአብሔር ከመመረጡ አስቀድሞ ለአርባ ዓመታት የቆየው በፀጥታ ውስጥ ነበር። እርሱ በፖለቲካና በሁካታ ከተሞላው ከፈርዖን ቤተ መንግሥት ርቆ ነበር የተቀመጠው።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ ዘንድ ጥልቅ ሰላምና ዘላለማዊ ግኑኝነት ከአባቱ ጋር ቢኖረውም አገልግሎቱን በይፋ ከመጀመሩ በፊት በተራራ ላይ ለአርባ ቀናት ከአባቱ ጋር በመቆየት ለእኛ ከአባታችን ጋር የምንቆይበትን ምሳሌ በግልጽ አሳይቶናል።

ተራራ በኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ውስጥ የተለየ ሥፍራ አለው። ይህን አስመልክቶ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተነገረው ቃል እጅግ ድንቅ ነው:- «እያንዳንዱም ወደ ቤቱ ሄደ። ኢየሱስ ግን ወደ ደብረ ዘይት ተራራ ሄደ።» ዮሐ 7:53እና8:1።

የጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ ኢየሱስ ክርስቶስ ጥልቅ ተመስጦ የሚያሳልፍባት የእርጋታና የፀጥታ ስፍራው ነበረች።

የማርታ እኅት ማርያም በኢየሱስ ክርስቶስ እግር ሥር ትቀመጥ ስለ ነበር የፀጥታ ሕይወት ምሳሌ ሆናለች። ከፀጥታ ሕይወት ርቃ ራሷን በጭንቀት ባተሌ አድርጋ የነበረችው እኅቷ ማርታን ጌታ የገሠጸት እንዲህ ብሎ ነበር:- «. . . ማርታ

ማርታ:- በብዙ ነገር ትጨነቂአለሽ ትታወኪማለሽ፤ የሚያስፈልገው ግን ጥቂት ወይም አንድ ነገር ነው. . .» ሉቃ 10:41-42።

ይህ ከሆነ በሕይወታችሁ ውስጥ ያለውን የፀጥታ ማዕከል ፈልጋችሁ ታገኙታላችሁን?

በብዙ ነገሮች እየተጨነቃችሁም እየታወካችሁም ነው። ለመሆኑ መቼ ነው የምትረጋጉት? ኧረ መቼ?

(52)
አግባብነት የሌለው ጥላቻ

የእግዚአብሔር ልጅና መንፈሳዊ ተግባራትህን የምታከናውን የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ብትሆንም አግባብነት ከሌለው ጥላቻና ከውጤቱ በታች ልትሆን ትችላለህ።

አግባብ የሌለው ጥላቻ ማለት አንድን ሰው ያለ ምንም ዕውቀት፣ ያለ ምንም አሳብ፣ ምናልባትም ያለ ምንም ምክንያት ማጥቃት ማለት ነው።

ከዚህ በተጨማሪ አግባብነት የሌለው ጥላቻ ማለት አንዱን ሰው ያለ ምንም ዕውቀት፣ አሳብና ምክንያት በጠሉበት ተመሳሳይ ጊዜ ሌላውን ሰው ያለ ምንም ዕውቀት፣ ያለ ምንም አሳብና ያለ ምንም ምክንያት መደገፍና ስለ እርሱ መከላከል ማለት ነው።

የቆሮንቶስ ሰዎች አግባብ የሌለው ጥላቻ በጳውሎስና በአጵሎስ ላይ አሳድረው ስለ ነበር ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ወቅሷቸዋል ገሥጸአቸዋልም:- «. . . አንዱ:- እኔ የጳውሎስ ነኝ፤ ሁለተኛውም:- እኔ የአጵሎስ ነኝ ቢል ሰዎች ብቻ መሆናችሁ አይደለምን?» 1ኛ ቆሮ 3:4።

አግባብነት የሌለው ጥላቻ ከመንፈስ ፍቅር ጋር አይስማማም . . .

የምትተቸውን፣ የምትቃወመውንና የምታጠቃውን ሰው በምንም ዓይነት መንገድ ልትወደው አትችልም። «ፍቅር አያስታብይም. . . ክፉ ነገርን አያሳስብም. . .» 1ኛ ቆሮ 13:5።

አግባብነት የሌለው ጥላቻ ከእውነትና ከፍትሕ ጋር አይስማማም. . .

ብዙ ጊዜ አግባብነት በሌለው ጥላቻ ዙሪያ የሚወድቁ ጥቃቶች እውነተኛና ትክክለኛ አይደሉም። እነዚህ ጥቃቶች ከልብ ውስጥ የሚወጡ ጥላቻዎች ስለሆኑ ቢያንስ-ቢያንስ የተጋነኑና የተጨማመሩ ነው የሚሆኑት።

አግባብነት የሌለው ጥላቻ ያፈርሳል እንጂ አይገነባም. . .

አግባብነት የሌለው ጥላቻ ብርታትን ያዳክማል አንድነትንም ይለያያል። ኃይልን የሚጠቀመው በተገቢው መንገድ አይደለም። ኃይሉን የሚያባክነው በጭቅጭቅ፣ በመለያየት፣ በትችትና በቅራኔ ነው።

አግባብነት የሌለው ጥላቻ የመንፈስና የአሳብ ኅብረት ተቃዋሚ ነው . . .

በመሆኑም ለሌሎች ራሱን ስለሚያሳይ «ያመኑትም ሕዝብ አንድ ልብ አንዲትም ነፍስ ነበሩአቸው. . .» (ሐዋ 4:32) ተብሎ ከተነገረላቸው ከቤተ ክርስቲያን ልጆች ጋር ኅብረት የለውም።

አግባብነት የሌለው ጥላቻ «በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤አንድ ጌታ፣ አንድ ሃይማኖት፣ አንድ ጥምቀት . . . አለ።» (ኤፌ 4:4-5) በማለት ሐዋርያት የተናገሩት ትእዛዝ ተቃዋሚ ነው።

አግባብነት የሌለው ጥላቻ የፉክክርን መንፈስ ወይም ቅራኔን ወይም ሰዎችን መቃወምን ወይም በራስ የሚያኮራ መንፈስን ያበረታታል።

«ጀግኖችን የማምለክ» ወይም የማኅበረሰቡ ቁንጮ የመሆን አመለካከትን ይቀበላል።

ይህ በሚሆንበት ጊዜ በአንተ እይታ ውስጥ የሚቀረው የእኛ ቡድን፣ የእኛ ማኅረሰብ፣ የእኛ ቅርንጫፍ፣ የእኛ ቤተ ክርስቲያን (በወረዳ ደረጃ)፣ የእኛ ሀገር፣ የእኛ መንደር . . . የሚለው ብቻ ይሆናል።

(53)
መለያየት

ከቅዱሳን አንዱ እንዲህ በማለት ተናግሯል:- «አሥር ሺህ መላእክት አንድ ላይ ቢሰበሰቡ የሚኖራቸው አመለካከት አንድ ዓይነት ነው፤ጥቂት ሰዎች አንድ ላይ ቢሰበሰቡ ግን ሊስማሙ አይችሉም ወይም ይለያያሉ።»

መለያየት እኔነት በሰው ውስጥ መኖሩን አመልካች ፍንጭ ነው . . .

ከእግዚአብሔር በመራቅ በራሱ የሚንቀሳቀስ እኔነት የሚከተሉት ጠባያት ይኖሩታል:-

❖ ውጤቱ ምንም ይሁን ምን የራሱን አመለካከት በሌሎች ላይ በተጽዕኖ ለማሳደር ማነጣጠር ነው።

❖ በመለያየት አማካይነት ለሚመጡት አደገኛ ውጠቶች ምንም ጉዳይ አይሰጠውም።

እነዚህ ውጤቶች ምንድር ናቸው? በአንድ ወቅት አንድ የሥነ ጽሑፍ ባለ ሙያ እንዲህ በማለት ተናግሯል:- «ሁለት ንሥር አሞሮች፣በበድን ላይ ቢጣሉም በድኑን የወሰደችው ቀበሮ ናት።»

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል:- «እርስ በእርስዋ የምትለያይ መንግሥት ሁላ ትጠፋለች፤ እርስ በእርሱ የሚለያይ ከተማም ሁሉ ወይም ቤት አይቆምም።» ማቴ 12:25። የሚለያዩ ሰዎች ግን ይህን የጌታ ቃል ሁልጊዜ ይዘነጉታል።

ብዙ ጊዜ አንድ ቡድን የመለያየት እርምጃ ወስዶ አካባቢውን ያናውጥና ምንም ዓይነት ነገር እንዳልፈጸመ ሆኖ ይቀመጣል። እግዚአብሔር ግን በእርሱ አማካይነት ለደረሰው ጥፋት ደሙን ከቡድኑ ይቀበላል።

በወንድሞች መካከል ያለ መለያየት የፍቅር እጦት ምልክት ነው . . .

ወጣቶች ከሽማግሌዎች ጋር ተለያዩ ማለት ዓመፅ፣ የመታዘዝ እጦትና የማክበር እጦት ደረሰ ማለት ነው። እነዚህ ሁሉ ኃጢአቶች ናቸው።

መለያየት በሰው ውስጥ ኩራት ወይም ራስን ባለ ዋጋ ማድረግ መኖሩን ያረጋግጣል። በዚህ ጊዜ ነፍስ አባትን የሚያማክረው ስለማይኖር ድርሻው ከዚህ ጉዳይ ውጭ ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ስለ መለያየታቸውና ሥጋውያን ስለ መሆናቸው ገሥጾአቸዋል። 1ኛ ቆሮ 2። ይህም የሚያስረዳን የሚለያዩ ሰዎች ከመንፈስ ቅዱስ ኅብረት የራቁ መሆናቸውን ነው።

የሰውነታችን ብልቶች ለዚህ ሰውነት መልካም መሆን ተባብረው ይሠራሉ። ይህ ኅብረት ለሁሉም ከታወቃቸው ግን ሁሉም ሰዎች ወደ እነርሱ መልካምነት እንዲመለከት በጋራ ይሠራሉ።

ኅብረት የሌሎች ሰዎችን አመለካከት ያከብራል ወይም ሌላው ሰው እንዲህ ያለውን ነገር ያለ ምንም ዓመፅ፣ ቁጣና ሌሎችን የማዋረድ ወይም የማጥፋት ተግባር እንዲፈጽም ያለማምዳል።

በመለያየት መንገድ ውስጥ ላለ ለማንኛውም ሰው የተሰጠ ጠቃሚ ምክር:-

❖ ከሌሎች ሰዎች ጋር ከመለያየት ይልቅ እነርሱን ለማግኘት ሞክር።

❖ ዓላማ ያለህ ሰው በመሆን ከግል ጉዳዮች ራስህን አርቅ።

❖ ከጋራ መንፈስ ጋር ለመተባበር ራስህን አስለምድ።

(54)
መጠቀም የሚፈልግ ሰው

ለመጠቀም የሚፈልግ ሰው ምንጊዜም ቢሆን የሚሻው አትራፊነትን ነው። ብዙ ወሬ አያተርፈውም፤አንዲት ቃል ግን መላ ሕይወቱን ትለውጣለች። እርሱ እንደ ቅዱስ ፓፕኖቲ ከዝምታ ይጠቀማል። ይህ ቅዱስ ፓፕኖቲ በአንድ ወቅት ከእንግዶቹ ለአንዱ «ከዝምታዬ ካልተጠቀመ ከንግግሬም ሊጠቀም አይችልም።» ብሎት ነበር።

ቅዱስ እንጦንስ የሰማው አንድ ቃል ለምንኩስና ሕይወቱና ለመላእክታዊ ቅዳሴው መሠረት ሆኖታል። ሌላ የሰማው ቃል ደግሞ ወደ በረሃው ማዕከል እንዲገባና የብሕትውና ሕይወቱን እንዲጀምር አድርጎታል።

እግዚአብሔር በብዙ ቃላት ሊያስተምራችሁ አጥብቆ አልጠየቃችሁም፤ በአንድ ዓረፍተ ነገር በብቃት አስተምሯልና። አሥርቱ ቃላት አጫጭር ዓረፍተ ነገሮች ናቸው፤ይሁኑ እንጂ ሁሉንም ትምህርት ያጠቃለሉ ናቸው።

የጌታ ጸሎት በአጫጭር ዓረፍተ ነገሮች የተዋቀረ ቢሆንም ልመናን በጥልቀት ያቀፈ ነው።

ለመጠቀም የሚፈልግ ሰው በማንኛውም ዋጋ ቢሆን ትርፉን ይሻል።

ከመንፈስ የተወለደ ሰው ከአባቶች ቃል ለመጠቀም ሲል እነርሱን ያገኝ ዘንድ በጽናት ረዥም መንገድ ይጓዛል። አባቶችም ከማንም መጠቀም ይፈልጋሉ፤ከሕፃናትም እንኳ።

መልካም ነገርን ለማግኘት የሚጠይቅ ሁሉ ያገኛል . . .

ለእርሱ ወይም ለሌሎች ሰዎች ከማንኛውም ሰው በአጋጣሚ ወይም በድንገት ከተወረወረ ተባራሪ ቃል እንኳ ተጠቃሚ ይሆናል። ከራሱና ከሌሎች ሰዎች ስሕተቶችም አትራፊ ነው።

በአንድ ወቅት አንድ ቅዱስ ሰው «ዲያብሎስ እኔን በአንድ ተመሳሳይ ኃጢአት ሁለት ጊዜ የፈተነበትን ጊዜ አላስታውስም።» ብሏል። ይህ ቅዱስ አባት ይህን ቃል የተናገረው ከመጀመሪያው ውድቀቱ ስለተጠቀመና ለሁለተኛው ፈተናው ስለተጠነቀቀ ነው።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እምነትና ስለ እግዚአብሔር ጥበቃ እንድንማር የጠየቀን ከምድር አበቦችና ከሰማይ ወፎች ነው።

የማትረፊያ ምንጮች በብዛት አሉ። የምናገኛቸው ከሰባኪው ቃላት ወይም ከመንፈሳዊ መጻሕፍት ብቻ አይደለም፤በማንኛውም ቦታና በማንኛውም ጊዜ እናገኛቸዋለንና። ዋናው ነጥብ ግን ታተርፋለህ ወይስ አታተርፍም የሚለው ነው።

የእግዚአብሔር ድምፅ ለእያንዳንዱ ሰው በተለያየ መንገድ ስለሚደርስ «የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ።» ማቴ 11:15።

(55)
ጥበቅ ሥራ

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ «የእግዚአብሔርን ሥራ በቸልታ የሚያደርግ ርጉም ይሁን፤ . . .» ኤር 48:10።

«እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን፤የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ።» (ራእ 2:10) የሚል ቃል ስላለ ለእግዚአብሔር የሚሠራ ሰው እስከ ሞት ድረስ የታመነ መሆን አለበት። ታማኝነት ለአገልግሎት ዓይነተኛው መንገድ ነው።

በዚህ ጥብቅ ሥራ ውስጥ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በክርስቶስ ስም ይሠራው ስለነበረው ሥራ ምስክርነት ሲሰጡለት እንዲህ ብለዋል፦ «. . . ማንም ሳይከለክለው የእግዚአብሔርን መንግሥት እየሰበከ ስለ ጌታ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ ገልጦ ያስተምር ነበር።» ሐዋ 28:31። ስለ ሌሎቹ ሐዋርያትም እንዲህ የሚል ቃል ተጽፎአል፦ «ሐዋርያትም የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በታላቅ ኃይል ይመሰክሩ ነበር፤በሁሉም ላይ ታላቅ ጸጋ ነበረባቸው።» ሐዋ 4:33።

ከዚህ ጥብቅ፣ እውነተኛና ታማኝ ሥራ የተነሣ ነው የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ የተስፋፋው። እግዚአብሔር ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን አለቃ የተናገረውን ቃል አድምጡ፦ «. . . ሥራህን፣ ድካምህንና ትዕግሥትህን አውቃለሁ፤ . . . ታግሠህማል፤ስለ ስሜም ብለህ ጸንተህ አልደከምህም።» ራእ 2:2-3።

ጥብቅ ሥራ የሚገነባው በእምነት ላይ ነው. . .

የእምነትህ ክብደትና የሥራህ ጥቅም ይበልጥ እውነትና ሙሉ እየሆነ መጣ ማለት ሥራህ ይበልጥ ጥብቅ እየሆነ መጣ ማለት ነው። በሥራ ላይ የሚታይ ቸልተኝነት የእምነትና የጥቅሙን ጉድለት ጠቋሚ ነው።

ጥብቅ ሥራ የኃላፊነትን ስሜት አመልካች ነው. . .

ጻድቁ ዮሴፍ ለሰዎች ስንዴ እንዲሰፈርላቸው ባደረገ ጊዜ የብዙዎች ሕይወት ሙሉ ለሙሉ በእርሱ ታማኝነት ውስጥ እንዳለ ጠንቅቆ ያውቅ ነበር።

መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲሁ ነው። የብዙዎች ሕይወት የተመሠረተው በአገልጋዩ ታማኝነት ላይ ነው። እርሱ አገልግሎቱን ከዘነጋ የሚያገለግላቸው ሰዎች ይጠፋሉ።

ጥብቅ ሥራን የሚቆጣጠረው በሰውየው ውስጥ ያለው እርሱነቱ ነው። ይህን ሥራውን የሚቆጣጠረው በውስጡ ያለው ኅሊናውና የእግዚአብሔር ድምፅ ነው። ይህ ቁጥጥር የሚመነጨውም በውስጡ ካለው ስሜቱና ከመንፈሳዊ ቅንዓቱ ነው።

ጊዜ አጭር ስለ ሆነና እያንዳንዷ ደቂቃ እየቆጠረች ስለሆነ ማንኛውም መዘግየት ወይም ቸልተኝነት የራሱ የሆነ አደጋ ይኖረዋል።

ጥብቅ ሥራ ምንጊዜም ቢሆን ስኬታማ ነው. . .

ጥብቅነት ሥራን ፍጹም ስለሚያደርግ እንዲህ ዓይነቱ ሥራ ፍጹም ነው። ፍጹም ሥራ ደግሞ ስኬታማ ነው። ይህን አስመልክቶ ስለ ጻድቅ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈው «. . . የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል።» (መዝ 1:3) ተብሎ ነው።

ጥብቅ ሥራ ተከናውኖ እስኪጠናቀቅ ድረስ ዝግመት አይታይበትም። በመሰላቸት ስለማያምንም ዕረፍትን አይሻም።

እንዲህ ያለውን ሥራ የሚከውነው ሰው ሥራው እስኪያበቃና ፍሬውን እስኪቀምስ ድረስ አያርፍም። የአብርሃም ሎሌ የጌታው ሚስት የሆነችውን ርብቃን እስኪያገኝ ድረስ አላረፈም ነበር። እርሱን እንዲያርፍ በጠየቁት ጊዜ «. . . አታዘግዩኝ. . .» (ዘፍ 24:56) ነበር ያላቸው።

(56)
እኔ ብቻ

በአንድ ወቅት ነቢዩ ኤልያስ እርሱ ብቻ እግዚአብሔርን የሚያመልክ ስለ መሰለው «. . . እኔም ብቻዬን ቀርቼያለሁ. . .» (1ኛ ነገ 19:10) በማለት ተናግሮ ነበር። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር አምላክ ጉልበታቸውን ለበኣል ያላንበረከኩ ሰባት ሺህ ሰዎች እንዳሉት ነግሮታል።

እግዚአብሔርን የምናመልከውና መመሪያዎቹ ሁሉ በእኛ ዘንድ ብቻ እንዳሉ አድርገን ማሰብን የመሰለ አደገኛ አመለካከት የለም። ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔርን የሚያመልኩት ከሰባት ሺህ እጅግ የሚበዙ አማኞች መኖራቸውን እንዘነጋለን።

በመጥፋታቸውና በመበከላቸው በመላው ትውልድና በሁሉም ሰው ላይ የሚፈርዱ ሰዎች አሉ! እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር መመረጣቸውን ይዘነጋሉ። እነርሱ እነዚህን ሰዎች ባያውቋቸውም እግዚአብሔር ግን ያውቃቸዋል።

ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ሕግን የሚያውቁት እነርሱ ብቻ እንደ ሆኑ አድርገው ያስቡ ስለ ነበር ሕግን አጥብቀው ይከተሉ ነበር።

ይህን በማድረጋቸውም በትዕቢትና በልብ ደንዳናነት የተሞሉ ስለ ነበሩ ራሳቸውን ከሌሎች በላይ አድርገው ይቆጥሩ ነበር። እነርሱ ሌሎች ሰዎችን ኃጢአተኞች አድርገው ይመለከቱ ስለ ነበር ይፈርዱባቸው ነበር። እነርሱ ኢየሱስ ክርስቶስን እንኳ ሰንበትን የማያከብርና ሕግን የሚጥስ ብለው ወንጅለውታል። ሌላው ቢቀር ትሑት ሆኖ በቀራጮችና በኃጢአተኞች መካከል ስለ ተቀመጠ ከሰውታል።

ቅዱስ እንጦንስ በምድር ላይ ያለው መነኩሴ እርሱ ብቻ እንደ ሆነ አድርጎ በማሰብ ራሱን ሲያጸድቅ ሲጀምር እግዚአብሔር ከእርሱ የሚበልጠውን ቅዱስ ጳወሊን አሳይቶታል፡፡

ቅዱስ መቃርስም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ሲጠቃ እግዚአብሔር እስክንድርያ ውስጥ ባል አግብተው ወደሚኖሩና የእርሱን ቃል ከእርሱ ጋር እኩል በሆነ መንፈሳዊ ደረጃ ወደሚፈጽሙ ወደ ሁለት ሴቶች ልኮታል፡፡ የቀረው እርሱ ብቻ አይደለም፤እነዚህ ሴቶችም ጉልበታቸውን ለበኣል ካላንበረከኩት ሰባት ሺህ ሰዎች መካከል ነበሩ፡፡

እርሱ ብቻ ታማኝ አገልጋይ፣ እርሱ ብቻ ተሰጥዖ ያለው፣ እርሱ ብቻ መርሆና አሳብ ያለው ሌሎች ግን ምንም የሌላቸው አድርጎ የሚያስብ እንዲህ ያለው ኃጢአት ምንኛ ጎጂ ነው! እንዲህ ዓይነቱ ሰው ለአመራር ከእርሱ የሚበልጥ እንደሌለ አድርጎ የሚያስብ ነው!

ፍቅር ያለው ሰው ግን እርሱን የሚመስሉ ወይም ከእርሱ የሚበልጡ ሰዎች ቢኖሩ ደስ ይለዋል፡፡ ሙሴ ይህን አስመልክቶ ለነዌ ልጅ ለኢያሱ ሲናገር እንዲህ ነበር ያለው፡- «. . . የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ነቢያት ቢሆኑ እግዚአብሔርም በእነርሱ ላይ መንፈሱን ቢያወርድ አንተ ስለ እኔ ትቀናለህን?» ዘኁ 11:29፡፡ በራስ መታበይን በተመለከተ እንዲህ ያለው ጉዳይ ውስጡን አውኮታል፤ሌላው ሁሉ ቢቀር ጉዳዩ አላስደሰተውም፡፡ እርሱ የተጨነቀው ለእግዚአብሔር አይደለም፤ለራሱ እንጂ፡፡

(57)
ሕልም

ሀ/ አንዳንድ ሕልሞች ከእግዚአብሔር ናቸው፡፡

እንዲህ ዓይነቶቹ ሕልሞች ለአናጢው ለዮሴፍና ለሰብዓ ሰገል የታዩት ሕልሞች ናቸው፡፡ ጻድቁ ዮሴፍ በተመለከተው ሕልም ውስጥ ሕፃኑን ኢየሱስ ክርስቶስንና እናቱ ቅድስት ማርያምን ይዞ ወደ ግብጽ እንዲሸሽ ተነግሮታል፡፡ ሰብዓ ሰገልም ወደመጡበት ቦታ በሌላ መንገድ እንዲመለሱ የተነገራቸው በተመለከቱት ሕልም ነበር፡፡

ለ/ ከሰይጣን የሚመጡ ሕልሞች አሉ፡፡

እነዚህ ሕልሞች ሰዎችን በማታለል ከመንገዱ የሚያስወጡና ወደማይበጀው መንገድ የሚመሩ ወይም የሚያውኩት ሕልሞች ናቸው፡፡ «የበረሀ አባቶች ብሒል» በሚለው መጽሐፍ ውስጥ ስለ እነዚህ ሕልሞች የሚያወሳ ሰፊ ምዕራፍ ተካቷል፡፡

ሐ/ አንዳንድ ሕልሞች የውስጠ ኅሊና (subconscious) ውጤቶች ናቸው፡፡

የምታየው፣ የምትሰማው ወይም የምታነበው ነገር ከተለያዩ ምንጮች በስሜቶችህ ወይም በአሳቦችህ ይሰባሰባሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ በውስጠ ሕሊና ውስጥ ይከማቻሉ፡፡ እነዚህ ክምችቶች ከዓመታት በኋላ በአሳብ ወይም በጥርጥር ወይም በሕልም ሊገለጡ ይችላሉ፡፡

ይህ የተፈጥሮ የስሜት መልስ ነው. . .

በውስጠ ኅሊና ውስጥ የተከማቹት ክምችቶች በተለያዩ መንገዶች ሊገለጡ ይችላሉ፡፡ ስሞች፣ ጊዜያት ወይም ቦታዎች ሊለያዩ ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ ልክ እንደ

መቅረፀ ድምፅ (tape recorder) በውስጣችሁ በጥልቀት ያለውን ነገር ነው የሚገልጡላችሁ፡፡

መ/ ሕልሞች የአካላዊ አቅጣጫ ነጸብራቅ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

አንድ የደከመው ወይም የዛለ ሰው ወደ መኝታው ሄዶ ሲያንቀላፋ የሚቀሰቅሰው ሰዓት ቢጮህ እርሱ ለመቀስቀስ ስለማይፈልግ ከሚቀሰቅሰው ሰዓት አጠገብ ተቀምጦ ሊያልም ይችላል፡፡

ጠቢብ ሰው ሕልሞች እንዲመሩት አይፈቅድም፡፡

እንዲህ ዓይነቱ ሰው እያንዳንዱን ሕልም አያምንም፡፡ ሕልሞች ሁሉ ከእግዚአብሔር ናቸው ብሎም አይቀበልም፤ የተሳሳቱ ሕልሞች ሆነው ሲያታልሉት ይችላሉና፡፡

ክፉ ወይም መጥፎ ሕልሞች ለተለያዩ ምክንያቶች ሊገለጡ ይችላሉ . . .

አንዳንዶቹ ሕልሞች አካላዊ ወይም ስነ ልቦናዊ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ከዲያብሎስ የሚቃጡ ጥቃቶች ናቸው፡፡ አንድ ሰው ከእንቅልፉ ከነቃ በኋላ ስለ እነዚህ ሕልሞች ሊያስብ አይገባውም፤ አሳቦቹ ማረጋገጫ ሆነው ሲገለጡ ሌሎችን ምክንያት ሊያደርጉ ይችላሉና፡፡

(58)
የራስ አሳቦች

ብዙ ሰዎች የራሳቸውን አሳቦች የማሳተም፣ ለሌሎች እንደ መንፈሳዊ መመሪያ አድርገው የማቅረብና እንደ ጠቃሚ እምነት ሊከተሏቸው የሚገቡ የማድረግ ፍላጎት አላቸው፡፡

እነዚህ አሳቦች ይበልጥ አዲስና የማይታወቁ እየሆኑ ሲመጡ ይበልጥ አዲስ ሆነው ስለሚቀርቡ በሌሎች ሰዎች ዐይን ፊት የሚያስደስቱና አዋቂ የሚያስብሉ ይሆናሉ፡፡

ይህ አዲስ እውቀት ሰዎች ከሚያውቁትና ከሚያምኑት ይበልጥ የተለየ ስለሚሆን እነዚህ አሳቢዎች ይበልጥ ደስተኞች ይሆናሉ፡፡ ይህ ለእነርሱ የተሳሳተውን አጠቃላይ አሳብ በማስወገድ በምትኩ አዲስና ትክክለኛውን በቦታው ላይ እንደ ማስቀመጥ ነው፡፡

ይህ የአሠራር ዘዴ በማንኛውም ዓይነት እውቀት ውስጥ ሊሠራ ይችላል፡፡ በእምነት ውስጥ ግን ፈጽሞ ሊሠራ አይችልም፤የቀደመውን እምነት በማጥፋት በእርሱ ፍርስራሽ ላይ አዲስ እምነት መገንባት ተገቢ አይደለም፡፡

የቀደመው እምነት ጥብቅ ነው. . .

በእምነት ውስጥ አዲስ የሆነ ነገር ሁሉ ጥርጥር ሊሆን ስለሚችል በአባቶቻችን የተላለፈልንን የቀደመ እምነት የሚያጠፋ ነው፡፡

ስለሆነም የራሳቸውን አሳብና አመለካከት የሚከተሉ ሰዎች በሚችሉት አቅም ሁሉ ይህን አሳባቸውን የሚደግፉ ጥንታዊ ጽሑፎችን ለማቅረብ ይሞክራሉ፤ ካልተሳካላቸውም ከመፈብረክ ወደኋላ አይሉም፡፡

እነዚህ ሰዎች አሳቦቻቸውን ለመረዳት «የበረሀ አባቶች ብሒል» የሚለውን መጽሐፍ አያነቡም። እነርሱ የሚያነቡት ብሒሎችን ወይም የእነርሱን አሳብ የሚደግፈውን መጽሐፍ ብቻ በመምረጥ ነው።

እነርሱ የሚያነቡት ከጽሑፉ በፊት ወይም በኋላ ያለውን ንባብ ቆርጠው በማውጣት ነው። እነርሱ የሚያነቡት ቃሉ የተነገረበትን አንኳር ወይም አጠቃላይ አሳብ ነጥለው ካወጡ በኋላ ነው።

እነርሱ ይህን ጥቅስ የሚጠቀሙበት አሳባቸውን ለማረጋገጥ ነው። ይህን የሚያደርጉትም የጻድቁ ሰው አባባል እነርሱ ከሚሉት አባባል ጋር የሚቃረን ቢሆንም ነው።

ለእነርሱ አሳባቸውን የሚደግፍላቸውን እንጂ እውነትን ማግኘት አይፈልጉም። ይህ ማስረጃቸው እንዴት እንደተፈበረከና እንደተሳሳተ ማወቅ አያሳስባቸውም።

የተባረከኸው ልጅ ግን ከእምነትና ከዶክትሪን የተዛመዱ ጉዳዮች ሲገጥሙህ የራስህን አሳብ አታትም፤ቤተ ክርስቲያን የምታምንበትን እንጂ።

ወደ ራስህ የሚመጣውን ማንኛውንም አዲስ አሳብ አታስፋፋ። ይልቁንም ይህ አሳብ ወደ ሕዝቡ ከመበተኑ በፊት በኃላፊነት የሚመለከታቸው የቤተ ክርስቲያን አባቶች ብሒሎቻቸውን እንዲሰጡበት አድርግ።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማስተማር የራስን የግል አስተሳሰብ መግለጫ መንገድ አይደለም፤የሐዋርያትን ትምሕርትና ትውፊት ሳይለቅ ለሁሉም አንዲት እምነትን ማስተማሪያ መንገድ እንጂ።

(59)
ጸጥታ

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ ብሏል፦ «በውጭ የሆነ ሽልማት አይሁንላችሁ፤ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ የዋህና ዝግተኛ መንፈስ ያለውን የማይጠፋውን ልብስ ለብሶ የተሰወረ የልብ ሰው ይሁንላችሁ።» 1ኛ ጴጥ 3:4።

ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ ስለ ፀጥታ እንዲህ ብሎ መክሮናል፦ «. . . በጸጥታም ትኖሩ ዘንድ. . . እንለምናችኋለን።» 1ኛ ተሰ 4:11።

የጸጥታ ዓይነቶች ብዙ ናቸው። ከእነርሱም መካከል አንዱ የነርቭ ጸጥታ ነው።

አንድ ጠቢብ ሰው እንደተናገረ እነዚህኞዎቹ ነርቮች ፈጥነው አይቆጡም አይናደዱምም። ስለማይበሳጩም የተረጋጋ መልስ በመስጠት ችግሮችን በጸጥታ ይይዛሉ፤ንዴትንም ያጠፋሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፦ «ክፉዎች ግን እንደሚንቀሳቀስ ባሕር ናቸው፤ፀጥ ይል ዘንድ አይችልምና፤ውኆቹም ጭቃና ጉድፍ ያወጣሉና። ለክፉዎች ሰላም የላቸውም ይላል፤አምላኬ።» ኢሳ 57:21።

ሌላው ጸጥታ የልብ ፀጥታ ነው . . .

አንድ ሰው በውስጡ ያለው ልቡ በቁጣ ተሞልቶ ውጪያዊ እንቅስቃሴውን ሊቆጣጠር ይችላል። እውነተኛ የጸጥታ ሰው ከውጪም ሆነ ከውስጥ ጸጥ ያለ ነው።

የልብ ጸጥታ በቁጣ፣ በፍርሃት፣ በጥርጥር፣ በቅናትና በሌሎችም ስሜቶች ውስጥ ይገለጣል። ፍላጎትና ውስጣዊ ውጊያ በሰው ውስጥ ከባድ ትግል ያደርጋሉ።

እንዲህ ያለው ጸጥታ የውስጣዊ ሰላም አንዱ ክፍል ነው. . .

ከልብ ጸጥታ ደግሞ የአሳብ ጸጥታ ይመነጫል። ጸጥ ያለና የተስተካከለ አሳብ የሚሠራው ያለ ምንም መጨነቅ ወይም መታወክ ነው። ይህ ደግሞ አንድን ሰው ሥራውን ያለ ምንም ንጭንጭ ወይም ሽብር እንዲያከናውን ያደርገዋል።

እንዲህ ያለው የአስተሳሰብ ጸጥታ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገር ሰውን ወደ ጥበብ እንዲደርስ ያስችለዋል፦ «በሰነፎች መካከል ከሚጮኽ ከገዢው ጩኸት ይልቅ የጠቢባን ቃል በጸጥታ ትሰማለች።» መክ 9:17።

የስሜቶች ጸጥታ የአሳብን ጸጥታ ለማግኘት ይረዳል።

ይህ በመሆኑም አባቶቻችን ሰው ጸጥ ባለ ሰውነት ጸጥ ያለ መንፈስን ገንዘብ እንደሚያደርግ ስላወቁ የጸጥታ ሕይወትን አጥብቀው ፈልገዋል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ጸጥታ ጥቅም የተነገረው እጅግ ድንቅ ቃል፦ «የእስራኤል ቅዱስ፤ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፦ በመመለስና በማረፍ ትድናላችሁ፤በጸጥታና በመታመን ኃይል ይሆንላችኋል፤. . .» ኢሳ 30:15።

በጸጥታ ሕይወት ውስጥ ለመኖር እንናፍቅ፤ይህንንም ከእግዚአብሔር ዘንድ እንፈልገው።

(60)
መልካሙ መንገድ

የምንሠራው ሥራ በራሱ ወይም በዓላማዎቹ መልካም ነው ማለት ብቻ በቂ አይደለም፤የምንጠቀምበት ዘዴም መልካምና ጥሩ መሆን አለበት።

ለምሳሌ፦ ኃይል ወይም ከፍተኛ ጥብቅነት ወይም ጭካኔ ሥነ ሥርዓትንና መታዘዝን ለማግኘት ወይም ለማጎልመስ መልካም ዘዴዎች አይደሉም።

እነዚህ መንገዶች በአብዛኛው እያንዳንዱን ሰው የማያስደስቱ መንገዶች ናቸው። አንድ ሰው ያለ ምንም ኃይል ወይም ሽብር መልካም መንገዶችን ተግባራዊ በማድረግ ዓላማው ላይ መድረስ ይችላል።

በእምነትም ሆነ በአመለካከት ከአንተ ጋር ለማይስማሙት ሰዎች በመሐላ መልስ መስጠት መንፈሳዊ ዘዴ ወይም መንገድ አይደለም።

ይህን በማድረግህ አስቀድመህ የተስማማኸውን ሰው ታጣዋለህ። ጸሐፊ ወይም ደራሲ ከሆንህም አንባቢዎችህን ታጣለህ። እምነትና ሃይማኖትን አስመልክተህ ስትወያይ ትክክለኛው መንገድ ያለ ምንም መሐላ ወይም ስድብ ዓላማህን መግለጽ ነው። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላልና፦ «. . . ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።» 1ኛ ቆሮ 6:10።

ጥፋት ወይም መራር ሂስ ወይም ሌሎችን ለመጣል የሚደረግ ሙከራ ቅዱስ ቅንዓትን ለመግለጽ መልካም መንገዶች አይደሉም። ቅንዓት መገለጽ ያለበት ነገሮችን

ሆነ ብሎና ዓላማን በመያዝ በቀናነቱና በገንቢነቱ መሆን አለበት። ከዚህ በተጨማሪ በፍቅር በሚደረጉ ጸጥ ያሉ ጥናቶችና ተቀባይነት ባላቸው ውጤቶች መሆን አለበት። ቅዱስ ጳውሎስ ይህን አስመልክቶ ሲናገር «በእናንተ ዘንድ ሁሉ በፍቅር ይሁን።» (1ኛ ቆሮ 16:14) ብሏል።

መለያየት ለስብከት ወይም ለማኅበራዊ ወይም ለብሔራዊ ሥራ መልካም መንገድ አይደለም።

መለያየት ደረጃዎችን ይቀንሳል፤የመተባበር እጦትን ያረጋግጣል፤ ከሌላው አመለካከት ጋር ለመደራደርም አያስችልም። ከዚህ በተጨማሪ ሌላውን ወገን ለማሳመንና ለማሸነፍ ያለመቻል ምልክት ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲህ የሚል ቃል አለ፡- «ነፍሶችን የሚሰበስብ እርሱ ጠቢብ ነው።» ምሳ 11:30።

ጠቢብ ሰው ስለ መልካም ሥራዎቹ ሲል የሚመርጠው መልካሙን ዘዴ ነው።

የተሳሳተ ዘዴ ከመልካም ሥራ ጋር ሊሄድ አይችልም።

መልካም ሥራ ተገቢ ባልሆነ መንገድ ወይም ዘዴ ከተከናወነ ውጤቱ የብርሃንና የጨለማ ድብልቅ ወይም የጽድቅና የኃጢአት ውህደት ስለሚሆን ይህ መንፈሳዊነትን አያረጋግጥም።

ስለሆነም መንገዶቻችሁ ወይም ዘዴዎቻችሁ መልካም፣ እውነትና መንፈሳዊ ይሁኑ። ቢያንስ-ቢያንስ የሚጎዱ ወይም የማሰናከያ ድንጋይ እንዲሆኑ አትፍቀዱ።

(61)
መሠረታዊው የቅድስና ሥራ

አንዳንድ የቅድስና ሥራዎች ሙሉ ሳይሆኑ ሲቀሩ ሰው እነርሱን ሙሉ ለማድረግ አጥብቆ ይታገላል። ይሁን እንጂ በውስጣቸው የተለያዩ መልካም ሥራዎችን ያጠቃለሉ መሠረታዊ የቅድስና ሥራዎች አሉ።

ከሁሉ የሚበልጠው የቅድስና ሥራ ፍቅር ነው።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕግና ነቢያት ሁሉ በዚህ መሠረታዊ የቅድስና ሥራ ውስጥ መጠቃለላቸውን ተናግሯል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ተለያዩ የፍቅር የቅድስና ሥራዎች ሲገልጽ እንዲህ ብሏል፡- «ፍቅር ያስታግሣል፤ፍቅር ያስተሳዝናል፤ፍቅር አያቀናናም፤ፍቅር አያስመካም፤ፍቅር አያስታብይም፤ብቻዬን ይድላኝ አያሰኝም፤አያበሳጭም፤ክፉ ነገርን አያሳስብም፤ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤ሁሉን ይታገሣል፤ሁሉን ያምናል፤ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፤በሁሉ ይጸናል። ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም. . .» 1ኛ ቆሮ 13:4-8።

ስለሆነም ፍቅር ያለው ማንኛውም ሰው እነዚህ ሁሉ የቅድስና ሥራዎች አሉት።

ቅዱስ ጳውሎስ የጠቀሳቸው በሙሉ ለባልንጀሮቻችን የሚሆኑ የፍቅር ሥራዎች ናቸው።

ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር በተመለከተ የተለያዩ ጉዳዮችን እንደሚያጠቃልል ምንም ጥርጥር የለውም። ከሚያጠቃልላቸው መካከልም፡- ደረጃቸውን የጠበቁ ጸሎቶች፣ ተመስጦ፣ ውይይት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፣ ቤተ ክርስቲያንንና ምሥጢራቶቿን መውደድ፣ መንፈሳዊ ጉባኤ፣ ጾም፣ ስግደት፣ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት መጠበቅና ሌሎችም ይገኙበታል። የጌታን ትእዛዛት የምንጠብቀው እርሱ «ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው፤. . .» (ዮሐ 14:21) ስላለ ነው።

ሌላው መሪ የቅድስና ሥራ የመማረክ (የመሸነፍ) ሕይወት ነው።

መማረክ ወይም መሸነፍ ማለት ሕይወትን ይመራ ዘንድ ራስን በልብ ውስጥ ለሚኖር ለመንፈስ ቅዱስ አሳልፎ መስጠት ማለት ነው።

በዚህ ጊዜ ይህ ሰው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በላከው መልእክቱ «የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት ፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት ነው።» (ገላ 5:22-23) በማለት የተናገራቸውን የመንፈስ ፍሬዎች ያፈራል።

ድንቅ ከሆኑት የቅድስና ሥራዎች መካከል አንዱ ደግሞ ትሕትና ነው።

ትሑት ሰው ጨዋነትንና እርምሞን የተላበሰ ነው። እርሱ ራሱን ከቁጣ፣ በሰዎች ላይ ከመፍረድና ከጭካኔ ያራቀ ሰው ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ትሕትና፡- የልብ ጸጸትን፣ ራስ መውቀስን፣ የጽድቅ ዕንባን፣ ፍቅርን፣ ሁሉን መባረክን፣ የእያንዳንዱን ሰው በረከት መቀበልን፣ ከመናገር ይልቅ ማዳመጥን መምረጥን፣ ጉራ መንዛትን ወይም ራስን ከፍ-ከፍ ወይም ራስን ማወደስን ፈጽሞ ገንዘብ አለማድረግን፣ በሁሉም ነገር መርካትን፣ መደሰትን፣ ማመስገንንና የዋህነትን ያጠቃልላል።

(62)
የፍቅር ትርፍ

ማትረፍ የሚወድ ሁሉ ከማንኛውም ነገር፣ ከማንኛውም ሰውና ከማንኛውም አጋጣሚ ማትረፍ ይችላል።

እርሱ በማናቸውም ልምዶቹ ውስጥ ተጠቃሚ ነው።

እርሱ ከመልካሙም ሆነ ከመጥፎው ተጠቃሚ ነው።

እርሱ ከጻድቁ ሰው መልካም ምሳሌ፣ ፍቅርና መልካም አቀባበልን ገንዘቡ ያደርጋል። ከመጥፎው ሰው ደግሞ የትዕግሥትን፣ የጽናትንና የይቅርታን የቅድስና ሥራዎች ገንዘቡ ያደርጋል። አንተም ብትሆን የዚህን ተመሳሳይ መጥፎ ምግባር ጉዳትና ችግር ስታውቅ ማንኛውንም የቅድስና ሥራ ትማራለህ።

አንድ ጠቢብ ሰው «ዝምታን የተማርሁት ከለፍላፊ ሰው ነው።» ብሏል። ይህም ማለት የመለፍለፍን ጉዳት መገንዘቤ የዝምታን ጥቅም እንዳውቅ አድርጎኛል፤እንዲህ ያለውን መጥፎ ጠባይም እንዳስወግድ ረድቶኛል።

ከስሕተቶቻችንና ከሌሎች ሰዎች ጥፋቶችም መማር እንችላለን።

ጠቢብ ሰው ከስሕተቶቹ ማትረፍን ስለሚያውቅና የሕይወት ልምድን ስለሚያካብት ዳግመኛ በእነዚህ ስሕተቶች ተጠልፎ አይወድቅም። ብዙ ልምዶች ሰው የጠቃሚ ነገሮች ምንጭ ነው።

ማትረፍ የሚፈልግ ሰው የሚያተርፈው ከሚያገኛቸው ሰዎች ብቻ ሳይሆን ከተፈጥሮም ነው።

ጠቢቡ ሰሎሞን እንዲህ ብሏል፦ «አንተ ታካች ወደ ገብረ ጉንዳን ሂድ፤መንገዷን ተመልከተህ ጠቢብ ሁን።» ምሳ 6:6። ጉንዳንን ለእኛ የጥቅማችን መገኛ አድርጎ መመልከት ምንኛ ድንቅ ነገር ነው!

ከተፈጥሮ እንደምንጠቀም ከአጋጣሚዎችም እንጠቀማለን። በእኛ ላይ ከደረሰውና በሰዎች ላይ ከደረሰው ገጠመኝም እንጠቀማለን። ለመማር ንቁ ለሆኑ ሁሉ እነዚህ የሕይወት ጠቃሚ ትምህርቶች ናቸው።

የሰነፉ ባለጸጋ ታሪክ ለብዙ ሰዎች መማሪያ ነው። በመጽሐፍ ውስጥ የተመዘገቡት ታሪኮችና አጋጣሚዎች በሙሉ እንደ ታሪክ ገጠመኞች መማሪያዎች ናቸው። ይህን አስመልክቶ አንድ የጽሑፍ ባለሙያ ሲናገር «ታሪክን በልቡ የሚጠብቅ ሰው በዕድሜው ላይ ዕድሜ ይጨምራል።» ብሏል።

የጥቅም ምንጮች የሆኑት መንፈሳዊ አባቶች ብቻ አይደሉም።

ልብ ጥቅም እስከፈለገ ድረስ እግዚአብሔር በእርግጥ በተለያዩ መንገዶችና ዘዴዎች ይልካቸዋል።

(63)
መስቀል

መስቀል የሕማም ምልክት ነው። ሦስት መስቀሎች ይህን ነገር ይገልጣሉ፦

የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ስለ ጽድቅ ሲባል የሚቀበሉት ሕማም ምልክት ሲሆን ሌሎቹ ሁለቱ መስቀሎች ደግሞ ለኃጢአት ቅጣት ሲባል ሕማም የሚቀበሉባቸው መስቀሎች ናቸው። እነዚህ ሕማማት ደግሞ ለሁለት ይከፈላሉ፦ ከእነዚህ ሕማማት በአንዱ ውስጥ ያለው ሰው ንስሐ ገብቶ የሚመለሰው ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በኃጢአቱ ምክንያት የሚያጉረመርመውና የሚያማርረው በመጨረሻም በኃጢአቱ የሚሞተው ሰው ነው።

- ስለ ጽድቅ ብለው የሚሸከሙት መስቀል እንዲሁ በዓይነቱ የተለያየ ነው፦

የፍቅርና የመሥዋዕትነት መስቀል መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን በጽናት የተቀበለውን ሕማም የሚያሳየውን መስቀል የሚመስል ነው፦ «ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከማኖር ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም።» ዮሐ 15:13።

በመባ ውስጥ ሌላ መስቀል አለ። ታላቁ መሥዋዕት ደግሞ ለራስህ ከሚያስፈልግህ ነገር ላይ አንስተህ የምታቀርበው መባ ነው። አንተ የምትፈልገውን ነገር ሌሎች እንዲወስዱት በማቅረብ ውስጥ ሕይወቷ የነበሩትን ሁለት የነሐስ ሳንቲሞች ለቤተ መቅደስ ያቀረበችውን መበለት ያስታውሰናል።

ሌላው መስቀል ደግሞ በጽናት ውስጥ ያለው መስቀል ነው። ሁለተኛውን ጉንጭ ማዞርና ሁለተኛውን ምዕራፍ መጓዝ ለዚህ ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ መስቀል ውስጥ ያለው የሰውን ነቀፋ መሸከም ብቻ ሳይሆን በጥላቻ ስሞቻችንን የሚያጠፉትን ሰዎች በፍቅር መውደድም ነው።

ይህን ሊያደርግ የሚችል ማነው? መስቀል ነዋ!

መንፈሳዊ ቃሳትና ጥቅማቸው

በመንፈሳዊ ውጊያዎች ውስጥ እንዲሁ መስቀል አለ። ነፍስ ሥጋን ድል በመንሳቷ ውስጥ፤መከራን በመቀበልና የዓለምን ውጊያ በመታገሥ ውስጥ፤በሥጋና በዲያብሎስ ውጊያ ውስጥ፤ሥጋንና ምኞትን በመስቀል ውስጥ፤ራስን በማሸነፍ ውስጥ፤በጠበበው ደጅ መግባት ውስጥ መስቀል አለ።

ስለ ጽድቅ የሚቀበሉት መከራ መስቀል ነው። ይህ ለጀማሪዎች ነው። ፍጹማን ለሆኑት ግን መስቀል ደስታና መደሳደል ሆኖ ይቀየራል።

የመንገዱ ጥበት የሚታወቀን በመንገዱ መግቢያ ላይ ነው። ከዚህ በኋላ ግን ትእዛዛትን በመቀበል ውስጥ ደስታ ስለሚሰማን መንገዱን እንወደዋለን። እዚህ ደረጃ ላይ ስንደርስ መንገዱ አያደክመንም፤በመጀመሪያ መስቀል የነበረው መንገድ ደስታ ሆኖ ይቀየራልና።

ሰማዕትነት በመጀመሪያ መስቀል ቢሆንም በኋላ ደስታ ሆኖ ይለወጣል። ቅዱሳን ሰማዕትነትን ስለሚሹት ሞትን ይናፍቁታል፤ በዚህም ሐሴት ያደርጋሉ።

ስለ እግዚአብሔር መድከምና መከራ መቀበል የሚጠቃለለው በደስታ ነው።

ይህ በመሆኑም መጽሐፍ ቅዱስ መከራ መቀበልን ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ አድርጎ ይቆጥረዋል፦ «ይህ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቶአችኋልና፤ስለ እርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም፤. . .፡ ፊልጵ 1:29።

መስቀል በሕይወታችሁ ውስጥ ደስታ የሚሆነው መቼ ነው?

(64)
እምነት

እምነት ማለት ከሥነ መለኮት ትምህርትና ከቤተ ክርስቲያን የሚማሩት ድርቅ ያለ የአመለካከት ስብስብ አይደለም። ይልቁንም እምነት ማለት ጥልቅ ውስጣዊ አመለካከትና በእግዚአብሔር፣ በባሕርያቱና በሥራው ሙሉ ለሙሉ ማመን ማለት ነው።

በእግዚአብሔር፣ በሕልውናው፣ በእንክብካቤውና በጥበቃው ማመናችን ለልባችንና ለአሳባችን ውስጣዊ ሰላምና መደሳደል ይሰጥልናል፨ ይህ ደግሞ እግዚአብሔር እስካለ ድረስ በእርሱ መተማመንን ያድለናል። እኛ ለራሳችን ከምናደርገው እንክብካቤ የበለጠ እርሱ ለእኛ ያደርግልናል። ስለሆነም በዚህ ሰላም ውስጥ መኖርና እስከ መጨረሻው ድረስ መቀጠል አለብን።

ጭንቀት ከእምነት ጋር ስለሚቃረንና አማኙ ሰው በእግዚአብሔር ፍቅር፣ እንክብካቤና ጥበቃ ውስጥ ስለሚኖር በዚህ አይታወክም።

እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ እንደሚኖር የሚያምን ሰው የሁሉም ሥፍራ ቅድስና ይታወቀዋል፤እርሱ በዚያ ሥፍራ ዘወትር አለና። እግዚአብሔር ባለበት ሥፍራ ላይ ሁሉ መተማመን ስለሚሰማው በድርጊቶቹ ሁሉ ጥንቁቅ ይሆናል፤ እግዚአብሔር እንደሚያየው፣ እንደሚሰማውና ሥራዎቹን ሁሉ እንደሚከታተል ይታወቀዋልና።

እንዲህ ዓይነቱ ሰው ከማንኛውም ኃጢአት ጋር ሲጋፈጥ ከጻድቁ ዮሴፍ ጋር «እንዴት በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት እሠራለሁ?» (ዘፍ 39:9) ይላል።

እግዚአብሔር አሳቡን እንደሚያነብ፣ የልቡን ምሥጢሮች እንደሚያውቅ፣ ስሜቶቹንና ፍላጎቶቹን እንደሚረዳ የሚያሳውቅ እምነት ያለው ሰው እነዚህ ስሜቶቹን

ሁሉ በሚመረምረው አምላክ ፊት የሚቆመው በእፍረት ነው እንጂ በድፍረት አይደለም፡፡

ስለሚመጣው ዓለምና እግዚአብሔር ለሁሉም ሰው እንደ ሥራው፣ እንደ አሳቡ፣ እንደ ስሜቱና እንደ አነጋገሩ የሚከፍልበት ቀን እንደሚመጣና ይህ ከንቱ ዓለም እንደሚጠፋ ይህ እምነቱ ያሳውቀዋል፡፡ ይህ እውቀቱም ለዚያ አስፈሪ ቀን ዝግጅት ማድረግ እንደሚገባውና ከሞት በኋላ ላለው ዘላለማዊ ሕይወት እንዲሠራ ያደርገዋል፡፡

አንድ ሰው ይህን አሳቡን በልቡ በመጠበቅ ከነቢዩ ዳዊት ጋር እንዲህ ይላል፡- «አቤቱ ፍጻሜዬን አስታውቀኝ፤የዘመኔ ቁጥሮች ምን ያህል እንደ ሆኑ፤እኔ ምን ያህል ወደ ኋላ እንደምቀር አውቅ ዘንድ፡፡» መዝ 38:4፡፡

እምነት ማለት በኅሊና ማመን ብቻ ማለት አይደለም፤ሰውን በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ለመምራት በልቡ ውስጥ የሚኖር ድርጊት እንጂ፡፡

ሰው እግዚአብሔርን የሚቀበለው ለተወሰነ ጊዜ ብቻ አይደለም፤ ይህ የዕድሜ ልክ ሥራ ነውና፡፡ በዚህ ሥራ ውስጥ ያለ ሰው ደግሞ በመተማመን እንዲህ ይላል፡- «እምነት ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው፡፡» ዕብ 11:1፡፡

ስለሆነም እምነት የሚለውን ጉዳይ ከብዙ አቅጣጫ ስንመለከተው ከሁሉም መልካም አመለካከቶችና ሥራዎች ጋር የሚሆን የክርስቲያን ሕይወት ማለት ነው፡፡

(65)
ጸሎት

ጸሎትን ቀለል ባለ ትርጉሙ ስንመለከተው ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ማለት ሲሆን በጥልቅ ትርጉሙ ስናጤነው ግን ከእግዚአብሔር ጋር የሚሆን ግንኙነት ማለት ነው፡፡

ጸሎት ቃላት ከመሆኑ በፊት የነበረ የፍቅርና የጥልቅ ስሜቶች ግንኙነት ነው፡፡

ያለ ፍቅር የሆነ ንግግር ትርጉም አልባ ነው፡፡

ይህ በመሆኑም እግዚአብሔር በተግሣጽ ቃል እንዲህ ብሏል፡- «. . . ይህ ሕዝብ በአፉ ወደ እኔ ይቀርባልና፤በከንፈሮቹም ያከብረኛልና፤ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነውና፤. . .» ኢሳ 29:13፡፡

ከዚህ የተነሣ የክፉ ሰው ጸሎት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የለውም፡፡ እንዲህ ያለው ጸሎት የፍቅር ውጤት ስላልሆነ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ነው፡፡ እንደ ፈሪሳዊው ሰው በትዕቢት ተነፍቶ ይቅርታ ለመጠየቅ መቆም በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የለውም፡፡

ልባቸውን ሳያጠሩ ወደ እርሱ የሚጸልዩትን ሰዎች እግዚአብሔር እንዲህ ይላቸዋል፡- «እጃችሁንም ወደ እኔ ብትዘረጉ ዓይኔን ከእናንተ እሰውራለሁ፤ልመናንም ብታበዙ አልሰማችሁም፤እጆቻችሁ በደም ተሞልተዋልና፡፡ ታጠቡ ሰውነታችሁንም አንጹ፤የሥራችሁን ክፋት ከዓይኔ ፊት አስወግዱ፤ክፉ ማድረግን ተዉ፤. . .» ኢሳ 1:15-16፡፡

ጸሎት ሰማይና ምድርን የሚያገናኝ ድልድይ ነው፡፡ በመሆኑም ሰማይና ምድርን ባገናኘው ከያዕቆብ መሰላል ጋር ይነጻጸራል፡፡

ጸሎት የገነት ቁልፍ ነው፡፡ የመላእክት ቋንቋና ሥራ ነው፡፡ የመንፈሳውያንም ሕይወት ነው፡፡ ጸሎት ማለት ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የሚሆንበትን የሚናፍቅበት ጊዜ ነው፡፡ ጸሎት ማለት የተወሰነው ያልተወሰነውን፤ፍጡሩ ፈጣሪውን፤ነፍስም መገኛ ዋንና ደስታዋን የሚናፍቁበት ጊዜ ነው፡፡

በጸሎት ውስጥ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ከቁሳዊው ዓለም በላይ ከፍ ከፍ ይላል፡፡

የጸሎት ውጤታማነት የሚለካው ሰውየው ጸሎቱን ለመጨረስና ለማቆም ባለመቻሉ ነው፡፡ ጸሎቱን ለመፈጸምና አሜን ብሎ ለማቆም የሚጣደፈው ግን የጸሎቱ ውጤታማነት ቀደም ሲል ከተመለከትነው ተቃራኒ ነው፡፡

በጸሎቱ ስኬታማ የሆነ ሰው ጸሎቱን ለመተው ወይም ለማቆም አይችልም፡፡ ይልቁንም «ነፍሴ የወደደችውን አገኘሁት፤ያዝሁትም፤ . . . አልተውሁትም፡፡» (መኃ 3:4) በማለት ተወዳጁን መዝሙር ከመላእክት ጋር ይዘምራል፡፡

በጸሎቱ ስኬታማ የሆነ ሰው ምንም ይሁን ምን ሌላ ምንም ዓይነት ሥራ ለመሥራት አይመርጥም፡፡ ቅዱሳን ስለ ጸሎት ሲሉ ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ የሚያደርጋቸውንና በሙሉ ልባቸው የወደዱትን ፍጹም ጸጥታና ዝምታ በመፈለግ ከዓለሙና በዓለሙ ውስጥ ካለው ቁሳዊ ነገር አምልጠው ወጥተዋል፡፡

ጸሎት እዚህ ምድር ላይ ተጀምሮ በሰማይ የሚጠናቀቀው የእግዚአብሔር መንግሥት ቅምሻ ነው፡፡

ሰው ከጸሎት ጋር ከተጣበቀ ሕይወቱ ጸሎት፤ጸሎትም ሕይወቱ ይሆናል፡፡

ሙሉ ሕይወቱ በአንድ ዓረፍተ ነገር «ሕይወቱ ጸሎት ነበር፡፡» ተብሎ የተጻፈለት አንድ ቅዱስ ሰው ነበር፡፡ የተጀመረ ጸሎት ቀጣይነት ያለውና የማያቋርጥ መሆን አለበት፡፡ ሰው ከተኛ በኋላ እንኳ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ንግግር አይቋረጥም፡፡ ጸሎት በውንም ሆነ በህልም አይቋረጥም ማለት ነው፡፡ «በመኝታዬ አስብሃለሁ፤. . .» (መዝ 62:6) የሚለው ቃል ለዚህ የተጠቀሰ አይመስላችሁም?

(66)
የመሥዋዕትነት ሕይወት

በአጠቃላይ እግዚአብሔር ከአንተ የሚጠይቀው ልብህን ነው፡- «ልጄ ሆይ ልብህን ስጠኝ፤. . .» ምሳ 23:26፡፡ እርሱ ልብህን ሲጠይቅህ የሚጠይቅህ ፍቅርህን ነው፡፡ የፍቅር ማስረጃው ደግሞ መሥዋዕትነት ነው፡፡

ስለሆነም ሕይወትን ጨምሮ ማንኛውም መሥዋዕት የሚቀርብበት ሕይወት መንፈሳዊ ሕይወት ነው፡፡ «ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው . . .» ሐዋ 20:35፡፡

ስለ እግዚአብሔር ብላችሁ የምትተዉት ነገር መኖር አለበት፤ ፍቅራችሁን ለእርሱ ማቅረብ አለባችሁ፡፡ ፍቅራችሁ ስለ እግዚአብሔር ብላችሁ ከምትተዉት ነገር ጋር ተነጻጻሪ ነው፡፡

የአባቶች ሁሉ አባት የሆነውን አብርሃምን ተመልከቱት! እርሱ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት የጀመረው እንዴት ነው? ግንኙነቱን የጀመረው እግዚአብሔር ሲሆን የጀመረውም እንዲህ በማለት ነው፡- «. . . ከአገርህ፣ ከዘመዶችህም፣ ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ፡፡» ዘፍ 12:1፡፡

አብርሃም ስለ እግዚአብሔር ሲል ቤተሰቦቹንና አገሩን ትቷል። እግዚአብሔር ከአንተ የሚጠበቀው ይህ ብቻ ነው ብሎታል እንዴ? አላለውም። አብርሃም ወደ እንግድነት ምድር ከወጣ በኋላ እንኳ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎታል፦ «የምትወደው አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያም ምድር ሂድ፤በዚያ መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው. . .» ዘፍ 22:2።

አብርሃም ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ልጁን መሥዋዕት አድርጎ ለማቅረብ ሄዷል።

ሙሴም እንዲሁ የልዑልነት ማዕረግን፣ ንጉሣዊ ቤተ መንግሥትን፣ ብልጽግናንና ሥልጣንን መሥዋዕት አድርጓል፦ «ከግብፅም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፍ የሚበልጥ ባለ ጠግነት እንዲሆን አስቧልና. . .» ዕብ 11:26።

ሐዋርያትም ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብለው ጠይቀውት ነበር፦ «እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ፤. . .» ማቴ 19:27። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም እንዲህ ብሏል፦ «ስለ ጌታዬ እውቀት ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን እቆጥራለሁ፤ስለ እርሱ ሁሉን ተጎዳሁ፤ክርስቶስንም አገኝ ዘንድ. . .» ፊልጵ 3:8።

እናንተ ያላችሁን ሁሉ ስታቀርቡ ወይም ስትሰጡ መሥዋዕትነት ከፍተኛው ደረጃ ላይ ደርሷል ማለት ነው። ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን ያሏትን ሁለት ሳንቲሞች መባ አድርጋ ያቀረበችው መበለትና ያላትን ምግብ ሁሉ ለነቢዩ ኤልያስ ያቀረበችው መበለት ናቸው። ጌታ እንዲህ ብሏል፦ «. . . ያለህን ሁሉ ሸጠህ ለድሆች ስጥ፤በሰማይም መዝገብ ታገኛለህ፤ መስቀሉንም ተሸክመህ ና፤ ተከተለኝ. . .» ማር 10:21።

እግዚአብሔር ራሱ ይህን ፍቅር የመሥዋዕት ምሳሌ አድርጎ ሰጥቶናል፦ «. . .እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።» ዮሐ 3:16። «ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከማኖር ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም።» ዮሐ 15:13።

ሰማዕታት ራሳቸውን ለሞት አሳልፈው ሰጥተዋል። እነርሱ ለክርስቶስ ካላቸው ፍቅር የተነሣ የራሳቸውን ሕይወት አልወደዱም።

ውድ አንባብያን፤እናንተስ? ለሰው ልጆች ሲል ሰው ለሆነው፣ ራሱን አሳልፎ ለሰጠውና በመስቀል ላይ ለሞተው ለኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕት አድርጋችሁ የሰጣችሁት ምንድር ነው?

እንደ ሰማዕታት ሕይወታችሁን መሥዋዕት አድርጋችሁ እንድትሰጡ አንጠይቃችሁም፤ያ ጊዜ ልዩ ነበርና።

የምትወዷቸውን ኃጢአቶች ስለ ክርስቶስ ስትሉ መሥዋዕት አድርጋችሁ ልታቀርቡ የሚገባችሁ ዋናው ነገር ይህ ነው።

(67)
ለቅድስና ሙሉ መሆን

ለቅድስና አዋቂ ሆኖ መቅረብ ቅድስናን ያጠፋዋል። ጥበብ ለቅድስና የሚሰጠው ትርጉም ብርቱና ተግባራዊ ነው።

የመቻልና የመታገሥ ቅድስና ምሳሌ ሊሆን ይችላል፦ «በመታገሣችሁም ነፍሳችሁን ታገኛላችሁ።» ሉቃ 21:19። ለራሳችሁ ጊዜ በመስጠትም ብዙ ችግሮችን ልታቃልሉ ትችላላችሁ። ሰዎች ችኩሎችና ትዕግሥት የሌሾች እንዲሆኑ የሚያደርገው

ዲያብሎስ ነው። እርሱ ይህን በሰዎች ላይ የሚያመጣው ከማወክና ዕረፍት ከማሳጣት በተጨማሪ ነው።

ያም ሆነ ይህ ግን ፈጣን እርምጃ ሊወሰድባቸው የሚገባ ጉዳዮች አሉ። ፈጣን ባለ መሆን ጉዳዩ ወደ ሐዘንና ወይም ወደ ጥፋት ሊያደርስ ይችላል።

ለምሳሌ፦ ኃጢአተኞችን መፈለግና ማግኘት፤ሰውን ከኃጢአት ሥፍራ ማግለል፤የቤተሰብ ችግር የተወሳሰበ ሆኖ ፍርድ ቤት ከመድረሱ በፊት መፍትሔ መስጠት፤በኃጢአት ውስጥ ያለ ሰው በሌሎች ላይ አደጋ ከማምጣቱ በፊትና ኃጢአቱ የከፋ ወንጀል ከመሆኑ በፊት መገሠጽና ሌሎችም ተመሳሳይ ጉዳዮች ፈጣን እርምጃ ሊወሰድባቸው የሚሹ ጉዳዮች ናቸው።

ንስሓ ከትዕግሥትና ከቆይታ ጋር የሚሄድ ሥራ አይደለም።

የመቻልና የመታገሥ ቅድስና ጥበብ ከሌለበት ልክ አዋቂ ሆኖ ለሚቀርብ ሰው ምንም ሥራ እንደማይሠራ ሁሉ በራሱ ብቻውን የሚሰጠው ጥቅም የለውም።

በዙሪያችን ያሉትን ሁኔታዎች ሳናገናዝብ ጥበብን ከጨዋነትና ከአርምሞ ቅድስና ነጥለን የምንመለከት ከሆነ የበዙ ስሕተቶች ላይ እንወድቃለን።

የመቻልና የመታገሥ ቅድስና ሥራ ሊሠሩ የማይችሉበት አንዳንድ የተቀደሱ ቅንዓቶች አሉ። እነዚህ ቅንዓቶች ጥቂት ቁጣዎችን ሊያስከትሉ ይችላሉ።

ይህ ቁጣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሰውና «ተቆጡ፤ነገር ግን ኃጢአትን አታድርጉ፤» (መዝ 4:4) ከሚለው ቃል ይቀናጅ ዘንድ ከልብ ንጽሕና ጋር መዋሀድ አለበት።

ከዚህ የተነሣ በቅድስና ሥራዎች ሁሉ ሙሉ መሆን ግድ ነው። እነዚህ የቅድስና ሥራዎች ደግሞ አንዱ ከሌላው ተለይቶ የሚሄድበት ምክንያት ሊኖር አይገባም።

ቅንዓት ጥበብን ሙሉ ሲያደርግ ጥበብ ደግሞ ትዕግሥትን ሙሉ ያደርጋል።

ስለ እግዚአብሔር ባሕርያት ስንነጋገር እግዚአብሔር በምሕረቱ እውነተኛ ነው፤ፍትሑም በምሕረቱ ውስጥ ነው እንላለን። የእግዚአብሔር ፍትሕ በምሕረቱ የተሞላ ነው፤ምሕረቱም በፍትሑ የተሞላ ነው።

በእግዚአብሔር ዘንድ ፍጹምነት ሲኖር በሰው ልጆች ዘንድ ደግሞ በቅድስና ሥራ ሙሉ መሆን አለ።

(68)
የቅዱሳን በዓላት

የቅዱሳን በዓላት የቅዱሳን ሰዎችን አማላጅነት በመሻት ብዙ አማኞች በሙሉ እምነት የሚሰበሰቡበት ዕለት ነው።

እነዚህ ሰዎች ቅዱሳን ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ቅርበት እንዳላቸውና እርሱ ጸሎታቸውንና አማላጅነታቸውን እንደሚቀበላቸው ያምናሉ። ከዚህ በተጨማሪ ይህ እምነት በመንፈስ ዘላለማዊነት፣ ከሞት በኋላ ባለው ሥራው፣ በምድር ላይ ካለችው ቤተ ክርስቲያን ጋር ያለውን የማይቋረጥ ግኑኝነትና ከዚህ ምድር በተለዩት በቅዱሳን መናፍስት ያምናል።

በእነዚህ በዓላት ብዛት ያላቸው ተአምራት ይታያሉ። ይህ የሚሆነውም በሕዝቡ እምነትና እግዚአብሔር የልባቸውን መሻት ስለሚሰጣቸው ነው። በቅዱሳን በዓላት የሚታዩትን ብዛት ያላቸው ተአምራት በሙሉ መዝግቦ ማስቀመጥ ተገቢ ነገር ነበር። ይህ የእያንዳንዱን ሰው እምነት ከማጠናከሩ በተጨማሪ ተአምራት የሚፈጸምበት ዘመን አለማብቃቱንና ተአምራት በቀደሙት ዘመናት የተወሰኑ አለመሆናቸውን ይገልጣል።

የቅዱሳን በዓላት በሚከበሩባቸው በእነዚህ ቀናት ከሚደረጉት ጉባኤዎች ቤተ ክርስቲያን ተጠቅማለች። በመሆኑም በእነዚህ ቀናት መንፈሳዊ መነቃቃት፣ እምነትን በጥልቀት የሚያሠርጹ ጠቃሚ መርሐ ግብሮችና ሕዝቡ በመንፈሳዊነት የሚመራበት ዝግጅት ይካሄዳል።

ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን ማንኛውንም ዓይነት ሳቅና ጨዋታ በማገድ ዕለታዊ ቅዳሴዎች ትቀድሳለች። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተደራጀ ውስጣዊ መገናኛ ብዙኀን ስላለ በእያንዳንዱ ቅዱስ ሰው ስም ዜማዎች፣ ስብከቶችና በሕይወት ዙሪያ ስለሚያጋጥሙ ጉዳዮች መንፈሳዊ ትምህርቶች የሚሰጡ ዝግጅቶች ይተላለፋሉ።

እነዚህ መርሐ ግብሮች ለቤተሰብ፣ ለሕፃናት፣ ለወጣቶች፣ ለሴቶችና ለሠራተኞች እንደሚያቀርቧቸው ዝግጅቶች የተለያዩ ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪ ይህን ጥቅም የሚሰጥ ዝግጅት ለማስፋፋት በኦዲዮ ቪዥዋል (በድምፅና በምስል) መሣሪያዎች በመታገዝ ለሕዝቡ የሚስቡ መንፈሳዊ ፊልሞችና ስላይዶች ይቀርባሉ። ይህ ደግሞ እንዲህ ያለው እይታ የሚቀርብባቸው አዳራሾች እንዲገነቡ ምክንያት ይሆናል።

በእነዚህ የበዓል ቀናት ቤተ ክርስቲያን የታተሙ በራሪ ጽሑፎችንና እንደ መስቀል፣ የቅዱሳን ምስሎችና ሥዕላት ያሉትን ቅርጻ ቅርጾች ታከፋፍላለች።

በእነዚህ የቅዱሳን የበዓል ቀናት ሰዎች የተቀደሱ መንፈሳዊ ቀናትን ስለሚያሳልፉ ታላቅ መንፈሳዊ በረከት ያገኛሉ።

ከዚህ ሌላ እነዚህ የቅዱሳን በዓላት አማኞች በኅብረት የሚገናኙባቸው ቀናት ናቸው። ይህ የኦርቶዶክሳውያን ተግባራዊ ሕይወት ከሚገለጥባቸው ጠባያት መካከል አንዱ ነው።

የቅዱሳን በዓላት ቤተ ክርስቲያን በሰማይና በምድር፤በዚህኛው ሕይወትና በሚመጣው ሕይወት አንድ የመሆኗን የሚያስረዱ ናቸው።

የቅዱሳን በዓላት ታላቅ በረከት የሚገኝባቸው ቀናት መሆናቸው ታውቋል። በተለይም በቤተ ክርስቲያን የበላይ አባቶች ትኩረት ከተሰጠው ወዲህ ምዕመናን ታሪካዊ አብያተ ክርስቲያናትን ይጎበኛሉ፤የተቀደሱ መሆናቸውንና ውጤቶቻቸውንም ያውቃሉ።

(69)
ከእግዚአብሔር ጋር መሥራት

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «. . . አባቴ እስከ ዛሬ ይሠራል፤እኔም ደግሞ እሠራለሁ. . .» (ዮሐ 5:17) ብሏል። ትኩረታችንን በጥቅሱ የመጨረሻው ዓረፍተ ነገር ላይ እናድርግ።

ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ራሱና ስለ ወንድሙ ስለ አጵሎስ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- «. . . ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነንና።» 1ኛ ቆሮ 3:9።

እግዚአብሔር በራሱ ሁሉንም ነገር ማድረግ ቢችልም እኛም አብረነው እንድሠራ ይፈልጋል። የሚፈልገው አብረነው እንድሠራ ብቻ ሳይሆን እንድንጥርና እንድንደክምም ነው። «. . . ነገር ግን እያንዳንዱ እንደ ራሱ ድካም መጠን የራሱን ደመወዝ ይቀበላል።» 1ኛ ቆሮ 3:8።

እግዚአብሔር የሚሠራበት ሐቅ ሰዎች ቸልተኞች እንዲሆኑ አይደለም።

በራእይ መጽሐፍ ውስጥ እግዚአብሔር በኤፌሶን ያለውን የቤተ ክርስቲያን አለቃ ስለ ሥራውና ስለ ድካሙ እንዲህ በማለት ባርኮታል፡- «ሥራህንና ድካምህን ትዕግሥትህንም አውቃለሁ፤ክፉዎችንም ልትታገሥ እንዳትችል፤እንዲሁም ሳይሆኑ ሐዋርያት ነን የሚሉትን መርምረህ ሐሰተኞች ሆነው እንዳገኘሃቸው አውቃለሁ፤. . .» ራእ 2:2።

ለመንፈሳዊው ሰው ሥራ ማለት ከእግዚአብሔርና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ኅብረት መፍጠር ማለት ነው። በአጠቃላይ ከመለኮታዊው አምላክ ጋር በሥራ ወዳጅ መሆን ማለት ነው።

ይህ ደግሞ በፈቃድ ዝግጁ መሆንና ከእግዚአብሔር ጋር የሥራ ወዳጅ መሆን ማለት ብቻ ሳይሆን እርግጠኛ የሥራ ተካፋይ ወዳጅ መሆን ማለት ነው።

ስለሆነም ለመንገደኞች በሚደረግ ቅዳሴ ውስጥ ለእግዚአብሔር «በባሪያዎችህ ሥራ ውስጥ ተካፋይ ሁን።» ብለን እንናገራለን።

በእግዚአብሔር መተማመን ማለት ታካች ወይም ግዴለሽ መሆን ማለት አይደለም፤ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት መፍጠር በእርሱ ኃይል መመካት እንጂ።

በሥራ ውስጥ እግዚአብሔር ለእርሱ ያለንን ፍቅርና መታዘዝ ይፈትሻል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ እንዲህ በማለት ተናግሯል፡- «ልጆቼ ሆይ፤በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት እንዋደድ።» 1ኛ ዮሐ 2:18።

እንደ ዳዊት እምነት ከሆነ ውጊያው የእግዚአብሔር ነበር፤ መተማመኑም በእርሱ ላይ ነበር። ይህ በመሆኑም ወንጭፉንና ጠጠሮቹን በመያዝ ከጎልያድ ፊት ለፊት ቆሟል።

ስለሆነም ከእግዚአብሔር ጋር መሥራትና እርሱ በምትሠራው ሥራ ውስጥ ከአንተ ጋር እንዲሆን እርሱን መጠየቅ አለብህ ማለት ነው። ሥራ ፈት እንዳትሆን ግን መጠንቀቅ አለብህ፤እግዚአብሔር ሰነፎችን አይወድምና።

አንተ ያለብህ መትከልና ውኃ ማጠጣት ብቻ ነው፤የሚያሳድገው እግዚአብሔር ነውና።

ስለሆነም በትሕትና ውስጥ ሆነህ እንዲህ በል፡- «. . . እንግዲያስ የሚያሳድግ እግዚአብሔር እንጂ የሚተክል ቢሆን ወይም የሚያጠጣ ቢሆን አንዳች አይደለም።» 1ኛ ቆሮ 3:7።

(70)
መንገዳችሁን መርምሩ

በመንገዱ ላይ የሚጣደፍና ምንም ይምጣ ምን መንገዱን መቀየር የማይችል ሰው አለ።

ይህ ሰው መንገዱ የተሳሳተ መሆኑ ከተረጋገጠለትና ውጤቱ ወደማያምር ፍጻሜ የሚያመራ መሆኑ ከተነገረው በኋላ በመንገዱ ላይ ችክ ብሎ ይቆያል።

ሄሮድስ መጥምቁ ዮሐንስን ካስገደለ በኋላ የሠራው ሥራ ትክክል አለመሆኑን እያወቀ ክብሩ እንዲጠበቅለት ያስብ ነበር።

ለእርሱ መንገድን መቀየር ማለት ከብርታትና ከጥብቅነት ጋር አብሮ ሊኀዝ የማይችል ወላዋይነት ነው። እንዲህ ዓይነቱ ችኮነት ይህን በሚያደርጉት ሰዎችና በተከታዮቻቸው ላይ የሚያመጣው ጉዳት ግልጽ ሆኖ እየታያቸው ይህን ጠባያቸውን ሊቀይሩት አይፈልጉም።

እንደነዚህ ያሉት አንዳንድ ሰዎች በዚህ ጠባያቸው ውስጥ ለዘመናት ሊቆዩ ይችላሉ . . . ይህ ጠባይም ለዘመናት የሚኀተት ቅራኔ ወይም ሙግት ሊሆን ይችላል።

ጉዳዩ ያበቃለት ቢሆንም ሰውየው ሊያቆመው አይፈልግም . . . ወይም ደግሞ መጨረሻው ባያምርም ሰውየው ጉዳዩን የማይተወው ግንኙነት አድርጎ ይይዘዋል።

እናንተ ግን መንገዳችሁን በየጊዜው መርምሩ. . .

ሁኔታዎችን፣ አካባቢንና የሚከተሉ ውጤቶችን መገምገም ምንም ስሕተት የለበትም። ሰው ይህን የሚያደርግ ከሆነ ላለፈው ሳይሆን ለአሁን አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይችላል።

የራስን መንገድ መመርመር ጠቢብነት ነው . . .

ቁም ነገሩ አንድ ጉዳይ ላይ መጣበቅ ሳይሆን የተጣበቁበት መንገድ ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጡ ላይ ነው።

ወደፊለጉት ግብ መድረስ የሚቻልበት መንገድ ይህ ነው።

እንዲህ ከሆነ ትኩረት ልትሰጡት የሚገባችሁ ጉዳይ ለግባችሁና ለዓላማችሁ ሊሆን ይገባል። ይህ የሚከናወነው ሊያገኙት የሚሹትን አመቺ ዘዴ በመምረጥ ነው።

በችኮነትና በመወላወል ሕይወታቸውን የሚያባክኑ ሰዎች ብዙ ናቸው።
ሌሎች ደግሞ በዚህ ተመሳሳይና የተሳሳተ መንገድ ላይ ብዙዎችን ከራሳቸው ጋር ያጠፋሉ።

ከላይ የጠቀስናቸው ሁለት ቡድኖች የሚኖሩት ያለ አንዳች መርሆ ሊሆን ይችላል።

እነዚህ ሰዎች የሚደገፉት በራሳቸው አሳብ ነው፤ከዚህ በበለጠም በስሜቶቻቸው ነው። በመሆኑም ሕይወታቸውን የሚያባክኑት በከንቱና ያለ ምንም ጥበብ ይሆናል።

(71)
ከስሕተቶች መጠቀም

ማንኛውም ሰው ለስሕተት የተጋለጠ ቢሆንም ከስሕተቱ የሚጠቀም ሰው ግን ብልኅ ነው። ይህ ሰው ዳግመኛ ኃጢአት እንዳይሠራ መንፈሳዊ ልምድን፣ ዕውቀትንና

ጥንቃቄን ገንዘቡ ያደርጋል። ከአባቶች አንዱ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- «ዲያብሎስ ለተመሳሳይ ኃጢአት ሁለቴ የቀሰቀሰኝን ጊዜ አላስታውስም።»

መንፈሳዊ ሰው በስሕተቶቹ ውስጥ ትሕትናን የራሱ ያደርጋል።

ይህ ሰው ስሕተቱን በመለየትና እንደ ሌሎች ሰዎች እንዴት ለስሕተት እንደሚጋለጥ በማወቅ ከስሕተቱ ይማራል። በመሆኑም አይኮራም ወይም እብሪት አይሰማውም ወይም ራሱን ከሌሎች ልዩ አድርጎ አይመለከትም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ።» (1ኛ ቆሮ 10:12) ብሎ የተናገረው ቃል በእርሱ ሕይወት ውስጥ ተግባራዊ ይሆናል።

እብሪተኛ ሰው ሲወድቅ ስለሚደክም ለውድቀት የማያበቁት ጥፋቶቹን በተደጋጋሚ መሥራቱን ይቀጥላል። በመጨረሻም ይሰላቻል፣ ተስፋ ይቆርጣል፣ ላይነሳም ወድቆ ይቀራል።
ብልኅ ሰው ግን በኃጢአቶቹ ውስጥ ያሉትን የዲያብሎስ ማታለያዎችና ውጊያዎች ይገነዘባል። እርሱ ዲያብሎስ ወደ ሰው ልጆች ነፍስ እንዴት እንደሚገባ እንዴት እርሱን መጠንቀቅ እንዳለበትና እንዴት ትክክለኛ ሰው መሆን እንደሚገባው ይማራል። ይህ ብቻ አይደለም፤አመጣጡንና መንገዱን ይበልጥ እየተረዳ ሲመጣም ሌሎችን ለመርዳት የሚያስችለውን ሁኔታ ያዘጋጃል።

መንፈሳዊው ሰው ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ተናገረ ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን ስለ ሌሎች ሰዎች በሚሆን ኀዘኑ ውስጥ ከስሕተቱ ይማራል። «ከእነርሱ ጋር እንደ ታሰራችሁ ሆናችሁ እስሮችን አስቡ፤የተጨነቁትንም ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እንዳለ ሆናችሁ አስቡ።» ዕብ 13:3።

ስለሆነም አንድ መንፈሳዊ ሰው ሲወድቅ ስለሌሎች ለወደቁ ሰዎች ይበልጥ ኀዘን ስለሚሰማው እነርሱን አይገሥጽም በእነርሱም ላይ አይፈርድም፤እርሱ ራሱ የዲያብሎስን ኃይልና የሰው ልጆችን ደካማ ተፈጥሮ ያውቃልና።

መንፈሳዊው ሰው ለራሱና ለሌሎች በሚያደርገው የጸሎት ልምምድ ውስጥ ከስሕተቱ ይጠቀማል። እርሱ የሰው ልጆች ድል ነሺነት የሚመሠረተው በእነርሱ ኃይልና ብልሃት ላይ ሳይሆን ምንጊዜም ቢሆን ወደ ድል በሚመሩን በእግዚአብሔር ዕርዳታ መሆኑን ጠንቅቆ ያውቃል። ይህ በመሆኑም ሰው «እርዳኝእድናለሁም፤. . .» (መዝ 118:117) እና «አምላካችን ስለ እኛ ይዋጋል፤. . .» (ነህ 4:20) በማለት በጸሎቱ ከእግዚአብሔር ጋር ይጣበቃል።

መጠቀምን የሚሻ ሰው ከራሱም ሆነ ከሌሎች ሰዎች ስሕተት ይጠቀማል።

ይህ በመሆኑም እግዚአብሔር ባጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሌሎችን ስሕተት እንዲጠቀስ አድርጓል። በዚህ መሠረት እኛ እንጠቀምበት ዘንድ የነቢያትና የጻድቃን ስሕተቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲጻፉ ፈቅዷል።

ከዚህ በተጨማሪ «. . . ከብርቱም ውስጥ ጣፋጭ ወጣ. . .» (መሳ 14:14) በማለት ያናገረ አምላካችን እግዚአብሔር ለድኅነታችን ይህን ዘንድ ከእያንዳንዱ ኃጢአት ጠቃሚ ትምህርት ሊሰጠን ይችላል።

በመሆኑም በሕይወታችን ዘመናት ከምናገኛቸው ሰዎች ሁሉ እንጠቀማለን ማለት ነው። ከጻድቅ ሰው ምሳሌ ስንወስድ ከእኛና ከሌሎች ሰዎች ኃጢአት ደግሞ ልምድና ንቃትን ገንዘብ እናደርጋለን።

(72)
ዕድገት

የመንፈሳዊ ሕይወት ጠባያት ከሆኑት መካከል አንዱ የማያቋርጥ ዕድገት ነው።

ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ግኑኙነቱን ንስሐ በመግባት ከጀመረ በኋላ እርሱን ከመፍራት እርሱን ወደ መውደድ ያድጋል። በፍቅር ውስጥ ያለ ዕድገት ለቅድስና እስኪደርስ ድረስ ይቀጥላል። በመጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፦ «ዳሩ ግን፦ እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ።» 1ኛ ጴጥ 1:15-16።

አንድ ሰው የቅድስና ደረጃ ላይ ከደረሰ በኋላ ዕድገቱ ይቆም ይሆን?

አይቆምም! ለፍጹምነት ማዕረግ ጥረት ያደርጋል እንጂ።

በፍጹምነት ጎዳና ላይ ጥረት የሚያደርግ ሰው ማብቂያው ላይ ፈጽሞ ሊደርስ አይችልም። በዚህ ጎዳና ላይ የፈለገውን ያህል ርቆ ቢጓዝም እንኳ የፍጹምነት ወሰን ላይ አይደርስም።

የፍጹምነት ደረጃዎች አሉ። እያንዳንዱ ደረጃም ከሌላው ደረጃ ከፍ ይላል።
ቅዱስ ሰው የነበረው ሐዋርያው ጳውሎስን ተመልከቱት። እርሱ እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ተነጥቋል የተለያዩ ተአምራትና ድንቅ ሥራዎችንም ፈጽሟል።

ይሁን እንጂ እርሱ ይህን ሁሉ ካደረገ በኋላ እንዲህ ነበር ያለው፦ «አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን እንደያዝሁ አይደለም፤ነገር ግን ስለዚያ በክርስቶስ ኢየሱስ ደግሞ የተያዝሁ ያን ደግሞ እይዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ። ወንድሞች ሆይ፤እኔ ገና እንዳልያዝሁ እቆጥራለሁ፤ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴም ወዳለው እየተዘረጋሁ፤በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ።» ፊልጵ 3:12-14።

ይህ ሐዋርያ እንዲህ ያለው የዕድገት አባባሉን የሚያጠቃልለው «እንግዲህ ፍጹማን የሆንን ሁላችን ይህን እናስብ፤. . .» (ፊልጵ 3:15) በማለት ነው።

ከዚህ የምንረዳው ጻድቅ የሆነ ሰው ሁሉ የኋላውን በመርሳት በፊቱ ወዳለው መዘርጋት እንዳለበት ነው።

እግዚአብሔር አምላክ አማኙን ሰው ያነጻጸረው ችግኝ ሆኖ ከሚያድገው የስንዴ ቅንጣት ጋር ነው። እርሱ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ነው ያለው፦ «. . ሌሊትና ቀን ይተኛልም ይነሣልም፤እርሱም እንዴት እንደሚሆን ሳያውቅ ዘሩ ይበቅላል ያድግማል። ምድሪቱም አውቃ በመጀመሪያ ቡቃያ ኋላም ዛላ ኋላም በዛላው ፍጹም ሰብል ታፈራለች።» ማር 4:27-28።

እናንተ ከችግኝ አንስቶ እስከ ዛላ ከዚያም እስከ ሰብል ድረስ ሳያቋርጥ እንደሚያድገው የስንዴ ቅንጣት ናችሁን?

ዕድገት ቀዋይነት ያለው ሙቀትን ስለሚሰጥ ለማደግ ሞክሩ። ዕድገት ቆመ ማለት በልብ ውስጥ ሙቀት የለም ማለት ነው። ይህ ደግሞ ሰብ ወደ ማለት ያመራል።

ለማደግ አለመቻልህ ከታወቀህ ቢያንስ-ቢያንስ የደረስህበት ቦታ ላይ ለመቆም ሞክር፤ወደኋላ ላለመመለስም ተጠንቀቅ።

(73)
የዘገየ አሳብ

አንዳንድ ጊዜ ሰው አንድ ነገር ስለሚያመጣው ውጤት ቀድሞ ሳያሰላስል ሥራውን እንዲሁ ያለ ግንዛቤ ይሠራል።

ሥራው ከተጠናቀቀና ጊዜው ከረፈደ በኋላ ግን ስለ ውጤቱ ሊያስብ ይጀምራል።

እንዲህ ዓይነቱ የዘገየ አሳብ ግን የተሳሳተ ነው።

ሌላው ሰው ደግሞ የተሳለውን ስእለት መክፈል በእርሱ አቅም የሚቻል ወይም የማይቻል መሆኑን ሳያረጋግጥ እንዲሁ ስእለት ይሳላል። ስእለቱን ከተሳለ በኋላ ግን ሊያስብበት ይጀምራል፤ስእለቱን ሊለውጥ ይሞክራል ወይም አለመቻሉን ይፋ ያደርጋል።

ይህ በተገቢው ጊዜ ያልተገለጠ የዘገየ አሳብ ነው።

አንዲት ሴት በተለያዩ የአያያዝ ጉድለቶች ወይም የአንድ ዘመዷን የተሳሳተ ምክር ከተቀበለች በኋላ ፍቅሯ ስለሚቀዘቅዝ ባሏን ታጣዋለች። ከዚህ በኋላ ለእርቅ የሚደረግ ማንኛውንም ጣልቃ ገብነት አትቀበልም። ባሏ ከእርስዋ ጋር የሚሆን ሕይወት የማይቻል የመሆኑ ነጥብ ላይ ሲደርስ እርሷ እርሱን ማጣት የማትፈልግ መሆኗን ልታስብ ትጀምራለች።

ይሁን እንጂ ይህ እጅግ ዘግይቶ የደረሰ የዘገየ ግንዛቤ ነው።

አንድ አባት ልጁን ማሞላቀቅ ለእርሱ ፍቅር እንደ ማሳየት አድርጎ ስለሚቆጥረው ልጁን ማደግ እንደሚገባው ለማሳደግ ይሳነዋል። በመሆኑም ልጁ የማይታዘዝ፣ ንህዝላልና ግዴለሽ ሆኖ ያድጋል። እነዚህ ጥፋቶች በሰብእናው ውስጥ በጥልቀት ስለሚተከሉ በአባቱ፣ በእናቱ፣ በእኅቶቹና በሌሎች ከእርሱ ጋር ግንኙነት ባላቸው ሰዎች ልብ ውስጥ ጥላቻ እንዲፈራ ያደርጋል። ከዚህ በኋላ አባቱ ልጁን የሚያሳድግበትን የአስተዳደግ ስልት ሊቀይርና ጥብቅ ወይም ክስታራ ሊሆን ቢያስብ ይህ የዘገየ አስተሳሰብ ነው የሚሆነው።

ይህ አባት ልጁን በሚገባ ለማሳደግ የተሳነው አሳቡ የዘገየ አሳብ ስለሆነ ነው።
አንድ ሰው መልካም አሳቦች ስላሉት ብቻ ይህ ለእርሱ በቂ ሊሆን አይችልም፤እነዚህ አሳቦቹ ንቁ፣ ከጅምሩ የተስተካከሉና ዕድሉን ሳያጡት በፊት የሚከወኑ መሆን አለባቸውና።

ሰነፎቹ ልጃገረዶች ወደ እግዚአብሔር መብራታቸውን ይዘው የተመለሱት ደጃፉ ከተዘጋ በኋላ ነበር። በመሆኑም እርሱ ወዳለበት ከቶውኑ ሊገቡ አልቻሉም።

በመኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን መጽሐፍ የተጠቀሰችው ልጃገረድ ደጃፏን ለውዷ ልትከፍትለት የተነሳቸው እርሱ ወደመጣበት ተመልሶ ከሄደ በኋላ ነበር። ስለሆነም እንዲህ ብላ ተናገራለች፦ «ለውዴ ከፈትሁለት፤ውዴ ግን ፈቀቅ ብሎ አልፎ ነበር።» መኃ 5:6።

ብዙዎች ዘግይተው ማሰብ ስለ ጀመሩ ሲጠቀሙ አልቻሉም በማያቋርጥ ጸጸትና ኀዘን ውስጥም ኖረዋል:: ይህ የዘገየ አሳብ በዔሳው ላይ ታይቷል:: እርሱ ብኵርናውን በታላቅ ልቅሶና በመራር የንስሓ ዕንባ ውስጥ ቢሻትም እንዴ አምልጣዋለችና ለእርሱ ልትሰጠው አልቻለችም:: ያዕቆብ ከዔሳው በኋላ ቢመጣም ብኵርናውን ሊወስድ ችሏል:: ከዚህ በኋላ ሁሉም ነገር አብቅቷል::

«አምላኬ አምላኬ፤ወደ አንተ እገሠግሣለሁ፤. . .» (መዝ 62:1) እና «. . . ተግተው የሚሹኝም ያገኙኛል::» (ምሳ 8:17) የሚሉት ቃላት ምንኛ ድንቅ ናቸው:: ቃላቱን የተናገሩት ሰዎች ቀድመው የነቁ ናቸው::

(74)
በዓመቱ መጨረሻ

ለአጀማመሩ ሳትዘጋጁ አዲሱ ዓመት ድንገት ደርሶ እንዲያስገርማችሁ አንፈልግም:: ስለሆነም ራሳችሁን ታዘጋጁ ዘንድ ትኵረታችሁን ወደዚህ እንስባለን::

❖ የዚህን ጉዳይ አስፈላጊነት ከልባችሁ ታውቁ ዘንድ በመጀመሪያ ከራሳችሁ ጋር ተቀመጡ:: የምትቀመጡት የነበሩባችሁን ስሕተቶች ለማወቅ ብቻ አይደለም፤ከዚህ የሚልቁትን መሠረታዊ ድካሞቻችሁን፣ ምክንያቶቻቸውንና መገለጫዎቻቸውን ለማወቅ ጭምር እንጂ::

ከራሳችሁ ጋር ከመቀመጥ እንደምታገኙት ውጤት ከሆነ ለንስሓ የተዘጋጃችሁ ትሆናላችሁ:: በተለይም የንስሓችሁን ክፉል ክፍሎች ለመናዘዝ ብቻ ሳይሆን ከሕይወታችሁ ጋር ከተገናኙ ከማናቸውም ጉዳዮች ጋር ለመደራደር ይሁን፤ ከቅርንጫፎቹ ይልቅ ሥሮቹ ይበልጣሉ::

❖ በዓመቱ መጨረሻ ላይ ቀጣዩን ዓመት በሁሉም ነገር የተቀደሰ ለማድረግ ምን መደረግ እንዳለበት እጥኑ:: ከዚህ በኋላ የንጋት ጸሎታችንን የምንጀምርባቸውንና «በጮርቃው ጅምር ደስ ይበለን!» የሚሉትን ድንቅ ቃላት ድገሟቸው::

❖ የክርስቲያንን ሕይወት ጠባያትና መሠረታዊ ጉዳዮች እናጢን እንጂ በዕለታዊ ሕይወታችን ውስጥ የሚታዩትን አፈንጋጭ ጉዳዮች እንመልከት::

በሕይወታችሁ ውስጥ የእግዚአብሔር ፍቅር ማዕከል የሆነው ወዴት ነው ያለው?

የእምነታችሁ፣ የቸርነታችሁ፣ ትሕትናችሁና ተስፋችሁ ወዴት ነው ያለው?

ከእግዚአብሔር ጋር ያላችሁ ግኑኝነት ምንኛ ጥልቅ ነው?

ወደ ጥልቁ ግባ፤በመንፈሳዊነትህ ገለባ አትሁን፤ራስህንም አዋቂ አድርገህ አትገምት::

❖ ሙሉ አንተነትህንና የዕድገትህንም መጠን ተመልከት::

በሕይወትህ ውስጥ ያለው መንፈሳዊ ኀንህ በየትኛው በኩል ሄደ?

የምትከተለው በየዕለቱ የምትሻሻልበትንና ዕድገት የምታመጣበትን ግልጽና ጥብቅ መንገድ ነው?

ወይስ በአንተ ዘንድ ያለው ከተቀደሰው መንገድ የሚያስወጣ ለውጥ ወይም ማስተካከያ ወይም ማፈንገጥ ነው? ወደ አንተ የመጡት አዳዲስ ነገሮች መምጣት ሳይገባቸው ነው የመጡት::

❖ ከራሳችሁና ከእግዚአብሔር ጋር ስትቀመጡ ለእናንተ የምሰጣችሁ መሪ ምክሮች የሚከተሉት ናቸው::

ሙሉ ለሙሉ ታማኞች ሁኑ::

ምክንያቶች በመፈለግና ወቀሳውን ሁሉ በሌሎች ሰዎች ወይም በአጋጣሚዎች ላይ በማሳበብ ራሳችሁን ነጻ አታውጡ!

በፍርድ ቀን እግዚአብሔር ስለ ሌሎች ሰዎች ወይም ስለ አጋጣሚዎች አይጠይቃችሁም:: የሚጠይቃችሁ ስለ ራሳችሁ ብቻ ነው::

ስለዚህ ወደ ራሳችሁና ወደ ራሳችሁ ብቻ ጠልቃችሁ ግቡ እንጂ ሌላ አታድርጉ::

(75)
በጥቂቱ የታመነ

በጥቂት ነገር ላይ የምትታመን ከሆንህ እግዚአብሔር በብዙ ነገር ላይ ይሾምሃል::

ልታደርገው በምትችለው ነገር ላይ ታማኝ ከሆንህ እግዚአብሔር ልታደርገው በማትችለው ነገር ላይም ይሾምሃል::

ከነቃህ በኋላ አሳቦችህን በመቆጣጠር ታማኝ ሁን:: በዚህ ታማኝ ሆነህ ከተገኘ ህ እግዚአብሔር ያለ ፈቃድህ በሚመጡብህና ልትቆጣጠራቸው በማትችላቸው ሕልሞች ላይ ይሾምሃል::

በአንድ ተሰጥኦህ ላይ ታማኝ ሆነህ ከተገኘህ እግዚአብሔር በአሥር ተሰጦኦች ላይ ይሾምሃል::

ከውጭ በሚመጡ ውጊያዎች ላይ ታማኝ ሆነህ ከተገኘህ እግዚአብሔር ከውስጥ በአሳቦችህና በልብህ በሚፈሱ መንፈሳዊ የተመሰጠ ምንጮች ላይ ይሾምሃል::

በልያ ላይ የምትታመን ከሆንህ እግዚአብሔር ራሔልንም ይጨምርልሃል:: ለአጋር ልጅ ርኅራኄ ካሳየህ እግዚአብሔር የሣራን ልጅ ይሰጥሃል:: ራስህን ከሲና በረሀ ካወጣህ እግዚአብሔር ወደ ምድረ ከንዓን እንድትገባ ያስችልሃል::

በጲጥፋራ ቤት ላይ ታማኝ ሆነህ ከተገኘህ እግዚአብሔር በፈርዖን ቤተ መንግስትና በግብጽ ሀብት ላይ ሁሉ ይሾምሃል::

በአርጤክስስ ቤተ መንግሥት ውስጥ ታማኝ ስትሆን እግዚአብሔር እንደ ነህምያ ቤተ መቅደሱን ኢየሩሳሌም ውስጥ እንድታንጽ ይሾምሃል::

ለእግዚአብሔር በሚታዩ ነገሮች ላይ ታማኝ ከሆንህ እግዚአብሔር በማይታዩ ነገሮችም ላይ ይሾምሃል:: በዚህም ዐይን ባላየው፣ ጆሮ ባልሰማውና በሰው ልብ ባልታሰበው ከተማ ላይ ይሾምሃል::

እግዚአብሔር ታማኝነትህን በማንኛውም ነገር ላይ ሊፈትን ይችላል:: ፈተናው አንድ ቀላል ትእዛዝ መጠበቅ ወይም ከአንዲት ፍሬ መከልከል ሊሆን ይችላል::

በእውቀት ዛፍ ላይ ታማኝነትህ ከተረጋገጠ እግዚአብሔር በሕይወት ዛፍና ከሰማይ በወረደው መና ላይ ይሸምሃል::

ያሉህን መክሊቶች አሳንሰህ አትመልከት:: ይልቁንም ባሉህ መክሊቶችህ ላይ ታማኝ ሆነህ ተገኝ:: እግዚአብሔር የሚመለከተው ያሉህን መክሊቶች ማነስ ወይም መብዛት አይደለም!ባሉህ መክሊቶች ላይ ታማኝ ሆነህ መገኘትህን እንጂ::

የኤል ፋዮም ጳጳስ የሆነው አባ አብራም በምሕረት ሥራዎቹና በነበረው ገንዘብ ሁሉ ላይ የታመነ ሰው ስለ ነበርና እግዚአብሔር በበዛ ምሕረት ላይ ስለ ሾመው የታመሙትን ድውያን ይፈውስና አጋንንትን ከሰዎች ያስወጣ ነበር::

(76)
ሙሉው እውነት

ስለ እግዚአብሔር ፍቅር የሚደረግ ንግግር ቢያስደስታችሁም ስለ ፍርዱ የሚደረግ ንግግር ግን ሊረብሻችሁ ይችል ይሆናል:: ያም ሆነ ይህ ግን ሙሉውን እውነት ልትጋፈጡት ግድ ነው::

የእግዚአብሔርን ፍርድ ከፍቅሩ የማይነጥለው እውነት መለኮታዊ እውነት ነው::

የእግዚአብሔር ፍርድ መሐሪ ሲሆን ምሕረቱ ደግሞ እውነት ነው::
የእግዚአብሔር ፍርድ በምሕረቱ የተሞላ ሲሆን ምሕረቱም በፍርዱ የተሞላ ነው::

ሁለቱ በአንድ ላይ ሙሉው እውነት ወይም አጠቃላዩ እውነት ነው::

ግማሽ እውነት ይዘን በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ልናስመስል አንችልም::

ስለ ተስፋ የተጻፉ ጽሑፎች ሊያፍለቀልቋችሁ ይችላሉ:: ስለ ጽድቅ፣ ስለ ንጽሕና፣ ስለ ትእዛዛትና ከአንተ ስለሚጠበቁ ነገሮች የተጻፉ ነገሮች ግን ሊያውኳችሁ ይችላሉ::

ሰማሃቸውም አልሰማሃቸውም ስለ ንጽሕና የሚነገሩ ንግግሮችን የተፈለገውን ያህል ከአንተ ለማራቅ ብትሞክርም ገንዘብህ እንድታደርገው ይጠበቅብሃል:: ሙሉውን እውነት በዐይኖችህ ፊት ልታኖረው ግድ ነው:: ለዳዊት በዐይኖቹ ፊት እንደ ብርሃን በሆነለት በእግዚአብሔር ትእዛዝ ደስ ይበላችሁ::

ቢያደሳድላችሁም ሆነ ቢያስለቅሳችሁ ሙሉውን እውነት ልታውቁትና ልትጋፈጡት ግድ ነው::

ትእዛዝ በዐይኖቻችሁ ፊት አስቸጋሪ መስሎ ቢታያችሁም ተጋፈጡት:: ተግባራዊ ታደርጉት ዘንድ የሚያግዛችሁ በውስጣችሁ ያለው ጸጋ እግዚአብሔር ነውና::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉውን እውነት ከእኛ ጋር ተከትሏል:: እንዲህ ብሎም ነግሮናል:- «በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ!. . .»:: ይህ ግማሹ እውነት ሲሆን ቀሪው ግማሽ እውነት ደግሞ «. . . ነገር ግን አይዞአችሁ!እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ::» (ዮሐ 16:33) የሚለው ነው::

የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ጠቃሚ ቢሆንም ሙሉ እውነት የሚሆነው ግማሽ የሆነው የእኛ እውነት ከእርሱ ጋር በሥራ በመተባበር ሲገለጥ ነው::

ግማሹ እውነት በክርስቶስ ለእኛ የተሰጠው ታላቁ ድኅነት ሲሆን ሌላው ግማሽ እውነት ደግሞ ይህን ታላቅ ድኅነት ገንዘብ ማድረግ መቻል ነው::

ከፊሉ እውነት የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችን ነው:: ሌላው ከፊል እውነት ደግሞ ከእግዚአብሔር ከተወለዱ በኋላ ኃጢአት አለመሥራት ነው፤ሙሉው እውነት ይህ ነውና::

(77)
ንስሓ ስለ መግባት

ንስሓ መግባት ማለት ተቀምጦ ታሪክ መተረክ ማለት አይደለም:: ስላጠፋኸው ጥፋት ምንም ሳትናገር ከሰዎች ጋር ለረዥም ጊዜ ወግህን ልታወጋ ትችላለህ::

ንስሓ ማለት በራስ ላይ መፍረድ ማለት ነው::

ንስሓ ማለት ካህኑ እያደመጠህ በእግዚአብሔር ፊት ራስህን መርገም ማለት ነው::

ይህንንና ያን በማድረግ ኃጢአት ሠርቼያለሁ በማለት ትናገራለህ::

ንስሓ ማለት ሌሎች ሰዎችን ማማረርና የእነርሱን የተሳሳቱ ሥራዎች ለራስህ ማቅረብ ማለት አይደለም!ራስህን መውቀስ እንጂ::

ስለሆነም ንስሓ መግባት ማለት ከንስሓ አባትህ ጋር ተቀምጠህ እርሱ ሳይጠብቅህ ስለ ዘነጋህ ወይም ስላልመራህና ጉዳይህን ስላልተከታተለልህ ወይም ስላልጠየቀህና ማንኛውንም መንፈሳዊ መመሪያ ስላልሰጠህ እርሱን ማማረር ወይም መውቀስ ማለት አይደለም:: ይህን ሁሉ ስታደርግ በራስህ ላይ እየፈረድህ ወይም ስሕተቶችህን እየገለጥህ አይደለህም:: በእርግጥም በዚህ ጊዜ እየፈረድህ ያለኸው በንስሓ አባትህ ላይ ነው::

ንስሓ ማለት ካረጁ ኃጢአቶችህ ነጻ ወጥተህ ምንም ዓይነት መንፈሳዊ ለውጥ ሳታመጣ አዲስ ኃጢአቶች ላይ መውደቅ ማለት አይደለም::

ኃጢአትን መናዘዝ ማለት ንስሓ መግባት ማለት ስለሆነ ምስጢሩ ምስጢረ ንስሓ ተብሎ ተጠርቷል::

ንስሓ መግባት ማለት አንድ ነገር ለማድረግ በልባችሁ ከወሰናችሁ በኋላ የንስሓ አባታችሁ በወሰናችሁት አሳብ ላይ ከእናንተ ጋር እንዲስማማ መጠየቅ ማለትም አይደለም:: ይህ ካልተሳካላችሁ ስለምትበሳጩ የእርሱን ማረጋገጫ ለማግኘት አጥብቃችሁ ትወተውቱታላችሁ:: ይህን ስታደርጉም እንደ ፈቃዳችሁ ሳይሆን እንደ ንስሓ አባታችሁ ፈቃድ እንደምታደርጉት ለማስመሰል ትጥራላችሁ::

ንስሓ ማለት ራሳችሁን በትሕትና በማዋረድ ጉዳያችሁን መግለጽና መመሪያ መቀበል ማለት ነው።

ንስሓ ማለት ከካህኑ ጋር በባልንጀራነት በማንኛውም ሥፍራ መቀመጥ ማለት አይደለም። ንስሓ ማለት ከካህኑ ጋር የመነጋገርና እርሱ ዕውቀቱን ተጠቅሞ እናንተ የወደቃችሁበትን ኃጢአት እንዲገምት መተው ማለትም አይደለም።

ንስሓ የራሱ ክብር ያለው ቅዱስ ምሥጢር ነው። ንስሓን ተግባራዊ ስታደርጉ የሠራችሁት ሥራ ይወቅሳችኋል። ስለሆነም ካህኑ እየሰማችሁ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአቶቻችሁን ትናዘዛላችሁ።

ንስሓ ማለት ጥፋቶቻችሁንና ድካሞቻችሁን ሙሉ ለሙሉ መርምሮ ለማወቅ በመጀመሪያ ከራሳችሁ ጋር የምትቀመጡት መቀመጥ ነው። ከዚያም ራሳችሁን ከወቀሳችሁ በኋላ የእግዚአብሔርን እርዳታ በመጠየቅ የጽድቅ ሕይወት ለመምራት ወስኑ።

ከዚህ በኋላ ወደ ንስሓ አባታችሁ ስትመጡ የተጸጸተ ልባችሁን ይዛችሁ ትመጣላችሁ። ከዚያም ስሕተታችሁን ትነግሩታላችሁ፤ይቅርታና ዕርቅ ትጠይቁታላችሁ፤ ለእናንተ የሚበጅ ምክርና መመሪያ እንዲሰጣችሁ ታሳስቡታላችሁ፤ እንዲጸልይላችሁም ትማጸኑታላችሁ።

(78)
የጥምቀት በዓል ተመስጦ

አዳም ከበደለ በኋላ ይቅርታ አልጠየቀም፤ይቅርታንም አልፈለገም።

ምንም በደል የሌለበት ቅዱሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን አዳምንና የልጅ ልጆቹን በመወከል እንደ በደለኛ በመጥምቁ ዮሐንስ ፊት ቆሟል። ኢየሱስ ክርስቶስ የቆመው ለእነዚህ ሰዎች ነው። ይህ ደግሞ በንስሓ ጥምቀት ውስጥ የላቀ ግርማ ያለው ጥምቀት ነው።

እርሱ የሰው ልጆችን ኃጢአት የተሸከመው በተሰቀለ ጊዜ ብቻ አይደለም፤የሰው ልጅ ሆኖ በኖረበት ዘመን ሁሉ እንጂ። ስለሆነም እግዚአብሔር አብ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ተደሰተ እንዲህ በማለት ተናግሯል፡- «. . . በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው።» ማቴ 3:17።

አንድ ሰው ለራሱ ሲፈርድና እንደ አዳምና እንደ ሔዋን ለራሱ ሰበብ ሲፈልግ ማየት እግዚአብሔርን አያስደስተውም። አዳምና ሔዋን ግን በእግዚአብሔር ፊት በራሳቸው ላይ መፍረድ ሲገባቸው ነው ሌላውን መውቀስ የጀመሩት።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ማንንም አልወቀሰም። ይልቁንም የሌላውን ኃጢአት ተቀብሏል፤በእርሱ ፋንታ በደሉን ተሸክሟል። ስለሆነም «. . . በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው።» (ማቴ 3:17) ብሎ የተናገረው አባቱን አስደስቷል።

ኃጢአት የሌለበት እርሱ የእኛን ኃጢአት ተሸክሟል ማለት ነው። አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአተኞች ጋር ተሰልፎ ከቀረበ በኋላ አገልጋዩ መጥምቁ ዮሐንስ እንዲያጠምቀው ለመጠየቅ አላፈረም። ታላቁ ነቢይ በዚህ ጉዳይ አፍረት ቢሰማውም ክርስቶስ በትሕትና እንዲህ ነበር ያለው፡- «. . . አሁንስ ፍቀድልኝ፤እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ዘንድ ይገባናልና. . .» ማቴ 3:15።

እርሱ ይህን በማድረግ ተግባራዊ ምሳሌ አሳይቷል። የሌሎችን ኃጢአት ስለ መሸከምም ትምሕርት ሰጥቷል።

እርሱ የእነርሱን ዋጋ የከፈለው በደስታ ነው።

የተፈለገውን ያህል የዋሆች ብንሆንም ለራሳችን እንፍረድ።

ይህን በማድረግም ጽድቅን ሁሉ እንሞላለን።

ይህን ቅድስና ገንዘብ ለማድረግ ራሳችሁን ታለማምዳላችሁ?

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- «የሌሎችን ኃጢአት መሸከም ካልቻልህና ከራስህ ጋር የምታነጻጽራቸው ከሆንህ ቢያንስ-ቢያንስ በሌላው ላይ በመፍረድ እርሱ የአንተን ኃጢአት እንዲሸከም አታድርገው።»

የሌሎች ሰዎችን ኃጢአት መሸከም ቢያቅተን እንኳ ወደ እኛ ለመቅረብ በሚያደርጉት ጥረት ውስጥ ያሉ ውድቀቶቻቸውን በማሰብ ቢያንስ-ቢያንስ ይቅርታ ልናደርግላቸው እንሞክር።

እንዲህ ባለ አካሄድ ክርስቶስን እንመስላለን፤የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ለመጠራትም የበቃን ሆነን እንገኛለን። ከሰዎች ጋር በምንስማማበት ይህን በሚመስል ርኅራኄያችንም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ይስማማል።

(79)
ዓመፅ ወይስ ጥብቅነት

ብዙ ሰዎች በጠባያቸው ውስጥ ዓመፅን ከጥብቅነት ጋር ይቀላቅላሉ።

አስፈላጊ ሲሆን ጥብቅነት መልካም ቢሆንም ዓመፅ ግን የተጠላና የማይወደድ ነው።

ሮብዓም ከሽማግሌዎቹና አብረውት ካደጉት ብላቴናዎች ጋር በተማከረ ጊዜ ሽማግሌዎቹ በጎውንና መልካሙን አቋም ይዞ እንዲገኝ ሲመክሩት ብላቴናዎቹ ባልንጀሮቹ ግን ዓመፀኛ እንዲሆን መከረውታል። እርሱ የዓመፅን አሳብ ስለ ተቀበለ ብዙ ከስሯል መንግሥቱም ተበትኗል። 1ኛ ነገ 12:6።

ይህ በመሆኑም ሮብዓም የተከተለው አመራር (ፖሊሲ) ውድቅ ሆኗል።

እግዚአብሔር የፈርዖንን ዓመፅ በመቃወም ቆሞአል። ከዚህ ዓመፅ የተነሣ የሕዝቡ ልቅሶና ዋይታ በእግዚአብሔር ስለ ተደመጠ ከመከራ አድኗቸዋል።

ዔሳውና ያዕቆብ ወንድማማቾች ነበሩ። ዔሳው የዓመፅ ምሳሌ ሲሆን ያዕቆብ ግን የመልካምነትና የጨዋነት ምሳሌ ነበር። ይህ በመሆኑም እግዚአብሔር ያዕቆብን ገና ከመወለዱ አስቀድሞ እንደ ወደደው መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክርልናል።

ዓመፀኛ ወይም ጠበኛ ሰው በልቡ ውስጥ ጭካኔ ሲኖር መልካሙ ሰው ተለይቶ የሚታወቀው ግን በርኅራኄው፣ በፍቅሩና በደግነቱ ነው።

ዓመፀኛ ሰው ዓመፁን የሚደግፍለት ውስጣዊ ትዕቢት በእርሱ ዘንድ ሊኖር ይችላል። ጨዋው ሰው ግን በመንገዶቹ ሁሉ ላይ አብዝቶ ትሑት ነው።

እግዚአብሔር አምላክ ትሕትናን እና የዋህነትን ያወደሰው እንዲህ በማለት ነው፡- «. . . ከእኔም ተማሩ፤እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፤. . .» ማቴ 11:29።

ዓመፅ ሰዎችን በኃይል እንድትቆጣጠራቸው ስለሚያስችልህ እነርሱን ጸጥ ልታሰኛቸው ትችል ይሆናል። ይሁን እንጂ ፍቅራቸውን ፈጽሞ ሊያስገኝልህ አይችልም።

እነርሱን ስለ መፍራት ሌሎችን እንዳይጎዳ ዓመፅን ተጠቅሞ ክፉውን ማራቅ ተገቢ ጉዳይ ነው። ከጸጥተኞቹና ከጨዋዎቹ ጋር ለመስማማት ሲባል ዓመፅን መጠቀም ግን ተገቢ ጉዳይ አይደለም። ዓመፅ ፈጥኖ ለሚሰማቸው ሰዎችም ሙሉ ለሙሉ አስፈላጊ ጉዳይ አይደለም።

ዓመፅ ለብልኅ ሰው ሁሉም ትክክለኛ መንገዶች ውድቅ ሲሆኑ የሚቀርብ አማራጭ ነው።

ዓመፅ የተፈጥሮው አንድ ክፍል በሆነበት ዓመፀኛ ሰው እና ሙሉ ለሙሉ ጸጥተኛ ሆኖ ሁሉም አማራጮች ሳይሠሩ ሲቀሩና አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ ብቻ ዓመፅ ውስጥ በሚገባ ሰው መካከል ከፍተኛ ልዩነት አለ። እንዲህ ዓይነቱ አሠራር ጥብቅነት ይባላል።

አንዳንድ ጊዜ ጥብቅነት ከዓመፅ ጋር ይኖራል. . .

(80)
ሁለቱ ደረጃዎች

በቅድስና ሕይወት ውስጥ ደረጃዎች አሉ። አሁን የምንመለከተው ሁለቱን ሲሆን እነርሱም፡-

መንፈሳዊ ደረጃና ማኅበራዊ ደረጃዎች ናቸው።

በመንፈሳዊነቱ የተከበረ ሰው በማኅበረሰቡም ዘንድ የተከበረ መሆን አለበት። ይሁን እንጂ ማኅበራዊ ሰው የግድ መንፈሳዊ ሰው መሆን የለበትም።

ማኅበረሰባዊው ሰው በዙሪያው ያሉ ሰዎችን ፍቅር ሊያገኝ ቢችልም መንፈሳዊው ሰው ግን እርሱ ባገኘበት መንገድ ይህን ፍቅር ላያገኝ ይችላል፤ያኛው ይህን ፍቅር የሚያገኘው በቀልድ ወይም በማዝናናት ወይም በፌዝ ወይም በውሸት ነውና።

እርሱ ሌሎችን ሊረዳ የሚችለው የመንፈሳዊው ሰው ኅሊና ሊቀበላቸው በማይችላቸው ዘዴዎች ሊሆን ይችላል።

ይህም ማለት ማኅበራዊው ሰው ሰዎችን ገንዘቡ የሚያደርገው መንፈሳዊ ባልሆኑ ዘዴዎች መንገድ ነው።

መንፈሳዊው ሰው ሰዎችን ገንዘቡ ሊያደርግ ቢወድም እግዚአብሔርንና ንጽሕናውን በማያሳጣው መንገድ ነው።

ስለሆነም ብቁ የሆነውንና ብቁ ያልሆነውን በመለካት ውስጥ ልዩነቶች አሉ።

ከምንም ነገር በላይ የመንፈሳዊው ሰው ዓላማ ሰዎችን የራሱ ገንዘብ ማድረግ አይደለም፤የእግዚአብሔር እንጂ። ለእርሱ መንፈሳዊ ዘዴው እንደ መንፈሳዊነቱ ታላቅ ነው።

አሳቢ ሰው ግን ሁለቱን አንድ ላይ ያቀናጃል።

እርሱ በማኅበራዊው መንገድ ስኬታማና በሁሉም ተወዳጅ ነው። በተመሳሳይ ጊዜ የሚጠቀመው ደግሞ ትክክለኛውንና ጥፋት የሌለበትን መንገድ ነው።

መንፈሳዊው ሰው እንደበቱ እንዳይሳሳት ለራሱ ዝምታን ማለማመድ ቀላል ነው። ከዚህ የሚበልጠው ግን ያለ ምንም ስሕተት ቀና የሆነውን ቃል እየተናገረ ሰዎች ከእርሱ ጠቃሚ ቃላትን እንዲያገኙ ማድረግ የሚችለው መንፈሳዊ ሰው ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ጥበበኛ ተናጋሪ ስለሆነ ሰዎች በንግግሩ ይደሰታሉ።

ለመንፈሳዊው ሰው ከቀልድ ተቆጥቦ ሁልጊዜ ኮስታራ በመሆን መኖር በጣም ቀላል ነገር ነው። ከማይቋረጥ ኮስታራነቱ ጋር ተስማምተው ሊኖሩ የሚችሉት ግን ጥቂቶች ናቸው። እነዚህ ሰዎች ሊመለከቱ የሚፈልጉት መንፈሳዊ ሰው በፈገግታ የተሞላውንና ደስተኛውን መንፈሳዊ ሰው ነው። እነርሱ የሚሹት ከእርሱም ሆነ ከእነርሱ ስሕተት ሳይኖር ከእነርሱ ጋር የሚስቀውን መንፈሳዊ ሰው ነው።

መንፈሳዊ መሆን ማለት ሰዎችን የማያናግር መቃብር መሆን ማለት አይደለም።

መንፈሳዊነት ከማኅበረሰቡ መገለልና ከጥፋቱ ጋር የሚያደርገው ነገር የለውም። ይህ ባይሆን ኖሮ ሃይማኖት ለማኅረሰቡ የሚያደርገው መልካም ነገር አይኖርም ነበር. . .

ከማኅበረሰቡ ጋር መስማማት የመንፈሳዊነት አንዱ ጎን ነው። ይህ ደግሞ ከማኅበራዊነት የሚልቅ ከፍተኛ ደረጃ ነው። አንዳንዶች ይህን ደረጃ ዝቅ አድርገው ማስቀመጣቸው ግን ብልኅነት አይደለም፤ይህ የራስ ወዳድነት አንዱ ክፍል ነውና።

(81)
ጥቂትና ብዙ

ታዋቂ ከሆኑት አባባሎች መካከል አንዱ፡- «ቋሚ የሆነው ጥቂት ብዙ ከሆነው የተዛባ ነገር ይበልጣል።» የሚለው ነው።

ይህ አባባል ለመንፈሳዊ ሕይወትም መልካም ነው።

ብዙ ሰዎች ከአቅማቸው በላይ በሆነ በጣም ፈጣንና ከባድ በሆነ እርምጃ ነው የሚጀምሩት። ይሁን እንጂ በዚሁ ሊቀጥሉ ስለማይችሉ ያፈገፍጋሉ።

የዚህ ውጤቱም ኀዘንና ተስፋ መቁረጥ ነው የሚሆነው።

ትክክለኛው መንፈሳዊ አቅጣጫ የሚጠቁመን ማንም ሰው በተገኘው ነገር ሁሉ እንደ አቅሙ መጠን እንዲጀምር ነው። ምክንያቱም ጥቂት የሆነው ቋሚ ነገር ለመንፈሳዊ ሕይወት መረጋጋትን ስለሚያድል ነው።

ግራ በመጋባት ምክንያት ጥብቅ ሆነው የማይቀጥሉም ብዙዎች ናቸው። ይህ ደግሞ የሚያረጋግጥልን በጥበብ የተሞላ ምክርን የመከተልና የማደራጀት ጉድለት መኖሩን ነው።

በመካከለኛ ሁኔታ የሚጸም ሰው ከፍተኛው የመንፈሳዊነት ደረጃ ላይ እስኪደርስ ድረስ ቀስ በቀስ እያደገ ይሄዳል:: ይህ ደግሞ ሊቀጥሉበት ከማይችሉት ከከፍተኛው ደረጃ ከጀመሩ በኋላ ምንም የጀመሩ እስከማይመስል ድረስ ቀስ በቀስ እየተንሸራተቱ ወርደው ከሚወድቁበት ደረጃ ይሻላል::

«ጥቂት» ስንል በችሎታችሁ ውስጥ ያለውን ጥቂት ነገር ነው እንጂ በስንፍናችሁ ውስጥ የምታገኙትን ጥቂት ነገር ማለታችን አይደለም::

እግዚአብሔር ጥቂቱን ባርኮ የማሳደግ ችሎታ አለው. . .

በመንፈሳዊነትህ ውስጥ ጥብቅ በሆነው ምድር ላይ መራመድ አለብህ:: የምትራመደው እርምጃ ምላሽ ያለው መሆን አለበት:: ይህን እርምጃ ተራምዳችሁ ካለፋችሁ በኋላ ቀጣዩን ተመሳሳይ እርምጃ ትራመዳላችሁ:: ምንጊዜም ታዲያ ከእያንዳንዱ እርምጃ ልምድ ትወስዳላችሁ::

(82)
ጥቅም

ብዙዎች የሚጠቅምን ቃል ይጠይቃሉ:: ለመሆኑ ሁሉም ከቃሉ ተጠቃሚዎች ናቸው?

ጥቅም ያለ ምንም ጥርጥር ሁለት መገኛዎች አሉት!. . .

የመጀመሪያው ቃሉ ለማነጽ መልካም መሆኑና ጠቃሚነቱ ሲሆን!ሁለተኛው ደግሞ ቃሉን የሚያዳምጠው ሰው የሚጠቀም ዓይነት መሆኑ ነው::

ለመጠቀም የሚወድ ሰው ከቁጣ ቃል ወይም ከከባድ ቃል ወይም ለሌላ ሰው ከተነገረ ቃል ይጠቀማል::

አባቶቻችን በኖሩበት ዘመን ለሰዎች የተናገሯቸውን ቃላት እስከ ዛሬ ድረስ እኛን እየጠቀሙን ነው::

ጥቅም የሚሰጡ ቃላት ሊገኙ የሚችሉ ናቸው:: እኛ በታማኝነት ከፈለግናቸው በአጠገባችን ይገኛሉ:: ሕይወትን ለሚሹ ሁሉ መጻሕፍት ጥቅም በሚሰጡ ቃላት የተሞሉና በሕይወት ውስጥ የሚንቆረቆሩ መሪ አንደበቶች ናቸው::

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥቅም የሚሰጡ ቃላትን ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት አለቆች ሁሉ ከተናገረ በኋላ ወዲያውኑ እንዲህ ነው ያለው:- «. . . ጆሮ ያለው ይስማ::» ራእይ ምዕ. 2 እና3::

ጥቅም የሚሰጥ ቃል የሚሰማ ጆሮ፣ የሚጠቅም ፍቅርና ከዚህ ፍቅር ጋር የሚተባበር ውጤታማ ፈቃድ ይፈልጋል::

ጥቅም የሚሰጡ ቃላትን ማወቅ ብቻ በቂ አይደለም:: «ብዙ ከሚያውቅ ብዙ ይጠበቅበታል::» ከሚለው አባባል አንጻር እውቀት በራሱ ፍርድ ነው:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሰዎች ላይ የሚፈርዱ ሰዎች በፈረዱት ፍርድ እንደሚፈረድባቸው ሲናገር «ስለዚህ አንተ የምትፈርድ ሰው ሁሉ ሆይ፤ የምታመካኘው የለህም፤በሌላው በምትፈርድበት ነገር ራስህን ትኰንናለህና፤ አንተው ፈራጁ እነዚያን ታደርጋለህና::» ሮሜ 2:1::

አንዳንዶች ክርስቶስን ቢሰሙትም በሰሚቸው ቃላት ተጠቃሚዎች ሊሆኑ አልቻሉም:: አንዱ እንዲያውም ስለ ሀብቱ ሲል እያዘነ ትቶት ሄዷል::

ብዙዎች ቃሉን ቢወዱትም ተግባራዊ አላደረጉትም::

ሌሎች ቅዱስ ጳውሎስን ከሰሙት በኋላ «. . . ይህ ለፍላፊ ምን ሊናገር ይወዳል?» (ሐዋ 17:18) ብለውታል:: ይህን በማለታቸውም ከቅዱስ ጳውሎስ ንግግር ሊጠቀሙ አልቻሉም:: በዚህ ቦታ ላይ ጥቅም የሚሰጥ ቃል ቢኖርም ያለ ምንም ጥቅም ነው የቀረው::

እናታችን ሔዋን ከእግዚአብሔር ቃል ብትሰማም በቃሏ ተረጎመችው እንጂ አልተጠቀመችበትም:: በእርግጥም የወደቀችው ወዲያውኑ ነው::

ሰዎች የሚጠቅሙ ቃላትን ይጠይቃሉ:: ለመሆኑ ጥቅም በንግግር ብቻ ይገኝ ይሆን?

(83)
ሥርዓቶች

ብዙ ሰዎች በአምልኮታቸውና ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት ውስጥ ይበልጥ ትኩረት የሚሰጡት ለሥርዓቶች ስለሆነ ፍሬ ነገሩን ይረሱታል::

ለምሳሌ:- በጸሎት ጊዜ ከእግዚአብሔር ፊት ቆመው ከእርሱ ጋር ሲነጋገሩ ትኩረት የሚሰጡት ለቃላቱና ቃላቱ ለላቸው ርዝመት ነው:: ጸሎት ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኝ ድልድይ ከመሆኑ አንጻር ይህ ሥርዓት ብቻ ነው፤ይህ በመለኮታዊው አምላክ ፊት የመቆም ስሜት ነውና::

በጾም ውስጥ አንዳንዶች የሚያተኩሩት ሳይመገቡ በሚቆዩበት ጊዜ ርዝመትና በሚመገቡት የምግብ ዓይነት ላይ ነው::

የጾም ፍሬ ነገር በአብዛኛው ራስን የመጠበቅ፣ የማሸነፍና የመቆጣጠር መመሪያ ከመሆኑም ሌላ ሥጋን ከቁሳዊውና ከመብል ደረጃ በላይ ከፍ ማድረግ ነው:: ብዙዎችን የሚያልፋቸው ይህ ነው::

ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል በሚደረግ ዝግጅት ውስጥ ብዙዎች አብዝተው ትኩረት የሚሰጡት ሰውነታቸውን ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ በውኃ ለማንጻት ነው እንጂ ስለ አካላዊ፣ ስለ መንፈሳዊና ስለ ንጽሕና ፍሬ ነገር ትኩረት በመስጠት አይደለም::

መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብም ቢሆን የአንዳንድ ሰዎች ትኩረት በሚያነቡት ንባብ ብዛትና በየዕለቱ በሚያደርጉት ድግግሞሽ ላይ ብቻ ነው:: ይህ ሥርዓት ነው:: የንባብ ፍሬ ነገር ግን በመረዳትና በተመስጦ ማንበብ ነው:: እንዲህ ያለው ንባብ ከትርጉም አልፎ የሚሄድ ከመሆኑም በላይ የንባብን ድርጊት ወደ መንፈስና ወደ ሕይወት የሚለውጥ ነው::

አንዳንድ ሰዎች ወደ ምንኩስና ሕይወት ከገቡ በኋላ ጥንቃቄ የሚወስዱት በውጭ ለሚታዩት ነገሮች ማለትም ስለ ስግደትና ስለ ቁጥሩ ብዛት፤ስለ ጾምና ለረዥም ሰዓታት ያለ ምግብ ስለ መቆየት፤ራሳቸውን በአንድ በአት ውስጥ ቆልፈው ለማስቀመጥና የለበሱትን እስኪረሱ ድረስ በዝምታ ውስጥ ለመኖር ነው:: ከውስጥ የሆነው የልብ ንጽሕና ግን በእውነት ለዓለም መሞት ሲሆን የምንኩስና ዓላማውም ለሥርዓቶች ትኩረት መስጠትን በመተው ከእግዚአብሔርና ከፍቅሩ ጋር መኖር ነው::

ብዙ ጊዜ ስለ ሥርዓቶች ሲባል አገልግሎት ይጠፋል:: ትኩረታችን ሙሉ ለሙሉ የሚውለው ምን ብለን እንደምንናገር በማሰብ ላይ ብቻ ይሆናል:: የምንናገረው

ቃል ውጤቱ የሰዎችን ልብ በመለወጥ ወደ እግዚአብሔር ፍቅር ለመምራት መሆኑ በብዙዎች ዘንድ ይዘነጋል። እነዚህ ሁሉ የሥርዓት ዓይነቶች ናቸው። በአገልግሎት ውስጥ ያለውና ጥልቀት የሚሰጠው የአገልግሎት ዓላማ ነፍሳትን ማዳን ነው። ስለሆኑ ይህ ወዴት ነው የደረሰው?!

ሥርዓቶች የእግዚአብሔርን መንግሥት ፈጽሞ አይገነቡም። ይህ ደግሞ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለጻፎችና ለፈሪሳውያን የተናገረውን ቃል ያስታውሰናል፦ «. . . በውስጡ ቅሚያና ስስት ሞልቶ ሳለ የጽዋውንና የወጭቱን ውጭ ስለምታጠሩ ወዮላችሁ።» ማቴ 23:25። ጌታ እነርሱን ያመሳሰላቸው በውጭ አምረው ውስጣቸው በርኩሰት ከተሞሉ መቃብሮች ጋር ነው።

እግዚአብሔር ለሥርዓቶች ትኩረት ስለማይሰጥ «ልጄ ሆይ፤ ልብህን ስጠኝ፤» (ምሳ 23:28) በማለት ተናግሯል። ይህ በመሆኑም እግዚአብሔር ይበልጥ የሚፈቅደው ትእዛዛት ቃል በቃል እንዲተረጎሙ ሳይሆን በውስጣቸው ባለው ፍቅር እንዲሆን ነው። እግዚአብሔር ፍቅርን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፦ «ኦሪትና ነቢያት በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት (በፍቅር ትእዛዛት) ጸኑ።» ማቴ 22:40።

(84)
ፈተናዎች

ከዲያብሎስ ቅናት የተነሣ ብዛት ያላቸው ፈተናዎች ሊከሰቱ ይችላሉ።

ዲያብሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ሰው ካገኘ ይቀናል ይቆጣልም። የያዘው መንፈሳዊ ሕይወት ጥብቅ መሆኑን ለማረጋገጥ ስለሚፈልግም በተለያዩ ፈተናዎች ያጠቃዋል።

ይህን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ መሞከሩን አይተናል።

እግዚአብሔር አብ በዮርዳኖስ ወንዝ ለልጁ ለኢየሱስ ክርስቶስ «. . . በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው።» (ማቴ 3:17) በማለት ሲመሰክር በሰጠው ታላቅ ክብር ዲያብሎስ ደስ አልተሰኘም። በዚህ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ በእርሱ ላይ አርፏል። መጥምቁ ዮሐንስም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ በማለት መስክሯል፦ «ተጎንብሼ የጫማውን ጠፍር መፍታት ከማይገባኝ ከእኔ የሚበረታ በኋላዬ ይመጣል።» ማር 1:7። ይህ በመሆኑም ዲያብሎስ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመፈተን ወደ ተራራ ሄዷል።

አንዳንድ ጊዜ የዲያብሎስ ውጊያ የመንፈሳዊ ሥራ ስኬታማነትን ያረጋግጣል። ይህ ደግሞ ሰውየው በሥራው እንዲተማመን ያደርገዋል።

የዲያብሎስ ፈተናዎች በዓይነታቸው በሁለት ይከፈላሉ። እነርሱም፦ መከራና ማባባል ናቸው።

መከራዎች አይጎዱም። መከራዎች የሚደርስበት ሰው ግን ከመከራዎቹ ይጠቀማል ትዕግሥትንም ይማራል። መከራዎች የእግዚአብሔርን እርዳታ እንድንለማመድም ያስችሉናል። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፦ «ወንድሞቼ ሆይ፤ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት።» ያዕ 1:2እና3።

ችግር የሚፈጠረው በኃጢአት ምክንያት በሚመጣ ፈተና ነው።

አንድ ኃጢአት ታማኙን ሰው ተመናጫቂ በማድረግ ሊፈትነው ይችላል። ሰውየው ተመናጫቂነትን ሳለመቀበል ቢቃወመውም «ወደ ፈተና አታግባን. . .» ብሎ ወደ እግዚአብሔር እስኪጮኽ ድረስ ዲያብሎስ ትግሉን አይተወውም።

ፈተናዎች ዲያብሎስ ተስፋ አለመቁረጡን አመላካች ፍንጮች ናቸው።

ጊዜው የተፈለገውን ያህል ቢራዘምም ዲያብሎስ ተስፋ አይቆርጥም ወይም እጁን አይሰጥም። እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስን ለአርባ ቀንና ለአርባ ሌሊት መፈተኑን አላቋረጠም ነበር። ክርስቶስ ድል ቢነሣውና ከእጠገቡ ቢያርቀውም እስከ ጊዜው ድረስ ነበር፤በመስቀል ላይ ሳለ ሊፈትነው መጥቶአልና።

የዲያብሎስን ፈተናዎች አንፈራቸውም።

በእኛ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ከዲያብሎስ ማታለያዎች ይበልጣል። በእኛ ውስጥ የሚሠራው መንፈስ ቅዱስም ዲያብሎስን ድል ሊነሣ ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ እግዚአብሔር በርኩሳን መናፍስት ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቶናል።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዲያብሎስን ፈተናዎች ሁሉ ድል ስለነሣ ለሰብአዊ ተፈጥሮአችን የድል መንፈስ አድሏል፤በድል ሰልፉም ላይ መሪያችን ሆኗል።

እግዚአብሔር በአምልኮታችን ውስጥ የተባረከ እንደ ሆነ በፈተናዎቻችንም ውስጥ የተባረከ ይሁን!

(85)
ሁሉም ነገር ለመንፈሳዊነታችሁ ይሁን

እግዚአብሔር አምላክ ሁሉንም ነገር የፈጠረው ለመንፈሳዊነታችሁ ነው. . .

ሰማይና ምድር የተፈጠሩት ቁሳዊ ጥቅም እንዲሰጧችሁ አይደለም። የሚሰጧችሁን መንፈሳዊ ትምህርት ለይታችሁ ማወቅ የምትችሉ ከሆነ የተፈጠሩት መንፈሳዊ ጥቅም ሊሰጧችሁ ጭምር ነው። «ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፤የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል።» መዝ 18:1።

መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ለመንፈሳዊ እውቀት ብቻ አይደለም። ለመንፈሳዊ ዕድገታችሁም ጭምር ነው። «. . . እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው።» ዮሐ 6:63። መጽሐፍ ቅዱስን ለጥናት በማንበብና መንፈሳዊ ጥቅም ለማግኘት በማንበብ መካከል ታላቅ ልዩነት አለ።

አገልግሎትም እንዲሁ ትምህርት ብቻ አይደለም። ትምህርት እንዲያው ወደ መንፈሳዊነት የሚመራ መንገድ ነው። ስለሆነም በአንድ የትምህርት ዓይነትና በሌላ የትምህርት ዓይነት መካከል ልዩነት አለ።

ለአሳባችሁ የሚስነዘር ትምህርት እንዳለ ሁሉ ልባችሁን የሚሞላ ትምህርትም አለ። አንዱ ትምህርት የተማረ ሰው አድርጎ ሲቀይራችሁ ሌላው ትምህርት ደግሞ የአምልኮ ሰው አድርጎ ይቀይራችኋል።

የምትቀበለው ትምህርት ለሌሎች ሰዎች መንፈሳዊነት ስትል የምትቀበለው ሳይሆን ለራስህም መንፈሳዊነት ስትል መሆን አለበት።

አድማጮችህ የሚጠቀሙትን ያህል አንተም መጠቀም አለብህ:: ከእነርሱ ጋር የማትጠቀም ከሆንህ ንግግርህ መንፈሳዊ ውጤቱን ያጣ ስለሚሆን እነርሱም ከአንተ አንዳችም የሚጠቀሙት ጥቅም አይኖራቸውም::

በቤተ ክርስቲያን ያሉ መዝሙራትና ዜማዎች ሙዚቃዎችና ቅኝቶች አይደሉም፤ለእግዚአብሔር የሚቀርቡ ጸሎቶች እንጂ:: እነዚህ መዝሙራትና ዜማዎች በልብህና በመንፈሳዊነትህ ላይ ጥልቀትና ውጤት አላቸው::

ስለሆነም እንዲያው በሚዘፍነውና በዜማ በሚዘምረው መካከል ልዩነት አለ::

ለሁሉም መንፈሳዊ ምክንያቶች ይህ ተግባራዊ ይሆናል::

ሌላው ሁሉ ቢቀር ድንገተኛ ክስተቶች ሁሉ ከእነርሱ መንፈሳዊ ጥቅሞች ታገኙባቸው ዘንድ በእግዚአብሔር የሚታዘዙ ናቸው::

አንዳንድ ሰዎች ድንገተኛ ክስተቶች ሲደርሱባቸው በጭንቀት ወይም በሥነ ልቦና ወይም በአእምሮ መታወክ ሊጎዱ ይችላሉ:: ሌሎች ደግሞ በሚያጋጥሟቸው በማናቸውም ነገሮች በመንፈሳዊነታቸው ሊጎዱ ቢችሉም የሚያጋጥሟቸው ነገሮች ሁሉ እነርሱን ወደ እግዚአብሔር ያቀርቧቸዋል::

የምታገኛቸው ሰዎች ወደ አንተ የሚላኩት በእግዚአብሔር ነው:: ከእነርሱ መጠቀምን የምታውቅ ከሆንህ እነርሱ በአንተ መንገድ ላይ የሚያልፉት ለአንተው መንፈሳዊ ጥቅም ሲሉ ነው:: ጻድቅ ሰው ለአንተ ምሳሌና በረከት ሲሆንህ አንተ ደግሞ ከመከራ፣ ከትዕግሥትና ለሌሎች ይቅርታ በማድረግ እነርሱን ከክፉ ከመጠበቅ ትጠቀማለህ::

(86)
ንስሓና ፍጹምነቱ

ሰው ይከተላቸው ዘንድ ንስሓ የራሱ የሆኑ ደረጃዎችና እርከኖች አሉት:-

1/ የመጀመሪያው ደረጃ በመጥፎ ሁኔታ ላይ እንዳሉ ማወቅና ይህን ለመለወጥ መነሣት ነው:: ይህም የሚሆነው በጠፋው ልጅ ላይ እንደ ሆነው ነው:: እርሱ ወደ ልቡ ሲመለስ የረሀብ የሞት አፋፍ ላይ መድረሱን ሊያውቅ ችሏል:: በዚህ ጊዜ ፍጹም የሆነው መፍትሔ ወደ አባቱ ቤት መመለስ ብቻ መሆኑን ተገንዝቧል::

2/ ሁለተኛው መፍትሔ ኃጢአትን መተውና ወደ እርሱ ከሚመሩ ከማናቸውም መንገዶች መራቅ ነው:: ኃጢአትን መተው ማለት ግን አንድን የተለየ ኃጢአት መተው ማለት ብቻ ሳይሆን ኃጢአትን በሙሉ መተው ማለት ነው:: ሰው እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስ ራሱን ሊያገኘው ይጀምራል::

ሰው በመንፈስ እያደገ ሲሄድ ከዚህ ቀደም ፈጽሞ ያላስተዋላቸውን አዲስ ጥፋቶች ይበልጥ እየተገነዘበ ይመጣል:: በዚህ ጊዜ እነዚህን ጥፋቶች ሊያጠፋቸው ይሞክራል:: ስለሆነም የእግዚአብሔርን መልክ መልሶ እስኪይዝ ድረስ ራሱን በሚያነጻባቸው በተለያዩ ደረጃዎች ውስጥ ማለፍ ይፈልጋል::

3/ በንስሓ ሕይወት ውስጥ ኃጢአትን መተው ቋሚ፣ ጥብቅና ያለ ምንም ወደ ኋላ መመለስ ሊሆን ይገባል፤የቅዱሳን ንስሓ እንዲህ ነበርና:: አውግስጢን በድጋሚ ወደ ኃጢአት መመለሱን አልሰማንም:: በሙሴ ጸሊምና በግብጻዊቷ ማርያምም እንዲህ ያለ ነገር አልታየም::

በእነዚህ ሁሉ የቅዱሳን ሕይወት የነበረው ንስሓ ወደ ኃጢአት መመለስ የሌለበት የተረጋገጠ ንስሓና ወደ እግዚአብሔር የተደረገ መመለስ ነበር::

4/ ቅዱሳን እንደሚናገሩት የንስሓ ፍጹምነት ኃጢአትን መተው ብቻ ሳይሆን ኃጢአትን መጥላትም ነው::

አንድ ሰው ኃጢአትን በእርግጥ ከተወ በኋላ በልቡ ኃጢአትን መናፈቁን የሚቀጥል ከሆነ ንስሓው ትክክለኛ ንስሓ አይደለም:: የዚህ ሰው ልብ ንስሓ አልገባም:: እንዲህ ዓይነቱ ሰው የሚያገረሽበት በመናፈቅ ብቻ ሳይሆን በድርጊትም ነው::

ያም ሆነ ይህ ግን መሠረታዊው ጉዳይ ልብ ነው:: እግዚአብሔርም እንዲህ ነው ያለው:- «ልጄ ሆይ፤ልብህን ስጠኝ:: » ምሳ 23:26:: ስለሆነም ሰው ንስሓ መግባት ያለበት ከልቡ ነው፤ ልብም ሙሉ ለሙሉ ሊሰጥ የሚገባው ለእግዚአብሔር ነው::

5/ እንዲህ ያለው ተነሣሒ ሰው ዳግመኛ ኃጢአት ሊሠራ አይችልም:: ምክንያቱም ስሜቶቹና ፍላጎቶቹ ኃጢአትን ሙሉ ለሙሉ ስለሚቃወሙትና ስለማይቀበሉት ነው:: ከዚህ በተጨማሪ ከኃጢአት ለመራቅ ብዙ ጥረት አያደርግም፤እርሱ ለኃጢአት ጥላቻ ስላለው ፈጥኖ ከእርሱ ይርቃልና::

6/ እውነተኛ ንስሓ ፍሬ ሊኖረው ግድ ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «እንግዲህ ለንስሓ የሚገባ ፍሬ አድርጉ፤ . . .» ማቴ 3:8:: ከእነዚህ ፍሬዎች መካከል የመጀመሪያውና ልብን የሞላው፣ ሕይወትን የሚለውጠውና የጽድቅ ፍሬ የሚያፈራው ለእግዚአብሔር የሚሆነው ፍቅር ነው::

(87)
ለእኛ የሆነ የእግዚአብሔር ፍቅር «ሀ»

ለእኛ የሆነ የእግዚአብሔር ፍቅር ምንኛ ታላቅ ነው! እግዚአብሔር ፍቅር ነው ማለት ብቻ ለዚህ በቂ ነው:: ስለ እኛም እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል:- «እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን::» 1ኛ ዮሐ 4:19::

የፈጠረን እኛ ሳንወደው አስቀድሞ እርሱ ስለወደደን ነው::

ለእኛ ካለው ፍቅር የተነሣ እኛን የፈጠረን በራሱ መልክና ምሳሌ ነው::

እርሱ እኛን የፈጠረን ሁሉንም ነገር ካዘጋጀልን በኋላ ነው:: ሰማይ ጣሪያ እንዲሆነን ከፍ ሲያደርግልን ምድርንም በላይዋ ላይ እንድንራመድ ለእኛ አስተካክሎልናል:: እርሱ ብርሃንን፣ ውኃን፣ አትክልቶችንና ገነትን አዘጋጅቶልናል::

ከዚህ በኋላ እኛን ፈጠረን::

በኃጢአት ስንወድቅም የድኅነትን መንገድ አዘጋጅቶልናል::

ለእኛ ካለው ፍቅር የተነሣ ይመሩን ዘንድ ነቢያትን ወደ እኛ ልኮልናል፤ ኀሊናም ቸሮናል:: ከዚህ በተጨማሪ አርቀን እናስተውል ዘንድ የሚያስረዳንን የተጻፈ ሕግ ሰጥቶናል::

ሥጋን እንዲለብስ ግድ ያሰውም የእኛ ፍቅር ነው። እርሱ ይህን የእኛ ሥጋ የለበሰው ሊቀድሰው ነው። እርሱ ስለ እኛ ሲል ሕግን በመቀበል ሰዎች እግዚአብሔርን የመፍራት መልክ እንዲኖራቸው አድርጎ በማቅረብ አባቱ እግዚአብሔር አብን አስደስቷል።

ለእኛ ካለው ፍቅር የተነሣም ስለ እኛ ሲል ሞቷል። «ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና፤. . .» 1ኛ ጴጥ 3:18።

እርሱ በመስቀል ላይ ሳለ ፍቅርን የሚያድል አምላክ ነበር። እርሱ የዓለሙን ሁሉ ኃጢአት በመሸከም በደሙ አጥቧል። እርሱ ምንም ኃጢአት ሳይኖርበት ስለ እኛ ኃጢአት ሲል እንደ ኃጢተኛ ተቆጥሮአል። ይህን በማድረጉም በእኛ ፋንታ መላውን ካሣ ከፍሎአል። .

ስለ እርሱ «. . . በዚህ ዓለም ያሉትን ወገኖቹን የወደዳቸውን እስከ መጨረሻ ወደዳቸው።» (ዮሐ 13:1) ተብሎ ተጽፎአል። እንዲህም ተብሎ ተጽፎአል:- «ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከማኖር ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም።» ዮሐ 15:13።

ስለ ወደደን እንዲህ ብሎናል:- «ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም፤ . . . ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ።» ዮሐ 15:15። ወንድሞቹ ብሎም ጠርቶናል:- «. . . በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው።» ዕብ 2:17። እኛም የሰማዩ አባት ልጆች ሆነናል:- «የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ፤. . .» 1ኛ ዮሐ 3:1።

ፍቅሩን ሊያሳየን ስለ ፈለገም እንዲህ ብሎናል:- «እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።» ማቴ 28:20። «ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ።» ማቴ 18:20።

ፍቅሩ በጥበቃው፣ በእንክብካቤውና በማንኛውም ነገር ለእኛ በሚያደርገው አመራር ውስጥ ታይቶአል።

(88)
ለእኛ የሆነ የእግዚአብሔር ፍቅር «ለ»

ለእኛ በሆነው በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ እርሱ እኛን የሚቆጥረን የራሱ ክፋይ አድርጎ ነው:- «እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ።» ዮሐ 15:5።

እንዲህም ብሎናል:- «. . . ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለ ሆንን . . .» ኤፌ 5:30። ወይም ደግሞ እርሱ ራስ ሲሆን ቤተ ክርስቲያን ደግሞ አካሉ ናት። ከዚህም በተጨማሪ:- «. . . በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ።» (ዮሐ 15:4) ብሏል። እኛን አስመልክቶ ለአባቱ ሲናገርም ይህን ብሏል:- «እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ፤እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን በአንድ ፍጹም እንዲሆኑ. . .» ዮሐ 17:22።

❖ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «. . . ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች . . .» (2ኛ ጴጥ 1:4) ተብሎ የተጻፈውና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር የሚያሳየው አገላለጽ ምንኛ ድንቅ ነው! ከዚሁ በተመሳሳይ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል:- «. . . የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችን ጋር ይሁን።» 2ኛ ቆሮ 13:4። በእርግጥ ይህ ኅብረት የሥራ

እንጂ የአካልና የባሕርይ አይደለም። በመሆኑም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ራሱና ስለ ወንድሙ ስለ ሲላስ ሲናገር ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነን ብሏል።

❖ የእግዚአብሔር ፍቅር ለእኛ ካለው አሠራር አንዱ በእርሱና በእኛ በሰዎች ዘር መካከል የዳበረው ወዳጅነት ነው። አብርሃም «አርከ እግዚአብሔር» ወይም «የእግዚአብሔር ወዳጅ» ተብሎ ተጠርቶአል። ስለ ሄኖክም እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል:- «ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም፤ እግዚአብሔር ወስዶታልና።» ዘፍ 5:24። ሙሴም ቢሆን ከእግዚአብሔር ጋር በተራራው ላይ ለአርባ ቀናት ቆይቶአል።

አሥራ ሁለቱ ሐዋርያትም ሌሎች ምሳሌዎቻችን ናቸው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእነርሱ ጋር የነበረው ኅብረት ልዩ ነበረና።

❖ እግዚአብሔር ደስታውን ከሰው ልጆች ጋር ማድረጉም ድንቅ ነው።

እርሱ የማይወሰን አምላክ ሆኖ በሚወሰኑት በሰዎች ዘንድ ትሕትናውን በመግለጥ ከእነርሱ ጋር ኅብረት ፈጥሮአል። ለእነርሱ በመገለጥም ቃል በቃል አነጋግሯቸዋል።

❖ ታሪክ እንደሚነግረን እነዚህ ሁሉ የእንክብካቤ አስደናቂ መንገዶች የተገለጡት እግዚአብሔር ለእኛ ካለው ፍቅር የተነሣ ነው። ለምሳሌ:- የቀይ ባሕር ለሁለት መከፈል፣ በምድረ በዳ የወረደው መና፣ ከጭንጫ ዓለት የፈለቀው ውኃ፣ በረሀቡ ዘመን የኤልያስ መጠበቅ፣ ጴጥሮስን ከእስር ቤት - ዳንኤልን ከአናብስት ጉድጓድ - ሠለስቱ ደቂቅን ከእቶን እሳት ማውጣትና ሌሎችም ማብቂያ የሌላቸው የእንክብካቤና የጥበቃ ታሪኮች ለእኛ ተደርገውልናል።

❖ እግዚአብሔር ለእኛ ካለው ፍቅር የተነሣ ምልክት ይሆኑን ዘንድ እነዚህን ቃል ኪዳኖች ለእኛ ምልክቶች አድርጎ ሰጥቶናል:-

«እነሆ እኔ በእጄ መዳፍ ቀርጬሻለሁ፤. . .» (ኢሳ 49:16)፤ «የእናንተስ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ ተቆጥሮአል።» (ማቴ 30:10)፤«አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ. . .» (ሕዝ 36:26)፤«. . . ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም።» (ዮሐ 10:29)፤ «. . . ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና፤. . .» (ዮሐ 14:2)።

❖ የተሰጡን ስጦታዎች ሁሉ እግዚአብሔር ለሰው ያለውን ፍቅር የሚገልጡ ናቸው።

የዘላለማዊነት ስጦታ፣ በእርሱ ክብር በአካል የሚሆን የትንሣኤ ስጦታና ሌሎችም ብዛት ያላቸው የመንፈስ ቅዱስ ስጦዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ፍቅር የተባረኩ ናቸው።

(89)
የፍቅር መሥዋዕት

ፍቅር የሚፈተነው በሕማም፣ በመከራና መሥዋዕት በመሆን ነው።

መሥዋዕት መሆን የማይችል ሰው የማይወድ ወይም የማያፈቅር ሰው ነው . . . የሚወድ ከሆነ ግን ለመውደዱ ማንኛውንም ነገር መሥዋዕት አድርጎ ያቀርባል።

የአባቶች ሁሉ አባት የተባለው አብርሃም ለእግዚአብሔር ካለው ፍቅር የተነሣ ወገኖቹንና የአባቱን ቤት ትቶ በመውጣት በእንግድነት በድንኳን ውስጥ ኖሯል።

ይሁን እንጂ አብርሃም ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር ጫፍ የደረሰው አንድ ልጁን በመሠዊያው ላይ ባጋደመው ጊዜ ነበር። እርሱ በልጁ ዙሪያ እንጨቶች ሰብስቦ ካቀጣጠለ በኋላ መሥዋዕት አድርጎ ሊያቀርበው ቢላዋ የያዘ እጁን ቃጥቶ ነበር።

ዳንኤል እግዚአብሔርን በወደደ ጊዜ ወደ ተራቡ አናብስት ይወረወር ዘንድ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ አቅርቧል። ሦስቱ ወጣቶችም እንዲሁ ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር ያረጋገጡት በእቶኑ እሳት ውስጥ በመወርወር በከፈሉት መሥዋዕትነት ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን ፍቅር የገለጠው እንዲህ በማለት ነው፡- «አዎን፤በእውነት ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ጌታዬ እውቀት ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን እቆጥራለሁ፤ . . .» ፊልጵ 3:8-9።

አባቶቻችን ሰማዕታትና ካህናት ለእግዚአብሔር ካላቸው ፍቅር የተነሣ ደማቸውን፣ ሕይወታቸውንና መደላደላቸውን መሥዋዕት አድርገው አቅርበዋል።

እነርሱ ለእግዚአብሔር የተለየ ፍቅር ስለነበራቸውና ሥቃይን ስለተለማመዱት ፈጽሞ ፈርተው አያውቁም ነበር።

ሰውን መሥዋዕት ከመሆን የሚያግዱት የተለያዩ እንቅፋቶች አሉ። እነርሱም፡- የመደላደል ፍቅር፣ የክብር ፍቅርና የራስ ፍቅር ናቸው።

ሰው ለወደደው አንድ ነገር ማንኛውንም ነገር መሥዋዕት አድርጎ ያቀርባል።

አባታችን ያዕቆብ ከራሄል ጋር በፍቅር በወደቀ ጊዜ ስለ እርሷ ብዙ መሥዋዕትነት ከፍሏል። እርሱ ራሔልን ለማግኘት ለሃያ ዓመታት ያህል በቀን ሀሩርና በሌሊት ቁር መድከም ነበረበት። ይሁን እንጂ ለእርሷ ከፍተኛ ፍቅር ስለ ነበረው እነዚህ ዓመታት ለእርሱ እንደ ጥቂት ቀናት ነበር ያለፉለት።

እናንተስ ስለ እናንተ ሲል በመስቀል ላይ መሥዋዕት ሆኖ ለቀረበው ለኢየሱስ ክርስቶስ የምታቀርቡለት መሥዋዕት ምንድር ነው?

የሚወድ ሰው ለእግዚአብሔርና ለሕዝቡ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ያቀርባል።

ሰው በመጀመሪያ መሥዋዕት ለማድረግ መለማመድ ያለበት ከእርሱ ውጪ በሆኑ ነገሮች ማለትም በገንዘብ፣ በጊዜ እና በሀብት ላይ ነው። ከእርሱ ውጪ የሆኑ ነገሮችን መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብ የማይችል ሰው እንዴት ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ሊያቀርብ ይችላል?!

መሥዋዕትነት መክፈል ካልቻልህ ሌሎች ሰዎችን አትወድም ወይም የምትወደው ራስህን ብቻ ነው።

(90)
የእግዚአብሔር መፍትሔዎች

በእውነትም እግዚአብሔር ብዙ መፍትሔዎች አሉት።

እኛ ስለ ችግሮቻችን የምናስበው በዚህ ውሱን አሳባችን ነው። የእግዚአብሔር እውቀትና ጥበብ ግን የማይወሰን ነው።

ነገሮች ሲወሳሰቡ ውስብስብነታቸው ለእኛ ለሰው ልጆች አንጻራዊ ነው። ለእግዚአብሔር ግን አንዳችም የተወሳሰበ ነገር የለም። ሁሉም ነገር ለእርሱ ቀላል ነው፤ የእርሱ መፍትሔዎችም ብዙ ናቸው።

እግዚአብሔር በመካከል የሚገባው በትክክለኛው ጊዜና አመቺ በሆነው መንገድ ነው። የእርሱ መፍትሔ በአሳቦቻችን ውስጥ የሌለ፣ ፈጽሞ ያልታሰበና ያልተጠበቀ ሊሆን ይችላል።

«እርሱ ግን፡- በሰው ዘንድ የማይቻል በእግዚአብሔር ዘንድ ይቻላል አለ።» ሉቃ 18:27።

ጻድቁ ኢዮብ እንደተናገረ በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉም ነገር ይቻላል፤አንዳችም ከባድ ነገር የለም፡- «ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደ ሆንህ፤አሳብህም ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል አወቅሁ።» ኢዮ 42:2።

እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ይቆጣጠራል፤ሁሉንም ነገር ይመለከታል፤ ከእርሱ የተሸሸገም ምንም ነገር የለም። እርሱ በምሥጢር ወይም በጨለማ ማየት ይችላል። ሁሉም ነገር በእርሱ ዓይኖች ፊት የተገለጠ መልሱም የታወቀ ነው።

ይህ በመሆኑም ሙሴ የተናገረው ቃል መልካም ነው፡- «. . . ዛሬ ለእናንተ የሚያደርጋትን የእግዚአብሔርን ማዳን እዩ። እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል፤እናንተም ዝም ትላላችሁ።» ዘጸ 14:13-14።

የእግዚአብሔር መፍትሔዎች ብርቱ ናቸው፤ማዳኑም ታላቅ ነው።

አማኞች የእግዚአብሔርን ማዳን በተስፋ ይጠባበቃሉ፤በተስፋም ደስ ይላቸዋል።

ባለፉት ቀናት ለእነርሱ የሆነ የእግዚአብሔር ሥራ አሁን በሚሠራው፣ ወደፊት በሚሠራውና በማንኛውም ጊዜ በሚሠራው የእግዚአብሔር ሥራ ላይ ያለ እምነታቸው ይበልጥ እንዲጨምር ያደርጋል።

እግዚአብሔር - እግዚአብሔር ነው። የእርሱ ፍቅርና ጥበቃ አይቀየርም።

በመሆኑም በዳዊት የመዝሙራት መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፡- «እግዚአብሔር ከክፉ ሁሉ ይጠብቅሃል፤ነፍስህንም ይጠብቃታል። ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም እግዚአብሔር መውጣትህንና መግባትህን ይጠብቃል።» መዝ 120:7እና8።

ለሕይወታችን መፍትሔ የምናገኘው ከእግዚአብሔር እንጂ ከሰዎች አይደለም። ሁላችንም በእግዚአብሔር እጆች ውስጥ ነን። ከእግዚአብሔር ውጪ በራሱ የቆመ ወይም ከእርሱ ግዛት የወጣ ማንም የለም።

ስለሆነም ከእኛ ጋር ባለው በእግዚአብሔር ሥራ እንተማመናለን።

መዝሙረኛው ዳዊት «እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ። በርታ ልብህም ይጽና፤ እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ።» መዝ 26:14።

የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን።

(91)
እግዚአብሔር አለ

እግዚአብሔር የሌለበት ችግር በራሱ ለሰዎች ችግር ሊፈጥር ይችላል:: እግዚአብሔር የገባበት ችግር ግን ችግር ሊያስከትል አይችልም::

በእግዚአብሔር ስታምኑ የእርሱ በመካከል መግባት ለልባችሁ ደስታና መተማመን ያድላል:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «. . . በተስፋ ደስ ይበላችሁ . . .» (ሮሜ 12:12) በማለት ተናግሯል::

❖ የአናብስቱ ጉድጓድ ለዳንኤል አስፈሪ ነበርን?

በእርግጥ አልነበረም:: እርሱ «. . . አምላኬ መልአኩን ልኮ የአንበሶችን አፍ ዘጋ. . .» (ዳን 6:22) የሚለውን ቃል ያውቅ ነበርና::

❖ የሚነደው እቶን እሳት ለሦስቱ ብላቴናዎች የመጥፊያቸው ምክንያት ነበረ እንዴ?

አልነበረም:: ጉዳዩ ሌላ ነበር:: የአማልክት መልክ ያለው አራተኛ ሰው በእሳቱ መካከል ከእነርሱ ጋር ይመላለስ ነበር::

❖ ግዙፉ ሰው ጎልያድ ለዳዊት አስፈሪ ነበር እንዴ?

እርሱ እግዚአብሔርን ሳይዙ ከጎልያድ ጋር ለውጊያ እንደተሰለፉት ሠራዊት አልነበረም:: ዳዊት ብርቱ ሰው ስለ ነበር ጎልያድንና ማስፈራራቱን አልፈራም፤እርሱ ወደ ሰልፉ የገባው እግዚአብሔርን ይዞ ነበርና:: «. . . አንተ ሰይፍና ጦር ጭሬም ይዘህ ትመጣብኛለህ፤እኔ ግን ዛሬ በተገዳደርኸው በእስራኤል ጭፍሮች አምላክ ስም በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ:: እግዚአብሔር ዛሬ አንተን በእጀ አሳልፎ ይሰጣል. . .» 1ኛ ሳሙ 17:45::

እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የመሆኑ መተማመን ስሜት የመተማመናችን ምክንያት ነው::

የእግዚአብሔር ስም ጻድቅ የሚመሸግበት ብርቱ ምሽግ ነው::

«እግዚአብሔር ከክፉ ሁሉ ይጠብቅሃል፤ነፍስህንም ይጠብቃታል:: ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም እግዚአብሔር መውጣትህንና መግባትህን ይጠብቃል::» መዝ 120:7እና8::

«ሁልጊዜ እግዚአብሔርን በፊቴ አየዋለሁ፤በቀኜ ነውና አልታወክም::» መዝ 15:8::

በእውነትም እግዚአብሔርን በችግር ውስጥ መተው ችግርን ያቃልላል::

❖ ኤልያስ የእግዚአብሔርን ስም ይዞ አክአብን ተጋፍጦታል::

ሙሴና አሮንም ፈርዖንን በእግዚአብሔር ስም ተጋፍጠውታል:: ቅዱስ ጳውሎስም በእግዚአብሔር ስም ፊስጦስንና አግሪጳን ተጋፍጧል::

❖ እግዚአብሔር ለእነዚህ ቅዱሳንና ለሌሎች እነርሱን ለመሰሉ ሰዎች ብርታታቸው ነበር::

መዝሙረኛው ዳዊት እንዲህ ብሏል:- «ኃይሌም ዝማሬዬም እግዚአብሔር ነው፤እርሱ መድኃኒት ሆነልኝ::» (መዝ 117:14)፤ እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው፤የሚያስደነግጠኝ የሚያስፈራኝ ማነው?» መዝ 26:1::

❖ መፍትሔ የምናገኘው ከእግዚአብሔር እንጂ ከሰዎች አይደለም:: በችግሮቻችን ሁሉ ፊት እግዚአብሔርን ካስቀደምን እርሱ ብርታቱን ያድለናል::

አንድ ቀን ደከምሁ ማለት የእግዚአብሔርን ኃይል ዘነጋሁ ማለት ነው::

(92)
ሌላው እይታ

ነገሮችን የምንመለከተው ከአንድ የተለየ መንገድ፣ ከአንድ የተለየ ጥግ እና ከአንድ የተለየ የትኩረት አቅጣጫ ነው:: ይሁን እንጂ የምንመለከተው ሁሉንም ነገር አይደለም::

ከእግዚአብሔር እይታ ጋር የሚስማማው በእምነት የሚሆነው ሌላ እይታ ነው::

❖ ዮሴፍ በወንድሞቹ አማካይነት እንደ ባሪያ በመሸጡ ውስጥ የምትመለከቱት ምንድር ነው?

በጲጥፋራ ቤት ውስጥ ከነበረው ታማኝነት አንጻር በእስር ቤት ባሳለፈው ቆይታው ውስጥ የምትመለከቱት ምንድር ነው?

ልንመለከት የምንችለው ሁሉ ክፋት፣ ቅናትና ክህደት ነው::

ኢ-ፍትሐዊነትና መጥፎ ዕጣም እንመለከታለን::

እግዚአብሔር ግን ለእነዚህ ሁሉ ነገሮች የነበረው እይታ ሌላ ነበር::

ዮሴፍ የሚከብርበት መንገድም ይህ ነበር::

የአስቆሮቱ ይሁዳ ያደረገውን ርካሽ ክህደት ከማለት በስተቀር ምን ልንለው እንችላለን::

ጴንጠናዊው ጲላጦስ የሠራው ሥራ ከፍራቻ፣ ከኢ-ፍትሐዊነትና ለክፋት ውጤታማ ከመሆን ሌላ ምን ሊሆን ይችላል?

ስለ ሐና እና ስለ ቀያፋስ ከቅናት፣ ከውሸትና ከሴራ ውጪ ምን ልንናገር እንችላለን?!

ወደ እነዚህ ነገሮች ከተመለከትን በኋላ የምንናገረው መከሰት አልነበረባቸውም ብለን ነው::

እግዚአብሔር ግን ሌላ እይታ ነው ያለው::

እርሱ ድነታችንን የሚመለከተው በእነዚህ ሰዎች ሁሉ አማካይነት የተፈጸመ የስቅለቱ ውጤት አድርጎ ነው።

መጥፎውን መልካም አድርጎ የሚቀይረው እግዚአብሔር ነው።

ይህን ማለት ግን የእነርሱ ክፋት መልካም ነበር ማለት አይደለም።

በእርግጥም ይህን ማለት አይደለም። እዚህ ላይ ሌላው እይታ እግዚአብሔር ከመራራ ውስጥ ጣፋጭ ማውጣት መቻሉና ሁሉንም ነገሮች ለእርሱ ቅዱስ ስም ክብር እንዲሆኑ ማድረግ መቻሉ ነው።

❖ ዮናስ መርከቢቱ ላይ ቢሳፈርም በጣም ብርቱ ነፋስ መርከቢቱን ሊያሰጥማት ደርሶ ነበር። መርከበኞቹ ፈርተው ስለ ነበር የጫኗቸውን ዕቃዎች ወደ ባሕሩ ወርውረዋል።

ይህ ሁሉ መጥፎ ነበር ወይስ በዚህ አሳዛኝ የባሕር ጉዞ ላይ ሌላ እይታ ነበር?
ሌላው እይታ በቁጣ በተሞላው ባሕር ውስጥ የነበረው ማዕበል መርከበኞቹን በእግዚአብሔር እንዲያምኑ ምክንያት መሆን መቻሉ ነው።

❖ ውሱን እይታ እንዳለን ምንም ጥርጥር የለውም። እናንተ መከራን ማየት ትችሉ ይሆናል እንጂ እግዚአብሔር የዚህ መከራ ቀና ውጤት አድርጎ የሚያመጣውን በረከት መመልከት አትችሉም።

በእምነት ከሆነ ግን በረከትን ማየት እንችላለን። «እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናምናለን።» ሮሚ 8:28።

(93)
ቅንነት

ቅንነት ወዳጅነቱን በምታምንለት ሰው የሚቀርብ ንጹሕ ፍቅር፣ እውነተኛ መነሣሣትና የታማኝነት ስሜት ነው።

ቅንነት የሚታየው በመከራ ጊዜ ሲሆን ጥንካሬውም የሚፈተነው በሥቃይ ጊዜ ነው።

በዚህ ቅንነት ውስጥ ቅዱስ ጴጥሮስ ለኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሎት ነበር፡- «. . . ከአንተ ጋር የምሞት እንኳ ቢሆን ከቶ አልክድህም . . .» ማር 14:31። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ብሏቸው ነበር፡- «ነገር ግን እናንተ በፈተናዎቼ ከእኔ ጋር ጸንታችሁ የኖራችሁ ናችሁ፤ . . .» ሉቃ 22:28።

ክርስቶስ በተሰቀለ ጊዜ በዚህ ቅንነት ውስጥ የነበሩት ቅድስት ድንግል ማርያምና ፍቁረ እግዚእ ዮሐንስ በአጠገቡ ቆመው ነበር። ከዚህ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ቅንነት ውስጥ የነበረው የአርማትያሱ ዮሴፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ ከመስቀል ላይ አውርዶ ከኒቆዲሞስ ጋር እንዲገንዘውና ለራሱ ባዘጋጀው መቃብር ውስጥ እንዲያኖረው ጲላጦስን ጠይቆት ነበር።

እነዚህ ሰዎች በነበራቸው ቅንነት ውስጥ ስለ እነርሱ ምን ሊባል እንደሚችልና ምን ሊደርስባቸው እንደሚችል ያሰቡት ነገር አልነበረም።

መሥዋዕትነት የቅንነት ልዩ ጠባይ ነው። ቅንነት ያለው ሰው ስለ ፍቅሩና ስለሚወደው ሰው ካልሆነ በስተቀር ራሱን ይረሳል ምንም ነገርም አያስታውስም።

ሩት ለአማቷ ያሳየችውን ቅንነት መጽሐፍ ቅዱስ ገልጦልናል።

ሩት ለኑኃሚን እንዲህ ነበር ያለቻት፡- «. . . ወደምትሄጅበት እሄዳለሁና፤ በምታድሪበትም አድራለሁና. . . በምትሞችበትም ቦታ እሞታለሁ በዚያም እቀበራለሁ . . .» ሩት 1:16-17።

አባቱ ቢገሥጸውና ቢቆጣውም ዮናታን ለዳዊት ካለው ፍቅር የተነሣ ከእርሱ ጋር የኖረው በቅንነት ነው።

ዮናታን ከሞተ በኋላ ዳዊት ከዚህ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ቅንነት ለዮናታን ቤተሰቦች በሙሉ መልካምነቱን ገልጦአል። 2ኛ ሳሙ 9:1።

በዚሁ ቅንነት ሰማዕታት ራሳቸውን ለክርስቶስ ፍቅር አሳልፈው ሰጥተዋል። ቅዱሳን አባቶችም ስለ ክርስቶስ ሲሉ በዓይነታቸው የበዙ መከራዎችን ተቀብለዋል።

ለቤተሰቦቻቸው፣ ለመምህራኖቻቸው፣ ለመንፈሳዊና ለሥጋዊ አባቶቻቸው፣ ለሕዝቦቻቸው ወይም ለሚኖሩባቸው የተለዩ መመሪያዎች ቅን የሆኑ ሰዎች አሉ። ይህ ቅንነት እስከ ሞት የሚኖር ቅንነት ነው።

ከዚህ የተለዩ የቅንነት ዓይነቶችም አሉ። ለምሳሌ፡- ሐኪም ለበሽተኛው፤ጠበቃ ለደንበኛው፤አስተማሪ ለተማሪዎቹ፤ደራሲ ለአንባብያኑ፤የጥበቃ ሠራተኛም ለሚጠብቃቸው ሰዎች የሚያሳዩት ቅንነት አለ።

አንዳንድ ሰዎች ቅን የሚሆኑት ከሥራቸውና ከኅሊናቸው አንጻር ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ ስለ ፍቅርና ስለ ታማኝነት ሲሉ ነው። አንዳንዶቹ ደግሞ እንዲሁ በተፈጥሮአቸው ቅኖች ስለሆኑ ነው። እነዚህ ሰዎች ለሁሉም ሰው የሚያሳዩት ቅንነት ተመሳሳይ ቢሆንም ለሚወዷቸው ሰዎች ደግሞ ልዩ ነው።

ቅንነት ምንኛ ድንቅ ነገር ነው! ታላቅነት፣ ፍቅርና ወርቃማ አክሊል ነው።

(94)
የቤተ ክርስቲያን ሰላም

«አቤቱ ጌታችን ሆይ፤አንዲት፣ ቅድስት፣ ዓለም አቀፋዊትና ሐዋርያዊት የሆንች ቤተ ክርስቲያንህን አስባት፤በሰላምም ጠብቃት።» የሚለው ጸሎት ስለ ቤተ ክርስቲያን በየዕለቱ የሚጸለይ ጸሎት ነው።

ይህን ጸሎት ከሌሎቹ የንስሓ ጸሎቶች ሁሉ በፊት እንጸልየዋለን። በመሆኑም በሰርክ ጸሎት ማዕጠንት ላይ እንጸልየዋለን፤በነግህ ጸሎት ማዕጠንት ላይ እንጸልየዋለን፤ካህኑ በመሠዊያው ዙሪያ እየዞረ ዘወትር ሲጸልይም ይህን ጸሎት ይጸልያል።

ቅዳሴ ከመጀመሩ በፊትና መባ ከመቅረቡ በፊትም እንዲህ ብለን እንጸልያለን፡- «አንዲት፣ ቅድስት፣ ዓለማቀፋዊትና ሐዋርያዊት ለሆነችው የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ሰላምና ቅድስና አድላት።»

ካህናት ሲሾሙም ይህን የዘወትር ጸሎት እንጸልያለን።

ለንጉሥ ወይም ለፕሬዝደንት በሚደረግ የዘወትር ጸሎት ውስጥም:- «አንዲት፣ ቅድስት፣ ዓለማቀፋዊትና ሐዋርያዊት ለሆነችው ቤተ ክርስቲያንህ ሰላም ስትል ልቡን ዳስሰው።» በማለት ስለ ቤተ ክርስቲያን እንጸልያለን።

የቤተ ክርስቲያን ሰላም የአባቶቻችን ሐዋርያትና የቅዱሳን ሁሉ አንዱና ዋነኛው ጠቃሚ ጉዳያቸው ነበር።

ለእነዚህ ሁሉ አባቶች ይህች ቤተ ክርስቲያን እስከ ሰማያዊው መንግሥት ድረስ የምትዘረጋ በምድር ያለች የእግዚአብሔር መንግሥት ምሳሌ ናት።

የምትወክለውም የእምነትን ምንጭና እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የመኖሩን እውነት ነው።

አንድ ሰው በጸሎቱ ውስጥ ለራሱ ከሚያቀርበው ጥያቄ ይልቅ ለእርሷ ስለሚጠይቅ ሰላሟና ደኅንነቷ የእያንዳንዱ ሰው የጸሎት መሠረት ነው። ይህ ጥያቄ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባስተማረን ጸሎት ውስጥ የተመሰጠአችን ማዕከል ስለሆነ «ስምህ ይቀደስ፤ መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን. . .» እያልን እንጸልያለን።

ስለ ቤተ ክርስቲያን መጸለይ በምዕመናን፣ በእረኞቹና በመጋቢዎቹ አንደበት ውስጥ ለብዙ መቶ ዓመታት የቆየ ታላቅ ጸሎት ነው። ራሳቸውን ከዓለም ለለዩ መነኮሳት በሚደረግ የቅዳሴ ጸሎት ውስጥ እንኳ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሰላም እንጸልያለን።

የመናኞች ሁሉ ታላቅ አባት የሆነው የመጀመሪያው ባሕታዊ አባ ጳውሊ ቅዱሱን አባ እንጦንስን ስለ ቤተ ክርስቲያን ሰላም መጠየቁ እንደምን ያለ ድንቅ ነገር ነው!

ይህን ጸሎት የምንጸልየው ከልባችን ጥልቀት ውስጥ ነው።

የምንጸልየው የቅዳሴ አንድ ክፍል አድርገን ሳይሆን እንደ ሕያውና እንደሚያቃጥል ስሜት እየሆነብን ነው።

እያንዳንዱ ሰው ስሜቶቹን ሁሉ በዚህ ጸሎት ውስጥ እንዲያሰፋ ይሁን። አሜን።

(95)
ሌሎች እንዲሰናከሉ ምክንያት መሆን

መሰናከል ውድቀት ነው። ሌሎች ሰዎች እንዲሰናከሉ በድርጊትም ሆነ በአሳብ ምክንያት የሚሆን ሰው ለውድቀታቸውም ምክንያት የሚሆን ሰው ነው።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሏል:- «. . . መሰናክል ግድ ሳይመጣ አይቀርም፤ነገር ግን መሰናክሉን ለሚያመጣው ወዮለት፤ከእነዚህ ከታናናሾች አንዱን ከማሰናከል ይልቅ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ባሕር ቢጣል ይጠቅመው ነበር።» ሉቃ 17:1-2።

ታናናሾች የተባሉት በዕድሜ ወይም በአሳብ ወይም በመለየት ችሎታ ታናሽ የሆኑት ናቸው። እነዚህ ሰዎች በነፍሳቸው ወይም በእምነታቸው ወይም በመንፈሳዊ ደረጃቸው ታናናሽ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለሆነም ማንኛውም ስሜታቸውን የሚጎዳ ድርጊት ሁሉ ያውካቸዋል።

አብዛኛውን ጊዜ በዕድሜ ታላላቅ የሆኑ የቤተሰብ አባላት ልጆች ሊሰሟቸው የማይገባቸውን ቃላት በእነርሱ ፊት ሲናገሩ ይደመጣሉ። እነዚህ ሰዎች እነርሱ

የሚናገሯቸውን ቃላት ልጆች የማይረዷቸው ይመስላቸዋል። ይሁን እንጂ እነዚህ ቃላት በአብዛኛው ስሜታቸውን ይጎዳሉ በኅሊናቸውም ውስጥ ተቀርጸው ይቀራሉ።

ወላጆች በትናንሽ ልጆቻቸው ፊት ሲነታረኩና ሲጣሉም ይኸው ተመሳሳይ ችግር በእነርሱ ላይ ይደርሳል። እነርሱ ታላላቅ ሰዎችን ሁሉን አዋቂ አድርገው ስለሚመለከቷቸው እንዲህ ያለው ነገር ስሜታቸውን ይጎዳል። የወላጆች ፍቺም በተመሳሳይ መልኩ ስሜታቸውን ያቆስላል።

ቤተሰቡ የሚገዛቸው ብዛት ያላቸው የመዝናኛ ቁሶች ልጆች ኃጢአት እንዲሠሩ የሚፈታተኑ ናቸው። ከእነዚህም መካከል:- የሬዲዮና የቴሌቪዥን መርሐ ግብሮች ወይም መጽሔቶች ወይም መጻሕፍት አንዳንዶቹ ናቸው። በቤተሰብ አማካይነት የሚዘጋጁ አንዳንድ ድግሶች እንዲሁ የልጆችን ስሜት የሚያውኩ ናቸው።

መጥፎ አርአያነት እንዲሁ ታናናሽ ልጆች በቃላት፣ በተግባር፣ በአለባበስና በራስ አያያዝ ኃጢአት እንዲሠሩ ይፈታተናቸዋል።

ታናናሽ ልጆች በአብዛኛው ውሸት የሚማሩት ከወላጆቻቸው ነው።

አጋኖ ማውራትንና በሌሎች ሰዎች ላይ መቀለድን የሚማሩትም ከቤተሰቦቻቸው ነው። ሌላው ቢቀር የእነርሱን ድርጊት፣ እንቅስቃሴና ድምፅ አስመስለው ያቀርባሉ።

ልጆች አስመስሎ ማቅረብን ይወዳሉ።

ለኃጢአት ወይም ለውድቀት የሚዳርግ ፈተና የሚመጣው ልጆች ከትልልቅ ሰዎች ከሚቀስሙት ትምህርት ወይም አሳብ ነው። ይህ ደግሞ በቤት ውስጥ በትምህርት ቤት ወይም ከጎረቤት ሊከሰት ይችላል። ይህ በትምህርት ውስጥ ያለ የአሳቦች ቅራኔ እና ግጭት ለልጁ መውደቅ ምክንያት ይሆናል።

ታናናሾች ያሉት በእኛ ታማኝነት ውስጥ ነው። በውስጣቸው መልካም ዘር መዝራት ባንችልም እንኳ ስሜቶቻቸውን መጉዳት እናስወግድ።

(96)
የመከራ ክብር

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ውስጥ እንዲህ በማለት ተናግሯል:- «. . . አብረንም እንድንከብር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን።» ሮሜ 8:17።

በዚህ መሠረት ስለ ክርስቶስ መከራ መቀበል አማኙን በዘላለማዊው መንግሥት ውስጥ የሚጠብቀው ክብር መለኪያ ነው።

ይህ በመሆኑም ቤተ ክርስቲያን ሰማዕታትን ከሁሉም ቅዱሳን ሰዎች ታስቀድማለች።

እነርሱ በቤተ ክርስቲያን ጸሎት ውስጥ የሚጠቀሱት ምድረ በዳውን በጸሎትና በተመስጦ ከሞሉት መናኝ አባቶች በፊት ነው። ከዚህ በተጨማሪ እነርሱ የሚጠቀሱት ቅዱስ ቃሉን በአገልግሎቶቻቸው ከሚያስፋፉት ከቅዱሳን አባቶቻችን ከፓትርያርኮችና ከጳጳሳት በፊት ነው። ይህ ሁሉ የሆነላቸው ስለ እግዚአብሔር ሲሉ መከራን በጽናት ስለ ተቀበሉ ነው።

በአገልግሎት ውስጥም የመከራ ልክ ግልጽ ነው። ሐዋርያው ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል:- «. . . ነገር ግን እያንዳንዱ እንደ ራሱ ድካም መጠን የራሱን ደመወዝ ይቀበላል።» 1ኛ ቆሮ 3:8። ስለሆነም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ላለው አለቃ በላከው ጦማር ውስጥ ይህን

ተናግሯል፡- «ሥራህንና ድካምህን ትዕግሥትህንም አውቃለሁ. . . ታግሠሃማል፤ስለ ስሜም ብለህ ጸንተህ አልደከምህም፡፡» ራእ 2:2 እና3፡፡ ድካምን ማስቀደም መልካም ነው፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲህም ተብሏል፡- «እግዚአብሔር . . . ያደረጋችሁትን ሥራ (ድካም) ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለም፡፡» ዕብ 6:10፡፡

የፍቅር ሕልውና የሚገለጸው ለወደዱት በሥራና በእውነት መከራ በመቀበል ነው፡፡ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ይህን አስመልክቶ ለመንፈስ ልጆቹ ሲጽፍ እንዲህ ብሏል፡- «ልጆቼ ሆይ፤በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ፡፡» 1ኛ ዮሐ 3:18፡፡

የፍቅር ጥልቀትም በመከራ ውስጥ ይገለጣል፡፡ ይህም የሚሆነው የፍቅር ደረጃ ወደ መሥዋዕትነትና ወደ አዳኝነት ከፍ ሲል ነው፡፡

ይህ በመሆኑም የእግዚአብሔር ፍቅር በጥልቀት የተገለጠው በደል የሌለበት እርሱ በደለኞቹ እኛን ለማዳን በመስቀል ላይ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ባቀረበ ጊዜ ነው፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ጥልቅ በሆነው ሕማማቱ ውስጥ ሳለ የክብሩ ጫፍ ላይ ደርሶ ነበር፡፡

ከዚህም የተነሣ ስለ ስቅለቱ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- «አሁን የሰው ልጅ ከበረ፤. . .» ዮሐ 13:31፡፡ የስቅለቱ ምስል የክብሩ ምስል ነው፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መከራን የሚቀበለው እንደ እግዚአብሔር ስጦታ አድርጎ ነበር፡፡

ስለዚህ ሲናገርም ይህን ብሏል፡- «. . . ይህ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቶአችኋልና፤ ስለ እርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም፤. . .» ፊልጵ 1:29፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም ስለ መከራ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- «የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፤ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራ ተቀብሎአልና፡፡» 1ኛ ጴጥ 2:21፡፡

(97)
ዕርገት

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በክብር ያረገው የስበትን ሕግ (law of ravity) ሙሉ ለሙሉ በመሻር ነው፡፡ እኛም የስበትን ሕግ በመሻር እንደ እርሱ ከፍ ፍ በማለት ከእርሱ ጋር የምንሆንበትን ተስፋ ሰጥቶናል፡፡ ይህንን ያረጋገጠልንም ንዲህ በማለት ነው፡- «. . . እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደ ሆነ ሁሉን ወደ እኔ ስባለሁ፡፡» ዮሐ 12:32፡፡

እርሱ በደመና ከፍ ከፍ ካለ በኋላ ከዐይኖቻቸው ተሰውሯል፡፡

ይሁን እንጂ እኛ ልጆቹን በደመና ከፍ ከፍ አድርጎ ከእርሱ ጋር እስከ ፍጻሜው እንሆን ዘንድ ሊወስደን ከመላእክቱና ከቅዱሳኑ ጋር በድጋሚ በሰማይ መና ይመጣል፡፡

እርሱ በአባቱ ቀኝ እንደ ተቀመጠ እኛም ከእርሱ ጋር በክበሩ እንቀመጣለን፡፡

በጎልጎታ የሰቀሉት፣ እንደ ኃጢአተኛ የቆጠሩት፣ ወቀሳንና ስድብን የተቀበለው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን መካከል በክብር ተነሥቶአል፣ ወደ ሰማይ በክብር አርጓል፣ በአባቱም ቀኝ በክብር ተቀምጦአል፡፡

ጎልጎታ የሕይወቱ አሳዛኝ መጨረሻ አልነበረም!የክብሩ መጀመሪያ እንጂ፡፡
ስለሆነም ከእርሱ ጋር መከራ የተቀበለ ሁሉ በእርግጥ ከእርሱ ጋር ይከብራል፡፡

ዕርገት በሐዋርያት ዘንድ ለመጨረሻ ጊዜ የታየ የኢየሱስ ክርስቶስ ገጽታ ነው፡፡ ዕርገት ዐይኖቻቸውን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ተቀመጠበት ከፍታ እንዲያነሡ አድርጓቸዋል፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «በክብር ያረገ፡፡» (1ኛ ጢሞ 3:16) በማለት የተናገረው ይህንኑ ለመግለጽ ነው፡፡

የክርስቲያን መከራ ከክብሩ ጋር አይነጣጠልም፡፡

ስለ እኛ መከራ የተቀበለው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቀዳሜ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ መከራ ሲቀበል ለእርሱ ተገልጦ ታይቶታል፡፡ ይህ በመሆኑም ስለ እርሱ እንዲህ ተብሎ ተጻፈ፡- «. . . ወደ ሰማይ ትኩር ብሎ ሲመለከት የእግዚአብሔርን ክብር ኢየሱስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየና፡- እነሆ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ አለ፡፡ . . . እስጢፋኖስም፡- ጌታ ኢየሱስ ሆይ!ነፍሴን ተቀበል ብሎ ሲጠራ ይወግሩት ነበር፡፡» ሐዋ 7:55-59፡፡

ወደ ምድር የወረደው እርሱ ወደ ሰማይም አርጓል፡፡

እኛም በመጀመሪያ ባንወርድ ኖሮ ለማረግ አንችልም ነበር፡፡

ወደ እግዚአብሔር ቀኝ ከማረጋችን በፊት ግን እርሱ መከራ ተቀብሎ መስቀል ላይ እንደ ወጣ እኛም እንደ እርሱ ራሳችንን ትሑታን በማድረግ መከራ ልንቀበል ግድ ነው፡፡

ክርስቶስ ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ እንዳለ በድጋሚ በሰማይ ደመና ወደ እኛ ተመልሶ በመምጣት ከእርሱ ጋር እስኪያደርገን ድረስ እኛም ዐይኖቻችንን እርሱ ወደ ተቀመጠበት ወደ አባቱ ቀኝ ዘወትር እናነሣለን፡፡

ከዚህ በኋላ ያለ ምንም መውረድ ወደ ላይ እንወጣለን . . . አሜን፡፡

(98)
የሐዋርያት ጾም

ማንም ቢሆን የሐዋርያትን ጾም አቅልሎ ሊያስበው አይገባም! የክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያን ለትውልዶች ያሳወቀችው እጅግ ጥንታዊ ጾም ነውና፡፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ጾም አስመልክቶ የተናገረው እንዲህ በማለት ነው፡- «ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል፤በዚያን ጊዜም ይጦማሉ፡፡» ማቴ 9:15፡፡

አባቶቻችን ሐዋርያት አገልግሎታቸውን የጀመሩት በጾም ነው:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም አገልግሎቱን በተራራ ላይ የጀመረው በጾም ነው::

ስለሆነም የሐዋርያት ጾም የተሰጠው ለአገልግሎትና ለቤተ ክርስቲያን ነው::

መምህራችን ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ይህን ጾም ይጾመው ስለ ነበር ስለ እርሱ «ተርቦም ሊበላ ወደደ . . .» (ሐዋ 10:10) ተብሎ ተጽፎአል::

በዚህ ረሀቡ ውስጥ ሰማያት ተከፍተው አሕዛብን ስለ መቀበሉ የሚያሳይ ራእይ ሊመለከት በቅቷል::

የሐዋርያት አባቶቻችን ጾም በራእይና በመለኮታዊ አመራር የታጀበ እንደ ነበር ሁሉ ከመንፈስ ቅዱስ ሥራና መምጣት ጋርም የተባበረ ነበር::

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- «እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ:- በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ:: በዚያን ጊዜም ከጦሙ ከጸለዩም እጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቷቸው:: እነርሱም በመንፈስ ቅዱስ ተልከው ወደ ሴሌውቅያ ወረዱ፤. . .» ሐዋ 13:2-4::

የሐዋርያት አባቶቻችንን ጾም የተለየ የሚያደርገው ጾምን፣ ጸሎትን፣ አገልግሎትንና የመንፈስ ቅዱስ ሥራን በውስጡ በማካተቱ ነው::

በጾማችን ወቅት መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር መሥራቱ ያስደስተናል::

ለአገልጋዮች ሥልጣነ ክህነት የሚሰጠው በጾም ወቅት ሲሆን እነዚህ የተሾሙ ካህናት አገልግሎታቸውን የሚጀምሩትም በጾም ነው::

እንደ ዮናስ ጾም (ጾመ ነነዌ) ከንስሓ ጋር የተቀናጁ አጽዋማትም አሉ:: ከዚህ በተጨማሪ በኢዮኤል የትንቢት መጽሐፍ ውስጥ እንደተጠቀሰው ከትሕትና ጋር የሚቀናጅ ጾም አለ::

እንደ አስቴር ጾም የተለየ ጥያቄ ለማቅረብ የሚጾሙ ሌሎች አጽዋማትም አሉ::

እንዲሁ ርኩሳን መናፍስትን ለማስወጣት የሚጾም ጾም አለ:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ጾም አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል:- «ይህ ዓይነት ግን ከጸሎትና ከጦም በቀር አይወጣም::» ማቴ 17:21::

ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋዎች መካከል አንዱን ከመቀበላችን በፊት የምንጾማቸው አጽዋማት አሉ:: እነዚህ ጸጋዎች ምሥጢረ ጥምቀት፣ ምሥጢረ ሜሮን፣ ምሥጢረ ቁርባንና ምሥጢረ ክህነት ናቸው::

የሐዋርያት ጾም ለአገልግሎትና ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠ ጾም ነው:: ይህም የሆነው ለአገልግሎት የሚሆን አስፈላጊ ነገርንና ጥቅም ለእኛ ለማስተማር ነው::

በመልካም መንፈሳዊ ሁኔታ ውስጥ እያለን ድካሞቻችንን በመገንዘብ ለማገልገል እንጾማለን::

ከበዓለ አምሳ በኋላ ባለው ወቅት ውስጥ ይህን ጾም አጥብቀን እንናፍቀዋለን::

(99)

የሚጠቅም ቃል

ብዙዎች ከአንድ ቃል ጥቅም ለማግኘት ይፈልጋሉ . . .

ካላነበቡት ወይም ካላዳመጡት በስተቀር የተጠቀሙበት አይመስላቸውም::

❖ ብልኅ ሰው ግን የአንድን ቃል ጥቅም በማንኛውም ነገር ውስጥ ይመለከታል::

❖ ሌላው እንኳ ቢቀር በሌሎች ሰዎች ዝምታ ውስጥ ጥቅምንና ጥበብን ይመለከታል:: እርሱ ከእነዚህ ሰዎች ንግግር ከመጠቀም ይልቅ በዝምታቸው ይጠቀማል::

❖ በሕይወት ከምታገኘው ከእያንዳንዱ ድንገተኛ አጋጣሚ ልምድ፣ ከራስህ ልምድና ከሌሎች ሰዎች ልምድ ለአንተ የአንድ ቃል ጥቅምን ይይዝልሃል:: ስለሆነም ብዙዎች ከመጻሕፍት፣ ከጽሑፎችና ከንግግሮች ከሚጠቀሙት ጥቅም የበለጠ ከአጋጣሚዎች ይጠቀማሉ::

❖ የሕይወት ልምድ ቁጥራቸው እጅግ በበዛ ጥቅም አስገኚ ቃላት የተሞላ ነው:: ይሁን እንጂ ሰው ከእነዚህ ልምድ አስገኚ ቃላት እንዴት እንደሚጠቀም ማወቅ አለበት::

ከዚህ የተነሣ ከአባቶች ጥበብ እንጠቀም ዘንድ ተጠርተናል!እነርሱ የበዙ ልምዶች አላቸውና:: እያንዳንዱ ልምድ ደግሞ በውስጡ ጥቅም የሚሰጥ አንድ ቃል አለው::

❖ ሕመምን ከብዙ ጉዳዮች አንጻር ከተመለከትነው በራሱ ጥቅም ሰጪ ቃል ነው::

ሕመም በመጻሕፍት ውስጥ የሌሉ ብሒሎችን በሕመምተኛው ጆሮዎች ውስጥ ያንሾካሹካል::

ከዚህ በተጨማሪ ሕመም በሕመምተኛው ዙሪያ ለሚገኙ ዘመዶቹ፣ ባልንጀሮቹና ጠያቂዎቹ ጥቅም የሚሰጥ ቃል ሊሆን ይችላል::

❖ ሞትም ቢሆን ለአባ እንጦንስና ለአባ ጳውሊ ጥቅም ሰጪ ቃል እንደ ሆነ ሁሉ ለሌሎች ብዛት ላላቸው ቅዱሳንም ሆኗል:: ብዙዎች ሞት በእርምም ውስጥ ሆኖ በሰዎች ልብ ውስጥ የሚያንሾካሹካቸውን ጥቅም ሰጪ ቃላት ያደምጡ ዘንድ የመቃብር ቦታዎችን መጎብኘት ልምድ አድርገውታል::

❖ ሰዎች አጠቃቀሙን በትክክል ካወቁት መከራም ለሰዎች ጥቅም ሰጪ ቃል ነው:: ይህም ሰው ከራሱ ልምድ ከሚያገኘው ወይም ከሌሎች ሕይወት ከሚመሰክረው ነገር ሊሆን ይችላል:: ይህ በመሆኑም መጽሐፍ ቅዱስ ከምድር አበቦችና ከሰማይ ወፎች እንድንማር ጠይቆናል:: ሰነፍም እንኳ ከጉንዳን ይማራል::

❖ ጥቅም ሰጪ ቃል በሁሉም ቦታ ላይ ስላለ ማንም ሊያጣው አይችልም:: በአጠቃላይ ግን ሰዎች በመንገዳቸው ላይ ከሚያጋጥማቸው ከማንኛውም ነገር አንድ ጥቅም ሰጪ ቃል ያወጡ ዘንድ የተመሰጦና የጥልቀት ስጦታን እንዲያገኙ ይሻሉ::

ይህ ጥቅም ሰጪ ቃል የተነገረ ወይም በዝምታ ውስጥ ያለ ወይም የተጻፈ ወይም የተመለከተ ሊሆን ይችላል:: የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ!!

(100)
ራስን መውደድ

እውነተኛው ራስን መውደድ የሚገኘው እኛነታችን እግዚአብሔርን እንዲወድ፣ በእኛ ውስጥ ያለ ቋሚ ማደሪያውን እንዲያፈቅርና ራሳችንን ለመንፈሱ ሥራ አሳልፎ እንዲሰጥ ስናለማምደው ነው።

በንጽሕና እና በትሕትና ካልሆነ በስተቀር ሰው በእግዚአብሔር ማደሪያ ፈጽሞ ሊደሰት አይችልም። ይህን ካደረግን ግን እኛነታችን የመንፈስ ቅዱስን ሥራ አይቃወምም ወይም የራሱን አላዋቂነት ከእግዚአብሔር ጥበብ አስበልጦ አይመርጥም።

ይህ ከተደረገ ደግሞ ራስን መውደድ ራስን በመካድ ውስጥ ይገለጣል።

በሥራ ውስጥ ያለ ራስን መካድ እንዲህ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል፦ «. . . ሐዋርያ ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ፤ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ፤. . .» 1ኛ ቆሮ 15:9-10። ከዚህ በተጨማሪ ራስን መካድ ማለት ራስን ማወደስና ራስን ማክበር ማለት ነው። «ለእኛ አይደለም፤አቤቱ ለእኛ አይደለም፤ነገር ግን ለስምህ ስለ ምሕረትህ ስለ እውነትህም ምስጋናን ስጥ።» መዝ 113:9።

በታላቅ ጥረት ውስጥ ያለ ራስን መካድ አማኙ ሰው የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመግንባት ሲል ምቾቱንና ሀብቱን መሥዋዕት አድርጎ የሚያቀርብበት መሆን አለበት።

ራስን መካድ ከእግዚአብሔርና ከሰዎች ጋር በመስማማት ውስጥ ይገለጣል።

እዚህ ላይ አንድ ሰው ሌሎች ሰዎችን በሁሉም ነገር ለራሱ ይመርጣል፦ «. . . በወንድማማች መዋደድ እርስ በእርሳችሁ ተዋደዱ፤ እርስ በእርሳችሁ ተከባበሩ፤. . .» ሮሜ 12:10።

ለሌሎች ሰዎች ሁሉ የሚሆን ተግባራዊ የፍቅር መሠረት ይህ ነው። ይህ ደግሞ የሚሆነው በክብር ብቻ አይደለም፤ለሌሎች በመስጠት፣ መሥዋዕትነት በመክፈልና በመድከም ጭምር እንጂ። አንድ ሰው ለሌሎች ሰዎች መሥዋዕት የሚሆነው ራሱን መሥዋዕት አድርጎ እስከ ማቅረብ ድረስ ነው። እዚህ ላይ ይህ ሰው የሌሎች ሰዎችን ኃጢአት ከራሱ ኃጢአት ጋር በማነጻጸር ኃጢአቶቻቸውን መሸከምን አይቃወምም፤ያለውን ሁሉ ለሌሎች ለመስጠትም ራሱን ይነፍጋል እንጂ።

አንዳንድ ሰዎች ግን ራሳቸውን በተሳሳተ ዓለማዊ መንገድ ሲወዱ ይታያሉ።

እነዚህ ሰዎች ለመግንባት በሚያደርጉት ሙከራ ያፈርሳሉ፤ከፍ በማድረግ ፋንታም ያጠፋሉ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፦ «ነፍሱን የሚያገኝ ያጠፋታል፤ነፍሱንም ስለ እኔ የሚያጠፋ ያገኛታል።» ማቴ 10:39።

ስለ እግዚአብሔር ሲሉ ዓለማዊ ደስታዎችን የሚተዉ ሰዎች በዓለማውያን ዘንድ የጠፉ ሆነው ነው የሚቆጠሩት፤ራሳቸውን ለመግዛት የሚያስችላቸውን እውነተኛ መንገድ በትክክል ቢያገኙትም እንኳ። ከእነዚህ ሰዎች መካከል መነኮሳት፣ የመንፈስ ልጆችና እግዚአብሔርን ለማገልገል ሲሉ ራሳቸውን የቀደሱ ሁሉ ይገኛሉ። እነዚህ ሁሉ ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር ሆነው «. . . እነሆ፤እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ . . .» (ማቴ 19:27) ይላሉ።

ራሱን የሚወድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ሲል መስቀሉን በየዕለቱ ተሸክሞ በቀጭኑ መንገድ ላይ ይጓዛል።

እንዲህ ዓይነቱ ሰው በእርግጥ ራሱን ይወዳል።

ዓለማዊና ሥጋዊ ፍላጎቶቹን በሙሉ የሚያስደስተው ግን ዓለሙንና ምኞቱን ይወዳል እንጂ ራሱን አይወድም።

በነገር ሁሉ ለእኛ ያደረገና የሚያደርግ እግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን።

ከዚህ ቀደም በተርጓሚው ተተርጉመው ለአንባብያን የቀረቡ መንፈሳዊ መጻሕፍት:-

1. የተራራው ስብከት
2. የዲያብሎስ ውጊያዎች
3. የነፍስ አርነት
4. ሀብታምና ድሀ
5. የተስፋ ሕይወት
6. መንፈሳዊው ሰው
7. መንፈሳዊ ውጊያዎች
8. መንፈሳዊው መንገድ
9. የባሕታውያን አባቶች ሕይወትና የመዝሙራት ተመስጦ
10. መንፈሳዊ ጾም
11. እግዚአብሔርና ሰው

ከመጽሐፉ የተወሰደ

(2) ከሰዎች ጋር ስለ መግባባት

ሰዎችን በተረዳጋጋሚ አትገሥጻቸው፤ ይህን ማድረግ ካለብህም ማንንም ለመጉዳት ወይም ላለማመን ስትል አታድርገው። በእነርሱ ላይ ሂስ እንድትሰጥና ለእነርሱ ጠላት ሆነህ እንድትቆም የሚያደርግህን ቃል ወይም ድርጊት ለይተህ አታንግ። . . . በሰዎች ደስታና ኀዘን ላይ ተካፋይ ሁን:- "ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ፤ ከሚያለቅሱም ጋር አልቅሱ።" ሮሜ 12:15። የሰዎችን ልብ ለማጽናናት ዕድሉን አትጡት።

(39) መስቀልህን ተሸከም፤ የምትሰቀል እንጂ የምትሰቅል አትሁን!

አንተ የምትሰቀል ከሆንህ እግዚአብሔር በዚህኛው ዓለም ሳይሆን በወዲያኛው ዓለም ከአንተ ጋር በመሆን ሙሉ መብትህን እንደሚመልስልህ እርግጠኛ ሁን። ይሁን እንጂ አንተ ሌሎች ሰዎችን የምትሰቅል ከሆንህ እግዚአብሔር አንተ ከሌሎች የወሰድኸውን መብት ለእነርሱ እስከሚመልስና እስኪቀጣህ ድረስ አንተን እንደሚቃወምህ እርግጠኛ ሁን።. . . . ስለ እውነት ወይም ስለ እምነት ብለህ ብትሰቀል ግን የምትቀበለው ማንኛውም ዓይነት መከራ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ እንደሚታሰብ ተማመን። ይህ ጉዳይ በመንግሥተ ሰማያት አክሊል ሲያቀዳጅ በምድር ደግሞ በረከትን ያሰጣል። እግዚአብሔር፣ ቅዱሳንና ሰማያት ሁሉ በአንተ ጎን እንደሚቆሙ እርግጠኛ ሁን።

(71) ከስሕተቶች መጠቀም

መንፈሳዊ ሰው በስሕተቶቹ ውስጥ ትሕትናን የራሱ ያደርጋል። ይህ ሰው ስሕተቱን በመለየትና እንደ ሌሎች ሰዎች እንዴት ለስሕተት እንደሚጋለጥ በማወቅ ከስሕተቱ ይማራል። በመሆኑም አይኮራም ወይም እብሪት አይሰማውም ወይም ራሱን ከሌሎች ልዩ አድርጎ አይመለከትም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ።" (1ኛ ቆሮ 10:12) ብሎ የተናገረው ቃል በእርሱ ሕይወት ውስጥ ተግባራዊ ይሆናል።

በብራና ማተሚያ ድርጅት ታተመ

ዋጋው ብር 14.00